# በሙት መንፈስ
# አገር ሲታመስ

ከአንዳርጌ መሥፍን
አ.አ
2005ዓ.ም

© የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው::

የመጀመሪያ እትም - ግንቦት 2005 ዓ.ም

የሁለተኛ እትም - ህዳር 2006 ዓ.ም

# ምስጋና

*የጅ ጽሑፉን ደከመኝ ታከተኝ ሣትል የእረፍት ጊዜዋን መስዋዕት አድርጋ ለተየበችልኝ ወይዘሪት ብርቱካን መንገሻ ምስጋናዬ እጅግ የላቀ ነው:: እንዲሁም የቴክኒክ ሥራውንና ፎቶ ግራፎችን በማሰባሰብ ለረዳኝ ወንድወሰን ከንፈ ምስጋናዬ የላቀ ነው:: በተረፈ ሥራዬ የተቃና እንዲሆንና ለውጤት እንዲበቃ በሐሳብ ላልተለያችሁኝ አንጋፋ ምሁራንና የሥራ ባልደረቦች ወጣቶች ምስጋናዬ በያላችሁበት ይድረሳችሁ!!*

*ደራሲው*

# ማውጫ

እንደ መንደርደሪያ ............ 5

## ክፍል አንድ

- በዋዜማው ............ 9
- እንደ ንግርት ............ 16
- የጠ/ሚንስትሩ ዜና ረፍት ............ 20
- ሕዝቡ ለጠ/ሚንስትሩ ሐዘኑን የገለጠው ካንጀት ነው ካንገት? ............ 24
- የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ............ 32

## ክፍል ሁለት

- ጊዜ ነው ዘመዱ ............ 35
- የፕሮፓጋንዳ ዶፍ! ............ 40
  - ➢ በሙት መንፈስ አገር ሲታመስ ............ 43
  - ➢ ታሪክ ፍቆ ታሪክ መሥራት አይቻልም! ............ 45
- ካዲሱ ጠ/ሚንስትር ምን ይጠበቃል? ............ 50
- ታላቅነት ምን ማለት ነው? እንዴትስ ይበየናል? ............ 58
  - ➢ ያንድ መሪ የቋንቋ አጠቃቀም ምን መሆን አለበት? ............ 59
  - ➢ በወሰኑት ውሳኔ ያለመፅናት ............ 63
- "የታላቁ መሪያችን ራእይ!" ............ 67
  - ➢ ያቶ መለስ እውነተኛ ራእይ ............ 59
  - ➢ "ዓባይን የደፈረ ጀግና!" ............ 75
  - ➢ ጀግንነት እንዴት? ............ 80
  - ➢ አንደበተ ርቱዕ ............ 83
- ያሰብ የባሕር በር ............ 87
- ጎሠኝነት አድሏዊነት ነው ............ 91
- ባማራ ሕዝብ ላይ በቀልተኛው ሕወሓት ............ 95
  - ➢ ያድዋ ድል ............ 98
  - ➢ ክርስትና ሃይማኖት ............ 99
  - ➢ ዓባይ ሦስተኛው ጠላት የገዛልን ............ 100
- የሕወሓት ሰዎች ምን እየቀበሩ ነው? ............ 103
  - ➢ ፍኖተ ገድል ወይንስ ፍኖተ ገደል? ............ 103
  - ➢ ለካ አማራ ጠፍቷል?! ............ 114
  - ➢ አናት ሲመታ እግር መቆም አይችልም! ............ 117
  - ➢ "ሆዱ ጩቤ አፉ ቅቤ!" ............ 119

- የሽብር ራእይ! ........................................ 122
- የፀረ-ሽብር ሕጉ ........................................ 124
- የፀረ-ሽብር ሕጉ ለምን አስፈለገ? ........................................ 126
  - ➢ የድኩላና የነብር ኑሮ ለምን? ........................................ 127
  - ➢ መልካም አሥተዳደር እንዴት? ........................................ 132
- ሽብር ፍለጋ ሞቃዲሾ ድረስ? ........................................ 136


## ክፍል ሦስት


- አንቀጽ 39 እንደ ዋሥትና ........................................ 140
- አፄ ቴዎድሮስ ........................................ 145
- አፄ ዮሐንስ 4ኛ ........................................ 151
  - ➢ "ምን ብጠላው በወንድሜ ላይ ደም አልይበት!" ........................................ 152
  - ➢ ካሣ ምርጫ አፄ ከሆኑ በኋላ የወሰዷቸው ርምጃዎች ........................................ 154
  - ➢ ስህተት 1 በወሎ ሙስሊሞች ላይ የወሰዱት ርምጃ ........................................ 156
  - ➢ ስህተት 2 በቤጌምድር ሕዝብ ላይ የፈፀሙት ነውረኛ ተግባር ........................................ 158
  - ➢ ስህተት 3 ከሪር አድሚራል ሔዊት ጋር ያደረጉት ስምምነት ........................................ 161
  - ➢ ስህተት 4 ራስ አሉላን ማጋዛቸው ........................................ 164
  - ➢ ስህተት 5 በጎጃም ሕዝብ ላይ የወሰዱት ያልተገባ ርምጃ! ........................................ 168
- ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ........................................ 175
- አፄ ኃ/ሥላሴ ........................................ 185


## ክፍል አራት


- የበቀል ማስታወሻ ሐውልቶች! ........................................ 190
- ፓርቲዎች ማደሪያዎች ወይንስ ማደናገሪያዎች ........................................ 202
- "ከኔ ወዲያ ላሣር!" ........................................ 211
- ብሔር ብሔረሰቦችና የባንዲራ ቀን! ........................................ 219
- "ልማታዊ መንግሥት!" ........................................ 223
  - ➢ ንፅፅር ........................................ 225
  - ➢ የመሬት ቅርምት ........................................ 231
- ኑ - እንወቃቀስ! ........................................ 236
  - ➢ ብሔራዊ ርቅ ........................................ 236
  - ➢ ዳሞትራ ........................................ 242
  - ➢ ማጠቃለያ ........................................ 244
- ዋቢዎች ........................................ 245




# እንደ መንደርደሪያ

የኢትዮጵያ ታሪክ ከሥር መሠረቱ ሲመረመር የጦርነት ታሪክ ነው:: በመሆኑም የሦስት ሺ ዘመን ታሪካችን በደም የቀለመ ነው:: ታሪካችን የጦርነት ታሪክ በመሆኑም ሥልጣን ርክክቡም በሰላማዊ መንገድ በሕዝብ ይሁንታ ሳይሆን አንዱ ሌላውን ገሎ ወይንም በጦርነት ድል አድርጎ ነው:: ድል አድራጊው በተራው ድል ሆኖ ወይንም ተገሎ፣ ቁናውን በቁና ተሠፍሮ እስከነ ሥልጣኑና ሥርዓቱ ያልፋል:: ታሪካችን እንዲህ እየሆነ በቂምና በበቀል እየተቋጠረ ካንዱ ዘመን ወደ ሌላው ዘመን ወይንም ካንዱ መሪ ወደ ሌላው መሪ በመሸጋገሩ ላለንበት ዘመንም ተስፋን የሚፈነጥቅ ሣይሆን የሚያጨልም ሆኗል::

ያገርን ክብር ላለማስደፈር ከውጭ ወራሪዎች ጋር የተደረጉትን የመከላከል ጦርነቶች ሣንጨምር በሥልጣን ንጥቂያ ምክንያት በየዘመኑ የተካሄዱት ጦርነቶች ይችን አገር ወደ ቴክኖሎጂ እንዳታመራ ደፍቀዋት ቆይተዋል:: ዛሬም ቢሆን ከሰበስ የጦርነት አዙሪት ውስጥ መውጣት አቅቶን ሀገራዊ ኃላፊነት በጎደለው ሁኔታ እየደፈቅናት እንገኛለን:: በጎሣ ሥርዓት የተዋቀረ መንግሥት አገሪቱን እንደ ጎስ ሊያቦናት ተቃርቧል::

በጦርነት ተፀንሰን፣ በጦርነት ተወልደን፣ በጦርነት ያደግን በመሆናችን ለሰላም ያለን ግምት በጣም ዝቅተኛ ነው:: በመሆኑም አምባገነን መሪዎች እንደፈለጉ የሚነዱን ፍጡሮች ሆነናል:: ለምን? እንዴት? ለሚሉት ምክንያታዊ ጥያቄዎች በቂ የሆኑ መልሶች የሉንም:: ርሳስ እንደ ቆሎ እየቆረጠመ ያደገ ፋኖ ቡድን ገንፎ በቅቤ ልዋጥ ቢል ያንቀዋል::

መሪዎችን በወቅቱ መግራትና አቅጣጫ ማስያዝ ባለመቻላችንና ምቹ በመሆናችን በዘመናቸው ሕዝብ የፈለገውን ሳይሆን እነሱ የፈለጉትን ሠርተው እንደፈለጉ ፈንጭተውና አተራምሰው፣ አንዱን ከሌላው አናክሰው ቂምና በቀልን አውርሰው ያልፋሉ:: የኋለኛው አምባገነን መሪ ከፊተኛው ድክመት ወይንም ውድቀት ቅንጣት ሳይማር በደመነፍስ እየተመራ፣ እንደ አደጉት አገራት ተፈጥሮን ሳንገራት እሷ ገርታን የመጨረሻ እጣችን ድህነት ሆነ::

ዛሬ ኢትዮጵያ ጥቂቶች በቁንጣን ጮቤ እየረገጡ የሚፈነጥዙባት ብዙዎች ደግሞ በጠኔ እንደ ቅጠል የሚረግፉባት አገር ሆናለች:: የኑሮ ውድነቱ ብቻ ሳይሆን ልዩነቱ የሰማይና የመሬትን ያህል ተራርቋል::

ለማመንም ያቸግራል፡፡ ጥቂቶች ሰማይ ጠቀስ ፎቆችን ባጭር ጊዜ ውስጥ ሲገነቡ አብዛኛው ሕዝብ ግን አንገቱን የሚያስገባበት ደሳሳ ጎጆ አጥቶ በመኖርና ባለመኖር መሀከል ሆኖ ሲንጠራወዝ ይታያል፡፡ የዚህ መልሱ ቀላል ነው፡፡ አምባገነን መሪዎች ከሥልጣን ላይ ለመቆየት ሲሉ በሚፈበርኩት ጦርነት አምራቹ ኃይል የሆነው ወጣቱ ክፍል በውትድርና እየተመለመለ ስለሚማገድ ነው፡፡ የሚለኮሱት ጦርነቶች ደግሞ የስበስ በመሆናቸው እልህ አስጨራሾችና ያገርን አንጡራ ሀብት እንዳለ የሚያወድሙ ናቸው፡፡

እጅግ የራቁትን የጦርነት ታሪኮች ትተን ከ1953 ዓ.ም ወዲህ ያሉትን ብንጠቅስ እንኳን ያመራባችንና የኋላ ቀርነታችን መንስዔ የስበስ ፍልሚያ ለመሆኑ ቅንጣት የሚያጠራጥረን አይደለም፡፡ የ1953 ዓ.ም ደለውጥ ሙከራ ዓላማ ከዚያ በፊት ይደረጉ የነበሩ የስበስ ደም አፋሳሽ ጦርነቶችን አስቀርቶ በሰላማዊ መንገድ የዘውዱ ሥርዓት ተጠብቆና ሕገመንግሥታዊ አድርጎ አገሪቱ በጠቅላይ ሚንስትር እንድትመራና ወደ ተሻለ የእድገት ጎዳና እንድታመራ ለመደረግ እንደነበር በወቅቱ የለውጥ አራማጆች ይዘዋቸው ከተነሱት ዓላማዎች መረዳት ይቻላል፡፡ ዳሩ ግን የዚህ ዓላማ ያልገባቸውና ቢገባቸውም ከታሪካችን የወረሱት ደም ማፍሰስ በደማቸው ውስጥ አለና የለውጡ ሙከራ በጥቂቶች ተቀልብሶ አሣዛኝ ደም ሊፈስ ችሏል፡፡ በወቅቱ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት (የዛሬው አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ) 15 ከፍተኛ ባለሥልጣናትና ሚንስትሮች መፈንቅለ መንግሥቱን በመሩት ኃይሎች ጭዳ ሆኑ፡፡ በ1967 ዓ.ም ደግሞ የዚህ ቁና ባራት እጥፍ አድጎ 60 ከፍተኛ ባለሥልጣናትና ሚንስትሮች ባሰቃቂ ሁኔታ ተረሽነው ባንድ ጉድጓድ ውስጥ ተቀበሩ፡፡ ከነዚህ ባለሥልጣናት መሀከል አብዛኛዎቹ ልዑል አሥራተ ካሣን ጨምሮ በ53 ዓ.ም የለውጥ እንቅስቃሴ ላይ ቀዝቃዛ ውሃ የቸለሱ ነበሩ፡፡ የዚህ ቁና በነበሩበት የጦር ክፍሎች እንኳን በቅጡ በማይታወቁ የበታች ሹሞችና መሥመራዊ መኮንኖች በሻለቃ መንግሥቱ ኃ/ማርያም (በኋላ ኮሎኔል) በሚመሩ እጅ ላይ ወደቁና ጥፋታቸው ምን እንደሆነ በውል ተለይቶ ሣይታወቅ በጅምላ ተረሽነው ባንድ ጉድጓድ ውስጥ ተከተው አፈር ተመለሰባቸው፡፡ ይህ ዓይነቱ ርምጃም ቂምና በቀልን ለትውልድ አውርሶ አለፈ፡፡

ኢትዮጵያ ገናና አገር እንዳልነበረች ሁሉ 60 ባለሥልጣናት ባንድ ሌሊት ተረሽነው፣ ባንድ ጉድጓድ ውስጥ የመቀበራቸው ሁኔታ እጅግ አስደንጋጭና አሸማቃቂ መሆኑ ብቻ ሣይሆን የኢትዮጵያን ክብርና መልካም ገጽታ ያጎደፈና ያራዊት አገር ያስባለ ነበር፡፡





ደርግ አንድ ዐይና ኢትዮጵያን ሥሎ "ያለ ምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም" በሚል ተስፋን አለምላሚ መርህ ይዞ ቢነሣም በዚህ አቋሙ አልዘለቀም፡፡ ርቅ ሣይቆይ 60ዎቹን በመረሸን ከደም አዙሪት ውስጥ ተዘፍቋል፡፡ ከዚህ በኋላ "አብዮት ልጇን ትበላለች" በማለት ድመት ይመስል ቀንበጦችንና አብረውት የተሰለፉትን ሣይቀር ቆርጥሞ በልቷል፡፡

አምባገነኖች ሥልጣን ላይ ሲወጡ መጠነ ሠፊ ደም አፍሰሰውና ያገርን ንብረት አውድመው ስለሆነ በሰላማዊ መንገድ ሥልጣን መልቀቅን አይሞክሯትም፡፡ እስቲወድቁ ድረስ ግን በሕዝብ ስም እየማሉና እየተገዘቱ፣ የሰላም አየር ባገሪቱ ውስጥ እንዳይነፍስ በሕዝቦች መሀከል ውዥንብር እየነዙ ሰላምን እነሱ አደፍርሰው "ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሃል" እንዲሉ መልሰው እየጮሁ በሉዓላዊነት ስም ዜጎችን በመዋጮና በባዛር ሰንገው በመያዝ እንደ መዥገር ተጣብቀው ንብረቱን ብቻ ሣይሆን ደሙንም ይመጡታል፡፡ ዛሬ ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታም ቁልጭ አድርጎ የሚያሣየን ይህንን ሀቅ ነው፡፡

ደርግ ከ1953 ዓ.ም ውድቀት አንዳች ትምህርት ሣይማር፣ ንጉሠ ነገሥቱን ጨምሮ "ፀረ-አብዮተኞች" የሚላቸውን "በፍየል ወጠጤ" ሽለላ "አድሃሪያን፣ ገንጣይ አስገንጣይ! ያረብ ምንደኞች! ግልገል ፋሽሽቶች! ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም! ፂዮናዊት እስራኤል. . ." በማለት 17 ዓመት ሙሉ አንድን ትውልድ በመንግሥትነቱ መዳኘት ተስኖት ራሱ ግንባር ቀደም ተዋናይ በመሆን በነጭ ሽብርና ቀይ ሽብር አቧድኖ ከጨፈጨፈና ካጨፋጨፈ በኋላ በመጨረሻ በ1981 ዓ.ም በተደረገው የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በዕለቱ ሜጀር ጀኔራል መርዕድ ንጉሤ የጦር ኃይሎች ኤታማጆር ሹምና ሜጀር ጀኔራል አምኃ ደስታ ያየር ኃይል አዛዥ ራሣቸውን ሲገሉ፣ ሜጀር ጀኔራል ፋንታ በላይን በምርመራ ወቅት እጅግ በሚዘገንን ሁኔታ ቀጥቅጠው ገለዋቸዋል፡፡ አሥመራ ላይም እነ ጄኔራል ደምሴ ቡልቱን 102 አየር ወለድ ክፍለ ጦር ከገደላቸው በኋላ ሬሣቸውን ባሥመራ ጎዳናዎች በመጎተት አሣፋሪና አሸማቃቂ ተግባር ፈፅሞባቸዋል፡፡ ይህ ድርጊትም ይችን አገር ደግሞ ያረመኔዎች አገር ያስባለና አንገት ያስደፋ ነበር፡፡ ቀሪዎቹን 12 ጀኔራሎችም ለታሪክ ምስክርነት እንዳይተርፉ በፍርድ ስም መንግሥቱ ኃ/ማርያም ረሽነዋቸዋል፡፡

በመጨረሻም ይህንን ሁሉ ጥፋት ካደረሱ በኋላ የደርጉ ቁንጮ ፕሬዚዳንት መንግሥቱ ኃ/ማርያም እንዳንበሣ ባገሱባት አገር እንደ ዉሻ ጅራታቸውን ሸጉጠው ወደ ሀራሬ ኮበለሉ፡፡ የቀሩትም ባገኙት አጋጣሚ

ሁሉ ወደ ጎረቤት አገራትና “ኢምፔሪያሊዝም” እያሉ ሲያወግዟት ወደ ነበረችው አሜሪካን ፈረጠጡ፡፡ የመሹለኪያ ቀዳዳ ያላገኙት ደግሞ የሰላም ስንቅ ሣይኖራቸው፣ እንደ ተዝረከረኩ አሁን በሥልጣን ላይ ላሉት እጃቸውን ሰጡ፡፡ ይህ ተግባራቸውም የሚያመለክተን ቀናውን በቁና መሰፈርን ነው፡፡

ከዚህ ላይ ግን ደርግን ብቻ አገር አጥፊ ብሎ መውቀስ አግባብ አይደለም፡፡ ሁሉም የድርሻውን ማንሣት አለበት፡፡ በተለይም መኢሶንና ኢሕአፓ የጎላ ድርሻ ነበራቸው፡፡ ይህንን ሀቅ ዛሬ መካድ አይቻልም፡፡ ዋናው ነገር ይኸ ሁሉ በዚያን ጊዜ ሆኖ አልፏል፡፡ ዛሬ ነው ዛሬን ሆኖ ማለፍ ያልቻለው፡፡ የሚያስቆጨው ደግሞ ካለፉት ስህተቶች ቅንጣት መማር አለመቻላችን ነው፡፡ ምን ይሻላል? እንጠያየቅ፣ እንመካከር፣ የመመካከሪያው ጊዜው አሁን ነው፡፡ ከዚህ በተረፈ የበረደውን ታሪክ ትተን ወደ ትኩሱ እንሸጋገር፡፡

መልካም ንባብ፡፡

<><><>





# ክፍል አንድ

*“ሥንቅና ውሸት እያደር ይቀላል” አበው*

## በዋዜማው

የ2004 ዓ.ም አየር ፀባይ እንደ መሪዎቹ ከፍቷል፡፡ በጋውን በሙሉ ፀሐያማና ርጥበት አዘል አየር ያልታየበት ወቅት ነበር፡፡ በልግ አብቃይ አካባቢዎች እንኳን ጠብታ ዝናብ አላዩም፡፡ አገሪቱን ተደጋጋሚ ድርቅ የመታት በመሆኑ አሁንም ይመታት ይሆን የሚል ሥጋትን ፈጥሮ አልፏል፡፡

ከተፈጥሮ ድርቅ ጎን ለጎንም አገሪቱን ማኅበራዊ ድርቅ እያነኮታት ነው፡፡ በፍትሕ እጦት፣ በፍርድ መዛባት፣ በሙስና ዝቅጠት ቀውስ ውስጥ ተዘፍቃ መልሕቅ እንደሌላት መርከብ እየዋዠቀች ትገኛለች፡፡ ይህነኑ የፍትሕ እጦትና የሙስና ዝቅጠት ታንዛኒያ የሚገኘ “ኪሊማንጃሮ” የተባለ ድርጅት አምስት መንግሥታዊ ተቋማትን በመውሰድ የሥርዓቱን ብልሹነት አጋልጧል፡፡

ባገሪቱ ውስጥ ፍትሕ ከመጥፋቱና ባለሥልጣናት ሙስና ውስጥ መዘፈቃቸውን ጠ/ሚንስትር መለስ ዜናዊ አምነው በተወካዮች ም/ቤት ባስሙት ንግግር “የመንግሥት ሌቦች” ሲሉ በምሬት ገልፀዋቸዋል፡፡

ፍትሕና ርትዕ ከመጥፋቱ የተነሳ ዜጎች በምሬት ከላያቸው ላይ ቤንዚን እያርከፈከፉ ክብሪት በመጫር ራሳቸውን እያቃጠሉ ተሰውተዋል፡፡ ለምሳሌ፡- በደቡብ ክልል ደውሮ ዞን ዋካ ከተማ መምህር የኔሰው ነብሬ የተባለ ወጣት ህዳር ၊ ቀን 2004 ዓ.ም በራሱ ላይ ቤንዚን አርከፍክፎ

ከብሪት ጭሮ በመለኮስ ራሱን አቃጥሎ ገሏል፡፡ መምህር የኔሰው ገብሬ ይህንን አሰቃቂና ዘግናኝ ርምጃ በራሱ ላይ ለመውሰድ የተገደደው እስከ ጠ/ሚኒስትሩ ድረስ በየደረጃው አቤት ቢልም ለደረሰበት በደል መልስ የሚሠጠው ባለሥልጣን በማጣቱ ተስፋ ቆርጦ ነው፡፡ የሚያሣዝነው ደግሞ የዞኑ ባለሥልጣናት "ብሔሩ ኦሮሞ እንደሆነና አእምሮው ንክ ነበር" ማለታቸው ነው፡፡ ኦሮሞ ይሁን አማራ፣ ትግሬ ይሁን ሌላ የኔሰው ገብሬ ቢያንስ ሰው በመሆኑ እንደ ሰው ሊታዘንለት የሚገባ ዜጋ ነበር፡፡ እንደ ዜግነቱም ፍትሕ ማግኘት ነበረበት፡፡ ከሞተ በኋላ "አእምሮው ንክ ነበር" ማለት ግን አሥከሬኑን ጥላሸት መቀባት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የኢህአዴግ ዋነኛ ባህሪው ነው፡፡ አንድ ጊዜ ብቻ ሣይሆን ሬሣንም ዳግም ጥላሸት በመቀባት ይገላል፡፡



*ራሱን አቃጥሎ የገደለው መምህር የኔሰው ገብሬ*

ፍትሕ ባገሪቱ ውስጥ ከመጥፋቱ የተነሳ እንደ የኔሰው ገብሬ ዓይነት ተመሳሳይ ርምጃ የወሰዱ ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ደብረማርቆስ ከተማም አንድ ዜጋ እንዲሁ በፍትህ እጦት ራሱን አቃጥሎ ገሏል፡፡ ከዚህ አዲስ አበባም






ጊዮርጊስ አደባባይ አንድ ፖሊስ ከመደበኛ ሥራው በመባረሩ በጠራራ ፀሐይ አንድ ቆርቆሮ ቤንዚን በላዩ ላይ አርከፍክፎ ከብሪት ጭሮ በመለኮስ ራሱን አቃጥሎ የካቲት 12 ሆስፒታል ገብቶ ተሰቃይቶ ሕይወቱ ሊያልፍ ችሏል፡፡ ይህ ዜጋ በእሳት እየተለበለበ እንዳለ "ራበኝ፣ የምበላው አጣሁ!" እያለ ሲጮህ ባቅራቢያው የነበሩ ሰምተውታል፡፡

በኑሮ ውድነት፣ በፍትሕ እጦት እየተማረሩ አንገታቸውን በገመድ እየሸመቀቁ የሚገሉም እየተበራከቱ መጥተዋል፡፡ ከፍትሕ ድርቀቱ እየከፋ መምጣት የተነሣ ከተጠቀሱት ለየት ያለ ርምጃ ለመውሰድም የሞከሩ ዜጎች አልታጡም፡፡

በዚሁ በደቡብ ክልል ዳውሮ ዞን የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰው ኃይል ኃላፊ የነበሩት አቶ ብሩክ አየለ የተባሉ "ፍትሕ አጣሁ" በማለት ፍ/ቤቱ ግቢ ውስጥ ካለ ረጅም ዛፍ ላይ እንደ ጦጣ ወጥተው "በዚች አገር የፍትሕ ሥርዓት እስካልሰፈነ ድረስ አልወርድም" በማለት ያካባቢውን ሕዝብ ማስጨነቃቸውን (*ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ቅፅ2 ቁጥር 37 ማክሰኞ ሚያዝያ 2 ቀን 2004 ዓ.ም*) ለንባብ አብቅታለች፡፡

ሌላው ከከፋ ጊዜ ላይ የመድረሣችን ምልክቱና በዚህ ዘመን ሰው ሆኖ መፈጠርን የሚያስጠላው አስከሬን በመኪና ተጎትቶ መጥቶ መሀል ከተማ ተሰጥቶ ውሎ እንደገና መሠቀሉ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ አሠቃቂ ርምጃ ዜጎች በፍርሃት ሰጥ ለጥ ብለው እንዲገዙ መቀጣጫ ለማድረግ ነው፡፡ በጥንቱ ልማድ ከፍተኛ ጥፋት አጥፍተዋል የተባሉ ሰዎች የሚወሰንባቸው የቅጣት ዓይነት እስከነ ሕይወታቸው ያጠፉት ጥፋት በግልጽ ተነግሮ ለመቀጣጫኔት ባደባባይ መስቀል ነበር፡፡ ከሞቱ በኋላ አሥከሬን በመኪና መጎተትና እንደገና ከዛፍ ላይ መስቀል ግን ሥርዓቱ በራሱ የሞተ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ይህ ባሥከሬን መጫወት ባገራችንም ሆነ በሰው ልጅ ባህሪ የተለመደ አይደለም፡፡ ይህንን እኩይ ተግባር ግልጽ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ እንዲህ ነው፡-

በግንቦት ወር 2004 ዓ.ም በሰሜን ጎንደር ታች አርማጭሆ ሳንጃ ከተማ አካባቢ አቶ ሸንከሩ ከፍ ያለውና አቶ ዳኛቸው አያሌው የተባሉ ሁለት ግለሰቦች ከፀጥታ ኃይሎች ጋር ባደረጉት የተኩስ ልውውጥ ይገደላሉ፡፡ ፖሊስ ግዳይ ስለቀናው አስከሬናቸውን በመኪና እየጎተተ አምጥቶ ሳንጃ ከተማ በማጋደም ሕዝብ እንዲመለከታቸው አድርጓል፡፡ በወቅቱ የዳኛቸው አባትና እናት እንዲሁም አያቶች ነበሩ፡፡ በስሜት እየተናጡ ለማልቀስ



*ራሱን አቃጥሎ የገደለው መምህር የኔሰው ገብሬ*

ሲሞክሩ በቆመጥ ቀምሰዋል፡፡ የሟቾች ወላጆች አስከሬኑን ወስደው ለመቅበር ጠይቀው ተከልክለዋል፡፡ በመጨረሻ ፲፩ ሰዓት ላይ እግራቸው በገመድ ታስሮ ከፖሊስ ጣቢያው ጀርባ ካለ ዛፍ ላይ ጭንቅላታቸውን ወደታች ዘቅዝቆ ፖሊስ ሰቅሏቸዋል፡፡ ይህ ዓይነቱ አሰቃቀልም የጭካኔ መገለጫ ይሆን እንደሆነ እንጂ የተለመደና የሰው ልጅ ባህሪ አይደለም *(ፍኖተ ነፃነት ቅፅ 2 ቁጥር 45 ማክሰኞ ግንቦት 28 ቀን 2004 ዓ.ም)*

ከፍ ብዬ የገለፅኩትን የጭካኔና የበቀል ርዝመት እግዚአብሔር በውኑ ገና ከመጀመሪያው ለምን የሰውን ልጅ የፍጥረታት ሁሉ የበላይ ገዥ አድርጎ በመፍጠሩ በጣም መፀፀቱን ኦሪት ዘፍጥረት ምእራፍ 6፣ ቁ 6-7 ተመልክቷል፡፡ ሌላ ማስረጃም ልጨምር፡-

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ሲፈጥር ተቃራኒ ፆታዎች አድርጎ ነው፡፡ ይህም መልካም ነገር ነበር፡፡ ይህ ግን በውኑ ፈርሷል፡፡ ተመሳሳይ ፆታዎች ጋብቻ እየፈፀሙ ናቸው፡፡ እነዚሁ ግብረ ሠዶማውያን በ2004 ዓ.ም በተቀደሰችና በተባረከች አገራችን መጥተው ስብሰባ አካሂደው የልባቸውን ሠርተው እነሱም ተሠርተው በክብር ተመልሰዋል፡፡

ሌላው የ2004 ዓ.ም የሕዝብ ንቅናቄ ዓወሊያ ት/ቤት የተጫረው የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ሃይማኖታዊ ነፃነታችን ይከበርልን ጥያቄ ነው፡፡ ይህ ንቅናቄ እጅግ የሰከነና ጥበብ የተሞላበት በመሆኑ የፀጥታ ኃይሎችን ቆመጥና የሥርጎ ገብ የደህንነት አባላትን ተንኮል ተቋቁሞ ሳይከፋፈል መዳዝ እስከቻለበት ጊዜ ድረስ ተጉዟል፡፡ መንግሥት እንደተለመደው የተለያዩ ድራማዎችን በመሥራት ለመከፋፈል ቢሞክርም አልሆነለትም፡፡ የመምህራን የደመወዝ ርከን ማስተካከያ ጥያቄም ሌላው ያሙቱ ክስተት ነበር፡፡ ይህ የመምህራን የደመወዝ ይጨመርልን ጥያቄ ቁጥራቸው በትክክል ያልታወቁ መምህራንን ከመደበኛ የማስተማር ሥራቸው ላይ አፈናቅሏል ወይንም ለመቀጣጫነት ከሥራቸው ተባረዋል፡፡

መንግሥት እንደ መንግሥትነቱ በጨዋነት "የመምህራኑ ጥያቄ ተገቢ ቢሆንም ባሁኑ ወቅት ደመወዝ ለመጨመር ያገሪቱ አቅም አይፈቅድም" ብሎ ባጭሩ መልስ መሥጠት ሲችል ጠ/ሚንስትሩ በተወካዮች ም/ቤት የመምህሩን ክብር በሚነካና በሚያዋርድ መልኩ እያበሻቀጡ በቁጣና በግለት ዘልፈዋል፡፡ ከዚህም ባለፈ ብዙዎች ከሥራ ገበታቸው በመፈናቀላቸው ምክንያት "ይቅርታ ጠይቁ" እየተባሉ ዳግም ውርደትና ሞት እንዲሸከሙ ተገደዋል፡፡ ይህ የከፋ ርምጃ ለመምህሩ ብቻ ሣይሆን ለሌሎች ዜጎችም





የወዮላችሁ የማስጠንቀቂያ ደወል ጭምር እንደሆነ ነው የሚታወቀው፡፡ የኢህአዴግ በትር ሁልጊዜ አንድን ሰው ሲፈነክት ሺዎች እየተሸማቀቁ አንገታቸውን ደፍተው እያማጡ እንዲኖሩ ዒላማ የሚያደርግ ነው፡፡

በሦስተኛ ደረጃ የ2004 ዓ.ም አብይ ንቅናቄ የዋልድባ ገዳም መነኮሣት የድረሱልን ጩኸት ነው፡፡ መንግሥት የገዳሙን ዙሪያና ከፊል የገዳሙን ይዞታ "ለሥኳር ፋብሪካ እፈልገዋለሁ" በሚል መነኮሣቱንና መናኒያኑን "ልቀቁልኝ" በማለቱ አሣዝኗል፡፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምሮ የተገደመን ገዳምና የምንኩስና ሥርዓት ለመጀመሪያ ጊዜ የተከናወነበትን የተቀደሰ ቦታ ደፍሯል፡፡ ይህንንም እኩይ ተግባር መነኮሣቱ ባለች ደካማ አቅማቸው ተቃውመዋል፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች፣ ለዜና አውታሮች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው የድረሱልን ጥሪም አሰምተዋል፡፡ ይህንን በማድረጋቸውም "ፀረ - ሰላም ኃይሎችና ሽብርተኞች" እየተባሉ በሚያሣፍር መልኩ ታስረዋል፤ ተንገላተዋል፤ ከዚህ አዲስ አበባ ድረስ ወኪሎቻቸውን ልከው ለጠቅላይ ቤተ ክህነት አቤት ቢሉም ሰሚ አላገኙም፡፡ ከዚህ በኋላ መነኮሣቱ ፍርዱ ወደ ማይዛባበቱ አምላክ መስቀላቸውን ዘቅዝቀው ሱባዔ መግባት ነበር፡፡ ሆኖ ያለፈውም ይኸው ነበር፡፡

ኢህአዴግ ካላጣው ቦታና መሬት ይህንን ዕድሜ ጠገብ የሆነ የተቀደሰ ገዳም ለምን ደፈረ? የሚለውን ጥያቄ መልሱን የሚያውቁት አንጋፋው ተጋዳላይ ዓባይ ፀሐይዬ ናቸው፡፡ በነገራችን ላይ ገዳም ማለት በግዕዝ ቋንቋ ደን፣ ጥቅጥቅ ያለ ጫካ፣ ማንም የማይደፍረው የተቀደሰ ቦታ ማለት ነው፡፡ በኢሕአዴግ ጊዜ ግን ተደፈረ፤ ረከሰ፤ ተናቀ፤ ለመሆኑ የሃይማኖት አባቶች ከፓትሪያሪኩ ጀምሮ በተዋረድ ያሉት አባቶች ይህ የተቀደሰ ቦታ ሲደፈር ምን አሉ? ለምንስ ዝም አሉ? ብለን ብንጠይቅ መልሱ የዚህ ዘመን ጳጳሣት በቆባቸው ስር ያለው ክፋትና ኅሰኝነት በእምነቱ ላይ አጥልቶበታል የሚል ይሆናል፡፡

አንዳንድ አዛውንቶች እንደሚሉት ከሆነ፣ መንግሥት ይህንን የሩቅ ጊዜ የተከበረ ገዳም ለማፍረስና በውስጡ ቅጠል በልተው፣ ቅጠል ለብሰው፣ ከከፋት ርቀው፣ በፆም በፀሎት የሚኖሩ መነኮሣትና መናኒያንን መኖሪያ አሣጥቶ ለማጥፋት ታጥቆ የተነሣበት ምክንያት የሦስት ሺ ዘመን ታሪክ ያላትን አገር ቅርሳቅርሶቿንና አሻራዎቿን ከታሪክ መደለዝ ጀምሮ ፍቆ ለማጥፋት አልሞ የተነሳው ፋኖ ከነበረበት ጊዜ አንስቶ በ21 ዓመታት የሥልጣን ዘመኑ ያልፈነቀለው ድንጋይ ያልቆፈረው ጉድጓድ የለም ይላሉ፡፡

የዚህ እኩይ ተግባር ሰለባ የሆነው አንዱ የዋልድባ ገዳም መሆኑ ነው። ኢሕአዴግ እስካሁን እንዳየነው ከሆነ የኢትዮጵያን ነባር አሻራዎች ከምድረ ገጽ አጥፍቶ የራሱን አሻራ ለመትከል ከዜሮ ተነስቶ በሱ ቋንቋ "አዲሲቷ ኢትዮጵያ" የሚላትን ለመፍጠር ነው። ይህንን በተመለተከ ወደፊት ደረጃ በደረጃ የምናየው ይሆናል።

አራተኛው የ2004 ዓ.ም አሣዛኝ ክስተት የኢትዮጵያን ሕዝብ ሕሊና ያደማና የዓለምን የመገናኛ ብዙሃን ትኩረት የሳበው የጉራፈርዳ ኗሪዎች (አማርኛ ተናጋሪ ዜጎች) ባቶ ሽፈራው ሽጉጤ የደቡብ ክልል ፕሬዚዳንት ቀጥታ ትእዛዝ ባንድ ቀን ብቻ በሺዎች የሚቆጠሩ ከኖሩበት አካባቢ ቤት ንብረታቸውን እየተነጠቁ መባረራቸው ነው። በዚህ ዜጎችን ለረጅም ጊዜ ከሚኖሩበት ቀየ የማባረር ዘመቻ አንዲት እናት በወለደችበት ዕለት ደሟን እያንጠባጠበች አዲስ አበባ ገብታለች። አንድ ወጣትም እየተደበደበ መኪና ላይ ቢጫንም በደረሰበት ድብደባ ተበሣጭቶ ከመኪናው ላይ ተወርውሮ በመፈጥፈጥ ራሱን ገሏል።

አቶ ሽፈራው ሽጉጤ ይህንን ዜጎች ከሚኖሩበት ቀየ ለቃችሁ ውጡ ትእዛዝ ሲያስተላልፉ በራሳቸው አነሣሽነት እንዳልሆነ በግልጽ ይታወቃል። ይሁ·ባይሆንማ ኖሮ የፌደራል መንግሥት ለምን ዝምታን መረጠ? "ያማራ ወኪል ነኝ" የሚለው ብአዴንስ ለይስሙላ እንኳን ለምን ድምፁን አላሰማም?

እነዚህ በገዛ አገራቸው ስደተኞች እንዲሆኑ የተፈረደባቸው ዜጎች ወንጀል በ1997 ዓ.ም እና በ2002 ዓ.ም አገር አቀፍ ምርጫዎች ኢሕአዴግን አልመረጣችሁም የሚል እንደሆነ ስደተኞቹ ራሳቸው በሥሬት ይገልፃሉ። ይህንን የዘር ማፅዳትና የጥፋት መንገድ አንድነት ፓርቲ በወቅቱ "ዜጎችን የማፈናቀልና የማባረር ተግባር ባስቸኳይ ይቁም!" በሚል ርእስ በፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ (በፓርቲው ልሳን) ቅጽ 2 ቁጥር 36 ማክሰኞ መጋቢት 25 ቀን 2004 ዓ.ም በርዕሰ አንቀጹ ላይ የሚከተለውን አስፍሯል፦

*"ገዥው ፓርቲ ሲያስፈልግ ብቻ እንደ ላንቲካ የሚጠቀስ ግን ደግሞ አንድ ሺ አንድ ጊዜ የሚረግጠውንና የሚደፈጠጠውን፣ ሲያሻው ደግሞ የሚቃወሙትን ለማጥቂያነት የሚያወጣውን ሕግ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የመዘዋወር መብት አንቀጽ 32 እንዲህ ይላል ‹ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይንም በሕጋዊ መንገድ አገሪቱ ውስጥ የሚገኝ የውጭ ዜጋ በመረጠው የሀገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የማግኘት እንዲሁም በፈለገው ጊዜ ከሀገር የመውጣት ነፃነት አለው› ይላል። ይህንን የማንኛውም ኢትዮጵያዊ ብቻ ሣይሆን ለውጭ ዜጋም የተሰጠን የመዘዋወር፣ ሀብት የማፍራት መብት ገዥው ፓርቲ የጣሰው ዛሬ ብቻ አይደለም። ካለፉት 21 ዓመታት በኢሕአዴግ ዕድሜ ልክ አብሮ ኖሯል። . . . ቤንች ማጅ ዞን ጉረፋርዳ ወረዳ ብቻ 22 ሺ የሚሆኑ አርሶ አደሮች እንዲወጡ እንደተፈረደባቸው ከራሳቸው ከተፈናቃዮቹ አንደበት ያገኘነው መረጃ ያመላክታል። . . . ምን እየተከናወነ እንደሆነ ምንም የማያውቁ ግን ደግሞ ነገ ‹ሀገሬ የት ነው?› ብለው የሚጠይቁ ህፃናትን ጠውልገው ማየት በጣም ያማል። . . . እነዚህ ዜጎች ቤተክርስቲያን ለመጠለል ሲገቡ በፖሊስ እየተገፈተሩ እንዲወጡ መደረጋቸውን ከተበዳዮቹ ሰምተናል. . ."* በማለት አንድነት በስፋት ከዘረዘረ በኋላ በመጨረሻ ተፈናቃዮቹ የደረሰባቸውን በደል ለኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት እንዲሁም ያማራ ሕዝብ ወኪል ነኝ ለሚለው ብአዴን እንዲያውቁት ጥሪውን አስተላልፏል። ለጥሪው መልስ የሰጠ አካል ግን አልነበረም። ብአዴንም ለነሱ ጆሮ የለውም። ብአዴን አማርኛ ተናጋሪ የሕወሓት ከንፍ እንጂ ያማራ ሕዝብ ወኪል አለመሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንቅቆ ያውቀዋል። ለዋልድባ ገዳምም ሆነ ለጉረፋርዳ ተፈናቃዮች ፈጥኖ የደረሰላቸው አንድዮ ብቻ ነው።

<><><>

# እንደ ንግርት

ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም ጀግናው ሕወሓት ኢትዮጵያን ከደርግ ላይ የተረከበበት እለት ነበር:: ከ21 ዓመታት በኋላ ግን የግንቦት ወር ለሕወሓት ታጋዳላዮች የተመቸች ወር አልሆነችም:: ከድርቄ ብርታት የተነሣ ንቦቹ የሚቀስሙት አበባ አላገኙም::

ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም አሜሪካን አገር በሬገን ማዕከል የቡድን ስምንት አገራት መሪዎች "የምግብ ዋስትናን" በተመለከተ ታላቅ ጉባዔ ከፍተው ነበር:: በዚህ ታላቅ ጉባዔ ላይ የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ዜናዊ ተገኝተው ነበር:: ተራ ደርሷቸው መናገር ሲጀምሩ ባልተጠበቀና ይሆናል ተብሎ ባልተገመተ ሁኔታ ካዳራሹ ውስጥ በምብ የተወረወረ ያህል የሚያስደነግጥ ነጎድጓዳማ ድምጽ ተሰማ:: በመጀመሪያ በእንግሊዘኛ ቀጥሎ ባማርኛ በመጮህ አዳራሹን አናጋው::


"Meles Zenawi is a dictator! Meles Zenaw is a dictator! Food without Freedom is nothing!"(**መለስ ዜናዊ አምባገነን ነው! መለስ ዜናዊ አምባገነን ነው! ምግብ ያለ ነፃነት ምንም አይደለም!"**) በማለት እንደ ብራቅ በመጮህ የተሰብሳቢዎችን ቀልብ ባንድ ጊዜ ለመቆጣጠር ችሏል:: ያድምፅ በስደት የሚኖረው የጋዜጠኛ አበበ ገላው ድምፅ ነበር:: ያ ድምፅም የኋላ ኋላ ከላይ የታዘዘ የንግርት ድምፅ እንደነበር በብዙዎች ታምኖበታል::



*ጋዜጠኛ አበበ ገላው*








*ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በቡድን 8 ጉባዔ ላይ*

የጠቅላይ ሚንስትር መለስን በቡድን 8 ጉባዔ ላይ መገኘትን በተመለከተ ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ግንቦት 14 ቀን 2004 ዓ.ም በቅጽ 2 በቁጥር 43 እትሟ "ኮንግረስ ማን ክሪስ ስሚዝ አቶ መለስ ቡድን 8 ጉባዔ ላይ መገኘታቸውን አወገዙ" በሚል ርእስ የባለሥልጣኑን ሐሳብ እንደሚከተለው አሥፍራ ነበር:-

*"የቡድን 8 አገራት ጉባዔ ላይ አቶ መለስ ዜናዊ መገኘታቸው ከጉባዔው ዓላማ ጋር ይቃረናል:: . . . ፕሬዚዳንት ኦባማ የቤኒን፣ የጋናና የታንዛኒያ መሪዎች ጋር በመሬት ቅርምትና በሰብዓዊ መብት ጥሰት የሚኮነኑትን ጠ/ሚንስትር መለስ ዜናዊንን መጋበዛቸው ከጉባዔው መንፈስ ጋር አይሄድም" የጥቅሱ መጨረሻ::*



*ኮንግረስ ማን ክሪስ ስሚዝ*

# እንደ ንግርት

ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም ጀግናው ሕወሓት ኢትዮጵያን ከደርግ ላይ የተረከበበት እለት ነበር። ከ21 ዓመታት በኋላ ግን የግንቦት ወር ለሕወሓት ተጋዳላዮች የተመቸች ወር አልሆነችም። ከድርቁ ብርታት የተነሣ ንቦቹ የሚቀስሙት አበባ አላገኙም።

ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም አሜሪካን አገር በሬገን ማዕከል የቡድን ስምንት አገራት መሪዎች "የምግብ ዋስትናን" በተመለከተ ታላቅ ጉባዔ ከፍተው ነበር። በዚህ ታላቅ ጉባዔ ላይ የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ዜናዊ ተገኝተው ነበር። ተራ ደርሷቸው መናገር ሲጀምሩ ባልተጠበቀና ይሆናል ተብሎ ባልተገመተ ሁኔታ ካዳራሹ ውስጥ በምብ የተወረወረ ያህል የሚያስደነግጥ ነጎድጓዳማ ድምጽ ተሰማ። በመጀመሪያ በእንግሊዘኛ ቀጥሎ ባማርኛ በመጮህ አዳራሹን አናጋው።


"Meles Zenawi is a dictator! Meles Zenaw is a dictator! Food without Freedom is nothing!"(መለስ ዜናዊ አምባገነን ነው! መለስ ዜናዊ አምባገነን ነው! ምግብ ያለ ነፃነት ምንም አይደለም!") በማለት እንደ ብራቅ በመጮህ የተሰብሳቢዎችን ቀልብ ባንድ ጊዜ ለመቆጣጠር ችሏል። ያ ድምፅ በስደት የሚኖረው የጋዜጠኛ አበበ ገላው ድምፅ ነበር። ያ ድምፅም የኋላ ኋላ ከላይ የታዘዘ የንግርት ድምፅ እንደነበር በብዙዎች ታምኖበታል።



ጋዜጠኛ አበበ ገላው








ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በቡድን 8 ጉባዔ ላይ

የጠቅላይ ሚንስትር መለስን በቡድን 8 ጉባዔ ላይ መገኘትን በተመለከተ ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ግንቦት 14 ቀን 2004 ዓ.ም በቅጽ 2 በቁጥር 43 እትሟ "ኮንግረስ ማን ክሪስ ስሚዝ አቶ መለስ ቡድን 8 ጉባዔ ላይ መገኘታቸውን አወገዙ" በሚል ርእስ የባለሥልጣኑን ሐሳብ እንደሚከተለው አሥፍራ ነበር፦

*"የቡድን 8 አገራት ጉባዔ ላይ አቶ መለስ ዜናዊ መገኘታቸው ከጉባዔው ዓላማ ጋር ይቃረናል። . . . ፕሬዚዳንት ኦባማ የቤኒን፣ የጋናና የታንዛኒያ መሪዎች ጋር በመሬት ቅርምትና በሰብዓዊ መብት ጥሰት የሚኮነኑትን ጠ/ሚንስትር መለስ ዜናዊን መጋበዛቸው ከጉባዔው መንፈስ ጋር አይሄድም" የጥቅሱ መጨረሻ።*



*ኮንግረስ ማን ክሪስ ስሚዝ*

ኮንግረስ ማን ክሪስ ስሚስ ያሜሪካን ኮንግረስ ማን፣ ያፍሪካ የዓለም ጤናና ሰብዓዊ መብቶች ንዑስ ኮሚቴ ሊቀመንበር ናቸው:: እኒህ ባለሥልጣን አቶ መለስ በ1997 ዓ.ም በሰላማዊ ዜጎች ላይ በፈፀሙት ግድያና በሰፊው በሚያካሂዱት የሰብዓዊ መብት ረገጣ ምክንያት ማዕቀብ እንዲጣልባቸው የሚያስችል ረቂቅ ያቀረቡ ሰው ነበሩ::

ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ዜናዊ ባበበ ገላው መፈከር መደንገጣቸውና ኮስሰው መታየታቸው እውነት ነው። ለደቂቃዎችም ቢሆን ንግግራቸውን አቁመው አንገታቸውን ደፍተው ሲቆዝሙ ተስተውለዋል::

ጠ/ሚንስትሩ እንደ ተሽማቀቁ ወደ አገር ቤት ቢመለሱም ዳግም ወደ መድረክ ብቅ ብለው አልታዩም:: ተውሎ ታድሮም ታመው ለህክምና ወደ ውጭ አገር እንደ ሄዱ በሹክሹክታ መወራት ተጀመረ:: የት አገር? የት ሆስፒታል? የተቸነከረ ምስጢር ነበር:: ጋዜጠኞች ግን እውነቱን ፈልፍለው ለሕዝብ ለማሣወቅ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ባለሥልጣናት ሰንገው ያዙ:: አቶ ሽመልስ ከማል የኮሙኒኬሽን ሚንስትር ዲኤታ ስለጠቅላይ ሚንስትር መለስ ህመም ማብራሪያ እንዲሰጡ ሲጠየቁ "ይህ የኢሳትና የእሳት ወሬ ነው" ሲሉ ሽመጠጡ:: እንዲህ እንዲህ እየተባለ የተጨበጠ ነገር ሳይገኝ ያፍሪካ ሕብረት 19ኛ የመሪዎች መደበኛ ጉባዔ ሐምሌ 7 ቀን 2004 ዓ.ም ከዚሁ አዲስ አበባ ሲካሄድ ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ዜናዊ አለመገኘታቸውና በምክትላቸው ባቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ መወከላቸውን ተከትሎ የሴኒጋሉ ፕሬዚዳንት ማኪ ሳቤ "አቶ መለስ በገጠማቸው ህመም ምክንያት በመሀከላችን ባይገኙም ፈጣሪ ምህረቱን ይስጣቸው!" በማለት ድብቁንና በሹክሹክታ ይወራ የነበረውን ይፋ አደረጉት:: ከዚህ በኋላ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ሚንስትሩ አቶ በረከት ስምዖን በተከታዮቹ ቀናት "ታመው ነበር፤ በቅርብ ቀን ድነው ሥራቸውን ይጀምራሉ" ሲሉ ግልጽነት የጎደለው የተውገረገረ መልስ ሰጡ::

ትንሽ ተሰነባብቶ ደግሞ በውጭ የሚኖሩ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን "እመኑን ጠቅላይ ሚንስትሩ ሙተዋል!" ሲሉ ርግጠኞች በመሆን በተለያዩ የመገናኛ አውታሮች አሠራጩ:: ይህንኑ ዜና ዋቢ በመጥቀስ ፍትሕ ጋዜጣ 30,000 ቅጅ ለማሣተም ብርሃንና ሰላም ድርጅት ከፍያ ፈፅመው እንዳትታም በመታገዷ ድርጅቱ ከ80 ሺ ብር በላይ ኪሣራ እንደ ደረሰበት የዝግጅት ክፍሉ ጋዜጠኞች አስታወቁ:: የኋላ ኋላም ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣም የፍትህ እጣ ደረሰባት::





ይህ በእንዲህ እንዳለ መታመማቸው እንኳን በቅጡ ሳይሰማ ፓትሪያርኩ ብፁእ ወቅዱስ አባ ጳውሎስ ነሐሴ 10 ቀን 2004 ዓ.ም ድንገት ማረፋቸውን የብዙሃን መገናኛዎች ይፋ አደረጉ:: አሟሟታቸውን በተመለከተ የፓትሪያሪኩ የቅርብ ረዳት የሆኑ አንድ አባት እንደገለፁት ከሆነ እሁድ ነሐሴ 6 ቀን ራሳቸው ቀድሰው፣ ሰኞና ማክሰኞ ደግሞ ቁመው አስቀድሰው እንደነበርና ማክሰኞ ወደ ማታ ገደማ ባልቻ ሆስፒታል ገብተው ረቡዕ እኩለ ሌሊት ላይ የፃዲቅ ሞት መሞታቸውን እንባ እያነቃቸው መጠነኛ ማብራሪያ ሰጡ:: ፓትሪያሪኩ ነሐሴ 17 ቀን 2004 ዓ.ም ታላላቅ የሃይማኖት መሪዎች ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናትና የእምነቱ ተከታዮች በተገኙበት በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ቤተክርስቲያን ሥርዓተ ቀብራቸው ተፈፅሟል::

<><><>

# የጠ/ሚንስትሩ ዜና ረፍት

ማክሰኞ ነሐሴ 15 ቀን 2004 ዓ.ም ከመስንበቻው ትንሽ ፈታ ያለ ቀን ነበር፡፡ ጧት ለሥራ ጉዳይ 4 ኪሎ አካባቢ ስለነበርኩ ሬዲዮ የማዳመጥም ሆነ ቴሌቪዥን የማየት እድሉ አልነበረኝም፡፡ 3 ሰዓት ላይ አንድ ጓደኛዬ ሞባይሌ ላይ ደውሎ፡- "ሰማህ?" አለኝ፡፡

"ምኑን?" ስል መልሼ ጠየኩት፡፡

"ጠቅላይ ሚንስትሩ አረፉ!" አለኝ፡፡

"ማን ነገረህ? እንዴት አወክ?"

"አሁን በሬዲዮ እየተነገረ ነው፡፡ ካንድ ቡና ቤት ጎራ በልና ተከታተል" አለኝ፡፡ እውነትም አርበኞች ሕንፃ ሥር ካለው ካፍቴሪያ ቁጭ ብዬ ቡና አዘዝኩና መከታተል ያዝኩኝ፡፡ የሐዘን ማርሹ፣ ዋሽንቱ አንጀት በሚበላ መልኩ ይተላለፋል፡፡ የሐዘን እንጉርጉሮውና የሐዘን ማርሹ ባጭር ጊዜ ውስጥ የተዘጋጀ አይመስልም፡፡ ጊዜ ተወስዶ የተቀናበረ ነው የሚመስለው፡፡

ከዚያው ካፍቴሪያ እንደተቀመጥኩ ከፓርላማው ጽ/ቤት ፊት ለፊት ካለው ህንፃ በርካታ ወጣቶችና ሴቶች በሰልፍ ሆነው እየተፈተሹ ወደ ውስጥ በጥድፊያ ሲገቡ አየሁ፡፡ ለምን ጉዳይ እንደተሰበሰቡ የገባኝ አሥከሬኑ በምሽት ወደ አገር ቤት ሲገባ ነበር፡፡

የጠቅላይ ሚንስትሩ አሥከሬን ለምን በምሽት ወደ አገር ቤት እንዲገባ እንደተፈለገ ግልፅ የሆነ ነገር ባይኖርም የፀጥታ ጉዳይ መንግሥትን ሳያሳስበው እንዳልቀረ መረዳት ይቻላል፡፡ ቀን እንዲገባ ያልተመረጠበት ምክንያት አንዳንድ በሥርዓቱ ለ21 ዓመታት ሲገፉና ሲንበሳቆሉ የነበሩ ዜጎች እንዲሁም ተምረው ሥራ ያጡ ወጣቶች በአለታዊ ስሜት ተገፋፍተው ሁከት ቢፈጥሩ ሁኔታዎች ሊበላሹ ይችላሉ በሚል ሥጋት ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ በምሽት ቢገባ ግን ሁሉም በየቤቱ ከትት ስለሚል በተረጋጋ ሁኔታ አሥከሬኑን ቤተ መንግሥት ማስገባት እንደ ሚቻል ታምኖበታል፡፡

አሥከሬኑ ካይሮፕላን ሲወርድ ወ/ሮ አዜብ መሥፍን እንባጥ ፍርጥ እያሉ ለያዥ ለገራዥ ሲያስቸግሩ ለመጀ ሪያ ጊዜ የሕዝቡን ቀልብ ለመሳብ ችለዋል፡፡ ቀን ከፓርላማው ፊት ለፊ ካለው ጽ/ቤት ሲገቡ ያየኋቸው





ወጣቶችና ሴቶች ፎረሞችና ሊጎች ኖረው አሥከሬኑን አጅበው የቦሌን ጎዳና በርጋታ ጉዞ እንደተጀመረ በየጎዳናዎቹ ዳር ያለው ኗሪ ሕዝብ አዲስ ክስተት ስለሆነበትና አሥከሬኑ በምን ዓይነት ሥነ ሥርዓት ተጉዞ ቤተ መንግሥት እንደሚገባ ለማየት በየቤቱ በራፍ አገርግሮ በመቆም በኢትዮጵያዊ ጨዋነት ከንፈሩን በሐዘን እየመጠጠ ሲገልጽ ወጣት ሊጎች በበኩላቸው "ጀግና አይሞትም!" እያሉ በጭፈራ መልክ ዳንኪራ ሲረግጡ ሌሎች ወጣቶች በስሜት እየተገፋፉ ከዳንኪረኞቹ በመቀላቀል የሐዘንተኛውን ጉዞ አደመቁት፡፡ አንዳንድ ርምጃ በተሄደ ቁጥርም ሕዝቡ በተለይም ወጣቶች እየተጨመሩ የሐዘንተኛውን ቁጥር ከማበራከትና ከማድመቅ አልፈው ጎርፍ አደረጉት፡፡ ይህ ሁኔታ ለካሜራና ለቪዲዮ ቀራጮች (ለመንግሥት ብዙሃን መገናኛዎች) ያልታሰበና ያልተጠበቀ ጮማ ሆነላቸው፡፡ በቀጥታ ስርጭት በማስተላለፍም አዲስ ታምር ለመፍጠር ችለዋል፡፡ ይህ ክስተትም አሥከሬኑ ምነው ቀን በመጣ የሚል ቁጭትን ሣይፈጥር አልቀረም፡፡

ከዚህ በኋላ እስከ ቀብሩ ፍፃሜ ድረስ በክልሎችና በዞኖች ከጫፍ እስከ ጫፍ ድረስ ደረት ደላቂዎች ሕዝቡን በተሰበሰበበት ሁሉ እየተገኙ አስደልቀውታል፡፡ እንዲህ ዓይነት ሐዘንም ለመሪዎች በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ስለመታዘዙኑ የሚጠቁም የታሪክ ማስረጃ የለም፡፡ ካንጀት ነው ካንገት ቆይቼ እመለስበታለሁ፡፡

በማግስቱ ረቡዕ ነሐሴ 16 ቀን 2004 ዓ.ም የኮሙኒኬሽን ሚንስትሩ አቶ በረከት ስምዖን በግዮን ሆቴል ለጋዜጠኞች በሰጡት አጭር ጋዜጣዊ መግለጫ "ጠ/ሚንስትሩ ድንገት በተፈጠረ ኢንፌክሽን ነው ሕይወታቸው ያለፈው" ሲሉ አስታወቁ፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን ዝርዝር ማብራሪያ ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ "የቀብር ሥነ ሥርዓት አስፈፃሚ ብሔራዊ ኮሚቴ የተቋቋመ ስለሆነ በዚያ በኩል ማንኛውም ነገር ይገለፃል" ብለው ዘጉ፡፡

ኢሕአዴግ ሕዝቡ የሐዘኑ ቀጥታ ተካፋይ መሆኑን ሲያረጋግጥ የቀብሩን ሥነ ሥርዓት ለ12 ቀናት በማራዘም የፖለቲካ ቁማሩን ይቆምር ጀመር፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ግን ታዋቂ ሰዎችን፣ አትሌቶችን፣ የሙዚቃ ሰዎችን፣ አዛውንቶችንና ወጣቶችን በቴሌቪዥን መስኮት ብቅ እያደረገ የፖለቲካ ትርፍ አግበስብሷል፡፡ ለምሳሌ፡-

አንጋፋው አትሌት ኃይሌ ገ/ሥላሴ በ97 ዓ.ም የቅንጅት አመራሮች ተጋፈው በታሰሩበት ወቅት ከኢሕአዴግ ጋር ለማደራደር ከተሰለፉት ሽማግሌዎች መሀከል አንዱ ነበር፡፡ ከዚህ ውጭ ኃይሌ በ10 ሺ ሜትር

እሯጭነቱ እንጂ ስለፖለቲካ ተሳትፎውና አቋሙ የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ በዚያች ረቡዕ ማለዳ ግን ስቴዲየም ለዚሁ ተግባር ተብለው በተሰበሰቡ አትሌቶች ፊት እንባውን በመንታ በመንታ በጉንጮቹ እያፈሰሰ ጠ/ሚንስትሩን የገለፀበት አኳኋን ግርምትን ፈጥሯል፡፡ ኃይሌ በሥራ እንጂ ከመንገድ ዳር ተጎልተው አምስት ሣንቲም ምፅዋት ለሚጠይቁ ልቡ ጠጣር ነው እየተባለ የሚነገርለት ኃይሌ ያን ዕለት ለጠ/ሚንስትሩ ያፈሰሰው እንባ ገራገርና ሆደ ቡቡ መሆኑን አጉልቶ የሚያሳይ ነበር፡፡

ከዚህ በኋላ ገዥው ፓርቲ ታዋቂ ሰዎችን በቴሌቪዥን እያቀረበ የጠ/ሚንስትሩን ትክለ ሰብእና እጅግ በማምጠቅ መገንባቱን ተያያዘው፡፡ ታላቅነታቸውን፣ ሩኅሩኅነታቸውን፣ ቅንነታቸውን፣ ለዚች አገር መድኅን ሆነው የተፈጠሩ መሆናቸውንና የጀመሩትን ሕዳሴቸውን ለማስቀጠል "ቃል እንገባለን!" እያስባለ ወደ ማስማል ተሸጋገረ፡፡

በሕዝቡ ያልተጠበቀ የሐዘን ተሳትፎ የተደናደነው የኢሕአዴግ መንግሥት የቤተ መንግሥት በሮችን ለሕዝብ ክፍት በማድረግ አዲስ ምዕራፍን ለመክፈትም ችሏል፡፡ ለፈርማ የሚሰለፈው አዛውንት፣ ወጣት፣ አሮጊት፣ በእድር፣ በቀበሌ፣ በፎረም፣ በሠራተኛ ማኅበራት፣ ባሥተዳደር . . . ቀጥታ ትእዛዝ ጧት የተሰለፈ እህል ውሃ ሣይቀምስ ወረፋ በመጠበቅ ብቻ ምሽት የሚገለግለው ሕዝብ ቁጥር እጅግ በርካታ ነበር፡፡ የመንግሥት የመገናኛ ብዙሃንም ዙር ጥምጥም የተሠለፈውን ሕዝብ ሌት ተቀን ተጠምደው በቀጥታ ሥርጭት በማስተላለፍ የፕሮፓጋንዳ ምርቱን አትረፍርፈውታል፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ግን በመሀከል አንዳንድ እንከኖች አልተፈጠሩም ማለት አይደለም፡፡

የሐዘን ጊዜው በመራዘሙና በመንዛዛቱ የተነሣ ሕዝቡ ወረቱን ጨርሶ በመሰላቸቱ በተለይም የቀበሌ መዝናኛዎችና ሙዚቃ ቤቶች በመዘጋታቸው ወይንም መዝናኛ ነክ እንዳያስተላልፉ በመከልከላቸውና ጭር በማለታቸው የተነሣ አንዳንድ ሙዚቃ ቤቶች የዕለት ኑሯቸውን ለማሟላት ሲሉ ዓለማዊ ዘፈኖችን በማሠማታቸው በፀጥታ ኃይሎች ጉሽሜና እንግልት ደርሶባቸዋል፡፡ እንዲሁም ቃሊቲ እስር ቤት "በጠ/ሚንስትራችን ሞት ተደስተሃል፣ ስቀሃል" በሚል ድብደባ የደረሰበት መሆኑን ባለቤቱና ልጆቹ ፍኖተ ነፃነት ዝግጅት ክፍል መጥተው እያለቀሱ ቃላቸውን ሲሠጡ አስተውያለሁ፡፡

የሐዘኑ ቀን ከመራዘሙ የተነሳ በየእለቱ አዲያዲስ ተውኔቶችን በቅስቀሳ መልክ ለሕዝቡ በሬዲዮም ሆነ በተሌሌዥን ከመተላለፍ አልተቋረጠም፡፡





<የሕዳሴው ግድብ በታላቁ መሪያችን ስም እንዲሰየም> ከሚለው ጀምሮ ለቁጥር የሚያታክቱ መልዕክቶች ተላልፈዋል፡፡ ጥላሁን ጉግሳ የመቶ ብር ኖት በመያዝ "የታላቁ መሪያችን ፎቶ በመቶ ብሩ ኖት ላይ እንዲወጣና ስንሸጥም ሆነ ስንገዛ ፎቷቸውን እያየን ራእያቸውን እንድንተገብር . . ." እያለ ሲወተውት የቀበሮዋን አባባል አስታውሶናል፡፡

ቀደም ሲል ከመቶ ብሩ ላይ የነበረው ያርበኛ ምስል "ያማራ ነፍጠኛ" ነው በሚል የተዛባ ትርጉም በመሥጠት ከኤርትራ መጎረድ ጋር ያርበኛውም ምስል አብሮ ተፍቋል፡፡ ዛሬ ታዲያ ምን ዓይነት ታምር ቢሠራ ነው የተጋዳላይ መለስ ምስል ከመቶ ብሩ ኖት ላይ እንዲቀመጥ የሚቀነቀነው? ሁሉንም ጊዜ ይፍረደው፡፡ ለማንኛውም ሕዝቡ ላቶ መለስ ያዘነው ካንጀቱ ነው ካንገቱ? ወደሚለው እንሸጋገር፡፡

<><><>

# ሕዝቡ ለጠ/ሚንስትሩ ሐዘኑን የገለጠው ካንጀት ነው ካንገት?

ሕዝብ በጠ/ሚንስትሩ ሞት ካንጀት ነው ካንገት ያዘነው? እንዴትስ ባንድ ጊዜ ከዳር ዳር ሊንቀሳቀስ ቻለ? ለሚለው ጥያቄ ብዙ መልሶች ሊኖሩት ይችላሉ:: ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደ ሞከርኩት የመጀመሪያ የመንግሥት ሥጋት የነበረው አሥከሬኑን በሌሊት እስከማስገባት የደረሰውና ለረጅም ጊዜ ከሕመማቸው ጀምሮ ዜና ረፍታቸውን ደብቆ የቆየው ሰፊ ዝግጅት ለማድረግና ሕዝቡ አመፅ አንስቶ ወዳልተፈለገ አቅጣጫ ሊሄድ ይችላል በሚል ሥጋት እንደሆነ ለመገመት ከባድ አይሆንም:: ለዚህ ደግሞ በመንግሥት በኩል ሲታሰረብ በቂ የሆኑ ምክንያቶች ነበሩት::

ሕዝቡ በታሪኩ መሪን አዝኖ ቀብሮ አያውቅም:: ያምፃል፤ አልጋ ሊነቀንቅ ይችላል እየተባለ ይደበቃል:: ውሎ አድሮ ግን "የሞትንም እኛ፣ የነገሥንም እኛ፣ ተረጋግተህ ሥራህን ሥራ" ተብሎ ባዋጅ መልክ ይነገረዋል::

በሌላ በኩልም የመንግሥት ሥጋት በዚህ 21 ዓመታት ውስጥ በጠ/ሚንስትሩ የጎሳ ሥርዓት ያልተማረረና አገሩን ጥሎ ያልተሰደደ፣ ከሥራው ያልተባረረ፣ ጡረታውን ያልተነጠቀ፣ ቤቱ በላዩ ላይ ያልፈረሰበት፣ ልጁ ያልተገደለበት፣ ባሏ ያልታሰረባት፣ የማምለኪያ ቦታዎቹ (ቤተ ክርስቲያናት፣ ገዳማትና መስጊዶች) ያልተቃጠሉበትና ያልተደፈሩበት ዜጋ ባለመኖሩ የጠ/ሚንስትሩን ሞት እንደ መልካም አጋጣሚ ወይንም ብሥራት በመጠቀም የዕልልታና የደስታ ፍንጥዝያ ሊያሣይ ይችላል የሚል ፍራቻና ሥጋት በመንግሥት በኩል **አልነበረም ማለት አይቻልም:: አንዳንዶች እንዲያውም ሐዘኑን የትግሬኛ ተናጋሪዎች** ብቻ ሣይሆን አይቀርም ብለውም የሡ እንደነበሩ ከሁኔታዎች መረዳት ይቻላል:: ለዚህ ደግሞ በቂ የሆኑ ምክንያቶች ነበሯቸው:: አንዳንድ አልቃሾች ሐዘናቸውን ይገልፁ የነበሩት በቅጡ አልነበረም:: ጠ/ሚንስትሩ ልክ በፀረ ሰላም ኃይሎች ወይንም በሽብርተኞች እንደ ተገደሉ አድርገው ነበር በእልህና በቁጭት እየዘለሉ ደረት ይደልቁ የነበሩት:: የዚህ ምክንያቱ ደግሞ የፓትሪያሪኩና የጠ/ሚንስትሩ ሞት በሦስት ቀናት ልዩነት ተከታትለው መሞታቸው ነበር:: ይህንን ከስተትም ከንግርት ጋር ያያዙት ጥቂቶች አይደሉም:: እንደተባለው ከሆነም የዋልድባ ገዳም መነኮሣትና መናኒያን መስቀላቸውን ዘቅዝቀው "እመብርሃን





የፍልሰታን ፆም ሳንጨርስ ታምር ካላሣየሽን. . ." ብለው ሱባዔ ገብተው ነበር እየተባለ ያንሰሞን በግልጽ ተወርቷል:: እንዲሁም በዚሁ ወር ባጋጣሚ የረመዳን ፆም ተገጣጥሞ ስለነበር ሙስሊሙ ማኅበረሰብ ዱዓ ገብቶ ነበር ተብሏል:: የጉራፋርዳ ስደተኞች እንባም በከንቱ ፈሶ አልቀረም የሚሉ ጥቂቶች አይደሉም:: ለመቀጣጫነት ከመደበኛ የማስተማር ተግባራቸው የተባረሩ መምህራን ሕሊናም አልቆሰለም ማለት አይቻልም:: ይኸ ሁሉ ተደማምሮ የሁለቱ ያንድ ቀየ ልጆች፣ ያንድ ዘመን ፈላጭ ቆራጮች ባንድ ጊዜ ተከታትለው ማለፋቸው ሥጋዎቻቸውን፣ አድናቂዎቻቸውንና የጥቅም ተጋሪዎቻቸውን አንጀት በልቷል:: ይህ እውነት ነው:: እናም ከእግዚአብሔር ጋር እልህ የተጋቡም አስመስሏቸው ነበር:: ይህ በግልጽ ተስተውሏል:: አንድ ተራቢ ወዳጄ "እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ ያጋዚን ክፍለ ጦር ሣያዘምቱበት አይቀርም" ሲል ትዝብቱን ገልፆዋል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ይህንን ሁሉ ገልብጦ አስነበባቸው::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨካኝ መሪዎች ምንም ያህል ግፍ ቢፈፅሙበት ከሞቱ በኋላ በክፉ አያነሳቸውም:: ወይንም አይወቅሳቸውም:: ከሞት በላይ ሌላ ቅጣት ስለሌለ ይቅር ባይ ነው:: ላቶ መለስ ያሳየው ቀናነትና ሐዘንም ከዚህ የመነጨ ነው:: ካድሬ ባለሥልጣናትና የጥቅም ተጋሪዎች ግን ይህንን የዋህነቱንና ቀናነቱን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም በሀገሪቱ ዙሪያ ከጫፍ እስከ ጫፍ ለ12 ቀናት ሕዝቡን የዕለት ጉሮሮውን እንኳን እንዳይዘጋ ሥራ አስፈትተው አዲስ አበባን ጨምሮ በክልል ዋና ዋና ከተማዎች በየመቶ ሜትር ርቀት ግዙፍ ግዙፍ ድንኳኖችን አስጥለው ደረት ማስደልቅን ተያያዙት:: ከዚህ ከፍ ሲልም አሥከሬን ቤተ መንግሥት አጋድመው የክብር መዝገብ በማዘጋጀት "ና ተሰናበት፣ ና በራእያቸው ልትመራ በፊርማህ አረጋግጥ!" እያሉ የፖለቲካ ግብአት አግበሰበሱበት::

ሕዝቡ ግን ወደ ቤተ መንግሥት የጎረፈበት ምክንያት ከዚያ በፊት በምንም አጋጣሚ ገብቶ ስለማያውቅ፤ ቤተ መንግሥት ምን ይመስላል? የሚል ጉጉት ስላደረበት በዚያች አጋጣሚ የተለየ ነገር ለማየት እንጂ ለጠ/ሚንስትር መለስ ሞት መሪር ሐዘን ተሰምቶት አሥከሬናቸውን ለመሰናበት እንዳልሆነ ከማንም የበለጠ ኢሕአዴጋውያን ጠንቅቀው ያውቁታል:: ርግጥ ነው በኢትዮጵያውያን ዘንድ፣ በሰው ልጅ ባህሪም አንድ ሰው ከሞተ በኋላ አይወቀስም፤ አይኮነንም፤ መጥፎ ሥራ ሠርቶም ከሆነ ለታሪክ ነው የሚተወው:: ሕወሓት ግን ያፄ ምኒልክን አጥንት ከመፍጨት ጀምሮ አንድን ብሔረሰብ ብቻ ነጥሎ "ነፍጠኛ!" በማለት ነፍጥ ቀርቶ በትር ባልያዘበት ዘመን ውሃ ሲወግጥ ይውላል:: ባንፃሩ ጠቅላይ ሚንስትር መለስ

ለዚች አገር ታምር እንደሰሩና ታምርም ለመሥራት ራእይ እንደነበራቸው የፕሮፓጋንዳ ዶፍ በማውረድ በመጠንም ሆነ ባይነት ፎቶግራፋቸውን ባዲስ አበባ ከተማም ሆነ በሌሎች ከተሞች በገፍ በማራገፍ ኢሕአዴግ እንደ ጉድ ቸብችቧል:: "ባንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ. . ." የሚባለው እንዲህ ያለው ነው:: ኢሕአዴግ መቸም ቢሆን ገንዘብና ፕሮፓጋንዳ ጠግቦ አያውቅም::

ፒያሳ አካባቢ አንድ ወጣት በግለት ድምፁን ከፍ አድርጎ "የታላቁ መሪያችን ፎቶዎች በሦስት ብር፣ ባምስት ብር፣ ባሥር ብር፣ ሙቶ እንኳን ሥራ ፈጣሪ!" እያለ በስሜት ይጮሃል:: ሰው በሚያስደንቅ ሁኔታ እየተሻማ ይገዛል:: አንዳንዱ ደግሞ እየሳቀ ፈጥኖ ወደ ጉዳዩ ይሄዳል:: ወጣቱ ውትወታውን ቀጥሏል:: ገረመኝና ወደሱ ጠጋ ብዬ:-

"እየቀለድክ ነው ከምርህ ሙቶ እንኳን ሥራ ፈጣሪ ያምትለው?" ስል ጠየኩት::

"እየቀለድኩ አይደለም ፋዘር፤ ከምሬ ነው:: እሱ ባይሞት ኖሮ ዛሬ የሱን ፎቶ ሸጬ ትርፍ አላገኝም ነበር" ሲል ፈገግ አስኝቶኛል::

እንዲህ እንዳሁኑ እንደ አቶ መለስ ፎቶ የቀድሞው ሠራዊት ሞት ተፈርዶበት በጅምላ በተበተነበት ወቅት ምንም ቤሣ ቢስቲን የሌላቸውና መጠጊያ ያጡ የመንግሥቱ ኃይለማርያምን ፎቶ ግራፍ ከፊታቸው ደርድረው:- "ስለቆራጡ፤ በቆራጡ ሞት አትለፉን!" እያሉ ምፅዋት ይጠይቁ ነበር:: በዚህ ወቅት ልጆቻቸው በቀይ ሽብር የተገደሉባቸው፣ ቤት ንብረታቸው የተወረሰባቸው ሁሉ በሐዘን ከንፈራቸውን እየመጠጡ መፅውተዋቸዋል፤ ያላቸውንና ያገኙትን ሰጥተዋቸዋል:: አንዳንድ የተቀደሱ ዜጎችና ትንሽ ርሾ ያላቸው የሠራዊቱ አባላት ወደ ተወለዱበት ቀየ እንዲሄዱ መሣፈሪያ የሠጡ እንደነበሩ የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ያይን ምሥክር ነኝ::

ይህ ሁሉ ምፅዋትና ለወገን እጅን ዝርጋታ ግን መንግሥቱ ኃይለማርያምን ወዶና አክብሮ ወይንም አፍቅሮ አልነበረም:: መንግሥቱን መውደድ ወይንም መጥላት ሌላ ነገር ነው:: ለተራቡና ለተቸገሩ መመፅወት የነበረና ያለ የሚኖርም የሰው ልጅ ክቡር ተግባር ነው:: በተለይም ያገሩን ዳር ድንበር ሲያስከብር የነበረ ሠራዊት የቁም ሞት ሲበየንበት ሕሊናን ይሠቀጥጣል::

እንደዚሁም ሁሉ መለስን መውደድም ሆነ መጥላት ሌላ ነገር ነው:: ለሞተ ማዘን ግን ሰብዓዊነትና ታላቅነት ነው:: ይህም ሆኖ አንዳንዶች በጠ/ሚንስትሩ ደንገተኛ ሞት አላዘኑም፣ እንጂ ታቸው አልተቆረጠም ማለት





አይቻልም:: መሪር ሐዘን የዋጣቸው፣ ያለጠቅላይ ሚንስትሩ መኖር የማይችሉ የሚመስሉ ግለሰቦችንም አስተውለናል:: ይህም አዲስ አይደለም:: አባት ቢሞት ልጆች እኩል እንዲያዝኑ አይጠበቅም:: እንደ ቀረቤታቸው፣ እንደ ጥቅማቸው፣ እንደ አፈጣጠር ባህሪያቸው የሐዘን ደረጃቸውም ይለያያል:: ይህ ሀቅ ነው:: እንባ ዝም ብሎ የመቋጠሪያ ከረጢቱን በጥሶ ወይንም ፈቶ አይፈስም:: ከዚህ አንፃር ባቶ መለስ ሞት ከልባቸው ካዘኑት አንዱ ታዋቂው ቱጃር ሼክ ሙሐመድ አልዓሙዲን አንዱ ናቸው:: የሜድሮክን ሠራተኞች መስቀል አደባባይ አሠልፈው እንባ እየተናነቃቸው ያሠሙት ንግግር ከእውነተኛ የልብ ወዳጅ የመነጨ ነበር:: ከዚህ በላይ ማዘን አይችሉም እንጂ ቢያዝኑም እንኳን ሲያንሣቸው ነው:: ሩብ ኢትዮጵያን የተቆጣጠሩ፣ የሻኪሶንና የለገደንቢን የወርቅ ማዕድን በንብረትነት የያዙ ኢንቬስተር ለጠ/ሚንስትሩ ሞት ቢደንግጡና ከልብ ቢያዝኑ የሚያስገርም አይደለም:: ከኢንቬስተርነትም አልፈው ጓዶችም በመሆናቸው የሐዘናቸው ጥልቀት ከዚህም ሊልቅ ይችላል:: በመሆኑም:- "ጅምራቸውን፣ ራእያቸውን እናሳካለን፣ እንጨርሠዋለን. . ." ሲሉም በሠራተኞቻቸው ፊት ቃል ገብተዋል:: በእንዲህ ዓይነቱ የልብ ወዳጅ አበው ስንኝ አላቸው:-

*"የበላ ሆድ ያልቅስ፤ የጠጣ ሆድ ያልቅስ*
*የኛማ እንባ ደርቋል ቤታችንን ሲፈርስ!"*

የሐዘኑን ድባብ በተመለከተ በሌላ መልኩም እያነፃፀሩ ማየት ይቻላል:: ወይንም ገልብጦ ማንበብ ተገቢ ነው:: እንደሚታወቀው 97 ዓ.ም ኢሕአዴግ ሚያዝያ 29 ቀን መስቀል አደባባይ በጠራው ሕዝባዊ ስብሰባ ወደ 500 ሺ የሚጠጋ ሕዝብ ተገኝቶ ነበር:: ይህ ሕዝብ ግን በማባበልም ሆነ ነፃ ትራንስፖርት እየቀረበለት በከናቲራና በቁልፍ መያዣ እየተደለለ ተግበስብሶ የመጣ ሕዝብ ነበር:: ጠ/ሚንስትሩ በሕዝቡ ብዛት ከመስከራቸው የተነሳ *"ይህንን ሕዝብማ ይዘን እንከን የለሽ ምርጫ እናካሄዳለን! ያላንዳች ማጭበርበር እናሸንፋለን! አሳዩዋቸው! ቅጧቸው!"* ሲሉ የድንፋታ ንግግር አደረጉ::

በማግስቱ ሚያዝያ 30 ቀን የታየው ትዕይንት ሕዝብ ግን ቆሽታቸውን አደበነው:: ይህ ትእይንተ ሕዝብ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ታይቶ እንደማይታወቅ ብዙዎች ይናገራሉ:: "ትናት ለከናቲራችን ዛሬ ላላማችን!" እያሉ ወጣቶች፣ አዛውንቶች፣ ሴቶች፣ ወንዶች ወደ መስቀል አደባባይ መትመም የጀመሩት ገና ከጧቱ ጀምረው ነበር:: የህዝቡን ብዛት እስከ ሦስት

ሚሊየን እንደሚጠጋ በወቅቱ ተዘግቧል፡፡ በዚህ ታሪካዊ ትእይንተ ሕዝብ ላይ ጦጣዎች፣ ዝንጀሮዎች፣ ውሻዎችና ርግቦች ተካፋይ ሆነዋል፡፡ አንድ ውሻ ቁምጣ ሱሪውን ታጥቆ ከጌታው ፊት በኩራት በመቆም ምላሱን እያውለበለበ፡-

"አጥንት ከጋጥኩ ድፍን 15 ዓመቴ!" የሚል መፈክሩን በከረባቱ አንጠልጥሎ ይዞ ተመልካቹን ሲያስቅ ውሏል፡፡ ይህ እንግዲህ ትናንት ሆኖ ያለፈ ነው፡፡ በነገራችን ላይ ከ97 ዓ.ም ሚያዝያ 30 ቀን ወዲህ ኢሕአዴግ ከራሱ በስተቀር ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ትእይንተ ሕዝብ በመስቀል አደባባይ ቀርቶ በትልልቅ አዳራሾች እንኳን ላለመፍቀድ ምሏል፡፡ ሕዝብ ግን ከኔ ጋር ነው ብሎ ልቡ ወልቋል፡፡




*ሚያዝያ 30 ቀን 1997ዓ.ም. ትዕይንተ ሕዝብ*





ይህንን እውነት ለማረጋገጥ እስቲ ደግሞ በዚህ 21 ዓመታት ውስጥ በጠ/ሚንስትሩ የጎሣ አመራር የተሰቃያችሁ፣ ቤታችሁ በላያችሁ ላይ የፈረሰባችሁ፣ አገር ያጣችሁ፣ ከምትኖሩበት ቀየ ንብረታችሁን እየተዘረፋችሁ የተባረራችሁ፣ ባሎቻችሁ ወይንም ልጆቻችሁ በእሥር ቤት እየማቀቁባችሁ ያሉ፣ ወገኖቻችሁ አገር ጥለው የተሰደዱባችሁ፣ ጧሪ ቀባሪ ያጣችሁ፣ ባሎቻችሁ፣ እንዲሁም እህት ወንድሞቻችሁ የተገደሉባችሁ፤ እስቲ እናንተ ደግሞ መስቀል አደባባይ ወጥታችሁ በተፈጠረው አጋጣሚ ደስታችሁን ግለፁ ቢባል መሬት ልትሸከመው ከምትችለው በላይ የሕዝብ ሱናሚ መስቀል አደባባይን አይደለም አዲስ አበባን ባሰጠማት ነበር፡፡

በሌላ በኩልም የሐዘኑ ሁኔታ ባህላዊ ይዘትም አለው፡፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ በተለይም ባማራው ሕዝብ የቆየ ጠንካራ ባህል አለ፡፡ ይኸውም በሩቅ ጊዜ የሞቱ ሁሉ በትኩሱ ሬሳ እየተታወሱ እንደ አዲስ ይለቀስላቸዋል፡፡ አንድ ምሳሌ ልጥቀስ፡-

ያፄ ቴዎድሮስ 2ኛ ባለቤት የእቴጌ ጥሩወርቅ አባት ደጃዝማች ውቤ ኃይለማርያም በእስር ላይ እንዳሉ ይሞቱና እቴጌይቱ ቤተመንግሥት ይረዳሉ፡፡ በዚህ ጊዜ በቴዎድሮስ ቤተመንግሥት ታላቅ ሐዘን ይሆናል፡፡ ደጃዝማቹን የሚያወቋቸውም የማያውቋቸውም ተንሠቅስቀው ያለቅሳ ሉ፡፡ ይህንን ያስተዋሉ አንዲት የቤጌ ምድር ወይዘሮ፡-

*"ደጃዝማች ውቤ ሁልጊዜ ደግነት*
*ዛሬ እንኳን ለድሃ እንባ አተረፉለት!"* ብለው ማልቀሳቸው ይነገራል፡፡ የዚህ ምክንያቱ ግልጽ ነው፡፡ በቴዎድሮስ ጊዜ በየማግስቱ ዘመቻ ስለነበር በየፍልሚያው ሜዳ የሚሰውት እየተበራከቱ በመምጣታቸው መርዶ የሚባል ቀርቶ ነበር ይባላል፡፡ በዚህ ምክንያት በእቴጌይቱ አባት ሞት አስመስለው ባሎቻቸው የሞቱባቸው፣ ልጆቻቸው እንደወጡ የቀሩባቸው ተንሠቅስቀው በማልቀስ የቆየ ርማቸውን አውጥተዋል፡፡ ዛሬም ለጠቅላይ ሚንስትር መለስ የታዘነው የሐዘን ድባብ ከላይ ከጠቀስኩት ጋር በጥብቅ የሚመሳሰል ነው፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆነኝ አንድ ወዳጄ ያንድ ትልቅ መንግሥታዊ መ/ቤት ባልደረባ ነው፡፡ በቴሌቪዥን በመሐረብ ዐይኖቹን እየጨመቀ እንባ ለማውጣት ሲታገል አየሁት፡፡ የዚህ ወዳጄ አንዱ ወንድሙ በ98 ዓ.ም በተባራሪ ጥይት መርካቶ ላይ ተገሎበታል፡፡ ሌላኛው ወንድሙ በዚህ ተበሳጭቶ በኬንያ እንደወጣ ቀርቷል፡፡ ነገሩ ስለከነከነኝ ማታ ስልክ ደውዩ፡-

“ካንጀትህ ነው ካንገትህ ለሐዘን የተሰለፍከው?” ስል ጥያቄ አቀረብኩለት፡፡

ከት ብሎ ሣቀና “የመንግሥት ሠራተኛ እንደመሆኔ መጠን ሐዘኔን እንደማንኛውም ሠራተኛ መግለጽ የግድ ነበረብኝ፡፡ በሌላ በኩልም በኔ የደረሰውን ግፍ ታውቀዋለህ፡፡ አንዱ ወንድሜ ተገሏል፤ ሌላው ደግሞ ተሠዷል፡፡ እንባ አልወጣ አለኝ እንጂ ደስታምኮ ያስለቅሳል፡፡ አትሌቶች ሲያሸንፉ ያለቅሱ የለም እንዴ?” ሲል መልስ ከኔ ሳይጠብቅ ስልኩን ዘጋብኝ፡፡ በወቅቱ እንዲህ ዓይነት አስመሳዮችም መኖራቸው እውነት ነው፡፡

ሌላው ሐዘኑን የምር ያስመሰለው የገዥው ፓርቲ የሚከተለው የከፋ የጥርነፋ ሥርዓች ነው፡፡ ሁሉንም የመቆጣጠርና የመጠርነፍ አባዜ የተጠናወተው በመሆኑ ለእንደዚህ ዓይነቱ ከስተት በሠልፍ ለማስወጣት አመችቶታል፡፡ በተለይም ከ97 ዓ.ም ወዲህ ከህፃን እስከ ሽማግሌ፣ ከወጣት እስከ አዛውንት፣ የሠፈር አሮጊቶችና የሃይማኖት አባቶች ሳይቀሩ ١ለ5 ተጠርንፈዋል፡፡ ገዥው ፓርቲ ሰውን የሚያህል ክቡር ፍጡር በየምክንያቱ እንደቁሳቁስ ጠፍሮ መንቀሳቀሻ ማሳጣት ታሪክ ይቅር የማይለው ብሔራዊ ውርደት እየፈፀመ ይገኛል፡፡ በገጠር እናቶች በጤና ኤክስቴንሽን ስም አባወራዎች በርከን ሥራ ስም ١ለ5 ተጠርንፈዋል፡፡ ተማሪዎች ባስጠኝ ስም ١ለ5 ተጠርንፈዋል፡፡ አስተማሪዎች በት/ቤት በመምህራን ማህበር ስም ተጠርንፈዋል፡፡ የከተማ ወጣቶች በኮብል ስቶን፣ በጥቃቅንና አነስተኛ አምራቶች ስም፣ ሽማ ሠሪዎች በሽማኔዎች ማህበር ስም፣ ነጋዴዎች በነጋዴዎች ማህበር፣ ሠራተኞች በሠራተኞች ማህበር ስም ተጠርንፈዋል፡፡ ሙያተኞች በሙያ ማህበራቸው በኩል ተጠርንፈዋል፡፡ ወጣቶች በሊግ፣ ሴቶች በፎረም ስም ተጠርንፈዋል፡፡ ብቻ ምኑ ቅጡ ሁሉም በያለበት ١ለ5 ተጠፍሯል፡፡ ሌላው ቀርቶ እስረኞች እንኳን ከ١ለ5 ጥርነፋ አላመለጡም፡፡

ምናልባት አንዳንዶቻችን ያልተጠረነፍን ነፃ ሰዎች ሊመስለን ይችል ይሆናል፡፡ ግን ነፃ ሰዎች አይደለንም፡፡ ባንድ ወይንም በሌላ ምክንያት ሳናውቅ በጥርነፋው ውስጥ ተካተናል፡፡ በሠፈር ውስጥ ለውስጥ በሚሠሩ መንገዶች ወይንም የወል ፅዳትን በተመለከተ ወይንም በፀጥታ አጠባበቅ ስም ባንዱ ወይንም በሁሉም መጠርነፋችንን ርግጠኞች ሁኑ፡፡ በነዚህ ሁሉ የለሁበትም የምትሉ ካላችሁ ደግሞ በዕቁብ ወይንም ላስከሬናችን መውጫ ብለን ባቋቋምናቸው እድሮች ስም ተጠርንፋችኋል፡፡ በዚህ ርግጠኛ ሁኑ፡፡ እድሮቻችን የኢሕአዴግ ካድሬዎች መፈንጫዎች ከሆኑ ቆይተዋልና፡፡ ባጭሩ ኢሕአዴግ ጓዳችን ድረስ ዘልቋል፡፡





በዚህ የጎሣ ዘመን ሌላው ቀርቶ ባልና ሚስት ሰላም የላቸውም፡፡ በኑሮ ውድነት ይጠበሳሉ፤ በትራንስፖርት ችግር፣ በፍትሕ እጦት ይታመሳሉ፡፡ አንድ ሆነው ተመካክረው በባልና ሚስት ወግ የቤት ውስጥ ችግሮቻቸውን መፍታት አይችሉም፡፡ ባልን ለማጥመድ ሚስት በማታውቀው ሁኔታ ተጠርንፋለች፡፡ ሚስት ነቃ ያለች ከሆነች ደግሞ ባል በትንሽ ነገር ተደልሎ የገዛ ሚስቱን ይጎዳል፡፡ ወይንም ያናድዳል፡፡ በተለይም የተለያዩ ጎሳዎች ከሆኑ ችግራቸው የከፋ ነው፡፡ ቀልዳቸው ሁሉ ምር ሆኖ በተለያየ አቅጣጫ ይመነዘርና ለብጥብጥ ይዳርጋቸዋል፡፡ አራትና አምስት ልጆችን ወልደው ትዳራቸውን የፈቱና ልጆቻቸውን የበተኑ ጥቂቶች አይደሉም፡፡ በዚህ በዚህ ምክንያት ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፈሯል፤ ደንዝዟል፤ እንዲህ በመሆኑም መስሎ አዳሪ፣ ቀጣፊ፣ አጎብዳጅ፣ ሠጋጅ ሆኗል፡፡

እንግዲህ በዚህ ሁኔታ የተፈራቀቀ ሕዝብ ١ለ5 ተጠርንፎ ለሚተላለፍለት አስቸኳይ ጥሪ ቅፀበታዊ መልስ ከዳር ዳር ቢሠጥ አይፈረድበትም፡፡ ዘመኑ ደግሞ ዘመነ ቴክኖሎጂ ነው፡፡ ከሞባይል ጀምሮ የተራቀቁ የመገናኛ አውታሮች የተዘረጉበት ዘመን መሆኑን ልብ ልንል ይገባናል፡፡ በተረፈ ግን ሕዝቡ ለጠ/ሚንስትሩ ሞት ያሣየው የሐዘን ተሣትፎ ካንጀት ነው ካንገት ለሚለው ጥያቄ በቂ የሆነ መልስ ባሁኑ ሰዓት መስጠት አስቸጋሪ ነው፡፡ ቀላሉ መልስ ለታሪክ ማቆየቱ ነው የሚሻለው፡፡

<><><>

# የቀብሩ ሥነ ሥርዓት

ዕለቱ ነሐሴ 27 ቀን 2004 ዓ.ም ነው:: ጧት ያየሩ ፀባይ ደመናማና የጨፈገገው ቀን ቢሆንም ዝናብ አልነበረም:: እየቆየም ፈታ ያለ ቀን ሆነ::

አሥከሬኑ ላንደየና ለመጨረሻ ጊዜ ለሥንብት በጧት በከፍተኛ ወታደራዊ ማርሽ ታጅቦ ከቤተመንግሥት ወጥቶ መስቀል አደባባይ ከተዘጋጀለት ቦታ በክብር አርፏል::

ያፍሪካ መሪዎች ጥቂቶች ተገኝተዋል:: ጥቂቶች ደግሞ ወኪሎቻቸውን ልከዋል:: የዓለም ታላላቅ መሪዎች አንዳቸውም ባይገኙም የተወሰኑት አሜሪካንን ጨምሮ ወኪሎቻቸውን ልከዋል::

ሁሉም በተዘጋጀላቸው ፕሮግራም መሠረት በቅደም ተከተል መሪዎቹ ንግግር አድርገዋል:: እጅግ የተንዛዛና አሠልች ንግግር ያደረጉት ያሜሪካዋ ተወካይ ነበሩ:: በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ነበሩ:: ከኮብል ስቶን ሠራተኞች ጀምረው አላስፈላጊ የሆነ ምሥጋና እየደረደሩ ማሯቸውን ንግግር ነበር ያደረጉት:: ይልቅ አጭርና ግልጽ ንግግር ያደረጉት የሟቹ ባለቤት ወይዘሮ አዜብ መሥፍን ነበሩ:: ከላይ እስከታች ከል ለብሰው:-

*"መለስን የማውቀው ገና ልጅ ሆኜ ነው:: መለስ አሥተማሪዬ ነው:: መለስ ፍቅረኛዬ ነው፤ መለስ ባሌ ነው፤ መለስ የልጆቼ አባት ነው፤ መለስ ለኔም ሆነ ለልጆቹ ከፍተኛ ፍቅርና አክብሮት ነበረው:: ይሁን እንጂ ከኛ ጋር የሚዝናናበት ጊዜ አልነበረውም:: ጊዜውን ለኛ ሠውቶ አያውቅም:: ሌትም ቀንም ይሠራ ነበር:: አሁን እኔ ብቻዬን ነኝ:: ለልጆቼ እናትም አባትም ሆኜ የማሣደግ ኃላፊነት ወድቆብኛል:: ወደፊት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሆኘ የባለቤቴን ጅምሮች ሳይሸራረፉ እንዲቀጥሉ የበኩሌን ጥረት አደርጋለሁ:: ለዚህ ደግሞ ፍርዱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ እተወዋለሁ . . ."* ነበር ያሉት::

የመስቀል አደባባዩ ሥነ-ሥርዓት በመንዛዛቱ ምክንያት ከሰዓት በኋላ ዶፍ ዝናብ በመውረዱ ሐዘንተኛውን ተፈታትኖታል:: በሠልፍ የቆሙት ከፍተኛ መኮንኖች ይህንን ከባድ ወዝቦ ተቋቁመውታል:: አሥከሬኑን ጥለው መጠለያ ፍለጋ አልሄዱም:: ማርሽ የሚያሠሙ ሙዚቀኞችም ከሠልፋቸው ንቅንቅ አላሉም:: በዚህ ሁኔታ አሥከሬኑ በክብር ታጅቦ ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ደርሷል::





አሥከሬኑ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ እንደተጠቀለለ ከመኪና ወርዶ ግብዓተ መሬት ወደ ሚገባበት ሲወሰድም ባረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ቀለማት እንደተጠቀለለ ነበር:: በመጨረሻም ወደ መቃብር ሲወርድ በሰንደቅ ዓላማ እንደተጠቀለለ ነበር:: ጠቅላይ ሚንስትሩ በሥልጣን ዘመናቸው "ጨርቅ" እንዳሏት እንደ ጨርቅ በሷው ተጠቅልለው ላንደየና ለመጨረሻ ጊዜ ወደ መቃብር ሲወርዱ ብዙዎችን አሣዝኗል::

ሰንደቅ ዓላማ ያንዲት አገር የክብሯና የሉዓላዊነቷ መገለጫ፣ ከሌሎች አገሮች ተለይታ የምትታወቅበት ልዩ ምልክቷ መሆኑ እየታወቀ እንደተራ ጨርቅ ተጠቅልላ አብራ ስትቀበር ያገር ክብርና ሞገስ አብሮ የተቀበረ ያህል የሚያስቆጥር ተግባር ነበር የተፈፀመው:: "የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ምን እየሠሩ ነው?" ብለው የጠየቁም ጥቂቶች አይደሉም::

የጠ/ሚንስትሩ አሥከሬን በባንዲራ መጎናፀፉ ወይንም መሸፈኑ ነውር የለበትም:: ነውሩ አብሮ ከመቅበሩ ላይ ነው:: በመጋረጃ ታጋርዶ ባንዲራው ተገፎ መቅረት ነበረበት:: ፋኖዎቹ ግን ይህንን ሥርዓት የሚያውቁ አይመስሉም:: ወይንም ቢያውቁም ለባንዲራ ያላቸው ንቀት አሁንም እንዳልወጣላቸው ማረጋገጫ ነው::

ሌላው ከቀብሩ በኋላ እንደ ትንግርት ይወራ የነበረው "ጠ/ሚንስትሩን አሜሪካኖች ናቸው በጨረር የገደሏቸው" የሚል ነው:: ለዚህ ወሬ መነሻ ምክንያት የሆነው በሬገን ማዕከል የቡድን 8 መሪዎች ውይይት በሚያደርጉበት ወቅት ካቶ መለስ አጠገብ ተቀምጠው የነበሩት የጋናው መሪ ወዳገራቸው እንደተመለሱ ወዲያውኑ በመሞታቸውና ባጭር ጊዜ ልዩነት ደግሞ አቶ መለስ በመከተላቸው ያሜሪካኖቹ እጅ እንዳለበት መላ ምተኞቹ አምነው ሌሎችን ለማሣመን ወሬውን በሥፋት አሠራጩት::

የጋናውን መሪ ዴሞክራት ስለነበሩ "እሱም ብሎ ዴሞክራት፤ እኛ ባፍሪካ ውስጥ ከማስመሰል ያለፈ የዴሞክራሲ ነፋስ ሽው እንዲል አንፈቅድም!" በማለት ጥቅም ስላስቀሩባቸው ጥርሶቻቸውን ነክሰውባቸው ነበር:: ጠ/ሚንስትር መለስን ደግሞ "ከሄትለር የባሰ የዘር በሽታ የተጠናወተው አምባገነን ነው! መወገድ አለበት!" በሚል ወደ ቻይናዎች ፊቱን በማዞር ስለቀለደባቸው ቂም ቋጥረውበት ስለነበር ጋዜጠኛ አበበ ገላውን ወደ አዳራሽ እንዲገባ ፈቅደው "ነፃነት! ነፃነት! መለስ ዜናዊ አምባገነን ነው!!" በማለት አስጨኸው ሁለቱ መሪዎች በድንጋጤ ወደ አበበ ዞረው ዐይኖቻቸውን ሲያፈጡ በጨረር አንጫረሯቸው ሲሉ ይተርካሉ::

በመሠረቱ ይህ ዓይነቱ በመረጃ ያልተደገፈን ተራ አሉቧልታን እውነት ነው ብሎ አምኖ ለመቀበል ይከብዳል፡፡ ከዚህ ላይ እንደ ትልቅ ነገር ያሠፈርኩት ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁልጊዜ ለእንደነዚህ ላሉ እውነትነት ለጎደላቸው መናኛ ወሬዎች ተጋላጭ መሆኑን ለማሣየት ነው፡፡

ያም ሆነ ይህ ጠ/ሚንስትሩ ሊሠሩ በሚችሉበት የዕድሜ ደረጃ ላይ ደርሰው ማረፋቸው የሚያሣዝን ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ተጠያቂ የሚሆነው በሳቸው ሳንባ ሲተነፍስ የኖረው ፓርቲያቸው ነው፡፡ ለዚህም ነው ዛሬ በሳቸው ሙት መንፈስ እንግዛችሁ የሚሉን፡፡ በሥልጣን ዘመናቸው የተሠሩ ጥፋቶች ሁሉ ዉሾን ያነሳ ዉሾ ተብለው ከሳቸው ጋር እንዲቀበሩና በራእያቸው ሕዝብ ሲገዛ እንዲኖር ከጅምላ ጠመቃ ወደ ጅምላ መሀላና ቃል ማስገባት የተሄደው፡፡ ምንም ይሁን ምን ይዘገያል እንጂ የሳቸው ሙት መንፈስ ከተጠያቂነት አያድንም፡፡ ሁሉም ነገር ልክ ሊኖረው ይገባል፡፡ ሙትን ማስወቀስና ማስረገምም ሊሆን እንደሚችል ግንዛቤ ሊያዝበት ይገባል፡፡ ከዚህ ይልቅ የተሻለ የሚሆነው እሳቸውን "ነፍሳቸውን ይማረው" ብሎ እያንዳንዱ ባለሥልጣን የራሱን ራእይ ይዞ ነው መቅረብ ያለበት፡፡

<><><>





# ክፍል ሁለት

*ምን ያለው ዘመን ነው ዘመነ ውጥንቅጥ*
*በሬ እግሩን ነቅሎ በገደል ላይ ሲሮጥ*
*ዝንጀሮ እንዳልጦት ተንከባሎ ሲፈርጥ*
*ዉሻ ከዛፍ ወጥቶ ፍሬ ሲሸመጥጥ*
*ጦጣ ከሥር ሆና እጥንት ስትግጥ*
*ዶሮ ውተት ሠርቆ አደፍጦ ሲጨልጥ*
*ድመት ጥራጥሬ ጭራ ስጠለቅጥ*
*በዔሊ ሩጫ መሬት ሲንቀጠቀጥ*
*ቅጥፈት እንደገንፎ ሳይላመጥ ሲዋጥ*
*ዉሸት እንደ ማር ለጀሮ ሲጣፍጥ*
*ምን ያለው ዘመን ነው ዘመነ ውጥንቅጥ!!*

## ጊዜ ነው ዘመዱ

አበው ከሞታቸው ይልቅ አሟሟታቸው ያስጨንቃቸዋል፡፡ ለዚህም ነው "አሟሟቴን አሣምረው" በማለት አዘውትረው ሲፀልዩ የሚደመጡት፡፡ ይህ እውነት ነው፡፡ ጊዜ ሲከፋ አሟሟትም፣ የቀብር ሥነ ሥርዓትም አብሮ ሊከፋ ይችላል፡፡ ምን በጎ ነገር ቢሠሩት ጊዜ ካላገዘ አወደደቅ ይከፋል፡፡ ጊዜ ሲያግዝ ደግሞ ጨካኞችና አረመኔዎች በሠፈሩት ቁና ሣይሰፈሩ የከብር ሞት ሙተው በክብር ይቀበራሉ፡፡ "ለሟች ከማዘንና ከማልቀስ ይልቅ ለጊዜ ነው ማልቀስ" የሚባለውም ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ ጠቢቡ ሰለሞንም "ለሁሉም ጊዜ አለው!" ሲል ገና ቀድሞ ተናግሮታል፡፡

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሦስት ሺ የመንግሥትነት ዘመኑ በታሪኩ መሪዎቹ በሞት ሲለዩ ባንዲራውን ዝቅ አድርጎ ሰቅሎ ብሔራዊ የሐዘን ቀን አውጆ አዝኖ አያውቅም:: ይህ የቆየ ባህሉ ዛሬ በጠ/ሚንስትር መለስ ዜናዊ ሞት ምክንያት ጥቁሩ መጋረጃ መቀደዱ መልካም ጅምር ነው:: እሳቸውም የዚህ ታሪክ የመጀመሪያ ባለቤት መሆናቸው እድለኛ ያደርጋቸዋል:: ሕዝቡም ጨዋነቱን አስመስክሯል:: የቤተመንግሥት በሮችም ክፍት ሆነው ዜጎች መሪያቸውን እንዲሰናበቱ መደረጉም የሚያስወቅስና የሚያስነቅፍ አይደለም:: የሚያስወቅሰውና የሚያስነቅፈው የፖለቲካ ትርፍ ለማግበስበስ ሲባል አጋጣሚውን በመጠቀም ይህንን ቅንና ገራገር ሕዝብ "ና ቃል ግባ!" እያሉ በጅምላ ቃለ መሀላ ከማስገባቱ ላይ ነው:: ይህ ድርጊት ነውር ብቻ ሣይሆን ሕዝብንም መናቅ ነው:: ለእንዲህ ዓይነቱ የዘቀጠ ፕሮፓጋንዳ አበው ጥሩ ሥነ ቃል አላቸው:-

*"ኧረ ሰው አትናቁ ሰው እንዴት ይናቃል?*
*ትኋን እንኳን ባቅሙ አልጋ ያስለቅቃል!"* በማለት

ያቅራራሉ ወይንም ይሸልላሉ:: መነሻየ ወይንም የዚህ ጽሑፍ ዋና አርእስተ ጉዳዩ "ጊዜ" ስለሆነ ስለጊዜ ሳስብ አንድ ነገር ትውስ አለኝ::

እውቁ አቀንቃኝ ጥላሁን ገሠሠ ከ97 ዓ.ም በፊት አርፎ ቢሆን ኖሮ እንኳንስ በሠረገላ ታጅቦ በክብር ሊሸኝ ቀርቶ ዜና ረፍቱንም በቅጡ አይነገረንም ነበር:: እንዲያውም "አሣደህ በለው ያንን ወንበዴ!" የሚለው ዜማው እየተጠቀሰ ቢያንስ ላንድ ወር ያህል ይብጠለጠል ነበር:: ዳሩ ግን ጥሌ ጊዜ ዋስ ሆነችውና በጊዜ ተሸኘ:: ባንፃሩ ጊዜ ያላገዛቸው ታዋቂው ምሁር ፀጋዬ ገ/መድህን ከ97ዓ.ም በፊት በማረፋቸው ዜና ረፍታቸውን የሰማነው ባሜሪካን ሬዲዮ ድምፅ ነበር:: የዚያን ዕለት የኢትዮጵያ ሬዲዮ ማዶና በ18 ዓመቷ ተደፈረች ሲል ቁጭቱን ተረከልን:: የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አሟሟት ደግሞ ከዚህም የከፋ ነበር::

አበው "ጊዜ ሲከፋ ያሣደጉት ዉሻ ይናከሣል!" ይላሉ:: ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከቦይ እስካውት ጀምረው ኮትኩተው ባሳደጓቸው ወታደሮቻቸው ታንቀው ወይንም በትራስ ታፍነው ተገለው የትም ሽርንቁላ ውስጥ ተጣሉ:: አፄ ኃይለሥላሴ እንደማንኛውም መሪ የሚወቀሱባቸውና የሚነቀፉባቸው በርካታ ህፀፆች ቢኖሩም ታንቀው የሚገደሉ መሪ ግን አልነበሩም:: ላገራቸው እድገት ብዙ የደከሙ መሪ ነበሩ:: በተለይም በዲፕሎማሲው መስክ አንቱ የተባሉ ተግባራትን አከናውነዋል:: ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል:-





1. ኤርትራን ያላንዳች ደም መፋሰስ ከናት አገሯ በመቀላቀል አገራቸውን የባህር በር ባለቤት አድርገዋል:: ለዚህ ደግሞ ጠ/ሚንስትር አክሊሉ ሀ/ወልድ ትልቅ ባለድርሻ ነበሩ:: እኒህ የኢትዮጵያ ባለውለታ ታላቅ ሰውም ወንጀላቸው ምን እንደ ሆነ ሳይታወቅና የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳያውቀው ከ60ዎቹ ጋር አብረው ተረሸኑ::
2. አፍሪካ አንድነት ድርጅት ከመሠረቱት አንጋፋ መሪዎች መሀከል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ መሆናቸው ብቻ ሣይሆን ዋና ጽ/ቤቱ አዲስ አበባ እንዲሆን ጥረት አድርገዋል::
3. አፄ ምኒልክ የጀመሩትን ዘመናዊ ሥልጣኔ ገፍተውበታል፤ ወይንም አስፋፍተው ካባታቸው በውርስ ያገኙትን ትልቅ ግቢ ያሁኑን አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለቀው የመጀመሪያውን ዩኒቨርስቲ በዘመናቸው በመክፈት የእውቀት ብርሃንን ፈንጥቀዋል:: ታሪካቸውን በተመለከተ በመጠኑ በክፍል ሦስት የቀረበ ስለሆነ ከዚህ ላይ ዝርዝር ውስጥ አልገባም::

ደርግ ባቋራጭ ሥልጣን በመጨበጥ የንጉሠ ነገሥቱን መልካም ስምና ዝና ከታሪክ ማህደር ፍቆ ለማጥፋት ያልፈነቀለው ድንጋይና ያልቆፈረው ጉድጓድ አልነበረም:: ቆልምሞ ከገደላቸው በኋላ እንኳን የደርጉ ቁንጮ መንግሥቱ ኃይለማርያም ከቢሮው ሥር ቀብሮ 17 ዓመታት ተቀምጦባቸዋል ይባላል::

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በወታደሮቻቸው ሥልጣናቸውን እስከ ተነጠቁበት ጊዜ ድረስ "ፀሐዩ ንጉሥ" እስከመባል የደረሱ ንጉሥ ነበሩ:: ከዚህም ባለፈ አንዳንዶች አጥቶቻቸውን እየተው "ኃይለሥላሴ ይሙት" እያሉ ይምሉባቸው ነበር:: እሳቸውም ንግግር ባደረጉ ቁጥር "የምን ወድህና የምትወደን ሕዝባችን" በማለት ይናገሩ ነበር:: ከዚህ ላይ ግን አንድ መታወቅ ያለበት ቁምነገር ያለ ይመስለኛል:: ይኸውም ሕዝቡና ንጉሠ ነገሥቱ አንድም የድብብቆሽ ጨዋታ ይጫወቱ ነበር፤ አለያም የሕዝቡ አቋም ልክ ዛሬ እንደምናየው ከጥቅምና ከጊዜ ጋር አብሮ የሚዋዥቅ፣ አስመሳይና መስሎ አዳሪ ነበር ማለት ነው::

የኢትዮጵያ ሕዝብ የገዥ መደቦች የሚፈፅሙበትን ግፍና በደል በግልጽ ለመቃወምና የተጫነበትን የቀንበር ማነቂያ ቆርጦ ለመጣል አንድ አይደለም:: ብሶቱን የሚገልፀው በድብቅና ከፍ ሲልም በሥነ ቃል ነው:: በሌላ አገላለጽ አሽሟቂ ነው:: ገዝግዞ የሚጥል እንጂ ባንድ ጊዜ የተጠመደበትን ቀንበር ሠባብሮ የሚጥል አይደለም:: እስከዚያው ግን

መስሎ አዳሪ ነው:: እየከፋው ይስቃል፤ እየተረገጠ ከረጋጮች ጋር ሆኖ አብሮ ራሱን ይረግጣል:: አስገራሚ ሕዝብ ነው::

ደርግ ንጉሠ ነገሥቱን ባሮጌ ቮልስዋገን ጭኖ ወደ 4ኛ ክፍለ ጦር ሲወስዳቸው ባቅራቢያው የነበረው ወጣት "ሌባ! ሌባ!" እያለ ሲያፏጭባቸው "የእጃችሁን አትጡት!" ብለው እንደሚራገሙ ምንም ጥርጥር የለውም:: በመሆኑም ወጣቱ ትውልድ በነጭ ሽብርና በቀይ ሽብር ተቧድኖ በመተራረድ ልክ እንደሳቸው አሥከሬን የዚያ ሁሉ ወጣት ሬሳ በየጎዳናው ዳርና በየሸርንቋላው እንደ ዉሻ ሬሳ ተጣለ:: ይህ እንግዲህ እጅግ ዘግናኝና አሣፋሪ የታሪክ ጠባሣ ነበር:: ይህ ሁሉ ደም ፈሶም ያ-ትውልድ የጓጓለትን ሥልጣን ተረክቦ ቢሆን ኖሮ አያስቆጭም ነበር:: የሆነው ግን የተገላቢጦሹ ነው::

ኤርትራን ተዋግቶ ላስገነጠለና የባህር በር ላሣጣ፣ ባንድ ጎሣ ላይ መሠረቱን ለጣለ ፋኖ ቡድን አገርን አሥረክቦ በዓለም ዙሪያ እንደ ጨው ዘር ተዘርቶ ባዛኝ ሆነ::

ተረኛው ባለጊዜ ኢሕአዴግ አዲስ አበባ ገብቶ አገሪቱን ከተቆጣጠረ በኋላ ሥልጣኑን ለማደላደል ከተጠቀመባቸው ሥልቶች መሀከል አንዱና ዋናው በደርግ ጊዜ የተጨፈጨፉትን አፅም ከየተቀበሩበት ሠዋራ ቦታ እያስቆፈረ በማውጣት ደረት እያስመታ የብዙ እናቶችን ቀልብ ለመሣብ ሞክሯል:: እውነተኛ የሕዝብ ልጅ መስሎ ለመታየትም ጥራት አድርጓል:: የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን አፅምም ከተጣለበት አገኘሁ ብሎ ቆፍሮ በማውጣት ተወዳጅነትንና እንባ አባሽ መስሎ ለመታየትም ጥሯል:: ውሎ አድሮ ግን የንጉሣውያን ቤተሠቦች የንጉሡ አፅም በንጉሣዊ ክብር ከተገቢ ቦታው እንዲያርፍ በጠየቁት ጊዜ እንደማንኛውም ተራ ዜጋ መቅበር ትችላላችሁ ማለት ብቻ ሲበቃው ደርግ 17 ዓመታት ከዘፈነባቸው እጅግ በከፋ መልኩ ባንድ ምሽት የቴሌቪዥን ፕሮግራም ጥላሸት ቀባቸው:: እውነተኛ ባህሪው ይህ ነበር::

የሕወሓት ቁንጮ ባለሥልጣናትና ካድሬዎች ገና ጫካ ሳሉ ጀምረው ታሪክን መናድና የሕዝቦችን ሥነ ልቦና መስለብ፣ ያለፉ ነገሥታትን አፅም ማንበሳቆልና ጥላሸት መቀባት ዋና መለያቸው ነው:: በተለይም ያፄ ምኒልክ ከቡር አፅም ወደ አፈርነት ተቀይሮ ባለበት የዕድሜ ዘመን ላይ ተደርሶ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ እንደ ጠላ እህል እየተቆላ ይፈጫል:: ዛሬ ግን ጊዜ ደጉ "ለራስ ሲቆርሱ አያሣንሱ" እንዲሉ የባህር በር ቆልፈው ጉሮሮውን





ያነቁትን ሕዝብ ልክ እንደ ባለውለታ ተቆጥረው አቶ መለስን "ታላቁ መሪያችን!" ብለው ለማወደስና ሕዝብን ቃለ መሀላ ለማስገባት ነፋስ እንኳን አልቀደማቸውም::

የቀ.ኃ.ሥላሴንና ያቶ መለስን የክብር አቀባበር እንዲሁም የሐዘን ድባብ በተመለከተ አንድ አዛውንት ቁጭታቸውን ሲገልፁ:-

"ከእንግዲህ ለዚች አገር ቅን መሪ አያስፈልጋትም!" ሲሉ በምሬት ተናግረዋል::

በመሠረቱ ጠ/ሚንስትር መለስ ዜናዊ ጊዜ አገዛቸውና በክብር ተሸኙ እንጂ ሌላው ቢቀር በ97 ዓ.ም በአግዓዚ ጦር ባስጨፈጨፏቸው ወጣቶችና በዚህ 21 ዓመታት ውስጥ ባንድ ብሔረሰብ ላይ ባካሄዱት የዘር ማፅዳት ዘመቻ ወንጀል ተከሰው በዓለም ዓቀፉ ፍ/ቤት መቅረብ የሚገባቸው ሰው ነበሩ:: ዳሩ ግን ከሞት በላይ ሌላ ዋጋ ሊከፍሉ አይችሉምና ከተጠያቂነት አምልጠዋል:: ወደዚች ዓለምም ዳግም በይግባኝ አይመጡም:: ይህ ሲባል ግን በታሪክ አይጠየቁም ማለት አይደለም:: ጊዜው ሲፈቅድ የተደበቀውና የተቀበረው ሁሉ እየተቆፈረ ይወጣል:: እስከዚያው ግን በሙት መንፈሳቸው እየታመስን እንቆያለን::

# የፕሮፓጋንዳ ዶፍ!

ከጠ/ሚንስትሩ ቀብር ማግስት ጀምሮ በዋና ዋና አደባባዮች በታላላቅ ሕንፃዎች፣ በከፍተኛ መ/ቤቶች የጠ/ሚንስትሩ ፎቶ ግራፎች በቢል ቦርድ ማስታወቂያ (Bill Board) እየተሠራ አዲስ አበባን አጥለቅልቋታል:: እንዲሁም መሪ ቃሎች ወይንም መፈክሮች (ሞቶ) በዋና ዋና ጎዳናዎች ዳር ለዳርና መስቀልያ መንገዶች ፎቷቸው በቀለም ባጌጠ ታጅቦ አይረሴ እንዲሆኑ የታሰቡና ጠ/ሚንስትሩን ይወክላሉ ወይንም ታላቅነታቸውን ያጎላሉ የተባሉ ሐረጋትና ቃላት ተገጥግጦባቸዋል:: አንዳንዶቹ እሳቸው በሥልጣን ዘመናቸው በነበሩበት ጊዜ የተናገሯቸው ናቸው:: አንዳንዶቹ ግን የፈጠራ ሆነው ባድናቂዎቻቸው የቀረቡ ናቸው:: እነሆ:-

- *"ታላቁ መሪያችን ያወረሰንን ሀገራዊ ፍቅር፣ የዓላማ ፅናትና አይበገሬነትን ተቀብለን የህዳሴ ጉዟችንን ለማስቀጠል ቃል እንገባለን!!"*
- *"ጀግና ቢሞትም ሥራው አይሞትም!"*
- *"መለስ የኢትዮጵያ ሕዳሴ መሐንዲስ!" (በመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ት/ሚንስትር ፊት ለፊት) በነገራችን ላይ ት/ሚንስቴር ምን ሆኖ ነው የሙዋእለ ህፃናት ት/ቤት የመሰለው?*
- *"የሕዳሴው ግድብና ሰንደቅ ዓላማችን ብሔራዊ አርማችን ናቸው"*
- *"ታላቅና እጅግ አርቆ አሣቢ መሪያችን ሥራህ ሕያው ነው!" (ኡራኤል የቧንቧ ሥራዎች ነጋዴዎች)*
- *ብሩሕ ተስፋ ሕልሙን አርቆ ሠቅሎ ሩቅ እንደማተረ ከ40 ዓመት በላይ ያለ ረፍት ለወገኑ ቀንዲል ሆኖ ስለብርሃን እንደኖረ ያለፈ!" (አልፋ ሴራሚክ ካዛንቺስ)*
- *"ባለራዕይዎች ይሞታሉ! ራእያቸው ግን አይሞትም!" (ኢሣያስ ኡራኤል)*
- *"ጀግና አይሞትም! በመልካም ሥራው ሲታወስ ይኖራል! ሐዘናችን ጥልቅ ነው እንወድሐለን!!" (ኢሣያስ ማስታወቂያ)*
- *"ኢትዮጵያን አደራ!" ባምቢስ አካባቢ*
- *"ለሕዝብ የተፈጠረ! ለሕዝብ የኖረ! ለሕዝብ የሞተ! ታላቅ መሪ!" (ኤርምያስ ማስታወቂያ)*





- *"ያለምካትን ኢትዮጵያ እውን እናደርጋለን!" (ኢሣይያስ ማስታወቂያ ከየካ ክ/ከተማ ጋር በመተባበር)*
- *"ለወጣቶችና ሴቶች ተሣታፊነትና ተጠቃሚነት ያለመታከት የሠራ መሪ" (መገናኛ)*
- *"የሀገራችን ሕዳሴ መሐንዲስ!"*
- *"ለኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ነፃነት፣ እኩልነትና እድገት የታገሉ ታላቅ መሪ!"*
- *<"ያበረከትክልን የእድገት ራእይ ከኛ ጋር ይኖራል!" (ሙሐ የለስላሳ ኢንዱስትሪ መጠጦች ሠራተኞች ማህበር!)*
- *"ራእይህ ሕያው ሆኖ የሚኖር ያገር ሀብት ነው!"*
- *"ልማታዊ ራእይህን ለማሣካትና የሠጠኸንን አደራ ለመፈፀም ቃል እንገባለን!"*
- *"የእድገት ብርሃን የፈነጠቀ ራእይህ በሚሊዮኖች ብርታት ሆኖ ይዘልቃል!"*
- *"ለዴሞክራሲ፣ ለሰላምና ልማት የተጋ አፍሪካዊ መሪ!" (መስቀል አደባባይ)*
- *"ለመጭው ትውልድ ልማትን እንጂ ልመናን አናወርስም!"*

እንግዲህ መሪ ቃሎቹ እስካሁን የጠቀስኳቸው ናቸው:: እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት ግን አይደለም:: በከተማው ውስጥ በያሥር ሜትሩ ተገጥግጠዋል:: በመሪ ቃሎቹ ላይም ምንም ዓይነት አስተያየት መሥጠት አልፈለኩም:: አንባቢ በጥልቀት አንብቦ የራሱን ፍርድ እንዲሰጥ ነው የፈለኩት::

ያም ሆነ ይህ ከጠ/ሚንስትሩ ረፍት በኋላ ሁሉም ከፍተኛ ባለሥልጣናት አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝን ጨምሮ የየራሳቸውን ራእይ ይዘው ወደ ሥራ ቢገቡ ኖሮ እንዴት የተሻለ በሆነ ነበር:: ዳሩ ግን ሌትና ቀን እንደ ዶፍ የሚወርደው ፕሮፓጋንዳ እንቅልፍ የሚያስተኛ አይደለም::

ለመሆኑ "የመለስ ራእይ ሳይሸራረፍ ይቀጥላል!" ማለት ምን ማለት ነው? የመለስን ራእይኮ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለ21 ዓመታት እስቲያንገሸግሸው ድረስ ያውቀዋል:: ዛሬ የሚፈለገው ካዲሱ ጠ/ሚንስትር አዲስ ራእይ ነው:: እንዲያው ለመሆኑ አቶ ኃይለማርያም የራሳቸው የሆነ ራእይ የላቸውም? ሕወሓቶች ከኋላ ሆነው በርቀት መቆጣጠሪያ እየተቆጣጠሯቸው ባቶ መለስ ራእይ የሚመሩ ከሆነ ከባድ ፈተና ውስጥ ወድቀዋል:: እስከሙቸስ በሙት

መንፈስ አገር ሊመሩ ነው? ይህ ከባድ ጥያቄ ነው:: ከሁሉም በላይ የሚያሣዝነው ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው:: ሁልጊዜ በሙት መንፈስ ሲገዛ እንዲኖር ባፈቀላጪዎችና በጥቅም ተጋሪዎች ይበየንበታል:: አንድ የሩቅ ጊዜ ምሳሌ ልጥቀስ:-

አፄ ምኒልክ ካረፉ በኋላ በቅሏቸው ሰባት ዓመታት በሙት መንፈሳቸው ገዝታለች ይባላል:: ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ለሚለው ጥያቄ መሞታቸው ለሕዝብ በመደበቁ ምክንያት ነበር:: ንጉሠ ነገሥቱ በሕይወት ያሉ በማስመሰል ጧት ጧት በቅሎይቱ ባማረና ባጌጠ የወርቅ መጣብር ትጫኔንና የንጉሡ ምስል ከኮርቻው ላይ ጉብ ብሎ ከታላቁ ቤተ መንግሥት ብቅ ሲሉ ከፊት ከኋላ፣ ከቀኝ ከግራ ልክ እንደ ቀድሟቸው አጃቢው እያረበረበ ወደ እንጦጦ ሲያቀኑ ባካባቢው ያለው ሕዝብ መሬት እስከሚነካ ድረስ እጅ ይነሳል:: አጋፋሪዎቻቸውም በሠለጠኑ ፈረሶች እየቀደሙ "ጃንሆይ መጡ! መንገድ ልቀቁ!" እያሉ ያጋፍራሉ::

እናም ከዓለታት አንድ ቀን እንደተለመደው ምስላቸው ታጅቦ ከቤተ መንግሥት ወጥቶ ወደ እንጦጦ ሲያቀና ሕዝቡ ለጥ እያለ እጅ ሲነሣ አንድ ለሥራ ጉዳይ ሸዋ የመጡ ጎንደሬ በመገረም ቁመው ዝም ይላሉ:: በዚህ ጊዜ ካጠገባቸው የነበሩ አንድ የሸዋ መኮንን ተቆጥተው:-

"አንቱ ምን ተገትረው ያያሉ?! እጅ አይነሱም እንዴ?!" ይሏቸዋል:: ጎንደሬው በበኩላቸው ኮስተር ብለው:-

"ለማን ነው እጅ የምነሣው?" ሲሉ ይጠይቃሉ::

"ለጃንሆይ ነዋ! አሁንኮ ያለፉት አፄ ምኒልክ ናቸው!" ይሏቸዋል:: በዚህ ጊዜ ጎንደሬው ፈገግ ብለው:-

*"ሁልጊዜ አዋቂዎች ብልጥ እናንተ ብቻ*
*እኛ መች አጣናነው ባዶውን ኮርቻ!"* አሏቸው ይባላል:: ይህ በያነዬ ትልቅ የማረጋጊያ ጥበብ ሊሆን ይችላል:: የሚገርመው ግን ዛሬም እንደትናንቱ ቅኝቱ ሣይቀየር በ21ኛው ክፍለ ዘመን ኢሕአዴግ በጠ/ሚኒስትር መለስ የሙት ራእይ አገርን እመራለሁ ሲል ግርምትን ይፈጥራል:: ከዚህ ላይ ግን ጠ/ሚኒስትር መለስ በእውነት ሊታዘንላቸው የሚገቡ ሰው ናቸው:: ስንቱን ዕቃ ተሸከመውት ኖሯል? ባንድ ወቅት ዶ/ር አሸብር "መተኪያ የሌላቸው መሪ!" ሲሉ አሞካሽተዋቸው ነበር:: ለካስ እውነታቸውን ኖሯል:: ጠ/ሚኒስትሩን ቁራጭ ሥጋ ላይ እንደሚሠፍር ጉንዳን ሠፍረውባቸው የነበሩትን አስተውለው ነው::





# በሙት መንፈስ አገር ሲታመስ

አምባገነን መሪዎች አብራካቸው መሀን ነው:: እነሱን የሚቀናቀኗቸውንና የተሻለ እውቀት ያላቸውን አንድም በሥልጣን ዘመናቸው ቆርጥመው ይበሏቸዋል፤ **ወይንም አገር ጥለው እንዲሰደዱ ያደርጋሉ::** በተለይ ያፍሪካ መሪዎች ለዚህ ተጠቃሾች ናቸው::

ደርግ ቀ.ኃ.ሥን ከሥልጣናቸው አውርዶ "ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም" ብሎ ቢነሳም ብዙ ሣይርቅ 60ዎቹን ረሽኖ ከደም አዙሪት ውስጥ ተዘፍቋል። አብረውት የተሠለፉትን ሳይቀር ረሽኗል። ይህ ሁሉ ሲሆን መፈክርና ፕሮፓጋንዳ እንደ ዶፍ ያወርድ ነበር። ሕዝቡም በመሪ ካድሬዎች አቀንቃኝነት እየተቀበለ እስከ መጨረሻው ድረስ "ካብዮታዊ መሪያችን ከጓድ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ብልህ አመራር ጋር ወደፊት!" እያለ በፈጣኑ ባቡር ተሣፍሮ ባቡሩ ሐዲዱን ለቆ ሲምዘገዘግ በየፈርማታው እየተፈናጠሩ ወይንም እየተንጠባጠቡ የሚቀሩት ወይንም ተደፍጥጠው ያለቁት ቁጥር የትየሌሎዎች ናቸው:: በመጨረሻም የቁርጡ እለት ቆራጡና ብልሁ መሪያችን ቆርጠው ዚምባብዌ ሲገቡ "የተናቀ ከተማ ባህያ ይወረራል!" እንዲሉ ኢሕአዴግ ሥንቁን ባህያ ጭኖ አዲስ አበባ ገባ:: በእውነቱ የዚህ ዓይነት የጀግንነት ገድል የሚያስፈነድቅ ነበር:: ከዚህ የበለጠም ታላቅነትና ጀግንነት ሊኖር አይችልም:: ይኸ ሁሉ ጀግንነትም ያንድ ግለሰብ ሣይሆን የወል ነበር:: ዛሬ ተገልብጦ ግን ባቶ መለስ ሙት መንፈስ አገር ስትታመስ ማየት ይጎፈንናል::

ደርግ የኢትዮጵያን ሕዝብ በፕሮፓጋንዳና በመፈክር ጋጋታ አደንዝዞና ናላውን አዙሮ እሱ የሰሜን ፋኖዎችን መቋቋም አቅቶት ዉሻ እንደገባበት መንጋ ዝንጀሮ ብትንትን ሲል ሁሉም ነገር ባዶ ሆኖ ርቃናችንን ቀረን:: ዛሬም ኢሕአዴጋውያን የሚያወርዱት ፕሮፓጋንዳ የጤና አይደለም:: ራሳቸውን ሆነው መቅረብ ሲገባቸው ሊሆኑ ባለመቻላቸው ልክ በመንግሥቱ ኃ/ማርያም ሳንባ ሲተነፍሱ እንደነበሩ ባለሥልጣናት ግራ በመጋባት በያቅጣቻቸው ሕዝብን የውሃ ላይ ኩበት አድርገው እንደተበታተኑት ሁሉ ዛሬም ባቶ መለስ ሳንባ ሲተነፍሱ የነበሩ "ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ" ሆኖባቸው ግራ በመጋባት "ታላቁ መሪያችን የተለሙልንን ሕዳሴ ከግብ እናደርሳለን!" በሚል መሪ ቃል ሕዝብን በሙት መንፈስ ለመግዛት ማቀድ በጣም ነውር ነው:: ዝቅ ሲልም ንቀት ነው:: አለያም ሰው ማጣት ነው::

ወይንም ደግሞ እንደተለመደው ሕወሓት ከሕዝብ በስተጀርባ የሚሸርበው ሴራ አለ ማለት ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በየዘመናቱ በል የተባለውን ሁሉ እያለ የኖረ ሕዝብ መሆኑን ቀደም ሲል ለመጠቆም ሞክሬለሁ። ለምሳሌ ያህል አፄ ምኒልክን "እምዬ" ይላቸው ነበር። ይህንን ሲል ግን ምክንያት ነበረው። ካፄ ቴዎድሮስና ካፄ ዮሐንስ አመራር ጋር ሲነፃፀር ባንፃራዊ መልኩ በዘመናቸው ሰላም በመስፈኑ እንደናት ተቆጥረው "እምዬ" እንደተባሉ የእድሜ ባለፀጎች ይናገራሉ። መንግሥቱ ኃ/ማርያምም "ብልሁ፣ ቆራጡ፣" ይባሉ እንደነበር ቀደም ሲል ጠቅሻለሁ። የቁርጡ እለት ግን መንጌው እንደተባሉት ሆነው አልተገኙም። ቆራጥ አመራር ሰጥተው አገራቸውን ከውድቀት ማዳን አልቻሉም። የተሠጣቸው ወይንም የወጣላቸው የማንቆላጰሻ የቅፅል ስምና ተግባራቸው በጭራሽ አብሮ አልሄደም። ዛሬም ላቶ መለስ የሚዘንበው ፕሮፖጋንዳ አዲስ አይደለም። ከቆየው የቀጠለ ነው።

አንድ ሰሞን ደርግ በጦርነት ተወጥሮ በነበረበት ወቅት "ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር" የሚል መፈክር ነበረው። ዛሬም የኢሕአዴግ ከፍተኛ ካድሬዎችና ተከታዮቻቸው "ሁሉም ነገር ከታላቁ መሪያችን ጋር!" ወይንም "መንገዶች ሁሉ ወደ ካቴዲራል ቅድስት ሥላሴ ያደርሳሉ!" የሚሉ ይመስላሉ። ይኸ ሁሉ አዲስ አይደለም።

ቀ.ኃ.ሥላሴ ያልተባለላቸው ነገር አልነበረም። "ፀሐዩ ንጉሥ" ከሚለው ጀምሮ "የጠቅል አሽከር!" እየተባሉም ተፎከሮላቸዋል። ት/ቤቶች ሆስፒታሎች፣ ቴአትር ቤቶች ወዘተ በሳቸውና በልጆቻቸው ስም ተሰይመው ነበር። እነዚህ ሁሉ ዛሬ የሉም። ካብዮቱ ማግሥት ጀምረው ተፍቀዋል። ካለፈው ትምህርት አለመወሰዱ ደግሞ የሰውን ልጅ ከንቱነትና ስግብግብነት ያመለክታል።

ኮሎኔል መንግሥቱ የንጉሠ ነገሥቱን አሻራ አጥፍተው የራሳቸውን አሻራ ለማስቀመጥ ጥረት አድርገዋል። ፒያሣ የነበረውን ሐውልታቸውን አስፈርሰው የራሳቸውን የድል ሐውልት ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ፊት ለፊት አስቁመዋል። ደቡብ ክልል ሆሳዕና ከተማ በስማቸው የሚጠራ ሆስፓታልም ነበር። ዛሬ ስሙ ሣይቀየር አልቀረም። ኢሕአዴግም ይኸንኑ ፈለግ በመከተል አጠናክሯል።

የሕወሓት ኢሊቶች ሥልጣን እንደ ተቆጣጠሩ የኢትዮጵያን ታሪክ መቶ ዓመት ከሚለው ጀምሮ ባንዲራን "ጨርቅ" እስከሚለው ድረስ ብዙ ነገሮችን





ደልዘዋል። አማራ ክልል ዋና ከተማ በሆነችው ባሕርዳር ደርግ የሠራውን አይሮፕላን ማረፊያ "ግንቦት 20" ብለውታል። ግንቦት 20 ግን ላማራ ሕዝብ የመከራ ቋትን ያስታቀፈ ሥርዓት እንጂ የመና ዳቦ ከሠማይ ያዘነበለት ዕለት አይደለም። ምናልባት ሊሆን የሚችለው "ዶሮን ሲታልሏት በመጫኛ ጣሏት!" ዓይነት ነው።

ከዚህ አዲስ አበባ በቅርብ ርቀት የሚገኘው አንጋፋው የጦር ት/ቤት (ሆለታ ገነት) "ኃየሎም አርአያ" ተብሎ ተሰይሟል። ይህንን ኋላ ላይ እመለስበታለሁ። ለነገሩ ራሳቸውን ለመካብና ያልሆኑትን ሆነው ለመታየት የኢትዮጵያ መሪዎች ብቻ መለያ ባህሪ አይደለም። ያፍሪካ አምባገነን መሪዎች ጥቅል መገለጫ ባህሪ ነው።

ዳቪድ ላምብ የተባሉ ጋዜጠኛና ደራሲ "አፍሪካና አምባገነን መሪዎቿ" በተባለው መጽሐፋቸው እውነታውን አስቀምጠውታል።

. . .ሟቹ የኬንያ ፕ/ሬ ጆሞ ኬንያታ "ሙዜ" በሚባል ቅፅል ስም ይታወቁ ነበር። "ሙዜ" ማለትም በሷህሊኛ ቋንቋ "ብልሁ አዛውንት!" ማለት ነው። የታንዛኒያው መሪ የነበሩት ጁሊዩስ ኔሬሬ "መምህር" በመባል ሲንቆላጰሱ የማላዊው መሪ ደግሞ "የመሪዎች መሪ" ይባሉ ነበር። እንደኛው መሪ (እንደ አቶ መለስ "ታላቁ!" እየተባሉ እንደ ሚንቆላጰሱት ማለት ነው ወይንም እንደ ጥንት ነገሥታት "የንጉሦች ንጉሥ" ለማለት ነው።) ያይቬሪኮስቱ መሪ "የገበሬዎች ቁንጮ" ሲባሉ የኢኩዋቶሪያል ጊኒው ፕ/ሬ "ብሔራዊ ታምር ሠሪ!" ይኸ ደግሞ የተቀናጡ ናቸው። የኡጋንዳው ኢዲ አሚን ዳዳ "የእንግሊዝ ቅኝ ግዛትን ድል የመቱ" ብለው ራሳቸውን በራሳቸው ያንቆላጵሱ ነበር። እሳቸው ግን የእንግሊዝ አምሳ አለቃ ነበሩ። (ገጽ 47)

ወደኛዎቹ መሪዎች እንመለስና እንጠይቅ፤ ለመሆኑ ደርግና ሕወሓት ወይንም ኢሠፓና ኢሕአዴግ ለምንድን ነው መንግሥቱንና መለስን ለማግነንና እጅግ ለማላቅ የሚፈልጉት? ብለን መጠየቅና መልሱንም መፈለግ ያለብን ይመስለኛል። በዚህ ዙሪያ ማጠንጠን ተገቢ ነው።

## ታሪክ ፍቆ ታሪክ መሥራት አይቻልም!

ታሪክ እውነት ነው። እውነት በመሆኑም ማኅበራዊ ሳይንስ ነው። መጥፎም ሆነ ደግ እንዳለ ትውልድ እንዲማርበትና እንዲያውቀው እንዳለ

መቆየት አለበት፡፡ ከዚህ ባሻገር ታሪክ መደለዝና ታሪክ ፍቆ የራስን ከንቱ ታሪክ ለማስቀመጥ መስገብገብ የከፋት መንገድ ነው፡፡ የትም አያደርስም፡፡ ታሪክ የሚሠራው ለተሠሩ ታሪኮች ዋጋ መሥጠት ሲቻል ብቻ ነው፡፡ የደርግም ሆነ የሕወሓት ስብስቦች ያለፉ ታሪኮችን መኮነንና ማውገዝ አንድ የሚያደርጋቸው ነው፡፡ ርግጥ ነው ደርግ የሕወሓትን ያህል ታሪክ ለመደለዝና ለማጥፋት አልተንቀሳቀሰም፡፡ ይሁን እንጂ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ከታሪክ ማህደር ለመፋቅና አሻራቸውን ለማጥፋት ፏግሯል፡፡ ለምን? ጠይቁ፡፡

እንደሚታወቀው ደርግ የሠራዊት ስብስብ እንጂ እንደዚያን ዘመን ወይንም ወቅት አስተሳሰብ የነጋሢ ዘር ወይንም ደም ስለሌለው አልጋውን ወይንም ዙፋኑን ለመውረስ የሕግ ድጋፍ የለውም፡፡ ስለዚህ አልጋውን ለማፍረስና የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት ብዙ ማስመሰልና መቅጠፍ ነበረበት፡፡ በመሆኑም ሥልጣኑ ተቀባይነት እስከሚያገኝ ድረስ ሕዝቡን በመጀመሪያ ለማረጋጋት ሲል ልዑል አልጋ ወራሽ አሥፋው ወሰንን የዙፋኑ ወራሽ እንደሚሆኑ ተናገረ፡፡ ይኸም አንዱ ወደ ሚፈለገው ግብ ለመሸጋገሪያነት አገልግሏል፡፡ ቀጥሎ ልጅ ሚካኤል እምሩን ጠ/ሚንስትር አድርጎ ሾመ፡፡ ከውጭ አገር ወደ አገር ቤት ሲመጡ ቦሌ አይሮፕላን ማረፊያ ተቀብሎ ወደ ደርጉ ጽ/ቤት በመውሰድ ነፃ ሆነው እንዳይንቀሳቀሱና እንዳይሠሩ ቀይዶ በመያዝ በሌላ አገላለፅ ጥርስ የሌለው አንበሳ አድርጎ አስቀመጣቸው፡፡ ይህንን ሁሉ ሲያደርግም ንጉሠ ነገሥቱን ጭራቅና ስግብግብ፣ ወደ 11 ሚሊዮን የሚጠጋ ብር ውጭ አገር በሚገኝ ባንክ እንዳስቀመጡ አድርጎ በብዙሃን መገናኛ ጭፍን ፕሮፓጋንዳ በመንዛት ርቃናቸውን አስቀራቸው፡፡ የዘውዱንም ሥርዓት ሰወ በውላና የበበሰበሰ ሥርዓት ስለሆነ ተገርስሶና ከስሩ ተመንግሎ መውደቅ እንዳለበት አጠንክሮ ሰበከ፡፡

የዘውዱን ሥርዓት ለመገርሠስም ሆነ ንጉሠ ነገሥቱን እንዲተፉ ያደረጋቸውና ለደርግ እንደ ዋና ግብዓት የሆነው የወሎ ርሃብተኞች ምስል ነበር፡፡ ጆናታን ዲቢልቢ የቀረፀውን ፊልም ቤቴሌቪዥን በማስተላለፍ እንዲሁም በፊልም ቀርፆ በየከፍላተ ሀገራቱ እያዞረ በማሳየት ንጉሡን እስከነ ሥርዓታቸው እንዲተፉ አደረጋቸው፡፡ የናቶቻቸውን ጡት እንደነከሱ የሚያሸልቡ ህፃናትን በማሣየት ከጎን ደግሞ መሣፍንቱና መኳንንቱ ጮማ ሲቆርጡና በውስኪ ሲራጩ በማሣየት ንጉሡን የዲያቢሎስ ቁንጮ አድርጎ በማቅረብ ደጋፊና አዛኝ ተቆርቋሪ አሣጣቸው፡፡





ደርግ ከዚህ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱን መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም በቁጥጥር ሥር አውሎ በመቀጠልም ህዳር ወር መመሪያውን ሶሻሊዝም አድርጎ በየቀኑ አንዳንድ ተቋማትን እየወረሰ እምባገነንነቱን እያጠናከረ፣ አግረመንገዱንም ተቀባይነትንም እያገኘ ይጓዝ ጀመር፡፡

ደርግ አነሳሱ የውንብድናና የመፈንቅለ መንግሥት ዓይነት ስለነበር መጨረሻውም ማፈሪያ ነበር የሆነው፡፡ እስበሱ ሳይቀር እንዳበዱ ዉሾች ተቧጭቆ አገሪቱን ባዶዋን አስቀርቶ ያመለጠው አምልጦ የቀረው ልክ የኃይለ ሥላሴ ባለሥልጣናት እጃቸውን በጅምላ ለደርግ እንደሰጡት ሁሉ የደርጉ ስብሰቦችም ቁና ነውና በጅምላ እጃቸውን ለኢሕአዴግ በመሥጠት ወደ እስር ቤት ታጎሩ፡፡

በንጉሠ ነገሥቱ ጊዜ መሣፍንቱና መኳንንቱ ከያደፈጡበት እየወጡ እጃቸውን ለደርጉ በሰላም ሲሰጡ ሕዝቡ ገርሞት የሚከተለውን ግጥም ቋጥሮ ነበር፡-

*"ጥይት ሳይተኮስ ቦምብ ሳይፈነዳ*
*ያሁሉ መኳንንት እንደ በግ ተነዳ!"* ተብሎ ነበር፡፡

ደርግ በፈንታው ለኢሕአዴግ ተንጋግቶ ሀገር መከላከያ ሚንስቴር ሕንፃ ሄዶ እጁን ሲሰጥ፡-

*"ኢሕአዴግ ሲመጣ ባምቦ በኩል ቆርጦ*
*መንግሥቱ ሮጠ በኬንያ አቋርጦ!*
*ደህና ደህናው ሱሪ የትም ተጣለና!*
*ገመናችን ታየ ቀዳዳው ቀረና!"* ተብሏል፡፡

ልብ እንበል፤ ድርግ ነባር የኢትዮጵያ ሠራዊት ነው፡፡ ግን ደግሞ ሥልጣን የያዘው በሕገ ወጥ መንገድ አዛውንቱን ንጉሥ አታሎ የሳቸው ታማኝ ቋመምሰል ነበር፡፡ ስለዚህ ከሥልጣን ላይ ለመቆየት ደግሞ ንጉሠ ነገሥቱንም ሆነ ሥርዓታቸውን መኮነንና ማውገዝ ነበረበት፡፡ ሕወሓት በበኩሉ ሥልጣን የያዘው በትጥቅ ትግል ደርግን አሸንፎ እንጂ በሕጋዊ መንገድ በሕዝብ ድጋፍና ምርጫ አይደለም፡፡ ወይንም የንጉሣውያን ደም የለበትም፡፡ የፋኖ ስብስብ ነው፡፡ መሠረቱም አንድ ጎሳ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ራእይና ዓላማው እንዲሁም የመዳረሻ ግቡ ኤርትራን አስገንጥሎ ኢትዮጵያን የባህር በር ማሣጣትና የትግራይን ሪፐብሊክ እውን ማድረግ ነው፡፡ ይህንንም ሲደርግ ልክ እንደ ደርግ እሱም ሥልጣኑ ተቀባይነት እንዲኖረው ራሱን

"ዲሞክራት!" አድርጎ ማቅረብ ነበረበት፡፡ በተጓዳኝም የዘውዱንና የደርግን የኮሚኒስት ሥርዓት ማውገዝና አራማጆቹንም መኮነንና ጭራቅ አድርጎ በመሣል ለሕዝብ ማሣየትና በማያቋርጥ ፕሮፓጋንዳ ዛሬም ድረስ እንደ ዶፍ ማውረድ አለበት፡፡

ሌላው ቀርቶ ኤርትራን ተዋግቶ ማስገንጠሉንና ኢትዮጵያን የባህር በር ማሣጣቱን ሕጋዊና ፍትሐዊ እንደሆነ አድርጎ ዛሬም ድረስ ይሰብካል፤ ይከራከራል፤ ይሟገታል፡፡ ይህንንም ሲያደርግ ደጋፊ አላጣም፡፡ የሚመራበትን ሥርዓት በጎሳ አዋቅሮ ከየጎሳው የጎሳ ተጠሪዎችን በሱ ዙሪያ በማሰለፍ አገራዊ አጀንዳ አስለቅቆ ልክ እንደ መንደር ጭቃ ሹም ከመንደራቸው ውጭ እንዳያስቡ የነሱን ጥቅምና ክብር አስቀድሞ በመጠበቅ ያገርን ክብርና ጥቅም ሲጎዳ እያዩ እነዚህ የየጎሳው ወኪሎች አገር የተጎዳች አልመሰላቸውም፡፡ እንቁራሪት "እኔ ከምኖርባት ኩሬ ውጭ ሌላ ዓለም የለም!" ብላ እንዳለችው ዓይነት በመሆናቸው ሕወሓት ከሚያስበው ውጭ አያስቡም፡፡ ሕወሓት የሚናገረውና የሚለው ሁሉ ለነሱ የመለኮት ቃል ነው፡፡ እነዚህ ዜጎች "እናቴን ያገባ ሁሉ አባቴ ነው!" የሚሉ ናቸው፡፡ ከዚህ በመነሳት ሕወሓት ምን እየሠራ ነው? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው፡፡ ለምንድ ነው ከፍተኛ ካድሬዎቹና የጥቅም ደጋፊዎቹ "የታላቁ መሪችን ራእይ ሳይሸራረፍ እናስቀጥላለን" የሚሉት? ጠይቁ፡፡

ደርግ ነባር ሠራዊት ነበር ብለናል፡፡ ግን ደግሞ ነባሩን ሥርዓት ወይንም የዘውዱን ሥርዓት ይዞ ለመጓዝ ዙፋን የመውረስ ሕጋዊ መብት ስላልነበረው የዘውዱን ሥርዓት ማፍረስ ነበረበት፡፡ ይህንንም ሲያደርግ የሥርዓቱን አራማጆች ንጉሠ ነገሥቱን ጨምሮ ተከታዮቻቸውን ማውገዝና መረሸን ነበረበት፡፡ ባንፃሩ ሕወሓት የሥርዓት ለውጥ ቀርቶ ያሠራር ለውጥ እንዲኖር አይፈቅድም፡፡ የነበረው ሥርዓት ሳይሸራረፍ፣ ሳይበረዝና ሳይከለስ መቀጠል እንዳለበት ያምናል፡፡ ይህንንም ሲያደርግ የዚህ ሥርዓት ቁንጮ መሪ የነበሩትን አቶ መለስ ዜናዊንን ማድነቅና ማሞካሸት አለበት፡፡

ወገን የሰው ልጅ ሟች ፍጡር ነው፡፡ ጠ/ሚንስትር መለስም ሰው ነበሩና እንደሰው አለፉ፡፡ የሳቸውን ጅምር ትውልድ ጅረት ነውና ለመለስ ብሎ ሣይሆን ለራሱ ጥቅም ሲል ይጨርሳቸዋል፡፡ በሳቸው ሙት መንፈስ እንግዛችሁ ማለት ግን ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደሞከርኩት ሁሉ ኢሠፓ ውስጥ ሰው እንዳልነበር ሁሉ በኢሕአዴግ ውስጥም ሰው አለመኖሩን የሚጠቁም ነው፡፡ በማንኛውም መስፈርት ግን በሙት መንፈስ እንግዛችሁ ማለት ያሳፍራል፡፡





በመሠረቱ የማይሞትና ዘለዓለማዊ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ የኢህአዴግ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ግን አቶ መለስን ዘለዓለማዊ አድርገው ነው ያላንዳች ሐፍረት የሚሰብኩን፡፡ ከሙታን መሀከል ድንጋይ ፈንቅሎ የተነሣው ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፡፡ አቶ መለስን ማድነቅና ማወደስ የሚፈልጉ ካሉ በግላቸው ማድነቅ ይችላሉ፡፡ ሕዝብን ግን በሳቸው ሙት መንፈስ እንዲጨነቅ ማስገደድና በተለያዩ አጋጣሚዎች "የታላቁ መሪያችንን ራእይ እናሳካለን!!" እያሉ ቃለ መሀላ ማስገባት ተገቢም አግባብም አይደለም፡፡

በይደር ሲታዩና ለታሪክ ሲቆዩ የሚገባቸው ነገሮች ሁሉ ያለወቅታቸው እየተፈለፈሉ እንዲወጡ የመቀየሻ መጋዞች ጥርስ እየወጣላቸው ይመስለኛል፡፡ በተረፈ አዲሱ ጠ/ሚንስትር አዲስ ራእይ ነው ይዘው መቅረብ ያለባቸው፡፡ የነበረውን ከፋፋይ ሥርዓት ይዤ አስቀጥላለሁ ካሉ ከባድ ፈተና ይጠብቃቸዋል፡፡

◇◇◇

# ካዲሱ ጠ/ሚንስትር ምን ይጠበቃል?

በመሠረቱ አዲስ ጠ/ሚንስትር ሲሾም ሕዝብ ብዙ ተስፋዎችን ይጠብቃል፡፡ ከነዚህ ውስጥ፡-

ሀ. እሥረኞች በምሕረት ይለቀቃሉ ብሎ ሕዝቡ ያስባል፡፡ ይህ ደግሞ የተለመደና ሲሠራበት የኖረ በመሆኑ በጉጉት የሚጠበቅ ነው፡፡

ለ. በቆየው አመራር አስጨናቂና አፋኝ የነበሩ ሕጎችንና ፖሊሲዎችን ለምሳሌ (እንደ ሽብር ሕጉ፣ እንደ መሬት ሊዙ. . .) የመሳሰሉት እንዲሻሻሉ ወይንም አንድኛቸውን እንዲቀሩ ይደረጋሉ ብሎ ሕዝብ ተስፋ ያደርጋል፡፡

ሐ. የሕዝብን ንቅናቄ የፈጠሩና በቂ መልስ ሣይሰጥባቸው ቅሬታን እንደፈጠሩ በእንጥልጥል ላይ ያሉትን አዲሱ ጠ/ሚንስትር መፍትሄ ይሰጧቸዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ለምሳሌ፡-

የሙስሊሞች ሃይማኖታዊ የነፃነት ጥያቄ ወይንም ሃይማኖታዊ መብታችን ይከበርልን፣ የመምህራን የደመወዝ የማስተካከያ የርከን ጥያቄና ይህነኑ ተከትሎ ያለበቂ ምክንያት ለመቀጣጫነት ተብሎ ከማስተማር ሥራቸው የተባረሩ መምህራን ያላንዳች ቅድመ ሁኔታ ወደ መደበኛ ሥራቸው ሊመለሱ ይችላሉ ተብሎ በጉጉት ይጠበቃል፡፡

መ. የዋልድባ ገዳም ጉዳይም ሌላው እልባት ያልተሰጠበት ጉዳይ በመሆኑ ያዲሱ ጠ/ሚንስትርን ውሳኔ የሚጠብቅ ነው፡፡

እንግዲህ እነዚህንና እነዚህን መሰሎች ያልተፈቱና በእንጥልጥል ወደ አዲሱ አመት የተሸጋገሩ ችግሮች ቀና መፍትሄን የሚፈልጉ ናቸው፡፡ በማንኛውም መመዘኛ እነዚህና ሌሎቹም ያልጠቀስኳቸውን ውስብስብ ችግሮች እንዲቀጥሉ የሚሆኑ አይደሉም፡፡ ላዲሱ ጠ/ሚንስትር የከፉ ጋሬጣዎች ናቸው፡፡ መወገድ የሚገባቸው እንጂ እያስታመሙ እንኳን ለማቆየት የሚያስችሉ አይደሉም፡፡ እነዚህን ውስብስብ ችግሮች በጀርባ አዝሎ "የታላቁ መሪያችንን ራእይ ሳይሻራረፉ እናስቀጥላለን!" እያሉ መፎከር አቶ ኃይለማርያም ደሣለኝ ጭድ አዝሎ ወዘት መሆኑን ሊገነዘቡት ይገባል፡፡

እንኳንስ አንድ ጠ/ሚንስትር ይቅርና አንድ ሥራ አስኪያጅ ወደ አንድ መ/ቤት ተሹሞ ሲሄድ ያሠራር ለውጥ ያደርጋል፡፡ በምንም ሁኔታ የፊተኛው





ሥራ አስኪያጃ ይመራበት በነበረው ያሠራር መንገድ አይቀጥልም፡፡ የራሱን አዲስ ያሠራር ስልት ነው ይዞ የሚቀርበው፡፡ ይህንንም ሲያደርግ ቀደም ሲል የነበሩ ወይንም ቅሬታ ፈጥረው የነበሩ ያስተዳደር በደሎች ካሉ እነዚያን የሚወገዱበትን ዘዴ ፈልጎ ካስወገደ በኋላ በምትኩ ከሠራተኛው ጋር ሊያጣጥሙት የሚችሉትን ያሠራር ወይንም ያመራር ጥበብ ነው ይዞ መቅረብ ያለበት፡፡ ይህነን የማያደርግና በነበረው አሠራር የሚቀጥል ከሆነ ወደዚያ መ/ቤት ተሹሞ መሄዱ ፋይዳው ምንድን ነው? የሚል ጥያቄን ማስነሳቱ የግድ ነው፡፡

ያቶ መለስ ራእይዎችና ዓላማዎች ሳይበረዙና ሣይከለሱ የሚቀጥሉ ከሆኑ አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ያቶ መለስ እንደራሴ ወይንም ወኪል ሆነው የተሾሙ እንጂ የራሳቸው ራእይ ያላቸውና በራሳቸው የሚተማመኑ ናቸው ብሎ አፍን ሞልቶ ለመናገር ይከብዳል፡፡ ከሁሉም በላይ ያቶ መለስን ዝርዝር እቅዶችና ትልሞች ሳይሸራረፉ ይዘው ለመጓዝ ማስታወሻዎቻቸውን ማገላበጥ የግድ ነው፡፡ ይህንን ለማድረግ ደግሞ በየቀኑ ወይዘሮ አዜብ መሥፍንን ደጅ መጥናትና መለማመጥ ሊኖርባቸው ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከባድ ነው፡፡ የሚገርመው ደግሞ ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደሞከርኩት ሕዝብ ካዲሱ ጠ/ሚንስትር አንዳንድ ለውጦችን ሲጠብቅ አቶ መለስ ከተቀበሩ ማግስት ጀምሮ እጅግ በሚያሣዝን ሁኔታ ቤት ፈረሣ እንደ አዲስ መቀስቀሱ ነው፡፡ ይህ ተግባርም "የታላቁ መሪያችን" ራእይ ሳይሸራረፍ የሚቀጥል መሆኑን ከበቂ በላይ ማረጋገጫ ነው፡፡

ከ97 ዓ.ም የተሠሩ ቤቶች ባፍራሽ ግብረ ኃይል በታጣቂ እየታገዘ በኮተቤ ዙሪያ፣ በገርጂ፣ በካራ፣ በለገጣፎ፣ በሐና በሌሎቹም አካባቢዎች በሺዎች የሚቆጠሩ ቤቶች ፈርሰዋል፡፡ ይህ ዓይነቱ ክፉ ድርጊትም ያቶ መለስን ነፍስ ለሲዖል ይበላት ብሎ ለማስረገም ካልሆነ በስተቀር ሀገራዊ ፋይዳ የለውም፡፡ ውጤቱም ምሬትንና የቁርሾ ሥንቅን የሚያስቋጥር እንጂ የእድገት ፈር ቀዳጅ አይደለም፡፡

ደርግ ከኢሠፓኮ ወደ ኢሠፓ ሲሸጋገር አንዲት መዝሙር ቢጤ ነበረችው፡፡ "እኛው ነን! እኛው ነን! በችቧችን! በችቧችን!" የምትል ነበረች፡፡ እውነትም እነሱው ነበሩ፡፡ የተለወጠ ነገር ቢኖር ቅጠልያው ካኪ በሰማያዊ ካኪ መቀየሩ ብቻ ነበር፡፡ ዛሬም ኢሕአዴጋውያን አለመቀየራቸውንና በሙት መንፈስ እየተመሩ መሆናቸውን ቤት በማፍረስ እያሳዩን ናቸው፡፡

አንዳንድ ጊዜ የኢሕአዴግ ሹሞች የሚሠሩትን ላጤነ ሰው የበቀላቸው መነሻ ምክንያት አይታወቅም፡፡ ዜጎች የሠሩትን ቤታቸውን አፈራርሰው

ቆርቆሯቸውን ነቃቅለው መውሰድ በምን ሚዛን ሊቀመጥ ይችላል? የመንግሥት መኖርስ ትርጉሙ ምንድን ነው? መንግሥት በዜጎቹ ላይ ከሸፈተስ በማን ሊዳኝ ነው? እንደዚህ ከሆነ ከመንግሥት አልባዋ ሶማሊያ እኛ በምን እንለያለን? ይህንን ሳትስለቹ ጠይቁ፡፡

የቀበሌም ሆኑ የወረዳ ባለሥልጣናት ቤቱ ተሠርቶ እስከሚያልቅ ድረስ በቅርብ ርቀት ሆነው ሲከታተሉ ይቆዩና ባለቤቱ ጓዙን ጠቅልሎ ሲገባ ጠብቀው ያፈራርሳሉ!! ከነዚህ ዓይነቶቹ ጨካኞች ጋር ነው እየኖርን ያለነው፡፡ ምን ይሻላል? ጠይቁ፡፡

የማፍረሻ የትዕዛዝ ደብዳቤው የራስጌ መሥመር መሪ ቃል *"የታላቁ መሪያችንን ራእይ ተግባራዊ እናደርጋለን!!"* ነው የሚለው፡፡ አሰቡ እንግዲህ "የታላቁ መሪያችን" አንዱና ዋናው ራእያቸው ዜጎች እንዳቅማቸው ጎጆ ቀልሰው እንዲኖሩ ሣይሆን አፍራሽ ግብረኃይል አቋቁሞ የሠሯትን ጎጆ አፈራርሶ ቆርቆሮ ነቃቅሎ መውሠድ ነው፡፡ ይህንን ዓይነቱን ተግባርም በሕይወት ዘመናቸው ሲያስፈፅሙት የነበረ ነው፡፡ አሣፋሪውና አሣዛኙ ጉዳይ እሳቸው ካለፉ በኋላ እንኳን እጅግ በከፋ መልኩ በሙት መንፈሳቸው እየታመስን እንዲቀጥል መደረጉ ነው፡፡

ልብ እንበል፤ ዓይጦች እንደፍጡርነታቸው የሚኖሩበት ጉድጓድ አላቸው፡፡ ወፎችም ከዛፍ ላይ ጎጇቸውን ይቀልሳሉ፡፡ ሌሎቹም ፍጥረታት እንደየ አኗኗር ልማዳቸው መጠለያ አላቸው፡፡ ኢትዮጵያውያን ግን በነዚህ 21 ዓመታት ውስጥ የተረጋጋ ሰላም የላቸውም፡፡ እንደ ታዳኝ የዱር አውሬ እየበረገጉ የሥጋት ኑሮ ነው የሚኖሩት፡፡ ከረምት በመጣ ቁጥር ቤታቸው ከላያቸው ላይ እየፈረሰ በላይ ዝናብ በታች ጭቃ እያላቀጡ ይከርማሉ፡፡ ግፉ ማከተሚያ አጣ፡፡ ኧረ ምን ይሻላል? ጠይቁ፡፡ መልስ ሰጭ ባተገኙም አንድየ ይሰማችኋል፡፡ ይህንን አትጠራጠሩ፡፡

"ፋሽሽቱ ደርግ" የሚባለው እንኳን የገጠርን መሬት ቢወርስም ለገጠሩ አርሶ አደር እንዳቅሙ አከፋፈለ እንጂ በመያዣነት ይዞ ለራሱ ጥቅም አላዋለውም፡፡ የከተማ ቦታንና ትርፍ ቤትንም ቢወርስ ቤት ለሌላቸው ሰጠ እንጂ እንደ ዛሬዎቹ ባለሥልጣናት ዐይን ባወጣ መልኩ መሬትን በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ በሚስት ስም፣ በልጆች ስም፣ በዘመድ አዝማድ ስም ከዚህም በከፋና በሚያሳፍር መልኩ በዉሾችና በድመቶች ስም ቦታ እየተመራ አዲስ አበባንና የክልል ዋና ከተማዎችን አል ቀራመተም፡፡ ይህንን ጎምዛዛና ማፈሪያ ተግባር ነፍሳቸውን ይማረውና ፦ መለስ ባንድ ወቅት በተወካዮች





ም/ቤት ገልፀውታል፡፡ የዚህ ሁሉ ፅዋ ሞልቶ ሲፈስ የዚች አገር እጣ ፈንታ ምን ሊሆን ይችላል? ጠይቁ፡፡

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደሞከርኩት "አፋኙ ደርግ" እንኳን በነፃ ቦታ እየሰጠ አቅመ ደካሞችን ከባንክ ብድር የሚያገኙበትን አመቻችቶ እንዳቅማቸው በማኅበር ቤት ሠርተው እንዲኖሩ ያደርግ ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም ቤት ካልሠራችሁ እያለ ያስገደደበትም ወቅት እንደነበር ይታወቃል፡፡ ባንፃሩ "ዴሞክራቱ መንግሥት" መሬትን ነከሶ ይዞ የሕዝብ ጢሰኛ የመንግሥት ጉልተኛ ሥርዓት ዘርግቶ ወዳጆቹን ይተከላል፤ እሱን የሚቃወሙትን ወይንም እንደሰው ልጅነታቸው የተለየ ሐሳብ የሚያራም ዱትን ይነቅላል፡፡ መንቀል ብቻም አይደል እየተከታተለም ያሣድዳል፡፡

በመጀመሪያ ነገር የመሬት ፖሊሲ የለንም፡፡ በጅምላ ወይንም በደመነፍስ የዚህ ጎሣ የዚያ ብሔር ተወላጅ እየተባባሉ ዜጎች እስበሳቸው ሲጋጩ ኢሕአዴግ ገመድ አጓታች ዳኛ ሆኖ በመቅረብ የሥልጣን ዕድሜውን ከሱ አልፎ ወደ ልጆቹና የልጅ ልጆቹ ሳይሸራረፍ እንዲቀጥል በትጋት ይሠራል፡፡ የዜጎች አንድ መሆንና ሰላም ማግኘት ይጨንቀዋል፡፡ የባሩድ ጭስ እያሸተተ ያደገ በመሆኑ የሰላም አየር ያስነጥሰዋል፡፡

በመሠረቱ አንድ ዜጋ ያንዲት አገር ዜጋ ነኝ ሲል የመጀመሪያው መብቱ ያላንዳች ጥያቄ ወይንም ማመልከቻ ማንንም ፈቃድ ሣይጠይቅ በፈቀደበት ቦታ፣ በፈለገው ጊዜ ቤት መሥራት የቻለ እንደሆን ነው፡፡ ቤት በመሥራቱም በቆየው ወግ "ቤት ለንቦሣ" ይባላል እንጂ "ማን ሥራ አለህ?" ተብሎ አፍራሽ ግብረ ኃይል አይላክበትም፡፡ ማን አፍራሽ? ማንስ አስፈራሽ? የዜግነት መብት እኩል ነው፡፡ ባለሥልጣን፣ ተራ ዜጋ፣ ድሃና ሀብታም የሚባል ነገር የለም፡፡ ለዚህም ነው የገጠሩ ሕዝባችን ግማሹ ጋራ ላይ ሌላው ሜዳ ላይ ወይንም ወንዝ ዳር. . . ተበታትኖ መንደር መንድሮ የሚኖረው የማንንም ፈቃድ ስለማይጠይቅ ነው፡፡ ተበታትኖ መኖሩ ጥሩ ነው ባይባልም የዜግነት መብቱን መጠቀሙ ግን ያኮራዋል፡፡

በኢሕአዴግ ጊዜ ግን ይህ ዓይነቱ የዜግነት መብት ተፍቋል፡፡ አርሶ አደሩ የመንግሥት ጢሰኛ በመሆኑ ከብቶቹን እንኳን ለማሠማራት ከገበሬው ሊቀመንበር በጎ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

ወደ ከተማ ስንመጣ ደግሞ አንድ ዜጋ ቤት ለመሥራት የሚጠበቅበት ግዴታ በፕላን እንዲሠራ ብቻ ነው፡፡ ያለ ፕላን ሠርቶ ቢገኝ እንኳን እንዲያፈርስ የሚጠየቀው በሕግ ሆኖ የመሠረተ ልማት አውታሮች (እንደ

ውሃ፣ መንገድ፣ የመብራትና የስልክ) ዝርጋታዎች መሰናከል ፈጥሮ ሲገኝ ብቻ ነው:: እስከዚያው ግን ነፃና ባለመብት ነው:: በኢሕአዴግ ጊዜ ግን ይህንን መብቱን ተገፏል:: መንግሥት "መሬቱን ለልማት ይፈልገዋል" ባለጊዜ ዜጎች ቤታቸው በላያቸው ላይ እየፈረሰ ከጊዜው ጋር የማይመጥን ካሣ ቢጤ እየተወረወረላቸው የትም ይጣላሉ:: መሀል አዲስ አበባን አራት ኪሎ ከራስ መኮንን ድልድይ ጀምሮ እስከ ሽራተን ድረስ ያለውን፣ ሠንጋ ተራን፣ ልደታንና ጭርቆስን፣ ሌሎቹንም አካባቢዎች ያጤነ ዜጎች በዚህ ዘመን ተጠማኞች እንጂ (ያውም አሥጠማኝ ባለሥልጣን ከተገኘ) የዜግነት መብት የላቸውም::

ትንሽ ካዲስ አበባ ወጣ ስንል ደግሞ የሚገነቡት ፎቅ ቤቶችና ቪላዎች ትንግርት ያሰኛሉ:: ዱከምን፣ ለገጣፎን፣ ሱልልታን፣ ወይራ ሠፈርን፣ ዓለምገናን፣ አየር ጤናን መመልከቱ በቂ ነው:: በነዚህ አካባቢዎች የሚገነቡት ቤቶችና ድርጅቶች የዜጎቹን ማንነትና እነማን እንደሆኑ ቁልጭ አድርገው የሚያሣዩ ናቸው::

ኢሕአዴግ አገሪቱን እንደተቆጣጠረ ሰሞን አቶ መለስ ስለአዲስ አበባ ከተማ የወደፊት እጣፈንታ ተጠይቀው ሲመልሱ:-

*"ከቆዳማዋ ኃይለሥላሴ የሠፋች ከደርግ የጠበበች እንድትሆን እንፈልጋለን"* ብለው ነበር:: ያነዬ ኢ.አ እንዳሁኑ ሠንሻይንና አያት. . . የመሣሠሉ ግዙፍ ሕንፃ ገንቢ ድርጅቶች አልነበሩም:: በመሆኑም የከተማዋ ስፋት እስከዚህም የሚደነቅ አልነበረም:: ገርጂ አካባቢ እንኳን ጥቂት መንደሮች ብቻ ነበሩ:: በሌሎቹም አካባቢዎች ስፋቷ እንዲሁ የተመጠነ ነበር:: ዛሬ ግን በምስራቅ ያላንዳች ማጋነን አዳማ ከተማ ሊገጥም ትንሽ ቀርቶታል:: ወደ አዋሳ መስመርም ሞጆን አልፎ ቆቃ ግድብ ደርሷል:: በጅማ መሥመር ሠበታ ገጥሟል:: በደሴ መስመር እንዲሁ ሠንዳፋን አልፏል:: በጎጃምና ጎንደር መውጫ በኩልም ጫንጮ ገጥሟል::

ልብ እንበል፤ የከተማዋ መለጠጥ አይደለም ትንግርት የሚያሰኘው፤ እነማናቸው እንዲህ በጥድፊያና በወረራ መልክ መሬቱን እየተሻሙ ያሉት? የሚለው ጥያቄ ነው መመለስ ያለበት::

ኗሪው ሕዝብ እየተነቀለ ወይንም መደለያ ቢጤ እየተወረወረለት ኢንቬስተር ተብየዎች እጅግ በሚያስደንቅ ሁኔታ ከወደቀ ጥንብ ላይ እንደ ሠፈሩ ጥንብ አንሣዎች በጉምጀታ የሚቧጨቁት የዘመኑ ሹሞችና የባዕዳን ቱጃሮች ናቸው:: ቻይናዎችና ሕንዶች ዋንኛዎቹ ናቸው:: ሸሚያው ምን





ያህል እየተጧጧፈ መሆኑን ማረጋገጫው ደግሞ ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደ ሞከርኩት ሥግብግብ ባለሥልጣናት በዉሾቻቸው ስም ሣይቀር መቀራመታቸው ነው:: ሌላው መነሣት ያለበት ጥያቄ ሻጩ ማነው? የሚለው ነው::

እንደሚታወቀው አንድነት ፓርቲ "መሬት መሸጥ መለወጥ አለበት! ይህ የዜጎች የተሟላ መብት ነው!" ሲል በፕሮግራሙ አስፍሮ ይሟገታል:: አንድነት እንዲህ ሲልም ከመብት አንፃር እንጂ ዜጎች መሬታቸውን እየሸጡ ይሰደዱ ማለቱ አይደለም:: በመጀመሪያ ነገር መሬት ለኢትዮጵያውያን ከምንም በላይ ትርጉም እንዳለው ጠንቅቀው ያውቃሉ:: "እትብቴ የተቀበረበት" የሚል ሕዝብ እንጂ መሬቱን እየሸጠ የሚሰደድ ሕዝብ አይደለም:: የነቃ፣ ያወቀ ሕዝብ ነው::

አንድነት "መሬት መሸጥ መለወጥ" አለበት ሲልም በፍፁም ቅንነት ከመብት አንፃር ነው:: ግለሰቡ ከፍ ሲልም ሕዝቡ የማይገሠሥ መብቱ ሊከበርለት ይገባል ማለቱ ነው:: መሸጥ ከፈለገም ይሸጥ:: ገዥም ኢትዮጵያዊ ነው:: ሻጭም ሲሸጥ ለራሱ በቂ የሆነ አስቀርቶ ሌላውን ለተሻለ ኑሮና እድገት ቀይሶ እንጂ ዝም ብሎ ኢሕአዴግ እንደሚለው መሬቱን ሸጦ አረቂ ለመጠጣት አይደለም::

ለጊዜው ያንድነትን ፕሮግራም እናቆየውና የኢሕአዴግን "መሬት አይሸጥም አይለወጥም" የሚለው የማታለያ ሠብቅ ይዘን ሂደቱን እንመልከተው::

ኢሕአዴግ ባንድ በኩል ለሕዝብ የቆመ መስሎ "መሬት አይሸጥም" እያለ ይሰብካል:: በሌላ በኩል ደግሞ የሠከረ አሣ ዓመለጠህ በሚመስል ዓይነት እንደሸቀጥ ዜጎችን ከሥር መሠረታቸው እየነቀለ ይቸበችባል:: ነገ ትውልድ እንዴት ይሆናል? ብሎ የሚጨነቅ መንግሥት አይደለም:: ጨካኝ ድርጅት ነው:: ሹሞቹና ካድሬዎቹ ያላንዳች ርኅራኄ እንደ ቅርጫ ሥጋ መሬት ሲቀራመቱ እያየ ዝም ማለቱ ኃላፊነት የጎደለው ወይንም የሕዝብን አደራ መሸከም የማይችል ፓርቲ መሆኑን በቂ ማረጋገጫ ነው::

ኢሕአዴግ መሬትን ብቻ አይደለም ለውጭ አገር ቱጃሮች እየሸጠ ያለው፤ ዜጎችን ጭምር ነው:: ኤጀንሲ አቋቁሞ ዘመናዊ የባርያ ንግድን እያፋፈመ በብዙሃን መገናኛዎች ግን ለይምሰል አስከፊነቱን ይገልፃል፤ የግል ኤጀንሲዎችን ያወግዛል፤ በጎን ግን የባሪያ ፍንገላ ፈቃድ የሚሠጣቸው እሱ ነው:: የሚወነጅላቸው ሕገወጦች ናቸው ብሎ ሣይሆን "እኔ ብሸጣችሁ

ይሻላችኋል፤ ደህንነታችሁ የሚጠበቀውና ዋስትና የምታገኙት በኔ በኩል ስትሄዱ ነው" ለማለት ነው፡፡ ከግል ኤጀንሲዎች ጋር ጠቡ በጥቅም ብቻ ነው፡፡ ኢሕአዴግ ጉደኛ ድርጅት ነው፡፡ ገንዘብ አይጠግብም፤ ካይኑ ላይ ብር በቅሎበታል፡፡ እንግዲህ ኢሕአዴግ "መሬት አይሸጥም አይለወጥም" ሲል ሀቁ ከፍ ብዬ የገለፅኩትን ነው የሚመስለው፡፡

በመሠረቱ አንድ የከተማ ዜጋ የከተማ ቦታን ለማግኘትና ቤት ሠርቶ ለመኖር በሦስት መንገዶች መጠቀም ይችል ነበር፡፡

ሀ. ወላጆቹ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ በውርስ

ለ. በመመራት (በማዘጋጃ ቤት)

ሐ. በመግዛት ናቸው፡፡ ዛሬ ግን ሦስቱም መብቶች የሉም፡፡

የወላጆችን መውረስ ያለ ቢመስልም የቤቱን ጣራና ግድግዳ እንጂ መሬቱ የመንግሥት መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡ ጣራና ግድግዳውንም ቢሆን ስም ለማዛወር ውልና ማስረጃ ሲሄዱት ተቆልሎ የሚጠብቀው ገንዘብ ቤቱ ቢሸጥ አይወጣውም፡፡ ሌላው መነሳት ያለበት ጥያቄ ለምንድን ነው መንግሥት ራሱን ባለርሥት ሕዝብን ጢሰኛ በማድረግ የሚያስጨንቀው? ብለን ብንጠይቅ ሁለት መልሶችን እናገኛለን፡፡

አንደኛው ከፍ ብዬ ለመግለፅ እንደ ሞከርኩት እያንዳንዱ የመንግሥት ባለሥልጣን ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ልክ እንደ ውጭ ወራሪ ኃይል ከቁጥጥር ውጭ በሆነ መልኩ ከከፋ የመሬት ቅርምት ውስጥ በመግባት መሬትን በመሸጥና በመለወጥ የንግድ ተቋማትን በማቋቋም ተሠማርቷል፡፡ መንግሥታዊ ሥራና ኃላፊነት ጨርሶ ተረስቷል ማለት ይቻላል፡፡ ኢሕአዴግ "መሬት አይሸጥም አይለወጥም" ይላል እንጂ ደጋፊዎቼ ለሚላቸው ኢንቬስተሮች እንደ ጣቃ እየቀደደ በመሸጥ መጠነ ሠፊ ገንዘብ በማጋበስ ላይ ይገኛል፡፡ መልሶም ዜጎች ለመብታቸው እንዳይሟገቱ ለማፈኛነት ያውለዋል፡፡

ሁለተኛው፤ መሬትን በቁጥጥሩ ሥር ያደረገበት ምክንያት በሥልጣን ላይ ለመቆየት እንደመያዣ ዋስትናው አድርጎታል። በገጠርም ሆነ በከተማ መሬትን አንቆ ይዞ "እኔን ካልመረጣችሁኝ ከመሬቴ እነቅላችኋለሁ!" እያለ በማስፈራራት እንደመልካም አጋጣሚ እየተጠቀመበት ይገኛል፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን የጉራፈርዳ ተፈናቃዮች ናቸው፡፡





እነዚህ ዜጎች አማራ በመሆናቸው ብቻ አይደለም በገዛ አገራቸው ስደተኞች እንዲሆኑ የተበየነባቸው፤ በ97 ዓ.ም እና በ2002 ዓ.ም አገር አቀፍ ምርጫዎች ኢሕአዴግን አልመረጣችሁም በሚል የብቀላ ርምጃ እንደተወሰደባቸው ተፈናቃዮቹ ራሳቸው እያነቡ ተናግረዋል፡፡

እንግዲህ ይኸ ሁሉ ሠቆቃና የዜግነት መብት ገፈፋ፣ ቤት ማፍረስ፣ ከሚኖሩበት ቀየ ንብረትን እየወረሱ ማባረር፣ "የታላቁ መሪያችን" ራእይ ሳይሸራረፍ እንዲቀጥል የሚሹት የቅርምቱ ተካፋዮች ጩኸት በመሆኑ አያስገርምም፡፡ የሚያስገርመው ከረጋጮቹ ጋር ሆኖ ተረጋጩ አብሮ መጮሁና ራእያቸው እንዲቀጥል ቃለ መሀላ መግባቱ ነው፡፡ ይህ የሚገርም ነገር ነው፡፡ ወጣም ወረደ አዲሱ ጠ/ሚንስትር ይህንን ዓይነት ፍትሕ የጎደለው አሠራር ይዤ እጓዛለሁ ወይንም አስቀጥላለሁ ካሉ የከፋ አደጋ ይጠብቃቸዋል፡፡ አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝን ሕወሓት ከኋላቸው ሆኖ እየተቆጣጠረ የሚያሠራቸው ከሆነ ሊወጡት ወደማይችሉት ማጥ ውስጥ ይገባሉ፡፡ ወቅቱ ደግሞ ችግሮች ሊፈነዱ ጫፍ ላይ የደረሱበት ነው፡፡ ሥልጣን ላይ እንደመውጣቱና ቤተመንግሥት እንደመግባቱ በጭራሽ ቀላል ሊሆንላቸው አይችልም፡፡

# ታላቅነት ምን ማለት ነው? እንዴትስ ይበየናል?

"ታላቅነት" ምን ማለት ነው? ለሚለው ጥያቄ የግድ መዝገበ ቃላት ፍለጋ መሄድ አያስፈልገንም:: በጥሬ ፍችው:- በዕድሜው የላቀ፣ የበኩር ልጅ፣ የታናሾቹ ታላቅ. . . ማለት ነው:: በማኅበራዊ ፍችው ደግሞ "ታላቅነት" ማለት የተከበረ፣ ከሁሉም አንጋፋ፣ ምራቁን የዋጠ፣ መምከርና መዘከር የሚችል፣ ተፈርቶ የሚከበርና የሚፈቀር፣ የሚናገረው ሁሉ ተደማጭነት ያለው፣ ከወረዱ ሐስተሳሰቦች እጅግ የራቀ፤ አስተዋይ፣ አጭቶ የሚያገባ፣ የተጣሉን ተቆጥቶ የሚያስታርቅ. . . ማለት ነው:: በዕድሜቸው አንጋፋ የሆኑ ሁሉ ግን "ታላቅ" ተብለው አይከበሩም:: ፎሽፏሾችና ግልቦች ሆነው ሲገኙ "እንጨትም ይሸብታል" በማለት ይተቻሉ፤ ወይንም ይነቀፋሉ:: እንዲህ ዓይነቶቹ አዛውንቶች ለታላቅ ቁምነገር አይታጩም:: ባንፃሩ በዕድሜቸው ልጅ ቢሆኑም እንኳን በቁም ነገረኛነታቸው የሚታወቁ ከሆኑ "የልጅ አዋቂ" ተብለው ይከበራሉ::

"ታላቅነት" ባገር መሪ ደረጃስ እንዴት ይበየናል? ለሚለው ጥያቄ ባገር መሪ ደረጃ የሚሠጠው ዋጋና በሕዝቦች ሕሊና ውስጥ የሚያሣድረው ጫና በቀላሉ የሚገመት አይደለም:: አበው "ከንጨት መርጦ ለታቦት፣ ከሰው መርጦ ለሹመት!" ሲሉ ከቡርነቱንና ታላቅነቱን በሥነ ቃል ይገልፁታል:: ከዚህ እሳቤ ስንነሳ አንድ ያገር መሪ ታላቅነቱ በመጀመሪያ የሚመነጨው ከራሱ ተፈጥሯዊ ባህሪ ሲሆን ቀጥሎ ከወላጆቹ አስተዳደግና ባህሪ በከፊልም ቢሆን የሚወርሳቸው ባህሪዎች ይኖራሉ:: እንዲሁም ካደገበት አካባቢ ማኅበረሰብ የሚወርሳቸው ጉልህ ባህሪያዎች ይኖራሉ:: "ሰው አካባቢውን ይመስላል" የሚባለውም ያለ ምክንያት አይደለም:: በትምህርት የተገራና የተቃና እንዲሆንም ይጠበቅበታል:: ከዚህ አንፃር ሲበየን አንድ ያገር መሪ "ታላቅ ነው" ሊባል የሚችለው በመጀመሪያ አበው "ካያያዝ ይቀደዳል! ካነጋገር ይፈረዳል!" እንደሚሉት አንድ ያገር መሪ አነጋገሩ ለዛ ያለው፣ ማንንም የማያስቀይም በዘመናዊ አነጋገር <ዲፕሎማት> የህዝብን ቀልብ የሚስብ፣ ከፀያፍ አነጋገሮች በልማዳዊ አገላለፅ <ጋጠወጥ> ከምንላቸው አነጋገሮች የሚጠነቀቅ መሆን አለበት:: ባጭሩ ያንድ አገር መሪ ንግግር ጨዋና ለጥቅስ የሚበቃ መሆን እንዳለበት ይጠበቃል:: ይህ የሚገለፀው ደግሞ በቋንቋ ነው::





## ያንድ መሪ የቋንቋ አጠቃቀም ምን መሆን አለበት?

ቋንቋ የተሟላ ሐሳብን ለመግለፅ ወይንም ለሌሎች ለማስተላለፍ ወይንም ከሌሎች የተሟላ መልእክትን ለመቀበል የሁሉም ነገር የመክፈቻ የምስጢር ቁልፍ ነው:: እንደሚስጢር ቁልፍነቱም በተገኙ ሐረጋትና ቃላት እንደተፈለገ መልእክትን ማስተላለፍ አይቻልም:: ከሌሎች አካላት ጋር ሊያጋጩ፣ ሊያስከፉ ከሚችሉ አገላለፆችና አነጋገሮች መጠንቀቅ የተናጋሪው ግዴታ ይሆናል:: ውለው አድረው ሊመነዘሩ ከሚችሉ አገላለፆች መጠንቀቅ ደግሞ ካንድ ታላቅ መሪ የሚጠበቅ ውዴታ ብቻ ሣይሆን ግዴታም ነው::

አንድ መሪ በግልጽ ባደባባይ ንግግር በሚያደርግበት ወቅት ከሚመራው ሕዝብ ጋር የሚያላትመውን ንግግር ከተጠቀመ "ታላቅ" ሊባል ቀርቶ ትንንሾች በሚመዘኑበት ሚዛንም ሕዝብ አይመዝነውም:: በተለይም እንደዘበት በማናለብኝ ዓይነት የሚወረወሩ ቃላት የሌሎችን ሕሊና የሚጎዱና የሚያቆስሉ ከሆኑ ቁጣን፣ ቁጭትን፣ እልህን የሚቀሰቅሱና የጠብ አጫሪነት ምልክቶች የሚሆኑበት አጋጣሚ ብዙ ነው:: እንዲህ ሲሆን ያ መሪ ታላቅ ሳይሆን ጀብደኛና አምባገነን እንጂ ቅን መሪ ነው ተብሎ በታላቅነት አይመዘንም:: ከዚህ መሠረታዊ ፅንሰ ሐሳብ ስንነሳ አቶ መለስ እውነት እንደሚጮህላቸው ያሉ "ታላቅ መሪ" የሚባሉ ነበሩ? ይህንን በተመለከተ ከጥላቻ በራቀ መልኩ ሚዛናዊ በሆነ ሌላ ሣንጨምር እሳቸው ብቻ ከተናገሯቸው እጅግ በጣም ጥቂቶቹን እየመዘዝን እንመዝናቸው::

ጠ/ሚንስትር መለስ ዜናዊ በዚህ 21 ዓመታት ውስጥ እንዳስተዋልናቸውና እንደምናውቃቸው ንግግራቸውም ሆነ ጋዜጣዊ መግለጫዎቻቸው እንዲሁም በተወካዮች ም/ቤት ሪፖርት በሚያቀርቡበት ወቅት የሚጠቀሙባቸው ቃላት ካንድ መሪ የሚጠበቁ አልነበሩም:: ያቶ መለስ ንግግሮች አስደንጋጮች፣ አሽማቃቂዎችና አንገት አስደፊዎች ነበሩ:: አጠቃላይ አነጋገራቸው በግልፍተኝነት ሳይሰለቁ በግርድፉ የሚለቀቁ ነበሩ:: አስረጅ:-

"ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መቆንጠሷ" እንዲሉ ገና ከጫካ መጥተው የገሪቱ ፕሬዚዳንት እንደሆኑ ንግግራቸውን ያሟሹት ወይንም ከሕዝብ ጋር የተዋወቁት ባንዲራን "ጨርቅ" በማለትና በማዋረድ ነበር:: ከዚሁ አገላለፅ ጋር በተያያዘ "ከጨርቁ በስተጀርባ" ሲሉም በቀልተኛነታቸውን ጨምረውበታል:: እውነትም "ከጨርቁ በስተጀርባ" አለ ያሉትን ያማራ ሕዝብ እስከ እልፈተ ሕይወታቸው ድረስ እየተከታተሉ ሲበቀሉትና

ሲያሣድዱት አስተውለናል:: የሩቁን ትተን የቅርብ ጊዜዎቹን የጉራፉርዳ ተፈናቃዮችን መጥቀሱ ብቻ በቂ ማስረጃ ነው::

"በ1984 ዓ.ም መቀሌ ላይ ለትግራይ ሕዝብ ባደረጉት ንግግር <የትግራይ ሕዝብ እንኳንም ባዳህ አልሆንኩ:: እንኳንም ያብራክህ ክፋይ ሆኘ ካንተ ተፈጠርኩ!> ብለው ተናግረው ነበር:: ‹ይህ ንግግርዎ ምን ለማለት ነው?" ተብለው ከጊዜ በኋላ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ:-

*"ይህ ሕዝብ እንኳን የኔ ሆን ለማለት ነው:: አባባሉን ዛሬም የምፀፀትበት አይደለም:: በትግሉ ወቅት የትግራይ ሕዝብ በእሳት ተፈትኗል:: በእሳት ደግሞ ወርቅና ጨርቅ ይለያል:: (ይፈተናል) የትግራይ ሕዝብ በእሳት ተፈትኖ ጨርቅ አለመሆኑን አስመስክሯል:: . . . እኔም በእሳት የሚጠፋ ጨርቅ ሳይሆን በእሳት የተፈተነ ወርቅ ተመኘሁ:: በዐይኔ ወርቅ የሆነው የትግራይ ሕዝብ አካል በመሆኔ ደስ ይለኛል ብል ነውር የለውም" (ገጽ 13-14 መለሰ ከልጅነት እስከ እውቀት በትኩእ ባህታ)*

ጠ/ሚንስትር መለስ ዜናዊ ያነዬ ማለትም 84 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ነበሩ:: ይህ ማለትም ከጠባቧ የጎሣ ጉረኖ ወጥተው ከሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ወይንም ከውቅያኖሱ ገብተው እየዋኙ የነበረበት ወቅት ነበር:: በዚህ ጊዜ መቀሌ ዘልቀው የትግራይን ህዝብ በወርቅ መስለው ከማድነቅና ሌላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በጨርቅ መስለው ህሊናውን ከመጉዳት ባጭሩ "የትግራይ ሕዝብ በትግሉ ወቅት ያደረገልን ውለታና የከፈለውን ሁለንተናዊ መስዋእትነት በኔ አቅም ተነግሮ አያልቅም:: በከፈለው መሥዋእትነትም ዛሬ ቀጥታ የዴሞክራሲው ተጠቃሚ ሆኗል:: ትግሉ የጠየቀውን ዋጋም የከፈለው ይህንን ለማምጣት ስለነበር ዛሬ በውጤቱ ሊኮራ ይገባዋል:: ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የከፈለው ዋጋ የትግራይ ሕዝብ ይገነዘበዋል ብዬ አምናለሁ:: በንደዚህ ያለው የመብትና ለነፃነት ለሚከፈል መሥዋዕትነት አመስጋኝም ተመስጋኝም ሊኖር አይችልም:: ትልቁ ቁም ነገር አፋኙን የደርግ ሥርዓት አሥወግደን ለድል መብቃታችን ነው:: ለዘህ ስኬት ደግሞ የትግራይ ሕዝብ ግንባር ቀደም ተሣታፊ በመሆኑ ዛሬ ሊደሰት ይገባዋል:: እንኳንም ደስ አላችሁ! እንኳንም አብሮ ደስ አለኝ!" በማለት የትግራይንም ሕዝብ አወድሰው ሌላውን ሕዝብም ሣያስቀይሙና ሕሊናውን ሣያቆስሉ በጨዋ የመሪ አነጋገር መግለጽ ይቻል ነበር:: ከዚህ በወረደ ግን በወርቅና በጨርቅ እያነፃፀሩ መግለፁ መለስነትን አጉልቶ ከመግለፅ ውጭ ፋይዳ አልነበረውም:: ሆኖ ያለፈውም ይኸው ነበር::





የትግራይን ሕዝብም በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ወንድም ከሆነው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ለመነጠል የታለመ ንግግር ነበርም ማለት ይቻላል:: እውነታውም ይኸ ነው:: አልሆነለትም እንጂ የሕወሓት የመጨረሻ ግቡና ዓላማው ወርቁን የትግራይ ሕዝብ ከሌላው <ጨርቅ> ሕዝብ ለመነጠል ነበር::

በመጀመሪያ ነገር ወርቅና ጨርቅ ሊነፃፀሩ የሚችሉ ነገሮች አይደሉም:: መናኛ የሆነ ማነፃፀሪያ ነው:: ጨርቅ በጠለሸት ወይንም በእሳት ፍንጣሪ ሊቃጠል የሚችል ነው:: እንደ አቶ መለስ አገላለፅም ዝቅ አድርገን የምናየውም አይደለም:: ገመናችንን ከመከለል ጀምሮ ከብርድና ከፀሐይ የምንከላከለው በልብስ ነው:: የሰውን ልጅ ከብር ከሚያጎናፅፉት ነገሮች መሀከል አንዱና የመጀመሪያው ልብስ ነው:: አበው "ልብሴን ነውር በለው" የሚሉት ያለምክንያት አይደለም:: በመሆኑም ጨርቅም ከሚሰጠው ጥቅምና አገልግሎት አንፃር ዝቅተኛ ግምት የምንሠጠው አይደለም:: ይህም ሆኖ ከወርቅ ጋር ስናነፃፀረው ደግሞ ለወርቅ የምንሰጠው ግምትና ዋጋ እጅግ የላቀ ነው:: ወርቅ እንደ ልብስ በማንኛውም ተራ ግለሰብ እጅ ወይንም ጣት ተሰክቶ አናገኘውም:: የቅንጦት ወይንም የከበረ ማዕድን ነው::

የትግራይን ሕዝብ በወርቅ ለመሰልና ሌላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ዝቅ ለማድረግ ከተፈለገ ትክክለኛው የማወዳደሪያ ዘዴ ከብር፣ ከነሐስና ከመዳብ ጋር ማነፃፀር ይቻላል:: ከዚህ ዝቅ አድርጎ ለማዋረድም ከተፈለገ በቲማቲም ቆርቆሮ ወይንም ጣሣ መመሰል ይቻላል ::

በመሠረቱ የኢትዮጵያ ሕዝብና ጦርነት የተለያዩበት ጊዜ በውል አይታወቅም:: የውጭ ወራሪ መጣ በተባለ ጊዜ የዚህ ጎሣ ወይንም የዚያ ብሔረሰብ ሳይባባል ጠላት መጣበት ወደ ተባለበት ሥፍራ እየተመመ ተፋልሞ ጠላቱን ድል ነሥቶ ይመለሣል:: ወጉ፣ ባህሉ፣ ታሪኩ ይህ ነበር እንጂ አንዱን ወርቅ ሌላውን ጨርቅ የሚያደርግ በታሪካችን ውስጥ ተቀምጦ አልቆየንም:: ለዚህ አስረጅ የሚሆነን ያድዋ ዘመቻና ድል ነው::

ያድዋ ድል ጀግኖች አባቶቻችን እከሌ ከከሌ ተባብለው ሣይለያዩ እኩል ይኮሩበት ነበር እንጂ አዝማቹ አፄ ምኒልክ ስለሆኑ ያማራ ዘር ወርቅ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ጨርቅ ተብለው አልተፈረጁም ወይንም አልተመሰሉም::

እንደሚታወቀው አፄ ቴዎድሮስ (ካሣ) ከቋራ መንደር (ጎጥ) ተነስተው የድል አድማሣቸውን እያሠፉ የጎጃምንና የጎንደርን መሣፍንት ተራ በተራ እያንበረከኩ በመጨረሻም የሰሜኑን ደጃዝማች ውቤ ኃይለማርያምን ድል

አድርገው ደረስጌ ማርያም ላይ ዘውዳቸውን ከጫኑ በኋላ ወሎና ሸዋ በመሻገር ድል በድል በመሆን በመሣፍንት ተከፋፍላና ተዳከማ የነበረች ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ የመሠረት ድንጋይን አስቀምጠዋል፡፡ ታዲያ በዚያን ጊዜ ጎንደሮች የወርቅ ዘር ነበሩ ማለት ነው? ጠይቁ፡፡

ጊዜ የሰጠው ያሸንፋል፤ ጊዜ የጣለው ደግሞ ይሸነፋል፡፡ ከዚህ ውጭ አሸናፊውን በወርቅ ተሸናፊውን በጨርቅ መመሰል ግን በፍፁም ነውር ነው፡፡ ይህን ሁሉ የወረዱ ቃላት መጠቀም የተፈለገበት ምክንያት ኢትዮጵያዊነትን ላለመቀበልና ላለማድነቅ ነው፡፡ "እኛ ብቻ ነን ትልቆቹ፣ እኛ ብቻ ነን ጀግኖቹ" ለማለት ነው፡፡ ያሳፍራል! ከጠ/ሚንስቴሩ ንግግር እንጨምርበት፡-

". . .ዛሬ የሚሣደቡበት አፍ እንጂ የሚናከሱበት ጥርስ የላቸውም፡፡ ጥርሶቻቸውን አውልቀንላቸዋል፡፡ ማነው ያወለቀላቸው? እኛ ነን ያወለቅንላቸው፡፡ እንደ ቀድሟቸው ቢሆን ኖሮ ህውሄን ላይ ሄደው ነበር የሚጨፈጭፉን፡፡ አሁን ግን ጥርሶቻቸውንና ጥፍሮቻቸውን ቀምተናቸዋል፡፡ ያረጀ ዉሻ ጥርሶቹን አጥቶ ቢያላዝን ምናልባት ለዉሻው ይታዘንለት እንደሆነ እንጂ አያሣዝንም፡፡ ዉሻው እንደሆነ አይናከስም!!" *(እንደላይኛው)*.

ወገን እንግዲህ ይህ ንግግር ያንድ "ታላቅ" መሪ ንግግር ነው ብሎ ለመናገር አያሳፍርም? እነማን ይሆኑ ጥርሶቻቸውን ያጡትና ጀግነው ሕወሓት ያወላለቀባቸው? ነፍጠኛ አማራዎች ወይንስ ደርጎችና የደርግ ሠራዊት? ወይንስ በጅምላ የኢትዮጵያ ሕዝብ? ጠይቁ፡፡ ሌላ ማስረጃ ላክል፡-

*". . .ያነዬ ንግግሩ አንድ ነገር አስታወሰኝ፡፡ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ በተመስጦ እያየሁት ነበር፡፡ የግንቦት 20 በዓል በተከበረ ቁጥር የሚታዩ የደርግ ፊልሞች ነበሩ፡፡ ከነዚያ ውስጥ የኢሕአዴግ ሠራዊት ሰሜን ሸዋ የደረሰ ጊዜ መንግሥቱ ኃይለማርያም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን ሰብስቦ ‹ቂጣቸውን፣ በሣንጃ!. . › እያለ ነውረኛ ፉከራ ሲያሠማ የሚያሣይ ፊልም አንዱ ነው፡፡ መለስም <ጃኬታቸውን አሰወልቀን. . .> እያለ ሲፎክር ያ የመንግሥቱ ፉከራ ትውስ ብሎኝ እጄን አነሣሁና ‹ስተያየት?› አልኩኝና ‹ይቅርታ አነጋገርህ መንግሥቱን፣ መንግስቱን መሰልከኝ!› አልኩት፡፡ ቤቱ በድንጋጤ ተናወጠ፡፡ በተለይም ከኔ ጎን ተቀምጣ የነበረችው ገነት ዘውዴ ‹እንዴት ከመንግሥቱ ጋር ታወዳድረዋለህ?› በማለት ሰቅስቅ ብላ አለቀሰች፡፡" (የነጋሶ መንገድ ዳንኤል ተፈራ ገጽ 240)*





መንግሥቱ ኃይለማርያም "ቂጣቸውን በሣንጃ. . ." እየወጋ ያባረራቸው እነ ጀኔራል ከበደ ጋሸን ይመስለኛል፡፡ አቶ መለስ በበኩላቸው "ጃኬታቸውን እያስወለቅን አባረርናቸው. . ." ያሉት እነ አቶ ስየን ሣይሆን አይቀርም፡፡ በነገራችን ላይ ኮሎኔል መንግሥቱም ያቶ መለስን ያህል አይሁኑ እንጂ በተናደዱ ጊዜ የሚወረውሯቸው ቃላት አንገት አስደፊዎች ናቸው፡፡

በ81 ዓ.ም መፈንቅለ መንግሥቱ እንደ ከሸፈ መስቀል አደባባይ የድጋፍ ሰልፍ (የትንፋሽ ማዳመጫ) በተደረገበት ወቅት ኮሎኔሉ እልህ እየተናነ ቃቸው "የኢትዮጵያ ህዝብ ወርቅ ቢያነጥፉለት ፋንድያ ነው ይላል!. . ." በማለት ከጉያው ለመሸጎጥ የሚማፀኑትን ሕዝብ ዘልፈውታል፡፡ ሕዝቡ በበኩሉ "ፋንድያውን እግዚአብሔር ያውቀዋል!" እያለ በያቅጣጫው ተበትኗል፡፡

በመሠረቱ ያቶ መለስን አጉራ ዘለል ንግግሮች አንድ ባንድ እንጻፍ ካልን አንዘልቀውም፡፡ ጥቂት ምሳሌዎችን ብቻ ከጠቀስን በቂዎች ናቸው፡፡ ሌላው ቀርቶ ጥቅምት 9 ቀን 2004 ዓ.ም በተወካዮች ም/ቤት ተገኝተው ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጧቸው መልሶች እጅግ የሚያሳዝኑ ነበሩ፡-

"ሽብርተኞች! ፀረ ሰላም ኃይሎች! የቁራ ጩኸት ጪሂዎች!" ጋዜጠኞችን ደግሞ "የጋዜጠኝነትን ሀ ሁ ያልቆጠሩ! ጋጠዎጦች! ገተርስ! (gutters!)" በማለት እያንቋሸሹ ካንድ "ታላቅ" መሪ በማይጠበቅ አገላለጽ እያበሻቀጡ በም/ቤታቸው ገልፀዋቸዋል፡፡ ገተር ማለትም ቆሻሻ ትርኪ ምርኪ፣ ወድቅዳቂ እንደማለት ነው፡፡

ሕወሓት ከሁለት እንደ ተሠነጠቀ ሰሞንም ይናገሩ የነበረው በስሜታዊነትና በደመ ፍሉነት ነበር፡፡ "የበሰበሰ! የተግማማ! የበከተ!. . ." ድርጅቱን ይመስለኛል፤ መታደስ አለበት ለማለት ሣይሆን አይቀርም፡፡ ብቻ ፀያፍ ቃላትን ነበር ይጠቀሙ የነበሩት፡፡

እንግዲህ እነዚህ ሁሉ እንዲቀጥሉ ነው ሕዝብ ቃለ መሀላ የሚፈፅመው፡፡ ቀጥለን ደግሞ በወሰኑት ውሳኔ ያለመፅናታቸውን እንመለከታለን፡፡

## በወሰኑት ውሳኔ ያለመፅናት

ጠ/ሚንስትር መለስ ጎልተው ከሚታወቁባቸው ባህሪያት መካከል አንዱና ዋናው ሥነ-ምግባር የጎደላቸውን ቃላት ከመወርወር ቀጥሎ

በቃላቸው ወይንም በወሰኑት ውሳኔ መፅናት አለመቻላቸው ነው፡፡ አንድ መሪ ደግሞ “ታላቅ መሪ” ሊባል የሚችለው በወሰነው ውሳኔ መፅናት ሲችል ነው፡፡ አቋሙ የሚዋዥቅና ሁልጊዜ ከቅል ቀዳዳ ሲገባ መውጫ ፍለጋ ላይ ታች የሚረግጥና ትናንት የተናገረውን ሽምጥጥ አድርጎ ሲክድና ሌላ ሰው ሆኖ ሲቀርብ ያሣፍራል፡፡ ምንም ይሁን ምን፣ ጥሩም ይሁን መጥፎ አንድ መሪ የተናገረውን ቃል ማክበር ሲችል ነው፡፡ ከመወሰኑ በፊት ነው ደግሞ ደጋግሞ ማሰብ ያለበት፡፡ “አሥር ጊዜ ለካ አንድ ጊዜ ቁረጥ” የሚባለውም ያለምክንያት አይደለም፡፡ ርግጥ ነው ሐሳበ ግትርም መሆን አግባብ አይደለም፡፡ ይህ ሲባል ግን ከጊዜ ጋር ሙልጭልጭና ተንሸራታች መሆን የለበትም፡፡ ነውር ነው፡፡

አቶ መለስ አምባገነን በመሆናቸው ለሚወስኑት ውሳኔ ሰዎችን ማማከር ቀርቶ ከራሳቸውም ጋር የሚመካከሩ አይመስሉም፡፡ እንደመጣላቸው ይወስናሉ፤ እንደመጣላቸው ደግሞ ይሽራሉ፡፡ ይህንን በተመለከተ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰውየውን የሚፈታተኑና ግምት ውስጥ ያስገቡ ውሳኔዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ሌላው ቀርቶ ሰዎችን ለማጥቃትና ለመጉዳት ሲፈልጉ በ24 ሰዓት ሕግ የሚያስረቅቁ መሪ ናቸው፡፡ ጥቂት ምሳሌዎችን እነሆ፡-

እንደሚታወቀው በ83 ዓ.ም የሽግግር መንግሥቱ በግዮን ሆቴል ሲመሠረት ከየጎሳዎቹ የተውጣጡ ወይንም ጥሪ የተደረገላቸው የጎሳ መሪዎችና የእድር ሰብሳቢዎች ሳይቀሩ እንዲመክሩና እንዲዘክሩ እድሉ ሲሰጣቸው አማራ ግን አገሩን ተዋግቶ እንዳስገነጠለና የባህር በር እንደዘጋ ወይንም እየሸራረፈ ለባእዳን የኮቴ ማረፊያ መሬት እንደሸጠ ተቆጥሮ፣ በዚች አገር ላይ ወሳኝ ሚና እንዳልተጫወተ ታሪክ ይቅር በማይለው ሁኔታ ተገልሎ፣ አንድም ተወካይ ሣይኖረው በሆያ ሆየ ኤርትራን ለማስገንጠል ሁሉም አጨብጭቦ ያቶ መለስን ቡራኬ ተቀብሎ ተበተነ፡፡

በዚህ ጉባዔ ላይ “ታላቁ መሪያችን” ንግግር ባደረጉበት ወቅት “አማራ ለጊዜው ወኪል የለውም፡፡ ወደፊት ተደራጅቶ ወኪሉን እንደሚልክ ተስፋ እናደርጋለን” ሲሉ ምፀታዊ ንግግር አድርገው ነበር፡፡ ብዙም ሣይርቅ በ84 ዓ.ም መጋቢት ወር ላይ መላ አማራ ሕዝብ ድርጅት (መአሕድ) ሲመሠረት ግን አቶ መለስ ወዲያውኑ የመአሕድን አባላት ማሣደድ ጀመሩ፡፡

ሕወሓት በዚህም ሣይገታ ልክ ለአነግ ከጎኑ ኦሕዴድን እንዳቋቋመለት ሁሉ ለመአሕድም አዲስ ድርጅት እንኳን እስቲፈበርክ ጊዜ አልሰጥ ብሎት “ሁልህም ወደየ ወገንህ ቢባል ርኮት ወደ ቁርበት፤ አክንባሎ ወደ በረት





ተጠጉ” እንደሚባለው የኢሕዴንን አካላት ወደየ ጎሳቸው ከበተነ በኋላ ባህርዳር ላይ ብሔር አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) ተቋቋመ ተባለ፡፡ መሪውም በኋላ “ስኳር ሲልሱ ተያዙ” የተባሉት አቶ ታምራት ላይኔ ተሾሙለት፡፡

ተቃዋሚዎችን በተመለከተ ሲጠየቁ “ግማሽ መንገድ ድረስ ሔደንም ቢሆን እንቀበላቸዋለን” ብለው ነበር፡፡ በ97 ዓ.ም ካጠገባቸው ድረስ ሲሄዱላቸው ያጋዚን ጦር አዘው አስጨፈጨፏቸው! አመራሮቹንም ለቃቅመው ወደ እስር ቤት አጎሯቸው፡፡ ይህ ትልቅ የቃል እብለትና በቃል ያለመፅናትን ነው የሚያመለክተን፡፡

የጠ/ሚንስትር መለስን የቃል እብለትና በወሰኑት ውሳኔ ያለመፅናትን ሌላም ምሳሌ መጨመር ይቻላል፡፡ ይኸውም “የኦሮሚያ ዋና ከተማ አዳማ ነው” ተብሎ ተወሰነ፡፡ ሐውልትም፣ ቤተመንግሥትም፣ የተለያዩ ግዙፍ አዳራሾችም መጠነ ሠፊ ገንዘብ ፈሶ ተገነቡ፡፡ ይህንን ውሳኔ የኦሮሞ ወጣቶችና ምሁራን “የኦሮሚያ ዋና ከተማ ከዚሁ አዲስ አበባ (ፊንፊኔ) ነው” ሲሉ ተሟገቱ፡፡ በዚህ ምክንያትም ብዙዎች ተለጣፊ ስም ወይንም በዚያው በኦነግ እየተሳበበ የእስር ሰለባ ሆኑ፡፡ ከ300 የማያንሱ የኦሮሞ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው ታገዱ፡፡ ወይንም ለጭራሹ ተባረሩ፡፡ የተወገዙ፣ ከሥራቸው የታገዱ፣ በማስጠንቀቂያ የታለፉ፣ ከደረጃቸው ዝቅ ያሉ ቁጥራቸው በጣም ብዙዎች ነበሩ፡፡

የኦሮሚያ ዋና ከተማ አዳማ ይሁን ከተባለና ለኦሮሞ ሕዝብ ሁለንተናዊ እድገት ጠቃሚ ነው ከተባለ በውሳኔው መፅናት ተገቢ ነበር፡፡ ወይንም ከመነሻው የብሔሩን አዛውንቶች፣ ምሁራን፣ ወጣቶችን ማማከርና ማሣመን አግባብ ነበር፡፡ ይህ ባለመሆኑ 97 ዓ.ም የሕዝብ ንቅናቄ አገሪቱን ሲንጣት አቶ መለስ ከመቅፅበት እንደ ጋለ መደብ እጥፍ ብለው የተናገሩትንና የወሰኑትንም ከምንም ሳይቆጥሩ፡- “የኦሮሚያ ከተማ ወደ አዲስ አበባ ተመልሷል” በማለት አስታወቁ፡፡ ይህም ካንድ መሪ የሚጠበቅ አልነበረም፡፡

አቶ መለስ የኦሮሚያ ዋና ከተማ ካዳማ ወደ አዲስ አበባ ተመልሷል ሲሉ ስልቱና የከፋት ሥንቁ የኦሮሞን ሕዝብ ከቅንጅት ጋር ያስተናነቁ መስሏቸው ነበር፡፡ በወቅቱ ግን ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ “ደስታውን አንችለውም” ሲል እንጥላቸውን ዱብ አደረገው፡፡ የጠ/ሚንስትሩን አቋም ተለዋዋጭነትና በወሰኑት ውሳኔ የማይፀኑ መሆናቸውን የበረሃ ጓዳቸው የነበሩት አቶ ስየ አብርሃ እንዲህ ይሏቸዋል፡-

*"አቶ መለስ ሲከራከር ለመርህና ለእውነት ብዙም አይጨነቅም:: በወቅቱ ለያዘው ክርክር ትንሽም ቢሆን ይረዳኛል ብሎ ካመነ መርህንና እውነትን ገልብጦ የሚያነብ ነው:: . . ." (ነፃነትና ዳኝነት በኢትዮጵያ አቶ ስዬ አብረሃ ገጽ 20-21)* እንግዲህ "ታላቁ መሪያችን" እንዲህ ያለ አቋም ያላቸው መሪ ነበሩ::





# "የታላቁ መሪያችን ራእይ!"

በመጀመሪያ ደረጃ ራእይ ምንድን ነው? የግዕዙ ቃል እንዲህ ይለዋል:: "አትኩሮ መመልከት፣ ልብ ብሎ ማየት፣ በሕልምና በውን መሀከል በተመሥጦ አንድን ረቂቅ ነገር ለይቶ ማየት" ይላል:: የእንግሊዘኛው (OXFORD English Dictionary) በበኩሉ *"some thing seen in the imagination or in dream . . . wisdom in planning . . ." ይለዋል::*

እንግዲህ ስለጽንሰ ሐሳቡ ይህን ያህል ካልን ወደ መሠረታዊ ጉዳዩ ስንገባ እያንዳንዱ ሰው ይነስም ይብዛ እንዳቅሙ ያጭርና የረጅም ጊዜ እቅድ ይኖረዋል:: ይህንን እቅድም ለማሣካት ለጊዜው ያልጨበጠው ነገር ግን ነገ አሣካዋለሁ የሚለው መልካም የሆነ ራእይ ይኖረዋል:: ይህ ራእይም የተቀደሰና ከመንፈሣዊ ሕይወት ጋር የተቆራኘ በመሆኑ "ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ራእይ" እየተባለ እንደሚጠቀሰው ዓይነትም በተስፋ የሚጠበቅ ይሆናል::

ራእይ ባገር መሪ ደረጃ ሲሆን ደግሞ ሠፊና ጥልቀት ያለው ነው:: የሚሉዮኖችን ራእይ አቅፎ ወይንም ጠቅልሎ ስለሚይዝ ያገር ራእይ ነው ተብሎ ይታመናል:: መልካምና ቀና ራእይ ያላቸው መሪዎችም አገራቸውን ወደፊት ሊመጣና ሊደርስ ከሚችል ጥፋት አስቀድመው በመገንዘብ ሊታደጉ ይችላሉ:: መጥፎና እኩይ ራእይ ያላቸው መሪዎች ከሆኑ ደግሞ እነሱ ራሳቸው የጥፋቱና የውድመቱ ምንጮች ወይንም መነሻዎች ይሆናሉ:: ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑን ሂትለርና የኢራቁ መሪ ሣዳም ሆሴን ናቸው::

የሂትለር ራእይ በዘር ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የሌሎችን መብት እንዳለ ደፍጥጦ ጀርመንን የዓለም ኃያል አገር ማድረግ ነበር:: ሣዳትም ራሳቸውን የዐረቡ ዓለም መሪ በማድረግ ኢራቅን ማግነን ነበር:: በዚህ ምክንያትም ሁለቱም መሪዎች ብቻቸውን ሣይሆን አገራቸውንም ለውጭ ወራሪ ኃይሎች አጋልጠው ጠፍተዋል::

ስለራእይ ስናነሳ ካለፉት ነገሥታት መሀከል አፄ ቴዎድሮስ በግንባር ቀደም ይታወሱናል:: አፄ ቴዎድሮስ ሦስት ታላላቅ ራእዮች ነበሯቸው:: እነሱም:-

የመጀመሪያው ራእያቸው በመሣፍንት ተከፋፍላ እየታመሠች ያለችን አገራቸውን አንድ አድርገው ባንድ የማዕከላዊ መንግሥት ጥላ ሥር

ማጠቃለልና ገናን አገር መመሥረት የሚል ነበር፡፡ ቴዎድሮስ ይህንን ራእያቸው ሲያደርጉ ከባዶ ተነሥተው አልነበረም፡፡ ያዘመን ቅኝ ገዥዎች አፍሪካንና ሌላውን ዓለም እንደ ቅርጫ ሥጋ እየተቀራመቱ የነበሩበት ወቅት ስለነበር ኢትዮጵያንም አንድ ቀን ሊወሯት ይችላሉ የሚል ሥጋት ነበራቸው፡፡ በመሆኑም አንድ ሆኖ መመከት እንደሚቻል አመኑ፡፡

አፄ ቴዎድሮስ ሁለተኛው ራእያቸው ከውጭ የጦር መሣሪያ ገዝተው እነዚያን ቅኝ ገዥዎች መመከት እንደማይችሉ ግንዛቤ ነበራቸው፡፡ ከውጭ ገዝተው ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ቢያስቡ እንኳን ፈተናው ቀላል እንደማይሆንም ተረድተዋል፡፡ አንደኛ ወደቦቿ እንዳሁኑ በባዕዳን እጅ ተይዘውባት ነበር፡፡ ሁለተኛ አገራቸው በዐረቦች ዙሪያውን የተከበበች በመሆኗ ወደ መሀል አገር የጦር መሣሪያ ገዝቶ የማስገባቱ ነገር ተስፋ አሥቆራጭ እንደሚሆን አልተሠወረባቸውም፡፡

ሌላው ችግር የጦር መሣሪያውን አምራቾቹና ሻጮቹ እነዚሁ ቅኝ ገዥዎች መሆናቸው ነበር፡፡ እናም መገደያቸውን ለገዳዮቻቸው ያውም ቅኝ ለማድረግ እጩ ላደረጓት አገር በተፈለገ ጊዜና መጠን ሊሸጡላቸው እንደማይፈልጉ በማመናቸው ባገር ውስጥ፣ ባገር አፈር አስቀልጠው የጦር መሣሪያ ኢንዱስትሪ ለማቋቋም ቆርጠው ተነሱ፡፡

ያሰቡትን ከግብ ሣያደርሱ የአእምሮ ረፍት የሌላቸው ቴዎድሮስ የሃይማኖት መልዕክተኞች ነን ይሉ የነበሩትን ምእራባውያን ሚሽነሪዎችን በማባበልም፣ በማስፈራራትም፣ በማስገደድም ጋፋት ላይ የጦር መሣሪያ ማምረቻ ኢንዱስትሪ አቋቋሙ፡፡ ይህንንም ሲያደርጉ አበሻዎችን እንዲለማመዱ አብረው እንዲሠሩ አዘዙ፡፡ ይህ ራእያቸውም ተሣክቶላቸው ሰባቶፖልንና አነስተኛ አዳፍኔዎችን አሠሩ፡፡

ሰባስቶፖል ከጄኔራል ናፔር ጋር መቅደላ ላይ በመጨረሻዋ ሰዓት ሲዋጉ አንድ ጊዜ እንደተተኮሰበት መፈንዳቱ ይነገራል፡፡ የሚያሣዝነው ግን ውጥን ራእያቸው ወራሽ ወይንም አሥቀጣይ አጥቶ መክኖ ቀርቷል፡፡

ያፄ ቴዎድሮስ ሦስተኛው ራእያቸው ኢየሩሳሌምን ከቱርኮች ነፃ ማውጣት የሚል ነበር፡፡ ቴዎድሮስ አንዳንድ ጊዜ ሞቅ ባላቸው ጊዜ፡- "የኢትዮጵያ ባል የኢየሩሳሌም እጮኛ!" ይሉ ነበር ይባላል፡፡ አድናቂዎቻቸውም በበኩላቸው፡-

"ታጠቅ ብሎ ፈረስ ካሣ ብሎ ስም አርብ አርብ ይሸበራል ኢየሩሳሌም!" እያሉ ያነቃቋቸው ነበር፡፡ "አርብ አርብ ኢየሩሳሌም ይሸበራል" ሲሉም





ጌታችንና መድኅኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለው ዓርብ ቀን ስለነበር ያንን ለመዘከር እንደነበር ይታወቃል፡፡

## ያቶ መለስ እውነተኛ ራእይ

አቶ መለስ እውነት አሁን አድናቂዎቻቸው እንደሚጮሁላቸው ያሉ ለኢትዮጵያ ራዕይ የነበራቸው መሪ ነበሩ? የሚል ጥያቄ ብንጠይቅ መልሱ ግርምትን የሚፈጥር ይሆናል፡፡ ለማንኛውም ራሳቸው የጻፉትን መጽሐፍ በመጀመሪያ በጥንቃቄ አንብቦ ትክክለኛና ሀቀኛ ፍርድ መሥጠት ነው፡፡ እነሆ፡--

*«---አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በኤርትራ ጥያቄ ላይ ትክክለኛ አቋሙን እንዲወስድ ከሚያምታቱትና እንቅፋት ከሚሆኑበት ነገሮች መሀከል አንደኛው ጥያቄውን አስመልክቶ ያለው እውቀት ዝቅተኛ መሆኑ ነው፡፡ ይህም የኢትዮጵያ የገዥ መደቦች ሆን ብለው የሚያስፋፉት የውሸት ታሪክና አጉል ፕሮፓጋንዳ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ የኤርትራን ህዝብ ጥያቄ ትክክለኛነት በሚገባ እንዳያነሳና እንዳይገነዘብ አድርጎታል፡፡ ....ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል ነች፡፡ ይህቺን ከቀድሞ ጀምሮ የኢትዮጵያ አካል ሆና የቆየችን ክፍለ ሀገራችንን ኢምፔሪሊያሊስቶችና የዓረብ ሀገሮች ገንጥለው ሊወስዷት ነው፡፡ የነዚህ ኢምፔሪያሊስቶች ቅጥረኞች የሆኑ ጥቂት ኤርትራውያን ወንበዴዎችም ተሰብስበው ይወጉናል፡፡» የሚለው አጉል ፕሮፓጋንዳ በኢትዮጵያ ሕዝብ ጭንቅላት ውስጥ የፈጠረው ተጽዕኖ ዝቅተኛ ግምት የሚሰጠው አይደለም፡፡*

*"ይህንና ይህን የመሣሰለውን መሠረተቢስ የውሸት ፕሮፓጋንዳና የታሪክ ትንታኔ በመፃረር (በመቃወም) ተጨባጩንና ሐቁን በማውጣት የኤርትራ ድርጅቶችና የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኃይሎች ጭምር (ሕወሓትን ለማለት ነው) ያደረጉት ጥረትና ትግል የማይናቅ ቢሆንም መደረግ ከነበረው ጋር ሲነፃፀር ግን መጠኑ በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ሆኖም ይህን በመሣሰለው የገዥው መደብ የውሸት ፕሮፓጋንዳ ተጋርዶ በኤርትራ ሕዝብ ጥያቄ ላይ ትክክለኛና የጠራ አቋም ከመውሰድና ድጋፉን ከመሥጠት የተቆጠበበት ኢትዮጵያዊ ቁጥር ዛሬም ቢሆን ብዛት ያለው ሆኖ ይገኛል፡፡*

*"ከፍ ሲል ከተጠቀሰው የውሸት ፕሮፓጋንዳ እምብዛም የማይለይና ብዛት ላላቸው ኢትዮጵያውያን በኤርትራ ጥያቄ ላይ አቋማቸውን*

*እንዳይወስዱ እንቅፋት ሆኖ የሚገኘው ሌላው ምክንያት ቢኖር በአንድነት ላይ ያላቸው አመለካከት የተሳሳተ መሆኑ ነው።*

*"የኢትዮጵያ ገዥ መደቦችና አነፍናፊዎቻቸው የሰፊውን ሕዝብ ሐቀኛና ትክክለኛ ያንድነት ፍላጎትና ስሜትን መሠረት አድርገው ኤርትራ ከተገነጠለች ወደብ አጥተን ጉረሮችን እንደዘለን (እንታነቃለን)፣ የኤርትራ መሬት ተገንጥሎ መውሠዱ ነው፤ የኢትዮጵያ አንድነት መናጋቱ ነው፤ ስለዚህ እስከመጨረሻው የደም ጠብታ ተዋግተን ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል እንደሆነች ለዘለዓለም ማቆየት አለብን የሚል አጉል ፕሮፓጋንዳና ከፍተኛ ቅስቀሳ በማካሄድ ሰፊው ሕዝብ ባንድነት ጥያቄ ላይ የተሳሳተ አመለካከት እንዲወስድ አድርገውታል።"*

*(የኤርትራ ሕዝብ ትግል ከየት ወደየት? ደራሲ ተጋዳላይ መለስ ዜናዊ ገጽ ከ29-31)*



*አቶ መለስ የምትፈረካከሰዋን ኢትዮጵያ ዓይኖቻቸውን ጨፍነው በሕሊናቸው ሲመለከቱ*





እንግዲህ ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው አቶ መለስ ገና ከማለዳው በለጋ እድሚያቸው የዩኒቨርስቲ ትምህርታቸውን አቋርጠው በረሃ የገቡት የኢትዮጵያን ሕዝብን ከጭቆና አገዛዝ ለማላቀቅ ሣይሆን የናት አገራቸውን ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመገንጠልና ለማስገንጠል ነበር። ይህ እውነት ነው። አቶ መለስ ኤርትራን ካስገነጠሉም በኋላ እስከ እለተ ሞታቸው ድረስ ለዚያች ላስገነጠሏት የእናት አገር እጅግ አድርገው ታትረዋል። ሀቁና እውነተኛ ራእያቸውም ኤርትራን ከኢትዮጵያ አስገንጥለው ኢትዮጵያን ወደብ አልባ አድርጎ ወደ ድህነት አዘቅት ማዳፋት ስለመሆኑ ወደፊት ደረጃ በደረጃ የምናየው ይሆናል። በነገራችን ላይ የቋንቋ አጠቃቀማቸውም አብሯቸው ያደገና የጥላቻ መግለጫቸው መሆኑን ከዚህ ላይም ሥነ ምግባር በጎደለው ሁኔታ ሲጠቀሙበት እናስተውላለን። "አነፍናፊዎቻቸው! . . ." እያሉ ለዉሻ በሚገለፅበት ቋንቋ መግለፃቸው ያስቅቃል። በተረፈ ግን አቶ መለስ ገና ከጧቱ ወደ በረሃ ሲገቡ ይዘውት የሄዱት ራእይ ኤርትራን ማስገንጠል ለመሆኑ ብዥታ በጭራሽ አይፈጥርብንም። በዚህ ጥራዙ ባበጠ መጽሐፍ ውስጥም አንዲት መሥመር እንኳን ስለኢትዮጵያ በጎ ነገር አልፃፉም። ባንፃሩ ሰፍሮ የምናገኘው ነገሥታቱን እጅግ በወረዱና በቆሸሹ ቃላት ታሪካቸውን ማንቋሸሽና ማጥላላት፣ አንድነትንና ኢትዮጵያዊነትን የሚፈታተኑና ጨርሰው የሚንዱ ሐሳቦችን ነው የምናገኘው። ይህ ሁሉ ጥረታቸው ኤርትራን ለማስገንጠልና የግንጠላውን ድራማ ደግሞ ሕጋዊና እውነት ለማስመሰል ነው። እንዲህ ሲሉም ሊያሣምኑን ይሞክራሉ፦

*"የኤርትራ ችግር የቅኝ ግዛት ችግር ነው። ቅኝ ገዥዋም ኢትዮጵያ ነች" ይሉናል። (እንደ ላይኛው)*

ሌላ ማስረጃ እነሆ፦ *"ሕወሓት ደርግን ለመጣል ከሻዕቢያ ጋር መተባበሩ ይታወቃል። ከሻዕቢያ ጋር ተባብራችሁም የኢትዮጵያን ሠራዊት አፍርሳችኋል። አሁን ሌሎች ከሻዕቢያ ጋር ተባብረው እናንተን ቢገጥሟችሁ ለምን ይከፋችኋል?"* የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ሲመልሱ፦

*"ከሻዕቢያ ጋር አብረን የደርግን ሥርዓት ለመጣል የታገልንበት ሁኔታ እንዳለ የማይካድ ነው። የማይካድ ብቻ ሣይሆን የምንኮራበት ታሪካችንም ነው። . . ."* ይሉናል። አሁንም መቆርቆራቸውን ሲነግሩን፦

*"የኤርትራ ሕዝብማ ነፃነት ካገኘ በኋላ ባርነት በላዩ ላይ ተጭኖበታል። አሁን በገፍ ነው ወደ ኢትዮጵያና ወደ ሱዳን እየሸሸ ያለው" (መለስ ከልጅነት እስከ እውቀት ገጽ 73-76 በትኩአ ባሀታ)*

የሚገርም ነው፤ ተዋግቶ አስገንጥሎ ባርነት በላዩ ላይ ማስጫን? ኤርትራውያን ቢሆኑስ ጠልተዋት፣ ንቀዋት ከተገነጠሉ በኋላ እንዴት ተመልሰው ቅኝ ትገዛቸው ወደ ነበረችው አገር ይመጣሉ? ማንን ተማምነው ነው?

በመሠረቱ አቶ መለስ ለኤርትራ የነበራቸውን ራእይ ከዚህ በላቀ መልኩም መመልከት ይቻላል:: ኤርትራ በድፍረት ባድሜን በወረረችን ጊዜ ሳይቆረጡ የቆረጡ መስለው በተወካዮች ም/ቤት ፊታቸውን እልህ የተናነቃቸው በሚመስል ሁኔታ አንዲት ወረቀት እያጠፉ እየዘረጉ እንደገና እየቀደዱ "ይች ወረቅት በመጀመሪያ ወደነበረችበት መመለስ አለባት" እያሉ ያዙኝ ልቀቁኝ ሲሉ ጨርሶ! ቀይ ባሕር የሚያቆማቸው አይመስሉም ነበር:: ይህንን ሁሉ የደንፋታ ንግግር በተወካዮች ም/ቤት ፊት ያደረጉት ወደ ጦርነት ከመገባቱ በፊት ጉዳዩ በግልግል (በሽምግልና ይታይ) የሚል ሐሳብ ቀርበላቸው ስለነበር ነው:: ታዲያማ ያን ሰሞን በሳቸው የደንፋታ ንግግር የተሞላች አንዲት ወይዘሮ ባንድ የባድሜን በግፍ መወረር በተደረገ የተቃውሞ ሰልፍ:-

> መሌ ምን አለ
> አገሬን ለሰው አልሰጥም አለ!!"

ሴትየዋም፣ ተቀባዩ ሰልፈኛም መሌ ኤርትራን ተዋግተው ያስገነጠሉና የባሕር በር ያሳጡ መሆናቸውን የሚያውቁ አይመስሉም:: የሚገርም ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁልጊዜ ባፈጮሌዎች የሚነዳ መሆኑ ግን ያሣዝናል:: ከታሪክ ወይንም ካለፉ ድርጊቶች አለመማሩ ደግሞ የበለጠ ያናድዳል::

ኢጣሊያ በ1928 ዓ.ም በግፍ ወራን ባሸናፊነት አገራችን በተቆጣጠረችበት ወቅት እንዲህ እንዳሁኑ አንዳንድ ለሆዳቸው ቀድመው ያጎበደዱ ባንዳዎች እንደ አሸን ፈልተው ነበር:: እናም በሰላሙ ጊዜ ከጌቶቻቸው ፊት ተኮፍሰው በመቀመጥ ጠጅ በብርሌ ያንቆረቁሩ፣ ጮማ እንደ ጎመን ይቆርጡ የነበሩ ሁሉ ባንድ ጊዜ ግልብጥ ብለው አገራቸውንም ጭምር በመክዳት ለሞሶለኒ ጭፍሮች የጌታ በማደር ሞሶለኒንና አገዛዙን ማወደስ ጀመሩ:: ለምሳሌ:-

የበጌምድሩ (ያሁኑ ደቡብ ጎንደር) ገዥ የራስ ጉግሣ ወሌ አባ ደልድል (ደልድል የፈረሣቸው ስም ነው) ራስ ጉግሣ የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ባለቤት የነበሩት ናቸው:: የኒህ ስመ ጥር ማሲንቆኛ (ቅምጥል) በዚያን ዘመን አጠራር "አዝማሪ" ቀኛዝማች ምሲጋናው፤ ልብ እንበል፤





ቀኛዝማች ምሲጋናው የተከበረና ባለማዕረግ (ባለቀሚስ) ነበር:: ተራ አዝማሪ አልነበረም:: እናም የሚከተለውን ማንጎራጎሩ ይነገርለታል:-

> *"ገብሬ ገብሬ ነጭ እንጨቴ ወጣ*
> *ከእንግሊዝ ወዲያ በገንዘቡ አዳሪ ሞሶለኒ መጣ!*
> *በሰማይ በራሪ በምድር ተሽከርካሪ*
> *ሞሶለኒ መጣ በገንዘቡ አዳሪ!"* በማለት አሞካሽቶት ነበር::

ሊቀ መኳስ ቀኛዝማች ምሲጋናው ሞሶለኒን እንዳሞገሰው በገንዘቡ አዳሪም፣ ነፃ አውጭም አልነበረም:: ኢትዮጵያን ለመውረር የመጣው ገንዘብ ለመዝረፍ፣ ጥሬ ሀብቷን ለመቀራመት ነበር:: አዳሩ ግን አርበኞች እያየሉ ሲመጡ እነሱን ብርታትና ሞራል የሚሰጧቸው አዝማሪዎች ናቸው በተባለ ጊዜ ጀኔራል ናዚ (የሰሜን ኢትዮጵያ ገዥ የነበረው ነው) "አዝማሪዎችን ለቅማችሁ አምጡልኝ" ብሎ ቀጭን ትእዛዝ ባስተላለፈ ጊዜ ቀኛዝማች ምሲጋናው 15 መሰል ጓደኞቹን ይዞ፣ ማሲንቆውንና አጭር ባለሣንጃ መስኬቶውን አንግቦ በረሃ በመግባት ካርበኞች ጋር በመቀላቀል በሰላም ጊዜ አርበኞችን በማሲንቆው እያጫወተ በፍልሚያ ወቅት ደግሞ በመስኬቶው ብልቁባሾችንና ባንዳዎችን ማጫወቱ ይተረክለታል::

በመሠረቱ "መሌ ምን አለ አገሬን ለሰው አልሠጥም አለ!" የሚለው ሙገሳ ቀኛዝማች ምሲጋናው ለሞሶለኒ "በገንዘቡ አዳሪ!" ብሎ ካወደሰው ጋር የሚመሣሰል ነው:: ስለ እውነት እንመስክር ካልን ፋሽሽትነታቸው እንደ ተጠበቀ ሆኖ "መንጌ ምናለ አገሬን ለሰው አልሠጥም አለ!" ቢባል ሀቅ ነበር:: ባጭር ጊዜ ውስጥ 300ሺ ሚሊሺያ ሠራዊት አሠልጥነው ዜብራ የመሠለ መለዮ አልብሠው የሶማሊያን ወራሪ ሠራዊት ረግጢው አስወጥተዋል:: ኤርትራን ላለማስገንጠልም ከገንጣዮችና ካስገንጣዮች ጋር ተናንቀዋል:: አቶ መለስ ግን መባል የነበረባቸው "መሌ ምን አለ? ኤርትራን ሳላስገነጥል አልተኛም አለ!" ቢባል ነበር እውነት የሚሆነው:: የዚህን እውነተኛነት ቀጥለን ደግሞ እንመልከት::

ኤርትራ ባድሜን በድፍረት ወራ ከምሽግ ማጠናከር ጀምራ አይደር ት/ቤትን በጦር ጀት በመደብደብ እጅግ ዘግናኝና ትውልድ ሊረሳው የማይችል አረመኒያዊ አሣፋሪ ድርጊት በእንቦቀቅላዎች ላይ ፈፅማለች:: በዚህ ወቅት ለመከላከልም ሆነ መልሶ ለማጥቃት የጦር ጀቶች ከራሺያ ይገዙ ወይንም እንግዛ ሲባሉ አቶ መለስ ኧረ እንዴት ተደርጎ በማለት ጀቶቹ እንዳይገዙ አጥብቀው ተሟገቱ::

"ወዳጆቻችን አሜሪካኖች ይከፋቸዋል፤ ማዕቀብ ይጥሉብናል ወዘተ . . ." በማለት በቂ ያልሆኑ ምክንያቶችን እየደረደሩ የጦር ጀቶቹ እንዳይገዙ ተከራከሩ ::

ያቀረቧቸው ምክንያቶች በቂና አጥጋቢ ባለመሆናቸው ሌላ አሳማኝ ምክንያት እንዲያቀርቡ ሲጠየቁ የሚከተለውን አቀረቡ፡-

"አፄ ቴዎድሮስ የወቅቱ ልዕለ ኃያል ከነበረችው የእንግሊዝ መንግሥት ጋር መጠላታቸው ስህተት ነበር። ይህ ስህተታቸው ደግሞ ሕይወታቸውን ለማጣት ምክንያት ሆኗል። አፄ ምኒልክ ደግሞ ካድዋ ድል በኋላ ኤርትራን ለኢጣሊያ የሚለቅ ውል በመፈረም የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት አሣልፈው ሰጥተዋል. . ." በማለት የተናገሩትን አቶ ስዩ አብርሃ *"ነፃነትና ዳኝነት በኢትዮጵያ"* በተባለው መጽሐፋቸው በገጽ 20-21 ገልፀውታል።

*". . . አፄ ምኒልክ የውጫሌን ውል አልቀበልም ብለው ዓድዋ ላይ ያስመዘገቡትን የነፃነት ድል አቶ መለስ ገልብጦ አቀረበልን። አፄ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ የነበራቸውን ራእይ በዚህ ሰበብ ከፈረንጅ ጋር የገቡትን አተካራ መቅደላ ላይ መሸነፋቸውን ሲገነዘቡ የኢትዮጵያ መሪ በፈረንጅ ተማረከ የሚል አሣፋሪ ታሪክ ላለመተው በገዛ ሽጉጣቸው ሕይወታቸውን ማጥፋታቸውን በኢትዮጵያ ሥነ-ልቦና የተወውን አይበገሬነት ትቢያ ላይ ጥሎ ባጥፍቶ ጠፊነት ፈረጃቸው. . ."* ሲሉ በተጠቀሰው መጽሐፍ በተመሣሣይ ገጽ ገልፀውታል።

እንግዲህ "ታላቁ መሪያችን" ለኤርትራ የነበራቸው እውነተኛ ስሜትና ራእይ የተጠቀሰው ነበር። አገራችንን ከተቃጣብን ወረራ ለመከላከል ተዋጊ የጦር ጀቶች እንግዛ ተብለው ሲጠየቁ ዘመን ተሻግረው አፄ ቴዎድሮስንና አፄ ምኒልክን በመወንጀልና አግባብነት በሌለው ጉዳይ በመሡንቀር የጦር ጀቶቹ እንዳይገዙ ተከራከሩ። ይህንን ሀቅስ በምን ማስተባበል ይቻል ይሆን? ይህ ሁሉ ዙሪያ ጥምጥምና እስጥአገባ የጦር ጀቶቹ ተገዝተው ኤርትራ እንዳትነካ ለማድረግ ነበር። ከተነካች ደግሞ ያፄ ቴዎድሮስና ያፄ ምኒልክ እጣ ይጠብቀናል ለማለት ነው።

በዚህም አሉ በዚያ በድምፅ ተሸንፉና ጀቶቹ ተገዙ። ኤርትራም ቀመሰች፤ አቅሟንም አወቀች፤ ይሁን እንጂ አሁንም "ታላቁ መሪያችን" አልተኙም ነበርና ያዛዥነት ሥልጣናቸውን ተጠቅመው ጦሩ ይዞታውን ለቆ እንዲመለስ ትእዛዝ ሠጡ፤ ጦሩም እንጂቱ እያረረ ተመለሰ። "የታላቁ መሪያችን" ፕሮፓጋንዲስቶች ይህንንስ በምንና በነማን ያሳብቡት ይሆን? አሁንም





እንጠይቅ። "የታላቅነትና የጀግንነት" መስፈርቱ ምንድን ነው? አጥብቃችሁ ጠይቁ።

እንግዲህ "የታላቁ መሪያችን" እውነተኛ ራእይ ለእናት አገር እንጂ ላባት አገር እንዳልነበር እስካሁን በትንሹ የጠቃቀስኳቸው ከበቂ በላይ ማረጋገጫዎች ናቸው። ለኢትዮጵያ ራእይ ነበራቸው ከተባለም የብተና ራእይ እንደነበር ጣታቸውን የሚጠቡ ህፃናት ጠንቅቀው ያውቁታል። ያልተከሰተላቸው በጥቅም ናላቸው የዞረና ፍርፋሪ የሚለቃቅሙት ብቻ ናቸው።

## "ዓባይን የደፈረ ጀግና!"

ዓባይ ዛሬ እንደ አዲስ ነገር ወይንም እንደ ብሔር ብሔረሰቦች ከ83 ዓ.ም ግንቦት 20 ቀን ወዲህ ተፈልጎ እንደተገኘ ወይንም እንደፈለቀ ተቆጥሮ ተራ ውደሳ በፕሮፓጋንዳ እንደሚኽጎደጎድለት ያለ ወንዝ አይደለም። ዓባይ የወንዞች ሁሉ ንጉሥ፣ የኢትዮጵያ መልከዓምድር ሲፈጠር አብሮ የተፈጠረ ታላቅ ወንዝ ነው። በመሠረቱ ዓባይን ለማወደስና ስለዓባይ ለመተረክ ወይንም በዓባይ ለመኩራት በቅድሚያ የመቶ ዓመትን ታሪክ ከአእምሮ ውስጥ ፍቆ አውጥቶ በኢትዮጵያዊነት ማመንን ይጠይቃል። አለበለዚያ የብልጦች ኩሸት ከመሆን አያልፍም።

ዓባይ ለግብፃውያን ደግሞ የተለየ ትርጉም አለው። ሕይወታቸው ነው። ለብዙ ሺ ዓመታትም እንደ ዓምላካቸው ይቆጥሩት ነበር። ከኢትዮጵያ ይዞት በሚሄደው ጥቁር ቦረቦር አፈር ምክንያት ነቢዩ ሙሐመድ ከሜካ ወደ መዲና እስከ ተሰደዱበት ጊዜ ድረስ የቀናቸው መቁጠሪያም ነበር። በፈርዖኖች ጊዜም እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ወይንም የስኮቲሹ ተወላጅ ጀምስ ብሩስ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የመነሻ ምንጩን እስካረጋገጠበት ድረስ በግብፃውያን ዘንዳ የዓባይ መነሻ ምንጭ ከጨረቃ ተራሮች ሥር ነው ብለው ያምኑ ነበር። ለዚህም ነበር "ያምላክ ስጦታ" ብለው ያምኑ የነበረው።

ዓባይ ለግብፃውያን መዝናኛቸውም ነው። ከዚያ በረሃ ከዓባይ እየተጨለፈ የሚነፍሰው ርጥበታማ አዘል አየር ከምግብ የበለጠ ሕይወት ይሰጣቸዋል። የፈርዖን ልዕልታት መሸት ሲል ከፍቅረኞቻቸው ጋር ወይንም ደንገጦሮቻቸውን አስከትለው በዓባይ ወንዝ ዳርለዳር ይንሸራሸራሉ፤

ይዝናናሉ፤ ድምፁን ሣያሠማ እየተጉለመለመና በነፋስ ግፊት ሽቅብ ሽቅብ እየጋለበ፣ እየጋሸበ ሲነጥር ትንግርትን ይፈጥርባቸዋል፤ ይመስጣቸዋል፤ ጨረቃ ካለች በትዝታ ወይንም በሐሳብ ልጓም ተስበው ወይንም ጠልቀው ወደ ሰማይ በማንጋጠጥ የመነሻ ምንጩን ለማየት የጨረቃ ተራሮች ብለው በሕሊናቸው የሣሏቸውን ይማትራሉ፡፡ በምሽት የከዋክብቶች፣ የጨረቃዋ ብርሃን ከውሃው እየነጠረ የሚፈጠረው ሕብረ ቀለም ሲንፀባረቅ የወርቅና የእንቁ ፍንጥቅጣቂ ወይንም ፍንጣሪ ጭብር ብርታ ያማልላቸዋል፡፡ ለዚህም ነበር የፈርዖን ልዕልት ደንገጦሮቿን አስከትላ ስትንሸራሸር ህፃኑ ሙሴን በቅርጫት ተጥሎ ሲንሳፈፍ ያገኘችው፡፡ በነገራችን ላይ ነፃ አውጭው ሙሴ ዲዳ ነበር፡፡

ወደ አገራችን ስንመለስ ደግሞ ዓባይ ለኢትዮጵያውያን ልዩ ክብርና ሞገስ አለው፡፡ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ከተፈጠረች ጀምሮ ዛሬም ድረስ እጅግ የበዙ ውዳሴዎችና ሙገሳዎች ዘንበውለታል፤ እየዘነቡለትም ነው፡፡ ተቅራርቶለታል፣ ተፎክሮለታል፣ ተዘፍኖለታል፣ ተለቅሶለታል፣ ተመልኮበታል፣ ተደግሶለታል፣ ዛሬም ይህ ክብሩ አልቀነሰበትም፡፡

*"ዓባይ ጉደል ብለው አለኝ በታሀሣሥ*
*የማን ልብ ይችላል እስከዚያው ድረስ!*
*አንቾ ዓባይ ማዶ*
*እኔ ወዲህ ማዶ አንገናኝም ወይ ገደሉ ተንዶ!"*

የጥንት ነገሥታት ዓባይን ለመገደብ ያላለሙት ህልም አልነበረም፡፡ ዳሩ ግን "ዓባይን በጭልፋ" እየሆነባቸው ከምኞት አላለፉ፡፡

አፄ ፋሲል ለመጀመሪያ ጊዜ በዘመናቸው በሞጣ በኩል ከቤጌምድር ጋር የሚያገናኛቸውን ግዙፍ ድልድይ አሠርተው ነበር፡፡ ይህ ድልድይ እስከ ዘመናችን ድረስ የዘለቀ ነበር፡፡ በጠላት ወረራ ወቅት የጎጃምና የቤጌምድር አርበኞች በጧት በማታ እንዳይገናኙ ወይንም ካንዱ ክ/ሀገር ወደ ሌላው እንደፈለጉ እየፋነኑ ጠላትን እንዳያርበደብዱት የለየላቸው ባንዳዎች አፈረሱት፡፡ ዛሬ አሻራው ተጎርዶ ይገኛል፡፡

ዓባይ ያነዬ እንኳን ምንም ዓይነት የቴክኖሎጂ ብልጭታ ባገራችን ባልታየበት ዘመን አፄ ፋሲል ድልድዩን በማስገንባታቸው "ዓባይን የደፈሩ ጀግና ንጉሥ" አልተባሉም፡፡ ለምን ቢባል በዚያን ጊዜ እንዳሁኑ ምላስ አልረዘመም ነበርና፡፡ ሕዝቡ የንጉሡ፣ ንጉሡም የሕዝቡ በመሆናቸው የድብብቆሽ ጨዋታ አልነበረም፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ አፄ ፋሲል "ዓባይን





የደፈሩ ጀግና ንጉሥ" ለመባል በዘመናቸው የድልድዩ መሠራት በቂ የሆነ ምክንያት ነበር፡፡ ያም ሆኖ ነገሥታቱ በየዘመናቸው ዓባይን ለመገደብ ሲያልሙ ኖረዋል፡፡ ዓባይ ግን ሰዎችን ጨምሮ እንስሳትን፣ አፈሩን፣ ሣር ቅጠሉን ግንዱን ከቋጢኝ ጋር እያላጋና እያተራመሰ፣ እያግበሰበሰ ወደ ሱዳንና ግብፅ ያጉዛል፡፡ ኢትዮጵያውያን ለዚህም ሥነ ቃል አላቸው:-

"ዓባይ ማደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል!" ይሉታል፡፡ ሜድትራኒያን ባሕር ገብቶ የሚተኛ መሆኑን በዚያን ዘመን አያውቁም ነበር፡፡

ዓባይ ለኢትዮጵያውያን ምንም ጥቅም ባይሠጣቸውም ይኮሩበታል፤ ይመኩበታል፡፡ በተለይ ጎጃሞች ከናትና ካባታቸው የበለጠ ስለእውነት ለመናገር ሲፈልጉ "ግዮንን!" በማለት ይምሉበታል፡፡ ዓባይ ለጎጃሞች ኩራት ከመሆኑ የተነሣ በያመቱ ከግንቦት ወር ጀምሮ እስከ ሰኔ ወር መጨረሻ ከነጭ ዶሮ እስከ ነጭ ኮርማ ድረስ እንደየ አቅማቸው በወልና በተናጠል እያረዱ ያቋድሱታል፡፡ በነዚህ በተጠቀሱት ወራት ያባይ ዳርለዳር ትርምሱና ጫጫታው፣ ሁካታው፣ ለርዱ ማቋደሻ በያቅጣጫው ከላይ እስከታች የሚጨሰው ጭስ በራሱ የሀምሌን ጉም ይመስላል፡፡ ለእንግዳ ደራሽ ትእንግርት ነው የሚሆንበት፡፡

ዓባይ ጀምስ ብሩስ እንዳረጋገጠው ከሆነ የመነሻ ምንጩ በምእራብ ጎጃም ሰከላ ወረዳ ግሽ ከምትባል ትንሽ ተራራ ስር ነው፡፡

ዓባይ ከመነሻው ተነስቶ የምዕራብን አቅጣጫ በመያዝ የጎጃም ምድርን እያቆራረጠ በዘጌ በኩል በስተሰሜን ታጥፎ ጣና ሐይቅ ይገባና የጣናን ሐይቅ ለሁለት እየከፈለ በባሕርዳር ከተማ በመውጣት የደቡብ ምስራቅን አቅጣጫ በመያዝ ቤጌምድርንና (ያሁኑን ደ.ጎንደር) ከጎጃም ጋር እያካለለ፣ ሸዋ ምድር ሲደርስ ደግሞ ስላሌንና የደጀን ወረዳን እያዋሰነ እንደገና ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ በመታጠፍ ወለጋንና ጎጃምን፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝን ከጎጃም ጋር እያደናበረ ወደ ሱዳን አቅጣጫ ድምፁን አጥፍቶ እየተጥመለመለ ይፈሳል፡፡ ዓባይ የጎጃም ምድርን እንደ ዘንዶ ነው የተጠመጠመባት፡፡ ጎጃም ያባይ ደሴት ነው ማለት ይቻላል፡፡

ዓባይ ከመስከረም ጀምሮ እስከ ሰኔ ድረስ ኩል ባይመስልም የጠራ ነው፡፡ ሐምሌና ነሐሴን ግን ጎሽቶ አተላ ይመስላል፡፡ ዷሪዎቹ እንዲህ ይገልፁታል:-

*"ዓባይ ጥቁር ነበር ከሰል የመሰለ*

*እየቀላ ሄደ ደም እየመሰለ!"*

ኢትዮጵያውያን ለዓባይ አክብሮታቸውንና ፍቅራቸውን የሚገልፁለት ኮርማ በማቋደስ ብቻም አይደለም:: የልጆቻቸውን ስምም በመስጠት ጭምር ነው:: "ዓባይ፣ አባይነህ፣ ዓባይነሽ" በማለት ታላቅነቱን ወይንም የወንዞች ሁሉ ንጉሥነቱን ይገልፁበታል::

እንግዲህ ስለዓባይና ስለ ኢትዮጵያውያን ጥብቅ ቁርኝት እጅግ በትንሹ ይህን ያህል ካልኩ ወደ ተነሳሁበት መሠረታዊ ጉዳይ ወይንም "ዓባይን የደፈረ ጀግና!" ተብሎ በንፅፅር ስለቀረበበት እንመልከት::

ጠ/ሚንስትር መልስ ዜናዊ ዓባይ ለኢትዮጵያውያን ኩራትና ሞገሳቸው መሆኑንና ግን ደግሞ በማንኪያ የምትጨለፍ ጥቅም አለመስጠቱንና ከትውልድ እስከ ትውልድ ሲቆጩበት መኖራቸውን ደህና አድርገው ያውቃሉ:: በመሆኑም ባምስቱ ዓመት እቅድ ወይንም በትራንስፎርሜሽኑ ውስጥ ያልተካተተ ግን ደግሞ መካተት የሚገባው አብይ ጉዳይ በሌለበት ድንገት ተጣድፈው የመሠረት ድንጋይ በማስቀመጥ:-

"መሐንዲሶች እኛው፣ የገንዘብ ምንጮች እኛው፣ ቀያሾች እኛው፣ ገንቢዎች እኛው ሆነን ዓባይን ገድበን ሕዝባችንን ከርሃብ እናላቅቃለን!" ሲሉ ፕሮፓጋንዳ ለቀቁ:: ካድሬዎቻቸውና ጋዜጠኞቻቸው ይኸነኑ ተቀብለው አስተጋቡ:: ደጋፊዎቻቸውም ደገፏቸው::

እንደ እውነቱ ከሆነ በዓባይ መገደብ ማንም ቅር አይሰኝም:: ተግባሩም የተቀደሰና የሚደገፍ ነው:: በራሳችን እንሞክረው መባሉም መልካም ሐሳብ ነው:: ግን እንዴት? በነማን? መቼ? የሚሉት መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ግን ከፍተኛ ልዩነት አለ:: 97 ዓ.ም ምርጫ አያመጣው ጣጣ የለምና ልክ እንደ ውሃ ማቆሩ፣ ልክ እንደ ሚሊኒየሙ፣ ልክ እንደ ህዳሴው ተወዝፎ እንዳይቀር በሁሉም ዘንዳ ዛሬም ድረስ ሥጋት አለ::

ሌላው ሣይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ቁምነገር ሌሎቹን ሁሉ ትተን "የገንዘብም ምንጭ እኛው" ተብሎ የተስተጋባው መፈክር የቁጭትና የእልህ ቢመስልም ለምን? የሚል ጥያቄን ያጭራል:: አበዳሪ አገሮች ለጥቃቅኗ ነገሮች ለኢሕአዴግ መንግሥት ብር የሚያስታቅፉት ዓባይን የሚያህል ወንዝ ሲደፈር ለምን ብድር ከለከሉ? በመደፈሩ አኩርፈው ይሆን? ወይንስ የዓለም ዓቀፉ የገንዘብ ድርጅት ለግብፆች አዳልቶ? ይህ ጉዳይ በግልፅ የሚታወቅ ነገር የለም? ሕዝብ ግን ሊያውቀው የሚገባ ጉዳይ ነበር:: ሕዝቡ ሀቁን





ቢያውቅ ቁጭቱ ከዚህ የመነጨ ነው ማለት ይቻል ነበር:: ከሁኔታዎች መረዳት እንደሚቻለው ግን ከፍ ብዬ ለመግለፅ እንደሞከርኩት ያባይ ግድብ ጉዳይ ድንገተኛና ጥድፊያ የሆነበት አቶ መለስ የሚያውቁት ሕዝብ የማያውቀው አንድ የተደበቀ ምስጢር ይኖራል:: መንግሥት ራሱን ከጥርጣሬ ነፃ ማውጣት ደግሞ አልቻለም:: በፕሮፓጋንዳ ማሣመን ነው እየሞከረ ያለው:: ዝንተ ዓለም ሲፈስ የኖረን ወንዝ ባጭር ጊዜ ውስጥ ሰሪ ባንገት አሹልኩ ማለትን ምን አመጣው? የሚል ጥያቄንም ማስነሳቱ አልቀረም? የሚስጥሩ ቋጠሮ ያለውም ከዚህ ላይ ነው:: በዚህ ትልቅ አገራዊ ፋይዳስ ተቃዋሚዎችና የኢትዮጵያ ምሁራን ለምንድን ነው ያልተጋበዙት? ይህም ሌላው የምስጢር ቁልፍ ነው::

እንደ እውነቱ ከሆነ አቶ መለስ እንኳንስ ዓባይን የኢትዮጵያን ሕዝብ የደፈሩ ጀግና ናቸው:: ታሪኩን በመቶ ዓመት የቋጩ፤ ክቡር ባንዲራውን "ጨርቅ" ብለው ያንቋሸሹ ናቸው:: ዓባይን በዋናኮ አላቋረጡትም::

አቶ መለስ ከሻዕቢያ ጎን በመሰለፍ ወይንም በማበር በርዳ ተራዳ የኢትዮጵያን ሕዝብ በትጥቅ ትግል አንበርክከው ከሥልጣን ላይ የወጡ እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወዶና አፍቅሮ በራእያቸው ይጠቅሙኛል ብሎ መርጦ ከሥልጣን ላይ አላስቀመጣቸውም:: ሕዝቡን ደፍረውት፣ አንበርክከውት፣ ለ21 ዓመታት ተቀምጠውበት እያሉ "ዓባይን የደፈረ ጀግና!" መባላቸው ምን ዓይነት ትክለስብእናን ለመኳል ነው? በተረፈ ግን ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደሞከርኩት ነገሥታቱ ዓባይን ለመገደብ ሲያልሙ መኖራቸው በየታሪኩ ተጠቅሶ ይገኛል:: ሌላው ቀርቶ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ራሺያኖች ለግብፆች ያሰዋን ግድብ መሥራት ሲጀምሩ አሜሪካኖችም ለኛ አሁን እየተቆፈረ ካለበት አካባቢ በራሳቸው ወጭ ሁሉን ነገር ችለው ለመሥራት ተዋውለው እንደነበር የሚጠቁሙ ሠነዶች አሉ:: ዳሩ ግን ያሜሪካኖቹ ዓላማ ግብፆችን ከራሽያኖች ካምፕ ለመመንጨቅ እንጂ ለኢትዮጵያ አሥበውና ተቆርቁረው አልነበረም:: በመሆኑም ከጥናት ያለፈ አንዲት ነገር ሣይሠሩ ራሺያኖቹና ግብፆች ያሰዋን ግድብ ተሠርቶ እንዳለቀ በመቃቃራቸው ሲፋቱ አሜሪካኖቹ ጓዛቸውን ጠቅልለው ግብፅ ሲገቡ ያባይ ግድብ ጉዳይ ህልም ሆኖ ቀረ::

ዛሬም አቶ መለስ ተንደርድረው ባምስት ዓመቱ እቅድ ውስጥ ያልተካተተን ፕሮጀክት፣ ዓባይን የሚያህል ትልቅ ጉዳይ ድንገት ብድግ ብለው "ለመድፈር" የቻሉበት ምክንያት አሜሪካኖቹ ፈጥነው ካርድ እንዲመዙ ሣይጠቁሟቸው እንደማይቀሩ መጠርጠር ተገቢ ነው:: ግብፆች

በለውጥ ማዕበል ውስጥ እየተናጡ ባሉበት ወቅት ዓባይን ያላንዳች ውይይትና ድርድር ርግጠኛ ሆነው ለመገደብ መነሳታቸው ጊዜው አሁን ነው የሚሉ ነው የሚመስለው፡፡ አሜሪካኖች ደግሞ ከራሳቸው የረጅም ጊዜ የጥቅም አንፃር ይህንን ከማድረግ አይመለሱም፡፡ አቶ መለስም ትንሽ ፋታ የሚያገኙበትን መንገድ ካገኙ ለዘለቄታ መፍትሄ የሚጨነቁ ሰው አይደሉም፡፡ ይህ ሁሉ ሆኖም አቶ መለስ በዘመናቸው ያባይ ግድብ መጀመሩ በራሱ ምስጋና አያስነፍጋቸውም፡፡ "ዓባይን የደፈረ ጀግና!" እየተባሉ መንቆላጰሳቸው ግን ከንቱ ውዳሴ ነው፡፡ ውደሳውና ሙገሳው ያስፈልጋል ከተባለም ተሠርቶ አልቆ ጥቅም መስጠት ሲጀምር ይደርስ ነበር፡፡ እንደ መጀመሩ መጨረሱ አሣር ነውና!

## ጀግንነት እንዴት?

ፈረንጆቹ (Herism, agreat courage, a very brave act doing something agreat cost at to one self. . .) እያለ በምሳሌ እያስደገፉ ይተነትኑታል፡፡

በመሠረቱ ጀግንነት በብዙ መልኩ ሊበየን ይችላል፡፡ የግድ በጦር ሜዳ ጀብዱ የፈፀመ ብቻ ጀግና ሊባል አይችልም፡፡ የሥራ ጀግና (ጎበዝ ገበሬ፣ ጎበዝ ወዛደር፣ ጎበዝ ነጋዴ፣ ጎበዝ መምህር፣ ጎበዝ የጤና ባለሙያ. . .) እያልን ልንተነትን ወይንም ልንዘረዝር እንችላለን፡፡ ከት/ቤት ባጠቃላይ ውጤት ከተመሣሣይ ክፍሎች አንደኛ የወጣ ተማሪ ጎበዝ፣ ጀግና ተብሎ ሊደነቅ ይችላል፡፡ ቁምነገሩ አብረውት የተሰለፉትን ከማሸነፉ ላይ ነው፡፡

አትሌት ኃይሌ ገ/ሥላሴ አትሌት ቀነኒሣ በቀለ የ10 ሺ ሜትር ጀግኖች ሊባሉ ይችላሉ፡፡ ሌሎቹም አትሌቶቻችን በስፖርቱ በኩል አመርቂ ውጤት አምጥተው ያገራቸውን ባንዲራ በዓለም አደባባይ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ በማድረጋቸው ጀግኖች ሊባሉ ይችላሉ፡፡ ከዚህ እውነታ ስንነሳ ያቶ መለስ ጀግንነት ከየትኛው ዘርፍ (ካታጎሪ) ነው የሚመደቡት? በጦር ሜዳ ውሎ እንዳይባል፡-

*"ታጋዩ መለስ ለመጀመሪያ ጊዜ መቼና የት ተዋጋ?"* ተብለው ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፡-

*"መጀመሪያ ውጊያየን ያካሄድኩት በትውልድ ከተማየ ዓድዋ ውስጥ ነበር፡፡ ዓድዋ የነበረውን ባንክ ለመቆጣጠር ያካሄድነው ኦፕሬሽን ግን ሳይሳካ*





*ነበር የተመለስነው፡፡ ከዚያ በፊት አክሱም ላይ የተሣካ ኦፕሬሽን አካሂደን ነበር . . ." (መለስ ከልጅነት እስከ እውቀት ገጽ 8-9 በትኩእ ባሕታ)*

እንግዲህ ባንክ መዝረፍም ጀግና ካስባለ አነግ የለቀምቴን ባንክ፣ ኦብነግ የጅጅጋን ባንክ፣ ግንቦት 7 የውልቂጤን ባንክ ቢዘርፉ ጀግኖች ሊባሉ ነው ማለት ነው? በነገራችን ላይ ተጋዳላዮቹ ያኔ አክሱም የዘረፉት የብር መጠን 350 ሺ ብር እንደነበር በተጠቀሰው መጽሐፍ በጀግንነትና በኩራት የግርጌ ማስታወሻ ሆኖ ተቀምጧል፡፡ ጠያቂው ይቀጥልና፡-

*"ሌላ የደረሰብዎ ትልቅ አደጋ ይኖር ይሆን?" ብሎ ላቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፡-*

*". . .በግሌ ከሌሎቹ ጓዶች ጋር ሳነፃፅረው እስከዚህም ለሞት የሚያበቃ የሚተረከለት አደጋ ያመለጥኩበት ጊዜ የለም፡፡ አንድ ጊዜ ደርግ ራሴን በጥይት ጨረፍ አድርጎኝ ነበር . . ." (በተመሣሣይ መጽሐፍ ገጽ 19)*

እንግዲህ በጦር ሜዳ ውሏቸው ከዚህ የላቀ ጀብዱ አለማስመዝገባቸውን ራሳቸው እየመሠከሩ ነው፡፡ ታዲያ በየትኛው መስከ መድበን ጀግና እንበላቸው? በርግጥ ጀግንነቱ የተሠጣቸው ዓባይን በመድፈራቸው እንደሆነ ተደጋግሞ ተነግሮናል፡፡ ያባይ ጉዳይ ደግሞ ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደሞከርኩት ተጀመረ እንጂ ያልተጠናቀቀ በመሆኑ ጀግንነቱ በይደር የሚቆይ እንጂ መሠረቱ ስለተጣለና ቁፋሮ ስለተጀመረ አስቀድሞ ማሞካሸቱ በኋላ ውርደት ሲመጣ ማጣፊያው ሊያጥር ይችላል፡፡

በመሠረቱ አቶ መለስ በመሪነታቸው ከዚህም በላቀ መሥራትና መትጋትም ይጠበቅባቸው ነበር፡፡ ይህም ሆኖ ጥያቄው ታላቅነታቸውንና ጀግንነታቸውን ከኩሸትና ከተራ ፕሮፓጋንዳ ነፃ በሆነ መልኩ በምን እንግለፃቸው? ባንድ ወቅት የተከበሩ ዶ/ር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ የተባሉ ምሁር "ሞተኪያ የሌላቸው" ሲሉ አሞካሸተዋቸው ነበር፡፡ እንዲሁም በ1994ዓ.ም ዶ.ር ገመቹ የተባሉ ምሁር ጠ.ሚንስትር መለስ የከፍተኛ ት.ቤቶችን ምሁራንን ሰብስበው ባወያዩበት ወቅት "ሺ ምሁር ቢጨፈለቅ አንድ መለስን አይሆንም" ብለዋቸው ነበር፡፡ ይህ አባባል በትክክል ይገልፃቸው ይሆን? ወይንስ የግል ውደሣ? እስቲ ጠይቁ፡፡

*መንግሥቱ ኃይለማርያምን የግል አድናቂዎቻቸው "ብልሁ፣ ቆራጡ!"* ይሏቸው ነበር፡፡ እውነትም ቆርጠው ዝንምባቄ ሲገቡ እንደሣቸው ቆራጥ መሪ አጥተን ተዋረድን፤ ታሪካችንም ምስጥ እንደበላው ደረቅ እንጨት

ነኮተ:: ዛሬም ሣናስበው "ታላቁ መሪያችን" የውሃ ላይ ኩበት አድርገውን ዳግም ላይመለሱ በመሸለካቸው አብረዋቸው የተሰለፉት ጓዶቻቸው የሚይዙትን የሚጨብጡትን አጥተው ካረፉበት እለት ጀምረው በሳቸው ሙት መንፈስ አገር ሊመሩና ሊያስተዳድሩ ይዳዳቸዋል:: "ራእያቸውን ባስቀመጡልን፣ በነደፉልን. . . መሠረት ሳይሸራረፍ እንቀጥላለን" እያሉ ሕዝቡን የእንጀራ መቁረሻ ጊዜ አሣጥተው በመሸ በነጋ እየሠበሰቡ ቃለ መሀላ በማስገባት እያመሱት ይገኛሉ:: የነሱን ራእይ ከየት ያምጡት? "በታላቁ መሪያችን" ጫንቃ ታዝሎ ሆዱን ሲሞላ የኖረ ሁሉ ዛሬ ጉዱ ቢፈላ አያስገርምም:: የሚያስገርመው ሕዝብን በቃለ መሀላ ለመግዛት መታሰቡ ነው::

እውነት እንነጋገር ከተባለ እንኳን አቶ መለስ የቀድሞውን ሠራዊት እየነዳ አዲስ አበባ የገባው ጀኔራል ኃየሎም አርአያ ብሔራዊ ጀግና ሊባል ከቶ አይቻለውም:: ኃየሎም የሕወሓት ጀግና እንጂ በምንም መመዘኛ የኢትዮጵያ ጀግና ሊባል አይችልም::

ጀኔራል ኃየሎም አርአያና መሰሎቹ ጠ/ሚንስትር መለስን ጨምሮ ራእያቸውና ዓላማቸው ትግራይን ገንጥሎ ነፃ አገር መመሥረትና ኤርትራን ማስገንጠል እንጂ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከጭቆና አገዛዝ ለማላቀቅ አለመንቀሳቀሳቸውን በማያሻማ መልኩ ታሪካቸውና ተግባራቸው ቁልጭ አድርጎ ያሣየናል:: ሀቁ ይኸ ሆኖ እያለ በምን መሥፈርት ነው ኃየሎም አርአያ ብሔራዊ ጀግና ተብሎ ላገራቸው ስንት መስዋእትነት የከፈሉ ጀግኖች እያሉ አንጋፋው የጦር ት/ቤት (ሆለታ ገነት) በኃየሎም ስም የተሠየመው? ይህ ድርጊት ሕዝብን መናቅና ማን ይታዘበናል ብሎ አለመስጋትን ነው የሚያመለክተን::

አስፈላጊ ነው ተብሎ ከታመነበት ለጀኔራል ኃየሎም ትግራይ ውስጥ በስሙ አንድ ት/ቤት ሊሰይሙለት ይችላሉ:: ከዚህ ውጭ ግን ይህንን አንጋፋ የጦር ት/ቤት ስንት ጀግኖችን ያፈራ ባንድ ግለሰብ ስም መሰየም ከመጀመሪያውም ትልቅ ስህተት ብቻ ሣይሆን ትልቅ ድፍረትም ነው:: አንድ ጀግና ብሔራዊ ጀግና ነው ተብሎ ብሔራዊ አርማና ያገር ውክልና ስያሜ ሊሰጠው የሚቻለውና የሚገባው የውጭ ወራሪን ጠላት ረግጦ ያስወጣ እንደሆን ነው:: ለምሳሌ እንደ አፄ ምኒልክ አድዋ ተራሮች እስከነ ባለቤታቸው ወጥተው ወሰን ጥሶ የመጣን ጠላት መርቶና አዋግቶ ወይንም እንደ አፄ ዮሐንስ ጠረፍ ድረስ ወርዶ ላገሩ ዳርድንበር እንደ መጥምቁ ዮሐንስ አንገቱን የሠጠ ወይንም ደግሞ አልሆን ሲል በነጭ ወታደር ተማርኮ





ለትውልድ አሣፋሪ ታሪክ ላለማስቀመጥ ሲባል እንደ አፄ ቴዎድሮስ ጥይት እንደ ቆሎ ቆርጥመው ሕይወታቸውን ያሣለፉ ብሔራዊ ጀግኖች ተብለው ብሔራዊ ወይንም አገር አቀፍ የማስታወሻ ስያሜ ሊሰጣቸው ይችላል:: እንደ ኃየሎም አርአያ ያሉ የጎጥ ጀግኖች ግን ለጎጣቸው እንጂ በምንም ታምር ብሔራዊ ጀግኖች ተብለው አንጋፋው የኢትዮጵያ የጦር ት/ቤት በስማቸው ሊሰየም አይገባም፤ ነውርም ነው::

ጀግንነታቸው በወንድማማቾች መሀከል በተካሄደ ፍልሚያ እንጅ ከውጭ አጥቂ ወራሪ ጋር ባለመሆኑ የሁሉንም ስሜት አይገዛም፤ አይማርከም:: በርግጥ የትግራይ ጀግና ይሊባል ይችላል:: ይህ ያስማማናል::

በመሠረቱ አገር በውጭ ወራሪዎች እንዳትደፈርና እንዳትገሠሥ የጀግኖች መኖር የግድ ነው:: እነዚህ ጀግኖች ደግሞ የጎጥ ጀግኖች የሚባሉ ሣይሆኑ ብሔራዊ ጀግኖች ሊባሉ የሚችሉ መሆን አለባቸው:: ለሥልጣን ሽሚያ ሲባል በታሪክ አጋጣሚ የገዛ ወገንን እያረዱና እየጨፈጨፉ ጀግና የሚያስብል ከሆነ ክወንድሙ አስከሬን ላይ ሐውልት እንደማቆም ይቆጠራል:: በርግጥም የሕወሐት ጀግኖች በሕዝብ ልጆች አፅም ላይ በየቦታው የመሣለቂያ ሐውልቶችን አቁመውልናል:: በኋላ እመለስበታለሁ::

በመሠረቱ ጀግኖችን ልናገኝና ልናፈራ የምንችለው ቀደምት ጀግኖች ለሠሩት ሥራ ዋጋና አክብሮት መሥጠት ስንችል ነው:: ቀደምት ጀግኖች የሠሩትን ሀገራዊ ጀብዱ ትቢያ እያለበስንና እነሱን እንደ ብሥራት አማረ ያሉ እየዘረጠጡ በመስደብና በማዋረድ ሕዝብን አንገት በማስደፋት ወይንም በቀልን በበቀል ለመመለስ የከፋት ስንቅን የምናስቋጥር ከሆነ ብሔራዊ ጀግኖችን የማግኘት እድላችን በጣም ሩቅ ነው::

ጊዜው የተገላቢጦሽ ሆነና ያርበኞች ልጆችና የልጅ ልጆች እየተንቋሸሹና እየተዋረዱ የባንዳ ልጆችና የልጅ ልጆች እንዲሁም ምርኮኞች ሲወደሱና ሲንቆላጰሱ ማየትና መስማት በርግጥም ጨጓራን ይልጣል:: እንዲህ ዓይነቱን ቅጥ ያጣ ምስቅልቅል ዘመን አበው <<ቀን የሠጠው ቅል ድንጋይ ይሠብራል!>> ይሉታል:: ለማንኛውም ያቶ መለስን "ታላቅነትና ጀግንነት!" ለታሪክ ብናቆየው ነው የሚሻለው::

## እንደበተ ርቱዕ

አቶ መለስን አድናቂዎቻቸው "እንደበተ ርቱዕ" በማለትም ይገልፅዋቸዋል:: ይህ አገላለፅም አንድም ያንደበተ ርቱዕነትን ፍች ጠንቅቆ

ካለማወቅ የመጣ ጣጣ ይመስለኛል፡፡ ተናጋሪ፣ ተሳዳቢ፣ አሽሟቃቂና አሽሟጣጭ የሆነ ሁሉ አንደበተ ርቱዕ ከተባለ እውነትም የፍች ችግር አለ፡፡

ርቱዕ የግዕዝ ቃል ሲሆን ሲናገር የድምፁ ቅላፄ ያድማጭን ቀልብ ወይንም ሕሊና የሚገዛ፣ የሚመስጥ፣ የሚያማልል . . .ከሁሉም በላይ የሚጠቀምባቸው ቃላትና ሐረጋት የተመረጡና በልማዳዊ አነጋገር (ጋጠወጥ) ከምንላቸው በእጅጉ የራቁና ለባላንጣ ቀዳዳን የማይከፍቱ፣ ባንፃሩ የባለንጣን አንደበት የሚዘጉ መሆን አለባቸው ለምሳሌ፡-

ልደቱ ዓያሌው አንደበተ ርቱዕ ሊባል ይችላል፡፡ ሌላ ትርጉም ካልተሠጠው በስተቀር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋም አንደበተ ርቱዕ ነው፡፡ ሲናገር ነጎድጓዳማ ድምፁ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡ ከነዚህ አንፃር አቶ መለስ አንደበተ ርቱዕ ሊባሉ አይችሉም፡፡ በነዚህ 21 ዓመታት ውስጥ የሳቸውን ንግግር ላለማዳመጥ ስንቶች ናቸው ሬዲዮና ቴሌቪዥናቸውን ይዘጉ የነበረው? ወይንም ሌላ አማራጭ ጣቢያ ፍለጋ የሬዲዮ ኮርትና የቴሌቪዥን ቻናል ቅየራ መሥመር ጉርጎራ የሚገቡት? ይህንን ሀቅ የሚክድ አለ ብዬ አላምንም፡፡

በደርግ ጊዜ አንድ አዋጅ ሲታወጅ አንጋፋው ጋዜጠኛ አሠፋ ይርጉ ገና "አዋጅ" ማለት ሲጀምር ዐይኖቹን ከቴሌቪዥን ላይ የማያፈጥ፣ ጆሮዎቹን ከሬዲዮ ላይ እንደ አንቴና የማያቆም አንድም ዜጋ አልነበረም፡፡ ሁሉም ተመስጦ ያዳምጣል፡፡ የዚህ ምክንያቱ ያሠፋ ይርጉ የድምፅ ቅላፄ መረዋነትና ማራኪነት ቀልብ ገዥ በመሆኑ ነበር፡፡ ልደቱ ዓያሌውም ሲናገር በተለይም በክርክር ወቅት አፍን ያስከፍታል፡፡ ፈጣን መልሶቹ የባላንጣን አንደበት ወይንም ምላስ ከላንቃ የሚጣበቅ ተሰጥኦ አለው፡፡ ምን ይሆናል ታዲያ ተንሸራተተ!! "ተንሸራታች" ያልኩት ግን እኔ አይደለሁም፡፡ ሕዝቡ ነው፡፡ "ልደቱ ከህደቱ!"ም ብሎታል፡፡ "ተንሸራታች" ብል አንድ ነገር ትዝ አለኝ፡፡ ያኑ ሰሞን ሞባይል ልገዛ መርካቶ ሄጄ ሞባይሎች ከሚሸጡበት ሱቅ ጎራ ብዬ ዓይነታቸውን ሣማርጥ የሱቁ ባለቤት ወጣት፡-

"ፉዘር፤ ልደቱ ይሻለዎታል፤ እሱን ይግዙ" አለችኝና አንዱን አንስታ ለኔ ለማሣየት ገፋ አድርጋ በማንሸራተት እንዳየው ሰጠችኝ፡፡ ተቀበልኳትና አገላብጬ እያየሁ፡-

"ልደቱ በስሙ ሞባይል አሠራ እንዴ?" ስል ጠየኳት፡፡ ሳቅ አለችና፡-





"አየ፤ አላሠራም፡፡ ስለተንሸራተተ የዚህ ዓይነት ሞባይል መጠሪያው ሆነ" አለችኝ፡፡

"እንዲህ ከሆነ እንግዲያው እኔ የሚሸራተት ሞባይል አልፈልግም" ብዬ መልሼ ሰጧት፡፡ "እንግዲያውስ ሰሜ በለውን ይግዙ፡፡ እሱ ይሻለዎታል" ብላ ድጅኖ የሆነ ሞባይል አንስታ ሠጠችኝ፡፡

"ይኽ ደግሞ ለምንድን ነው ሰሜ በለው የተባለው?" ስል ጠየኳት፡፡

"ወድቆ ስለማይሠበር" አለችኝ፡፡

"እንግዲያው ወድቆ የማይሠበረውን ነው የምገዛው" ብዬ ሰሜ በለውን ገዝቸ ከሱቁ ወጣሁ፡፡ እውነትም ሰሜ በለው ወድቆ አይሠበርም፡፡ ይኸውና ከ98 ዓ.ም ጀምሮ ከጄ ሣይወጣ አለ፡፡ ቢያንስ ካሥር ጊዜ በላይ ወድቋል፡፡ ግን ፍንከች አላለም፡፡ ደግሞ የሌቦችን ቀልብ አይስብም፡፡

እንግዲህ አቶ መለስ ከላይ ለማስረጃ ያህል ካቀርብኳቸው ጋር ሲነፃፀሩ አንደበተ ርቱዕ ሊባሉ የሚችሉ ዓይደሉም፡፡ በርግጥ ተናጋሪ ሊባሉ ይችላሉ፡፡ የባላንጣን ቅስም የመስበርም ሆነ አሽማቀው አንገት የማስደፋት ልዩ ተሰጥኦ አላቸው፡፡ ይህ ግን ተሳዳቢነትን እንጂ አንደበተ ርቱዕነትን አያመለክትም፡፡ ሲናገሩ በፊታቸው ላይ የሚታየው የከፋ የቁጣ የደም ሥር መገታተር ንግግራቸውን ለማድመጥ የሚጋብዝ አይደለም፡፡ እንደዘበት የሚወረውሯቸው ቃላትና የፊታቸው መኮሣተር ሲታይ "የቤት ቀጋ የውጭ አልጋ" የሚባሉት ዓይነት ናቸው፡፡

አቶ መለስ ላምባሣደሮችና ለውጭ አገር ዜጎች የሚያሣዩት ፈገግታና በተወካዮች ም/ቤት ቀርበው ንግግር በሚያደርጉበት ወቅት ለተቃዋሚዎች የሚያሣዩት የፊታቸው መጨማደድና የሚወረውሯቸው ቅስም ሠባሪ ቃላት ጋር ተዳምረው በጭራሽ አንደበተ ርቱዕ ሊባሉ የሚችሉ አይደሉም፡፡ መባል ካለባቸው የፕሮፓጋንዳና የቅስቀሳ ሰው ናቸው፡፡ ስለዚህ ፕሮፓጋንዲስት ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡

በመሠረቱ ከመሰረቱ የተበላሸን ነገር ዛሬ በፕሮፓጋንዳ ጥቁሩን ነጭ፣ ነጩን ቀይ ቀለም በመቀባት መኳኳል አይቻልም፡፡ ሺ ጊዜ አብረቅራቂ ቀሚስ ቢያጎናፅፏቸው ቀሚሱ ሲገለጥ የምናገኛቸው የትግራይን ነፃ አውጭና ኤርትራን ተዋግተው ያስገነጠሉትን፣ ኢትዮጵያን የባሕር በር ያሳጧትን አቶ መለስ ዜናዊን ነው፡፡

አበበ ገላው በሬገን ማዕከል ያስደነገጣቸው ሰሞን "በድንጋጤ አንገታቸውን ደፍተው ነበር" የሚለውን ለማስተባበል ወይንም "ድንጋጤ ሲያልፍም አይነካቸው" ለማለት ታንክ ላይ ተቀምጠው መጽሐፍ እንደሚያነቡ ተርከውልናል፡፡ ታንኩ በውጊያ ወቅት እንደተዋጊ በሬ መድፉን ወደ ጠላት አቅጣጫ ደግኖ እሳት እየተፋ ከላዩ ላይ ተቀምጠው አንብበው ከሆነ ድፍረት ሣይሆን ደመነፍስነት ነው፡፡ ወይንም ደግሞ ባንዳንድ ፊልሞች እንደምናያቸው መናፍስት ናቸው ማለት ነው፡፡ በሰላም ጊዜ ታንኩ እንዳይግል ወይንም በፀሐይ ጨረር አንፀባርቆ ለጠላት እይታ እንዳይጋለጥ ከዛፍ ሥር ቁሞ ከዚያ ላይ ተቀምጠው አንብበው ከሆነ ጊዜያቸውን በዋዛ ፈዛዛ ባለማሣለፋቸው ሊደነቁ ይገባቸዋል፡፡ አንባቢነታቸውም የኋላ ሥንቅ እንደሆናቸው መገመቱ አይከብድም፡፡ ከዚህ ውጭ ግን መጽሐፍ አንባቢ መሆን የፍርሃትና የድፍረት ማነፃፀሪያ ሊሆን አይችልም፡፡ ለመሆኑ ፋኖ ታንክና መድፍ አለው እንዴ? ጠይቁ ፡፡

ከጓደኞቻቸው ጋር ቁራሽ ፍለጋ ካንድ መንደር ውስጥ ገብተው በንባብ ተጠምደው እማወራዋን ሊጥ አላስቦካ ማለታቸውንም <<መለስ ከልጅነት እስከ እውቀት>> የተባለው ስብስብ ሥራ አስነብቦናል፡፡ በዚህ አጋጣሚ አንድ ተረት መሠል ቁምነገር ትዝ አለኝ፡፡

አንድ አዳኝ አደን ውሎ ሣይቀናው ይመለሳል፡፡ ጓደኛው ከመንገድ ያገኘውና "የዛሬው ውሎህ እንዴት ነው? አልቀናህም?" ሲል ይጠይቀዋል፡፡

"አንዲት ድኩላ አግኝቸ እግሯንና ጆሮዋን አነባብሬ ባንድ ጥይት መትቸ ገደልኳት" ይለዋል፡፡

"ይህ እንዴት ሊሆንይችላል?"በማለት ሲጠይቀው፡-

"በኋላ እግሮቿ ጆሮዋን ስታክ ጠነበዝኳት" ሲለው፡-

"አሁን እውነት መሰለልህ" አለው ይባላል፡፡ ያቶ መለስ ፕሮፓጋንዲስቶች አቶ መለስን ልክ ሕዝብ እንደማያውቃቸው የተለየ ፍጡርና ለኢትዮጵያ መድሕን ሆነው የተፈጠሩ በማስመሰል ሲተርኩልን ትንሽ እንኳን ሕዝብ ምን ይለናል ብለው አለ መጨነቃቸው በራሱ ወደፊት ምርምር የሚያሻው ጉዳይ ነው፡፡ የሳቸውን ገድለታሪክ ለታሪክ አቆይቶ ወደ ሥራ ቢገባ እንዴት የተሻለና ያማረ በሆነ ነበር፡፡ ግን ማን ልበሙሉነት ይሰማው? ሁሉም ባለሥልጣናት በሣቸው ሙት መንፈስ በፍርሃት ተዘፍቀው እየበረገጉ ሥራ ትተው ሥራ እያሥተው ናቸው፡፡ ለማንኛውም የሚሻለው ልናስብ የምንችለውን ያህል ብናስብ ነው፡፡





# ያሰብ የባሕር በር

በቅድሚያ የባሕር በር ስንል ምን ማለታችን ነው? "በር" በጥሬ ፍችው መግቢያና መውጫ ማለት ነው፡፡ "የባሕር በር" ስንል ደግሞ ባሕርን ወይንም እውቅያኖስን አቋርጠን ወደ የብስ የምንዘልቅበት ወይንም ከየብስ ወደ ባሕር የምንገባበት ማለታችን ነው፡፡

"ያሰብ የባሕር በር" ስንልስ ምን ማለታችን ነው? ይህንን በተመለከተ ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም የሚከተለውን ይላሉ፡-

". . .የባሕር በር መብት ስንል ምን ማለታችን ነው?" በማለት ይጠይቁና "በተለምዶ አነጋገር <አሠብ>ሲባል ብዙዎች ወደቡን ብቻ የሚሸፍን አድርገው ይወስዱታል፡፡ በዚህ ጽሑፍ ‹አሰብ› ስንል ግን ከወደቡ ዓለም ዓቀፍ የባሕር በር ሕግ እንደ ሚደነግገው 12 ኖርቲካል ማይልስ ወደ ባሕር ዘልቆ (ገብቶ) ላይ ታቹን፣ የባሕሩንና የመሬቱን አካባቢ የሚሸፍነውን ሲሆን፤ ባዔ ኃይለሥላሴ ‹ያሰብ አውራጃ› በደርግ ጊዜ ‹ያሰብ ራስ ገዝ› ይባል የነበረውን ውሃውንና መሬቱን፣ ደሴቶቹን ሁሉ ያጠቃልላል› *(አሠብ የማናት ገጽ 170 ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም)*

እንግዲህ ስለ አሠብ አውራጃና ራስ ገዝ አሥተዳደር ይህን ያህል ካልን ስለ ወደቡስ ምን እንላለን? ወደብ በጥሬ ፍችው የሸቀጦች ማራገፊያ፣ መጫኛ፣ ማቆያና ማከማቻ ልንለው እንችላለን፡፡ ወደብ ላንዲት አገር ኢኮኖሚ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ ወደብ ያላት አገር ምንም ያህል ትንሽና የባሕር ዳርቻ አገር ብትሆን እንኳን ወደቧን ወደብ ለሌላቸው አገሮች በማከራየት ሕዝቦቿን መግባ መኖር አይሳናትም፡፡ ባንፃሩ ወደብ የሌላት አገር ምንም ያህል በቆዳ ስፋቷና በሕዝቧ ብዛትና በኢኮኖሚዋ የበረታች ብትሆንጂ የራሷን ጥሬ እቃዎች የማስወጫና የምትፈልጋቸውን የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በፈለገችበት ጊዜ ማስገባት ስለማትችል ለወደብ ኪራይ የምትከፍለው ክፍያ ከምታመርተው እጥፍ ስለሚሆን የትልቅ ድኩማን መሆኗ የግድ ነው፡፡ ኢትዮጵያንና ጅቡቲን በማነፃፀር ሀቁን መረዳት ይቻላል፡፡ ዛሬ ጂቡቲ የትንሽ ትልቅ ስትሆን ኢትዮጵያ ግን የትልቅ ትንሽ ሆና የሷ ገባር ሆናለች፡፡ ያውም ተለማምጠን፣ መብራት ዘርግተን እሷ 24 ሰዓት ስትንቆጠቆጥ እኛ ግን መብራት በፈረቃ እንደ ጨረቃ፡፡

ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም ከብዙ አቅጣጫ ቃኝተውና ፈትሸው ሀቁን እንዳስቀመጡት ከሆነ ባሁኑ ወቅት ለጂቡቲ በቀን ለወደብ አገልግሎት የምንከፍለው ኪራይ ከሦስት ሚሊዮን ዶላር በላይ ነው፡፡ ወደኛ ምንዛሬ ስንመልሰው ከሃያ ሚሊዮን ብር በላይ ነው፡፡ በዚህ ስሌት ስንሄድ በወርና ባመት የምንከፍለው ከፍያ የትየ ሌሌ ነው፡፡ ባጭሩ ሥርተን ለጂቡቲ ነው የምናስረክበው ማለት ይቻላል፡፡

ኢትዮጵያን የባሕር በር ለማሣጣትና ወደብ አልባ ለማድረግ የትግራይ ወጣቶች ገና ከማለዳው ጀምረው የተጠናወታቸው መሆኑን ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም እንዲህ ሲሉ ቁጭታቸውን ይገልፃሉ:-

"የሕወሓት መሪዎች ኤርትራን አስገንጥለው ኢትዮጵያን ወደብ አልባ እንድትሆን የሠረጸባቸው ምኞት ገና በተማሪነታቸው ‹ማህበረ ገሥገስቲ ብሔረ ትግራይ› የተባለ የተማሪዎች ማህበር ካቋቋሙበት ጊዜ ጀምሮ ነበር..." *(እንደ ላይኛው ገጽ 20)*

በነገራችን ላይ ይህ የዶ/ር ያዕቆብ "አሠብ የማናት?" የሚለው መጽሐፍ ከሕግ፣ ከሉዓላዊነትና ከታሪክ አንፃር እያጣቀሱ የሕወሓትን ደባ መነሻና የመዳረሻ ግቡን፣ የግብዖችንም ሴራ ያጋለጡበት በመሆኑ ያገሩ ውርደትና ሞት የሚቆጨው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ገዝቶ ሊያነበው የሚገባ መጽሐፍ ነው፡፡

ለመሆኑ የሕወሓት ከፍተኛ ያመራር አባላት ይህን ያህል ለኢትዮጵያ ጠላት የሆኑትና የባሕር በሯን ዘግተው ጉረሮዋን ያነቋት ለምንድን ነው? ጭካኔቸውስ ከምን የመነጨ ነው? ብለን ብንጠይቅ ለዚህ ዶ/ር ያዕቆብ የሚከተለውን መልስ ይሰጡናል:-

"‹ዛሬ ኢትዮጵያ የባሕር በር አያስፈልጋትም በጎረቤት አገራት ወደቦች ትጠቀማለች› የሚሉን የሕወሓት መሪዎች ባንድ በኩል ኤርትራን ለማስገንጠል ሲጥሩ በሌላ በኩል ደግሞ በመጀመሪያ <ታላቋ ትግራይን ፈጥረው> የትግራይን ሪፐብሊክን አቋቁመው የቀይ ባሕር ሰላጤን ከታላቋ ትግራይ ጋር ለመቀላቀል የወጠኑት ነበር" *(ዶ/ር ያዕቆብ እንደላይኛው ገጽ 53)*

እንግዲህ ሀቁ ይኸ ነው፡፡ የሕወሓት አመራሮች 21 ዓመታት ተጉዘው እንኳን "ኢሕአዴግ" ብለው የጠፈጠፉትን ለይመስልም ቢሆን ከግንባርነት ወደ ውህደት አሸጋግረው ኢትዮጵያዊ ካባ ማልበስ አልቻሉም፡፡ ይህም እንዳደፈጡ ለመሆናቸው አንዱ ማረጋገጫ ነው፡፡





ይህንን ሀቅ በተመለከተ ማስታወቂያ ሚንስቴር በ1995 ዓ.ም "የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳና ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ" ብሎ በሣተመው መጽሐፍ የሚከተለውን ይለናል:-

"ጎረቤቶቻችን ባለወደብ ሲሆኑ እኛ ግን ወደብ አልባ በመሆናችን በኢኮኖሚ እየለማን ስንሄድ በዚያው መጠን ብቃት ያለው አገልግሎት የሚያስፈልገው መሆኑ ሌላው ጉዳይ ነው፡፡" *(ገጽ 63)*

ኢትዮጵያን ጉረሮዋን ያነቃትና ያሣናቃት ድርጅት እንኳን ይህንን ያፈጠጠ ሀቅ መሸሸግ አልሆነለትም፡፡ <እየለማን በሄድን መጠን ሰፊ የወደብ አገልግሎት> እንደሚያስፈልገን የኢሕአዴግ መንግሥት ተገንዝቦታል፡፡ ጥያቄው ታዲያ ምን ይደረግ ነው? ማንስ ነው ወደብ ያሣጣን? እያደግንና እየለማን በሄድን መጠን ወደብ ፍለጋ ማረፊያ ዘፍ እንዳጣ አሞራ መከነፍ ነው? ጠይቁ፡፡

ይኸው ማስታወቂያ ሚንስቴር ያሳተመው መጽሐፍ አያይዞም እንዲህ ይለናል:-

". . .አደጋው ሁሉም ተባብረው ለኢትዮጵያ የወደብ አገልግሎት የከለከሉ እንደሆነ ነው . . ." *(እንደላይኛው ገጽ 64)* <ሁሉም ተባብረው የከለከሉን እንደሆነ> የተባሉት ሞምባሳ፣ ፓርት ሱዳን፣ በርበራን . . . ለማለት ነው፡፡

የኢሕአዴግ መንግሥት የወደብን አስፈላጊነትና ጠቃሚነት ከገለፁልን በኋላ መልሶ ደግሞ ወደብ ማስነጠቁን ወይንም ፈቅዶ መልቀቁን ሕጋዊነት ለማላበስ ሲል በተጠቀሰው መጽሐፍ እንዲህ ይለናል:-

". . .ባንድ ብኩል በተለይም ከወደብ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የኤርትራ ነፃነት ያልተዋጠላቸው ወገኖች አሉ" በማለት ለመኮነን ይሞክራል፡፡ *(እንደላይኛው ገጽ 69)*

ይኸው መጽሐፍ ከጂቡቲ ጋርም ዘላቂ ወዳጅነት እንደማይኖረን እንዲህ ይለናል "ባሁኑ ወቅት ጎልቶ የሚታይ ችግር ባይኖርም በጂቡቲ በኩል አለመግባባት ተፈጥሮ የወደብ አጠቃቀምን ሊያሰናክል ይችላል፡፡ የተለያዩ የውጭ ጣልቃ ገቦች (ዐረቦችን ለማለት ነው) በጂቡቲ ላይ ተፅዕኖ አሣርፈው አጠቃቀሙን እንዳያሰናክሉት በሩን ሊከፍትላቸው ይችላል. . ." በማለት ኢሕአዴግ ሥጋቱን ሣይደብቅ ይነግረናል፡፡ ስለዚህ ጂቡቲ እንዳታኮርፍና

ለውጭ ኃይሎች ቀዳዳ እንዳትከፍት በዚሁ ማስታወቂያ ሚንስቴር ባሣተመው መጽሐፍ ማባባል እንዳለብን እንዲህ ይለናል፡-

“የኤሌክትሪክ አገልግሎት ከኢትዮጵያ በርካሽ ዋጋ ማግኘት ሲችሉ ነው...” ይለናል፡፡ ዛሬ ጅቡቲ በርካሽም ቢሆን ለተጠቀመችበት የመብራት አገልግሎት ምን ያህል እንደምትከፍለን አናውቅም፡፡ እኛ ግን ለወደብ አገልግሎት በቀን በትንሹ ሦስት ሚሊዮን ዶላር እንከፍላለን፡፡

እንግዲህ የኤሌክትሪክ መብራታችን ለጊዜው ዋስ ጠበቃችን ሆኗል፡፡ ግን ደግሞ መብራቱ ድንገት በመብረቅ ወይንም በሌላ ምክንያት ቢቋረጥ የወደብ አገልግሎት ወዲያውኑ እንደሚቋረጥ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

የኢሕአዴግ መንግሥት የኬንያን ወደቦች እንደ አማራጭ ለመጠቀምም ምኞት እንዳለው ቢገልፅም ከዚያም ችግር እንዳለበት አልደበቀም፡፡ “በድንበር አካባቢ በዚህ አሥር ዓመት ውስጥ የከብት ዝርፊያ አለ፡፡ እንዲሁም በሰሜን ኬንያ አነግና መሰሎቹ መጠጊያ የሚያገኙበት አጋጣሚ አለ. . .” በማለት ከኬንያም ጋር አንድ ቀን ግንኙነታችን ሊደፈርስ እንደሚችል ሥጋቱን ይጠቁመናል፡፡ *(እንደላይኛው ገጽ 104)*

ልብ እንበል ወገን፤ ይህን ሁሉ መቅበዝበዝና መባከን ምን አመጣው? አበው እንዲህ አይነቱን መያዣ መጨበጫ ወይንም ውሉ የጠፋ ነገር ሲያጋጥማቸው “ሰዶ ማሳደድ ካማረህ ዶሮህን በቆቅ ለውጥ!” ይላሉ፡፡ ወደብ አስረክቦ ወደብ ፍለጋ ላይ ታች መባከንን ምን አመጣው? ጠይቁ፡፡

የሕወሓት/ኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ባንድ በኩል የወደብን አስፈላጊነትና ጥቅም ይተርኩልናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ቀደም ሲል ከግንጠላው ማግሥት ጀምሮ “ታላቁ መሪያችን!” አቅልለውና አናንቀው “ግመሎቻቸውን ውሃ ያጠጡበት” ነበር ያሉን፡፡ ይህ ግን እውነት ነው? ታዲያ አሠብን ለናት አገር አሥረክቦ ላለፈ መሪ ዛሬ እኛ አፋችንን ሞልተን “የታላቁ መሪያችንን ራእይ እናሳካለን!” እያልን ስንጮህ አናሳፍርም? መናጆነታችንስ አልበዛም? ወደብ አልባ ራእይ ይዘን ነው የምንጓዘው? ጠይቁ፡፡

◇◇◇





# ጎሠኝነት አድሏዊነት ነው

ጎሰኝነት እጅግ የከፋ አድሏዊነት ነው፡፡ ጎሰኝነት ከቻለ ሌሎቹን አጥፍቶ በዚች ምድር ላይ እኔ ብቻ ልኑር የሚል ህመምተኛ ሥርዓት ነው፡፡ ከዚህ ዝቅ ካለ ደግሞ ሌሎቹን አዳክሞና ማንነታቸውን ቀብሮ በሱ ማንነት ሥር ውጦ እያንሜሜ ከንስሳ ባነሠ መልኩ ረግጦ መግዛት ነው፡፡

ጎሣ ከነገድ ቀጥሎ የሚገኝ የማኅበረሰብ ስብስብ ሲሆን በሕዝብ ቁጥር፣ በፖለቲካም ሆነ በኢኮኖሚ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ በመሆኑ የበታችነት ስሜት በእጅጉ ያጠቃዋል፡፡ ጎሰኛ ግለሰቦችም በሌሎች የማኅበረሰብ አባላት ላይ የጥላቻ ሥዕል በአእምሮቸው ውስጥ በመሣል ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ከመበቀል ወደ ኋላ አይሉም፡፡ ለዚህም ነው ዛሬ አገራችን የጎሣ ነቀዝ ዱቄት እያደረጋት ያለው፡፡

ጎሰኝነት ገንግኖ ዘውድ ከመጫኑ የተነሣ እያንዳንዱ ጎሳ ወይንም ብሔረሰብ አገራዊ ራእይ ለቆ ከትንሽ እስከ ትልቅ ሁሉም በመንደር ቷጥሮ ወይንም ትንሽየ ኩሬ ውስጥ እንደ ሚያንቋርሩ እንቁራሪቶች ቁር ቁር ሲሉ ኢትዮጵያን ረሷት፡፡ በመርሳታቸውም ብልጦች አንጡራ ሀብቷን ሲበጠብጡ እነሱ የበይ ተመልካች ሆነው ቋንጣ እንዳየች ድመት አንጋጠው እያዩ ሜው! ሲሉ ያሣዝናሉ፤ ወይንም ያናድዳሉ፡፡

እንደሚታወቀው ሕወሓት አንድን ብሔረሰብ ብቻ ገንጥሎ ሉዓላዊት አገር ለማድረግ ለ17 ዓመታት በፋኖነት የቆየ ድርጅት ነው፡፡ በመሆኑም መግዛት እስከቻለ ድረስ እያምታታና በጎሳ ሽፋን ዜጎችን እስበስ እናከሶ እነሱ ሲፋጠጡ እሱ ግን የሥልጣን ዕድሜውን በማራዘም ከወርቅ ማዕድን ጀምሮ መሬትን ለትውልድ እንዳይተርፍ አድርጎ እንደተራ ሸቀጥ በማይመጥን ዋጋ በጭካኔ እየቸበቸበ ይገኛል፡፡ መግዛት ሲሳነው ደግሞ የትግራይን ሕዝብ የሙጥኝ በማለት “አማራና ኦሮሞ መጡብህ!” እያለ ዳግም ወደ በረሃ እስከ መግባት ድረስ ያልማል፡፡

ጠ/ሚንስትር መለስ ዜናዊ ኤርትራ ዘልቀው ንግግር ባደረጉበት ወቅት “በናንተ ጀርባ ላይ ያለው ቁስል በኔም ጀርባ ላይ አለ” ሲሉ ሠፊና መርዛማ ንግግር አሠምተዋል፡፡ ልብ እንበል፤ አቶ መለስ በናታቸው በኩል ኤርትራዊ ናቸው፡፡ ግን ደግሞ በታሪክ አጋጣሚ የኢትዮጵያ መሪ የመሆን እድል አጋጥሟቸዋል፡፡ ተዋግተው ባስገነጠሏት የናት አገር ሄደው ንግግር ሲያደርጉ

ግን ቂምና በቀልን በሚመሩት ሕዝብ ላይ አርግዘው እየወነጀሉና እያሳጡ ነበር:: "ዘር ከልጓም ይስባል" እንደሚባለው ከኤርትራውያን ጀርባ ላይ ያለው ቁስል በሳቸው ጀርባ እንዳለና እየተበቀሉላቸው መሆናቸውን ቁልጭ አድርጎ የሚያሣይ ነበር:: ለዚህም ነው በግንባር ቀደም በዚህ 21 ዓመታት ውስጥ ባማራ ሕዝብ ላይ መቋጫ የሌለው እንግልትና ወከባ እየተፈፀመበት ያለው::

የሕወሓት ሰዎች እውነትን መድፈር አይሆንላቸውም እንጂ በነሱም ሆነ በሻዕቢያ ጀርባ ላይ ያለው ቁስል በሌሎች ኢትዮጵያውያን ጀርባ ላይምከ አለ:: ጥያቄው ቁስሉ እንዴትና በምን ምክንያት ተፈጠረ? የሚለው ነው::

የሚያሳዝነው ደግሞ ይህ የጀርባ ቁስል ሳይፈርጥ ሌላ የጀርባ እባጭ መፈጠሩ ነው:: የመጀመሪያው እባጭ ወይንም የጀርባ ቁስል ሊፈጠር የቻለው ኤርትራ ሳትገነጠል እንድትኖር ከገንጣዮችና ካስገንጣዮች ጋር ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባደረገው ፍልሚያ ነበር:: ገንጣይና አስገንጣዮች በለስ ቀናቸውና ኤርትራ ተገነጠለች:: ቁስሉ በዚሁ ቢሽር ኖሮ በጎ በሆነ ነበር:: ግን አልሆነም:: ሊሆንም አይችልም:: በመሆኑም ርቀን ሣንሄድ ከ10 ኪሎ ሜትር ለማትሰፋ ባድሜ ያን ያህል ደም ማፍሰስ የጀርባ ቁስል ብቻ ሣይሆን የጭንቅላት ካንሠርም ነው:: ሕወሓት የፈጠረው ስለሆነ ግን ሕጋዊና ተገቢም ነው::

ይህ የከፋ ከፋፋይ የጎሳ ሥርዓት እንዲቀጥልም ያቶ መለስ ቅምጥሎች ዛሬ "የታላቁ መሪያችን ራእይ ከግቡ እናደርሳለን!" እያሉ በጎሳ መጋረጃ ውስጥ ሆነው ማሽሟጠጣቸው ደግሞ አንጀት ያቆስላል::

አቶ መለስ የጎሳ በሽታ የተጣባቸው መሆኑ የሚታወቀው ገና ከማለዳው ሥልጣን ላይ እንደ ወጡ ልክ ባንዲራን "ጨርቅ" እንዳሉ ሁሉ "ያከሱም ሐውልቶች ለወላይታው ምኑ ናቸው? የጎንደር የነገሥታት ግንቦች ለኦሮሞው ምኑ ናቸው? የላሊበላ ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት ለደቡብ ሕዝብ ምኑ ናቸው?" በማለት መናገራቸው ነበር:: እሳቸው እንዲህ ይበሉ እንጂ ኢጣሊያ በወረረችን ጊዜ ካክሱም ነቅላ የወሰደችው ሐውልት ወደ አገሩ ተመልሶ ሲተከል በክብር እንግድነት የተገኙት የወላይታው ተወላጅ የወቅቱ የተወካዮች ም/ቤት አፈ ጉባዔ የተከበሩ አቶ ተሾመ ቶጋ ነበሩ:: ይህስ እንዴት ይታይ ይሆን? ጠይቁ::

አቶ መለስ "ያከሱም ሐውልቶች ለወላይታው ምኑ ናቸው?. . ." ሲሉ ተራና እንደ ቀልድ የተናገሩት አይደለም:: የምራቸውን ነበር:: በረሃ ሳሉ





ይንተከተከባቸው የነበረውን ጥላቻና ትግራይን የመገንጠሉ በሽታ ከአእምሯቸው ውስጥ ያልተፋቀ መሆኑን ማረጋገጫ ነበር:: በሌላ በኩልም የሌሎቹን ኢትዮጵያውያን የባለቤትነት መብት ለመሸርሸርና ለማጥፋት የታለመ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም::

ሌላው ያቶ መለስ ጎሰኛነትና አድሏዊነት ከጢስ ዓባይ ተነትቶ ወደ ትግራይ የተወሰደው የኤሌክትሪክ መሥመር በጋይንት አድርጎ ሲያልፍ ጋይንቶች "እባካችሁን ትንሽ ለኛም ትረፉን" ሲሉ ጥያቄ ያቀርባሉ:: የግፍ ግፍ ጥያቄ ማቅረባቸውም ጥርጣሬን ፈጥሮ በኤሌክትሪክ ገመዱ ላይ አደጋ ሊያደርሱ ይችላሉ በሚል ስጋት በእያንዳንዱ ምሰሶ ስር ሦስት ሦስት አባወራዎች እንዲጠብቁ ይበየንባቸዋል:: እናም በምሽት በዚያ የሚያልፉ መንገደኞች በየምሰሶዎቹ ስር ቁመው ሲያዩዋቸው ገርሟቸው:-

"በምሽት ከግንድ ሥር ቁማችሁ ምን እየጠበቃችሁ ነው?" ብለው ሲጠይቋቸው:-

"የሕወሓት መኳንንት ራታቸውን ሲበሉ ቁመን መብራት እያበራን ነው!" አሉ:: ይህ አባባል እንደ ቀልድ የተነገረ ይምሰል እንጂ የምሬትና የቁርሾ መሆኑ ግን የሚካድ አይደለም:: ወይንም በሌላ ምክንያት ማስተባበል አይቻልም::

በሌላ ጊዜ በሌላ ጉዳይ ስለ ኤሌክትሪክ መብራት ለጠ/ሚንስትሩ ጥያቄ ሲቀርብላቸው "ይህ የጋይንት ሕዝብ ጥያቄ ነው" ሲሉ በቁጣ ነበር የመለሱት:: ይህ አባባላቸውም የሚያመለክተን ምን ያህል በከፋት እያኙ ይዘውት የቆዩ መሆናቸውን ነው::

ይህ በእንዲህ እንዳለ የባድሜ ጦርነት ይከሰታል:: የጋይንት ወጣቶች ለውትድርና ሲሆን ይፈለጉና ወታደር ካልሆናችሁ ተብለው መግቢያ መውጫ ያጣሉ:: በዚህ ወቅት ወላጆች "እባካችሁን እንደ መብራቱ ውትድርናውንም ዝለሉን" አሉ ይባላል::

ሌላው ሣይጠቀስ መታለፍ የሌለበት፤ ኢጣሊያ ባምስቱ ዓመት የግፍ ወረራ ለፈፀመችው የጦር ካሣ እንድትከስ ተበይኖባት የቆቃን ግድብ ሠርታ ከሳለች:: የኢትዮጵያ ሕዝብ በብዛት የሚያውቀው ሌላ የጦር ካሣም ከሣ ነበር:: እንደሚታወቀው ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኤርትራን ጨምሮ በ1933 ዓ.ም ነፃ ሲወጡ የጎንደር ሕዝብ ግን ነፃ የወጣው ካንድ ዓመት በኋላ 1934 ዓ.ም ነበር:: የዚህን ምክንያት "ጎንደር ያነዬ" በሚል ርእስ (ገና

ያልታተመ) የጻፍኩት ስለሆነ ከዚህ ላይ የማነሣው ነገር የለም፡፡ የሆነ ሆኖ ኢጣሊያ ለጎንደር ሕዝብ ስንት ሜጋ ዋት )እንደሚያመነጭ አላውቅም እንጂ አንድ ግዙፍ ጀኔሬተር ከሳ ነበር፡፡ ይህንን ጄኔሬተር ጎንደሮች በደም ባጥንታቸው ያገኙትን ወይንም የደማቸው ካሣ የሆነውን "ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሠብራል!" እንዲሉ ጀግናው ሕወሓት በሌሊት ነቅሎ ወስዶ ትግራይ ውስጥ ተክሎታል፡፡ ይህንን እብሪትና ክፋትስ በምን ቃል መግለፅ ይቻላል? ግፉና በደሉ ወይንም የጎሰኝነት አድሏዊነቱ በዚህም አያበቃም፡፡

ተከዜን የሚያህል ዓለም ዓቀፍ ወንዝ ወሰን ሆኖ እያለ ሴቲቱ ሁመራን፣ ወልቃይት ጠገዴን፣ ማይፀምሬን ወደ ትግራይ ክልል ከልለዋቸዋል፡፡ ይህንን በተመለከተ እውቁ አቀንቃኝ ፋሲል ደመወዝ፡-

*"ሴቲቱን ወሰዱት ያውም የኛን እጣ*
*እነሱ ምን ያርጉ ከኛ ሰው ሲታጣ!"*

ብሎ ቁጭቱን በመግለጹ ቀጠቀጡት፡፡ ከሞት ቢተርፍም ዳግም ወደ ሚወደው የኪነት ሙያ እስካሁን አልተመለሰም፡፡ ይህንንስ በምን ቋንቋ መግለፅ ይቻላል? ጠይቁ፡፡

እነዚህ ሠፋፊ ወረዳዎች በየትኛው ዘመን፣ በየትኛው ንጉሥ ጊዜ የትግራይ የግዛት ክልል ሆነው እንደነበርና ጎንደሮች ከፍ ሲልም አማራዎች ከትግራይ ሕዝብ ጋር ተፋልመው ተነጥቀው ወደ ጎንደር ተከልለው ስለመቆየታቸው የሚጠቁም የታሪክ ማስረጃ የለም፡፡ ይህ አድሏይነትና ጎሰኝነትም ሁለቱን እህትማማች ሕዝቦች በመልካም ጉርብትና እንዳይኖሩ የከፋ ቁርሾ ለመትከል ነው፡፡

የሕወሓት ፋኖዎች የጎንደርን ለም መሬት (ሰሊጥ፣ ጥጥ፣ ማሽላና የሙጫ ዛፍ) አብቃይ የሆኑ ወረዳዎችን በጊዜ አጋጣሚ ነጥቀዋል፡፡ ሌላ ዳኛና የታሪክ ምስክር አያስፈልግም፡፡ የተከዜ ወንዝ ራሱ የተፈጥሮ ምስክር ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ለጊዜው የሚባል ነገር የለም፡፡ ይኸ ሁሉ ግፍ እየተፈፀመ ያለውም "በታላቁ መሪያችን" ዘመን ነው፡፡





# ባማራ ሕዝብ ላይ በቀልተኛው ሕወሓት

የሕወሓት መሪዎችና ካድሬዎች ወንድማማች የሆነውን ያማራንና የትግራይን ሕዝብ ለምን ዘለዓለሙን በባላንጣነት በማፋጠጥ ሲያደሙት ለመኖር ታጥቀው እንደተነሱ መነሻ ምክንያታቸው ከነሱ በስተቀር ማንም ሊያውቅ አይችልም፡፡ እንደኔ የጥላቻ መነሻ ምክንያታቸው ግራ የገባው ክብሮም ብርሃነ (ከመቀሌ) እንዲህ ይለናል፡-

"ሁሌ የሚያሳስበኝ አንድ ነገር አለ፡፡ ይኸውም የሕወሓት ካድሬዎች ያማራ ሕዝብን ‹በነፍጠኝነት ስም› መወንጀል የዘር ፕሮፓጋንዳ በየቀበሌው ሲያወርዱበት እንደሚውሉ የብአዴን አባል ነን ባዮች አያውቁ ይሆን?" ሲል በመገረም ከጠየቁ በኋላ ግርምቱን በመቀጠል "ያማራ ሕዝብ እንደ ሕዝብ በየትኛውም ጊዜ ከማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ጋር ተባብሮ የሀገሩን ክብርና ዳርድንበር እንዲሁም ታሪክ ሲጠብቅ የኖረ እንጂ ፀረ-የትግራይ ሕዝብ ሆኖ አያውቅም፡፡ አለ ከተባለም በተጨባጭ ጊዜውንና ቦታውን ለይተው እስከነ ጥፋቱ መጠን ለትግራይ ሕዝብ ሊነግሩት ይገባል. . ." ይላል፡፡ *(ፍኖተ ነፃነት ቅፅ 2 ቁጥር 54 ማክሰኞ ነሐሴ 1 ቀን 2004 ዓ.ም)*

ክብሮም ብርሃነ እውነቱን ነው፡፡ ያማራ ሕዝብ የትግራይን ሕዝብ መቸና እንዴት? በነማን ዘመንስ ዘምቶ ዘርፎትና አቃጥሎት ይሆን? አፄ ምኒልክ በ1888 ዓ.ም አድዋ ተራሮች እስከነ ባለቤታቸው የዘመቱት ጣሊያንን ለማባረር ሣይሆን የትግራይን ሕዝብ ለመውረርና ለመዝረፍ ከሆነ ወይንም ከጣሊያን ጎን ተሰልፈው ወግተውት ከሆነም በግልፅ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይንገሩት፡፡ የትግራይ ሕዝብም በግልፅ እስከነ ምክንያቱና ጥፋቱ ይነገረውና አውቆት ወንድሙ የሆነውን ያማራ ሕዝብ በግልፅ ይውቀስበት፡፡ ያማራ ሕዝብም ሌውነት በትግራይ ሕዝብ ላይ አባቶቹ አሁን የሕወሓት ካድሬዎችና ታጣቂዎች ባማራ ሕዝብ ላይ እንደሚፈፅሙበት ያለ ግፍ ፈፅመውበት ከሆነ "ያባት ዕዳ ለልጅ ይተርፋልና" በግልፅ ወንድም የሆነውን የትግራይን ሕዝብ ይቅርታ ይጠይቅበት፡፡ ከይቅርታ የበለጠ ደግሞ ያበጠ ቁስልን የሚያፈርጥ የለም፡፡ አለበለዚያ በደፈናው ለሥልጣንና ያገርን ሀብት ለመዝረፍ ሲባል ያማራን ሕዝብ በተገኘ አጋጣሚ ሁሉ በጅምላ በትር ባል ያዘበት ዘመን "ነፍጠኛ!" እያሉ መዝለፍና በሌሎች ኢትዮጵያውያን እንዲጠላና እንዲፈራ መቀስቀስ የኋላ ኋላ መዘዙ ላገር አንድነት አይበጅም፡፡ ለትውልድ ጥበብን እንጂ የከፋትን ሥንቅ ቋጥሮ ማቆየት ከፉ የደም በሽታ ይመስለኛል፡፡ ነግ በኔ

ነውና ይህ የሕወሓት እኩይ ተግባር ሊገታና ሊቆም ይገባዋል፡፡ በዚህ ሁኔታስ አይጥና ድመት ተሁኖ እንዴት እንደ አንድ ሕዝብ አብሮ ተከባብሮ መኖር ይቻላል? ጠይቁ፡፡ በተረፈ የብአዴንን አመራሮች በተመለከተ በያጋጣሚው እነማን እንደሆኑ የተገለፀ ስለሆነና ሕዝቡም በሚገባ ስለሚያውቃቸው ከዚህ ላይ ስማቸውን እነከሌ እነ ከሌ እያሉ መዘርዘሩ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ ባጭሩ ግን አማርኛ ተናጋሪዎች የኤርትራና የትግራይ ልጆች ሆነው የጎንደር ሕዝብ ወይንም ሌላው ያማራ ሕዝብ አቅፎ ደግፎ፣ በጉያው ይዞ ኮትኩቶ ያሣደጋቸው ናቸው፡፡ "የናት ጡት ነካሽ!" ሆነው ዛሬ እየቀሰፉበት ያሉት፡፡ ታሪክ ይፍረደው፡፡



ክብሮም ብርሃን

የትግራይና ያማራ ሕዝቦች ከጥንት ጀምረው ኢትዮጵያ እንደ አገር ሥትመሠረት ከዳማት መንግሥት ጀምሮ አክሱም፣ ላሊበላ፣ ሸዋ፣ ጎንደር የነገሥታቱ በተለያዩ ጊዜያትና ዘመናት መቀመጫዎች ነበሩ፡፡ እንዲህ ሲኮንም የተጠቀሱት ሕዝቦች ብቻ ሣይሆኑ ሌሎቹም ሕዝቦች አብረው ኑረዋል፡፡ አብረው በመኖራቸውም ተጋብተዋል፤ ተዋልደዋል፤ የባህልና የቋንቋ መዳቀልንም ፈጥረዋል፡፡ በነዚህ ሂደቶችም ያማራና የትግራይ ሕዝቦች ማዕከል ወይንም ያንድነት ርሾ ስለመሆናቸው በየታሪኩ ተጠቅሶ






ይገኛል፡፡ ይህ ከሆነ ታዲያ ሕወሓት በትግራይ ሕዝብ ስም ባማራ ሕዝብ ላይ የሚያዘንበው የከፋት ፕሮፓጋንዳና የዘር ማፅዳት ዘመቻ ከምን የመነጨ ነው? ይህንን ጥያቄ ያማራ ሕዝብ ብቻ ሣይሆን የትግራይ ሕዝብም ሆነ ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብም ይህንን ሀቅ ጠይቆ እውነቱን ሊጨብጥ ይገባዋል፡፡ ሕወሓት እንደ ሌጣ ፈረስ ሊጋልበን አይገባም፡፡ ከእውነት የበለጠ ቁስልን የሚያሽር ነገር የለምና እያንዳንዱ ዜጋ ከከፋትና ከግል ጥቅመኝነት ተላቆ እውነት የመፈለጊያው ጊዜ አሁን ነው፡፡ በምንም መመዘኛ "በታላቁ መሪያችን ሞት!" እየተባልን ልንደለልና እንደ ሕፃን ልጅ በከረሜላ ልንታለል አይገባንም፡፡

ያማራና የትግራይ ሕዝቦች ከፉ በጎን በጉርብትና እኩል ተካፍለዋል፡፡ ከቋንቋ በስተቀር የሚለያያቸው የለም፡፡ ቋንቋንም ቢሆን ራቅ ያሉት የጎጃም፣ የደቡብ ወሎና የሸዋ አማራዎች ካልሆኑ በስተቀር የጎንደር አማራዎች ትግሬኛንም እኩል ካማርኛ ጋር ይናገሩታል፡፡ ዛሬ ጊዜ አገኘን ተብሎ ተከዜን ተሻግረው መሬት እስከ መከለል የተደረሰውም የጎንደር አማራዎች ትግሬኛ ቋንቋን በመናገራቸው ነው፡፡ ያንዱን ቋንቋ በጉርበትና፣ አብሮ በመኖር ወይንም በሌላ አጋጣሚ መናገርም በበጎ መልኩ ሊታይ ሲገባው መሬትንም የሚያስነጥቅ ከሆነ መጥፎ ሥንቅ ነው፡፡ ልብ እንበል፤ ቋንቋ ወሰን ከሆነ ያማሮች አገር ሠፊ ሊሆን ነው፡፡ የኛን ምሳሌ እንተወውና ቋንቋ ያንዲት አገር የደም፣ የሥጋና ያጥንት ወይንም የጎሳ ወሰን ከሆነ እንግሊዝ ቅኝ የገዛቻቸው አገሮች ሁሉ ማለትም እንግሊዘኛ ቋንቋ ተናጋሪ ያፍሪካ አገሮች የእንግሊዝ አካሎች ሊሆኑ ነው ማለት ነው፡፡ ይህ የቋንቋ ወሰን መዘዙ ብዙ ነው፡፡ልብ እንበል፤ ሕወሓት ተከዜን ተሻግሮ የጎንደሮችን መሬት ወደ ትግራይ መከለሉ ትልቅ የከፋት ሥንቅ ነው ለሁለቱም ሕዝቦች ያስቀመጠው፡፡

ጥንት በማልዱ መሣፍንቱ በሥልጣን ሽኩቻ ምክንያት የስበስ ጦርነት ቢያካሂዱም ከጦርነቱ ፍፃሜ በኋላ ቁርሾና በቀል የሚባል ነገር አልነበረም፡፡ አሸናፊው አገር ያስተዳድራል፤ ተሸናፊው አቅሙን አውቆ ይገብራል፡፡ ከዚህ ውጭ ለሕዝቦች የሚቆይ የከፋት ሥንቅ አልነበረም፡፡ ጦርነቶቹም ይካሄዱ የነበሩት በገዥ መደቦች መሀከል በሥልጣን ይገባኛል ምክንያቶች እንጂ አንድ ሕዝብ በራሱ አነሳሽነት ሌላውን ሕዝብ የወረረበት ጊዜ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ተከስቶ አይታወቅም፡፡ የገዥ መደቦችን ተከትሎ ግን የዚህ ጎሳ የዚያ ብሔረሰብ ሳይባል አብሮ እየዘመተ መውረሩና ጥፋት ማጥፋቱ እውነት ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ፍልሚያ ባህላችንም ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ይህም ሆኖ ያማራ ሕዝብ የትግራይን ሕዝብ የቁን የገዥ መደብ ወይንም ንጉሥ ተከትሎ



ክብሮም ብርሃን

ሄዶ ወይንም በራሱ አነሳሽነት እንደ ዘረፈውና እንዳቃጠለው ወይንም እንደ ጨፈጨፈው በታሪክ የሚታወቅ ነገር የለም:: ይህ ከሆነ ታዲያ ይህ ሥር የሰደደ ጥላቻና የደም ካንሠር የሆነ የጎሳ በሽታ ከየት መጣ? የሕወሓትን አመራሮች እንዴት ተጣባቸው? ይህንን የጠላትነት በቀልስ ከየት አመጡት? ብሎ አጠንክሮ መጠየቅ ተገቢ ነው::

ብዙ አዛውንቶች እንደሚሉትና እንደ ሚስማሙበት ከሆነ ይህ ሥር የሰደደ ጥላቻና ያመረቀዘ ከፋት ምንጮቹ ዐረቦቹና ቅኝ ገዥዎች ለመሆናቸው ምንም ጥርጥር የለውም:: የዚህ የጥላቻ ቫይረስ ተሸካሚ ደግሞ ሻዕቢያ መሆኑ አይካድም:: ተደጋግሞ እንደተገለፀውና እንደሚታወቀውም አብዛኞቹ የሕወሓት አመራሮች ጠ/ሚንስትሩን ጨምሮ አንዳንዶቹ ሙሉ በሙሉ አንዳንዶቹ ደግሞ በከፊል ከሻዕቢያ ጋር የደም አንድነት አላቸው:: ከዚህም ባሻገር አሠልጥኖ ባምሳሉ የቀረፃቸው ሻዕቢያ ነው:: የዚህን እውነትነት ለማወቅ በሦስት ከፍሎ ማረጋገጥ ይቻላል::

## ያድዋ ድል

እንደሚታወቀው ያድዋ ድል ነጮቹን (ቅኝ ገዥዎችን) ባላንጣ ገዝቶልናል:: ለምን? ቢባል ዓድዋ በቅኝ ግዛት ሥር ይማቅቁ ለነበሩትን ሁሉ ዐይኖቻቸውን የከፈተ ነበር:: በተለይም አፍሪካውያን የራሳቸው ድል አድርገው በመቁጠር ይኮሩባታል፤ ይመኩባታል:: በመሆኑም ካድዋ ድል ማግሥት ጀምሮ በቅኝ ገዥዎች ሥር ይገዙ የነበሩ አገሮች ሁሉ አመፁ::

ባንፃሩ የኢጣሊያ ሽንፈት የእንግሊዝም፣ የፈረንሣይም (የቅኝ ገዥዎች) ሽንፈት ተደርጎ ተወሰደ:: አፍሪካውያን በድሉ እንደኮሩ ሁሉ ቅኝ ገዥዎች ደግሞ በሽንፈቱ አፈሩ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የቅኝ ገዢዎች የቤት ሥራ እስበሱ እንዲናከስ ሴራ መቀየስ ሆነ:: የዚህ ሰለባ ደግሞ በግንባር ቀደም ከንፋ መመታት ያለበት አማራ ሆነ:: ለዚህም ነው በነዚህ 21 ዓመታት ውስጥ ያድዋ የድል ቀን ሲታሰብ ወይንም ሲከበር የምኒልክ ስም የማይጠቀሰው:: ይህ ከበቂ በላይ ማረጋገጫ ነው:: ዝርዝሩ ሠፊ ነው:: በመጠኑም ቢሆን ባፄ ምኒልክ አጭር ታሪክ ውስጥ ያሠፈርኩት ስለሆነ ከዚህ ላይ በጥልቀት አልገባም:: ለማመልከት የፈለኩት ያድዋ ድልም ላንድነታችንም፣ እስበሳችንም ለመናከስ የበኩሉን አስተዋፅኦ ማድረጉን ጠቆም አድርጌ ለማለፍና ያድዋ ዘመቻ አዝማቹ አፄ ምኒልክ በመሆናቸው ብቻ አማራን በቅኝ ገዥዎች ጥርስ ውስጥ ገብቶ እስካሁን እየታኘከ ያለመሆኑን ለማመልከት ነው::





## ክርስትና ሃይማኖት

ሌላው ኢትዮጵያን ሰለባ ያደረጋት "የክርስቲያን ደሴት" የሚለው ደረቅ የቆየ ምስል ነው:: ይህ መፈክር ግን ከሙስሊም ወንድሞቻችን ጋር ተቻችለንና ተፋቅረን፣ አንድ ሆነን ለመኖር እንቅፋት አልፈጠረብንም:: እንዲያውም በሚያስደንቅ ሁኔታ ተጋብተውና ተዋልደው ያንዱን እምነት ሌላው ወዶ ተቀብሎ ወይንም ሚስት ሙስሊም ባል ክርስቲያን ወይንም ደግሞ ባል ሙስሊም ሚስት ክርስቲያን ሆነው የሚኖሩባት አገር ብትኖር ኢትዮጵያ ብቻ ነች:: ለዚህ ሀቅ ወሎ፣ ሐረርንና ድሬዳዋን መጥቀስ ይቻላል:: እነዚህ ከሌሎች ሃይማኖት አጥሯቸው አያውቅም::

ኢትዮጵያ ምንም እንኳን በዚያን ዘመን "የክርስቲያን ደሴት" ተብላ ብትጠቀስም ከፍ ብዬ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ክርስቲያንና ሙስሊም ልጆቿን አቻችላና አስማምታ የኖረች አገር ስለመሆኗ ለ40 ዓመታት ያህል ኢትዮጵያ ውስጥ የኖሩት ጆን ሐዘወይ ስፔንሰር ሳይቀረውላታል:: *"ኢትዮጵያ የእስልምናን ወረራ ስትከላከል የቆየች አገር ብትሆንም ሙስሊም ሕዝቧን አቅፋ ለመኖር ችላለች. . ."* ሲሉ አድናቆታቸውን ገልፀዋል:: *(ጥርስ የገባች አገር ገጽ 179)* ምሁሩ *"የእስልምናን ወረራ ስትከላከል የቆየች"* ያሉት የቱርኮችን፣ የግብፆችንና የድርቡሾችን ተደጋጋሚ ወረራዎችን ማለታቸው ነው::

እንግዲህ ለኢትዮጵያ መገዝገዝ አንዱና ዋናው ክርስትና ሃይማኖት ነው ስንል የጥንት ነገሥታት በሚዘምቱበት ዐውደ ውጊያ ሁሉ የሚያፈቅሩትንና ለድል ያበቃኛል የሚሉትን ታቦት ይዘው ይዘምቱ እንደነበር ይታወቃል:: በመጀመሪያም የከተት አዋጅ ሲያውጁ "አገርህ ተደፈረች! ሃይማኖትክን የሚያረክስ ጠላት መጣብህ!" በማለት ነበር:: ለምሳሌ አፄ ምኒልክ አድዋ ሲዘምቱ ጊዮርጊስን ይዘው ነበር የዘመቱት ይባላል:: እናም እነ ባልቻ አባ ነፍሶ በጥቁር ፈረስ ከጠላት ምሽግ ድረስ እየጋለቡ በነፋስ ፍጥነት ከወዲያ ወዲህ እየተዋነኑ ሲያርበደብዱት የፋሽሽት ጦር መመከት ሲሳነው "እኛን ያጠቁን በጥርኝ ፈረስ የሚዋጉት ናቸው:: በተለይ አንዱ ጊዮርጊስ ሣይሆን አይቀርም!" ማለታቸው በስነ ቃል ከጊዜችን ድረስ ዘልቋል::

ዐረቦቹ በተለይም ግብፆች "የክርስቲያን ደሴት" የሚለው አባባል ሲመራቸውና ሲጎፈንናቸው የኖረ ለመሆኑ ተደጋጋሚ ወረራዎችን ያለምንም የመሬት የይገባኛል ጥያቄ ሳይኖራቸው ሙከራ አድርገዋል:: የዚህ ምስጢሩ የሃይማኖት መስፋፋትም ሊባል ይቻላል:: ዞሮ ዞሮ ግን የኦርቶዶክስ

ሃይማኖትን ለመገዝገዝ ነጮቹም ከጥቅማቸው አንፃር ተጨመሩበትና ኢትዮጵያን ለመበታተንና ለማዳከም አንዱን ብሔረሰብ ከሌላው ወይንም አንዱን ወገን ገዥ ሌላውን ወገን የተገዥ ወገን አድርገው በመሣል እስበሱ አስተናንቆ ማፋለምና ወደ ድህነት አረንቋ ውስጥ እንድንዘፈቅ አማራጭ ያልተገኘለት ምርጫ ሆነ:: ይህ ዘዴ ሲመረጥም ኦርቶዶክስ ሃይማኖትን ከተቻለ ማጥፋት ካልተቻለ በሌሎች የተለያዩ ሃይማኖቶች እንዲዋጥ ማድረግ ነው::

ይህ ቀመር ሲነደፍም የዚህ ሃይማኖት ቀንደኛ አማኝና ተከታይ ተደርጎ የተወሰደው ያማራ ዜጋ ነው:: ኦርቶዶክስን ማጥፋት ወይንም ማዳከም የሚቻለው በመጀመሪያ የእምነቱ ተከታይ የሆነው አማራ ሲመታ ነው በሚል ይመስላል በነዚህ 21 ዓመታት ውስጥ እጅግ በሚዘገንን ሁኔታ የመስቀልና የጥምቀት ዋዜማዎች እየተጠበቁ ታርደዋል:: በጅማ፣ ባርካ፣ ባሰቦት፣ የዋልድባ ገዳም ሣይቀር ወደ ስኳር ኢንዱስትሪነት እንዲቀየር የተበየነበት የዚህ ሃይማኖቱን የመገዝገዝ ቀመር ነው:: ይህ ሁሉ ጥፋት ባማኞቹ ላይና በገደማቱ ሲፈፀም የእምነቱ አባቶች ድምፃቸውን ሲያሰሙ አልተሰሙም:: ርግጥ ነው አንዳንድ ቢኖሩም ወይ ተሰደዋል ወይ ተገለዋል:: ዛሬ በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ በሁለት ሲኖዶስ የምትታወቅ ሀገር ብትኖር ኢትዮጵያ ብቻ ነች::

ሌላው ሴራ ከሙስሊም ወገኖቻችን ጋር ለማዳማትና እስከ መጨረሻው ድረስ ለማቆራረጥ የኢሕአዴግ ሹሞች ሲፈፅሙ ቆይተዋል:: ከቤተክርስቲያን አጠገብ መስጊድ እንዲሠራ ወይንም ካልጠፋ ቦታ ጥምቀተ ባህር የሚከበርባቸው ቦታዎች ለመስጊድ መሥሪያ እየተፈቀዱ ቦታና ጊዜ እየተመረጠ መጠነ ሠፊ ደም ፈሷል:: እነዚህን ሁሉ የሚቆሰቁሷቸው የዘመኑ ካድሬዎች ናቸው::

ይህንን እኩይ ተግባር ለመሞገት ወጣቱ ትውልድ ሰንፏል:: ወይንም አገራዊ ደባውን በቅጡ የተገነዘበው አይመስልም:: በምእራባውያን የኳስ ፍቅር ናላው ዞሯል:: በዘፈኑ፣ በዳንኪራው እየማለለ ሳይዋጋ የባእዳን ወይንም የውጭ ምርኮኛ ሆኗል:: ላባቱ ገዳይ እናቱን የሚድር ልጅ እየተወለደ ነው:: ያሣዝናል::

## ዓባይ ሦስተኛው ጠላት የገዛልን

በሦስተኛ ደረጃ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለዚች አገር ጠላት የገዛላት ዓባይ ወንዝ ነው:: ለምን? እንዴት? የሚሉ ጥያቄዎች እንደማይነሱ





ተስፋ አደርጋለሁ:: ባጭሩ ግን ዓባይ ለግብፆች ሕይወትና እስትንፋስ በመሆኑ ኢትዮጵያውያን አንድ ሆነው ተረጋግተው ከሠሩ የጥበብ ባለቤት ለመሆን የሚሣናቸው ነገር አይኖርም በሚል ምንጊዜም እንቅልፍ የማያስወስድ ፍርሃት አላቸው::

ኢትዮጵያውያን የጥበብ ባለቤት ሆነው ዓባይን ከመገደብ ጀምረው እስከ ማትነን ድረስ ቢራመዱ የኛ ሕልውና አከተመ ብለው ግብፃውያን ያምናሉ:: እናም ይህ ከመሆኑ በፊት ኢትዮጵያውያንን እስበሳቸው አስተናንቆ ማመስና ሰላማቸውን ማሣጣት ከተቻለ አይደለም የጥበብ ባለቤት መሆን ሠርተው የእለት እንጀራ ማግኘት ከማይችሉበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ ብለው አመኑ:: ለዚህም ነበር ኤርትራ ከናት አገሯ እንድትገነጠል ሁለንተናዊ ድጋፍ በመሥጠት የእህት ባላንጣ ከጉያችን በመፍጠር እኛኑ በኛው ያዳሙን:: ሕወሓት የዚህ ሴራ ውጤት ነው:: አገር ተዋግቶ አስገንጥሏል፤ የባሕር በር አሣጥቷል፤ እድገታችንን አኮስምኗል፤ ቀሪዎቹን የሀገሪቱን ብሔር ብሔረሰቦችና ጎሣዎች አንዱን ከሌላው በማናከስ የቀልን ዘር እየዘራ ይገኛል:: በዚህ ሁኔታ እስበሱ የተናከሰ ሕዝብ አንድ ሆኖ ተግቶ ሠርቶ ከድህነት አረንቋ ይወጣል (ይላቀቃል) ተብሎ አይታሰብም::

በመጀመሪያ መቅደም የነበረበት በሕዝቦች መሀከል ሰላም መፍጠር ነበር:: ሰላም ካለ ፍቅርና የሕዝቦች መተሳሰብ ይኖራል:: መተሳሰብ ካለ ደግሞ ሥራ ይፈጠራል:: ከተሠራ ደግሞ ብልጽግና ይኖራል:: ብልጽግና ካለ ደግሞ ጥበብ ይኖራል::

አፄ ቴዎድሮስ ደብረታቦር አጠገብ ጋፋት ላይ የጦር መሣሪያ ኢንዱስትሪ አቋቁመው ነበር:: ከሳቸው ውድቀት በኋላ ግን መክኖ ቀረ:: ቀጣዩ ንጉሥ አፄ ዮሐንስ አርማቸውን ለማንሣት አልፈቀዱም:: ምናልባት ከእንግሊዞች ጋር ልቃቃር እችላለሁ ብለው ሠግተውም ይሆናል:: ወይንም መርህቸው ሃይማኖቱ ስለነበር የጦር መሣሪያ ኢንዱስትሪው ጉዳይ አልተከሠተላቸውም ይሆናል:: ወይንም ደግሞ ያፄ ቴዎድሮስ ውጥን በመሆኑ ጠልተውት ይሆናል:: አሁን በዘመናችን እንኳን ደርግ የጋፋትን የጦር መሣሪያ ኢንዱስትሪ በማቋቋም ቀላል የጦር መሣሪያዎችን (ከላንሽኮብ፣ ማካሮብ ሽጉጥ. . .) ማምረት ጀምሮ ነበር:: ደርግ በቀመሩ መሠረት በወያኔ ባፍጢሙ ሲደፋ ጋፋት ኢንጂነሪንግም አብሮ ተደፋ:: አሜሪካኖች በሕወሓት በጎ ፈቃድ ፈንጂ አምካኝ ጥበበኞቻቸውን ልከው ጓዳ ጎድጓዳችን ሁሉ ፈትሸውና አምክነው ሄደዋል::

ይህ ሁሉ ሲሆን ግንባር ቀደሙና ቀንደኛ ጠላት ተብሎ ተፈርጆ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የሚዋከበውና የሚመታው አማራ ነው:: ይህ ሲባል ግን በሲዳማ፣ በጋምቤላ፣ በኦሮሚያ፣ በነገሌ ቦረና፣ በሶማሌ ክልል ግጭቶች አልነበሩም፣ ደም አልፈሰሰም ማለት አይደለም:: መጠኑ ይለያይ እንጂ ደም እንደ ጅረት ፈሷል:: ሁሉም ተቋስሏል:: በዚህ ሁኔታ እስበሳችን ተናክሰን አምራቹ ኃይል ወጣቱ ክፍል በምሬት አገሩን እየጣለ እየተሠደደ እንዴት ብለን ነው ከድህነት የምንላቀቀው? እስበሱ በጎሣ ጥላቻ የተናከሠ ሕዝብስ እንዴት ብሎ ነው አገራዊ ራእይ አንግቦ ተባብሮ ሠርቶ እንጀራ በልቶ የሚያድረው? ሌላው ቀርቶ ካንዱ ክልል ወደ ሌላው ክልል ተሂዶ በቀን ሠራተኛነት እንኳን ተቀጥሮ የማይሠራባትን አገር ምን ብሎ መግለጽ ይቻላል?

በመሠረቱ አማራ ራሱን እስካልተከላከለ ድረስ የመከራው ዘመን አያባራለትም:: የሕወሓት ሰዎች ዜጋችን ነው ብለው እንደማይተውትና እንደማይተኙለት ቀጥየ ከማቀርባቸው መረጃዎች መረዳት ይቻላል::





# የሕወሓት ሰዎች ምን እየቀበሩ ነው?

"መጥነው የጎረሱት አያንቅም!" ያበው አባባል:: አበው ይህነኑ አባባል በሌላ አቀራረብም እንዲህ ይገልፁታል "እፍ የሚጎርሰውን እጅ ይመጥነዋል!" ከዚህ ቁም ነገር ስንነሳ የሕወሓት ሰዎች የሚናገሩትንና የሚሠሩትን የሚመጥኑ አይደሉም:: አንድም በጀብደኝነት አልያም በበቀልተኝነት እንዳገኙ መቀርደድ ነው:: መንግሥት ሆነው እንኳን የሽፍታ ተግባር ሲፈፀሙ ትንሽ አይሰቀጥጣቸውም:: መንግሥት ማለት ትልቅ ሀገራዊ ኃላፊነትና ሚዛናዊ ዳኝነት የሚሠጥበት ተቋም መሆኑን በቅጡ የተገነዘቡት አይመስሉም:: አንድ የመንግሥት አካል በዜጎቹ ላይ በቀለኛ ከሆነ በማን ሊዳኝ ነው? ማንንስ ሊዳኝ ነው? ይህንን ጠይቁ:: ምኒልክን የወቀሰ ፋኖ እሱ ራሱ መልሶ የሚበጫጭቅ አውሬ ሲሆን ምን ትታዘባላችሁ?

## ፍኖተ ገድል ወይንስ ፍኖተ ገደል?

አማራ የዘመኑ ታዳኝ አውሬ ለመሆኑ የተጋዳላይ ብሥራት አማረ ሥራ በቂ ማረጋገጫ ነው:: የመጽሐፉ ርእስ "ፍኖተ ገድል" ሲሆን ፍኖት ማለት መንገድ ማለት ነው:: የገድል መንገድ ለማለት ነው:: ለኔ ግን "የገደል መንገድ ነው" ከማንም ጋር የማያኗኑር፣ የማያቃብር በጥላቻ ተመርዞ ጥላቻን የረጨ ሥራ ነው:: ለማንኛውም ሥራውን እነሆ:-

*"ከቴዎድሮስና ከዮሐንስ ይልቅ የምኒልክ ወደ ሥልጣን መምጣት ኢትዮጵያን አሁንም ድረስ የገጠሟትን ሰፊና ውስብስብ ፖለቲካዊ ማህበራዊና ጎሳዊ ችግሮች ያስከተለ ከስተት ነበር . . ." ይለናል (ብሥራት አማረ ፍኖተ ገድል ገጽ 26)*

ብሥራት አማራ ይቀጥልና አማራን ከደቡብ ሕዝብ ጋር ለማናከስ መርዝ ሲዘራ እንዲህ ይላል *"ሌሎች ሕዝቦችን በተለይ የደቡብ ሕዝቦችን፣ ዝቅተኛ፣ ያልሠለጠኑ፣ ምኛምኞች፣ የንብረት ባለቤትንትና የመብቶች እኩልነት የማይገባቸው፣ የዱር አራዊት አድርገው ቆጠሯቸው"* (ሥርዝ የራሴ) *ይለንና አያይዞ ". . .በኦርቶዶክስና ባከሱማዊነት ስም በንፁህ ሕዝቦች ላይ. . . ወራዳና ከፉ ተግባር. . . ከሰሜን ኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋርም* (ከትግሬዎች

*ለማለት ነው) በደቡብ ካደረጉት የማይተናነስ ደም አፋሳሽ ግጭት ደርሷል..." ይለናል:: (እንደ ላይኛው ገጽ 27)*

አፄ ምኒልክ በ1888 ዓ.ም "ከተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት!" ብለው አድዋ ተራሮች እስከነ ባለቤታቸው ዘልቀው ከኢጣሊያን ወራሪዎች ጋር ከመተናነቃቸው በስተቀር የትግራይን ሕዝብ የወረሩበትን ጊዜ በታሪክ አላውቅም:: ምሁራን አንድ በሉ:: ተጋዳላይ ብሥራት ግን "ከሰሜን ኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋርም. . . ደም አፋሳሽ ግጭት ደርሷል" ይለናል:: ተጋዳላይ ብሥራት ይቀጥልና:-

*"ለብቻ ለመነጠል የመረጡት ገዥዎች በመጨረሻ ያማራዊነት ፍልስፍና ለጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አጠናክረው ቀጠሉበት:: ብሔር ብሔረሰቦች በግዴታ አማራ ለማድረግ የተከተሉት ጎሣዊ ልዩነት . . . ባንድነትና በመብት እኩልነቶች ላይ ቅራኔ እንዲያመነጭ ምክንያት ሆኗል . . ." ይለንና ምሳሌ ሲያቀርብልን:-*

*"በወንጀል ሥራዎች የተነሳ ያከሱም ሕዝብ ያባረረውና ከ1962-64 ዓ.ም በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጊዜ ያከሱም ንቡረዕድ ተሹሞ የነበረው የሸዋው ኤርምያስ ከበደ ወልደ/ኢየሱስ ነው" ይለናል:: (እንደላይኛው ገጽ 27)*

ልብ እንበል፤ አበው "መጥነው የጎረሱት አያንቅም!" የሚሉት ያለምክንያት አይደለም:: ተጋዳላይ ብሥራት አንድ የሸዋ አማራ የሆኑ የቤተክህነት ሰው ያውም ጎሰኝነት ምን እንደሆነ ከነሱ በስተቀር ባልታወቀበት ዘመን አከሱምን ረገጧት ብሎ ምን ያህል እንደቆጠቆጠውና ምሳሌ አድርጎ እንዳቀረባቸው አስተውሉ:: "በወንጀል ሥራ የተነሳ ያከሱም ሕዝብ ያባረራቸው" ብሎናል:: የሠሩትን ወንጀል ግን አልገለፀልንም:: ሊገልፅልን ግን ይገባው ነበር:: ደግሞስ የቤተ ክህነት ሰዎች ጎሳና ቋንቋ ከመቸ ወዲህ ነው ወሰን ሆኖ የሚያግዳቸው? በተገኘ ቦታ፣ በተገኘ ጊዜ የክርስቶስን ቃል ይሰብካሉ፤ ያስተምራሉ፤ አድባራትን በቅንነት ያገለግላሉ፤ ያስተዳድራሉ፤ እንደ ብሥራት አማረ ስሌት ከሆነማ ዛሬ ጉድ ፈላ!! እስቲ ከዛሬው ጋር እያነፃፀርን ሕሊናዊ ፍርድ እነስጥ::

የቤተ ክርስቲያኗ ቀኖና ወይንም የሲኖዶሱ ሕግ በማን ጊዜ ነው የፈረሰው? አንድ ፓትሪያርክ በሕይወት እያለ አባሮ ወይንም መፈንቅለ ፓትሪያሪክ አድርጎ ሥልጣን ላይ የተቀመጡ አባት ብቅ ያሉበት ዘመንስ በማን ጊዜ ነው? በምኒልክ ጊዜ? ወይንስ በቀ.ኃ.ሥ ጊዜ? ዛሬ በኢትዮጵያ ታሪክም ሆነ በኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ታይቶም ሆነ ተሰምቶ





*በማይታወቅ ሁኔታ ቤተክህነት ባንድ ጎሳ ሰዎች ብቻ ታጭቃ ያላንዳች መቆርቆር እየታመሰችና እየተመዘበረች ያለችውስ በማን ዘመን ነው? ዛሬ በቤተክህነት ጠ/ጽሕፈት ቤት ዙሪያ የሌሎች እምነት ተከታይ ዜጎችን ፈልጎ ማግኘት ብርቅ እየሆነ ነው:: ሌላው ቀርቶ አባ ጳውሎስ እንዳረፉ ተጠባባቂ ፓትሪያሪክ እንዲሆኑ የተሰየሙት እንኳን ያርሲ ሀገር ስብከት ሊቀ ጳጳስ አቡነ ናትናዔል ናቸው:: የእምነት መለኪያው ዘር ከሆነ እኒህ አባት ከመጀመሪያውስ ቢሆን አርሲ ዞን ምን ሊያደርጉ ሄዱ? የኦሮሞ ዜጋ ጳጳሰው የዞኑን የእምነት ተከታዮች ማገልገል አይችሉም? ሁሉም ነገር ካባ ጳውሎስ ጎሳ ውጭ እንዳይሆን በቁጥጥር ስር ለማድረግ ነው? ይህ እውነት ለመሆኑ 6ኛ ፓትሪያሪክ ሆነው የተመረጡት አቡነ ማትያስ የትግራይ ተወላጅ ናቸው:: ሌሎች አባቶች ለሐይማኖታቸው ብቃት የላቸው ይሆን? ጠይቁ::*

እንደሚታወቀው ነፍሳቸውን ይማረውና አባ ጳውሎስ የሲኖዶሱን ሕግ አፍርሰው የፓትሪያሪክነቱን ሥልጣን ይዘው ከመንፈሳዊ ሕይወት ይልቅ ለሥጋዊ ቅምጥል ሕይወት ይሳሱና ይጎመጁ እንደነበር ባይናችን ያየነው ሀቅ ነው:: 3ኛው ፓትሪያሪክ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጭብጥ ጥሬ እየቆረጠሙ በባዶ እግራቸው የሄዱላትን ቤተክርስቲያን አባ ጳውሎስ ባንፃሩ ጥይት በማይበሳው መኪና ሲንፈላሰሱ አይተናል:: ከዚህም ዘለል ባለ መልኩ ሕዝብ ክርስቲያን ምን ይለኛል ብለው ሳይጨነቁና ሳይሰጉ ዛሬ ሲያልፉ ሊሠራ የሚችለውን ሐውልት በሕይወት እያሉ በሌ መድኃኒዓለም ባንዲት ቀበጥ ወይዘሮ አማካኝነት አሠሩ:: ይህንንስ የሕወሓት ሰዎች እንዴት ታዩት ይሆን? የናንተ ሲሆን ቅዱስ የሌላው ሲሆን ርኩስ:: ራስን ከመለኮት በላይ አድርጎ መኖር እንዴት ይቻላል?

በመሠረቱ መነኮሰ ማለት ሞተ ማለት ነው:: ሞተ ስንልም በሕይወት አለመኖርን ሣይሆን የዚችን ዓለም ጣፋጭ ሕይወት ንቆና ተጠይፎ ለዚያኛው ዘለዓለማዊ ሕይወት ሲቃይ መቀበልና ሥጋን ማድከም ማለት ነበር:: አቧታችን አባ ጳውሎስ ግን እንዲህ ያሉ አባት አልነበሩም:: በዘመናቸው እምነቱን ተከትሎ እጅግ ዘግናኝ የሆነ ደም ፈሷል:: እሳቸው በተገኙበት ታቦት እየዘረ መስቀል አደባባይ አጠገብ ከሚገኘው እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ጥር 1 ቀን 1989 ዓ.ም በጥይት የተገደሉት ባህታዊ ፈቃደ ሥላሴ የሚረሱ አይደሉም:: ከዚህ ሌላም እጅግ በሚያሣፍርና አንገት በሚያስደፋ መልኩ በዚህ ዘመን የፅላትና የቅርሳቅርስ ሽያጭ የተጧጧፈበት ዘመን ለመሆኑ ያደባባይ ምስጢር ነው:: ባንዳንድ አካባቢዎች ያላንዳች ማጋነን ሕንፃዎቻቸው ተገትረው እንደሆነ እንጂ ፅላቶቻቸው ከመንበራቸው

ውስጥ ስለመኖራቸው በቂ የሆነ ማረጋገጫ የለም። እንዲህ ዓይነት ምዝበራና ቅሠጣ (ዘረፋ) እየተፈፀመ ባለባት አገርና ዘመን ተጋዳላይ ብሥራት አማረ በ1962-64 ዓ.ም ለሁለት ዓመት በንቡረዕድነት ማዕረግ አክሱም ፅዮንን ለማገልገል ከመሀል አገር የሄዱትን አዛውንት "ከሸዋ የሄዱ አማራ" በማለት ሲያብጠለጥላቸው ያሣፍራል። ከጳጳሳት እስከ ዲያቆናት መጥተው ቤተክርስቲያኗን የሠፈሩባትንስ በምን ቋንቋ እንግለፃቸው? እነሱ በየትም ቦታ ተዘዋውረውና ተንደላቀው ኮርተው፣ የበላይ ሆነው እንዲኖሩ እግዚአብሄር በልዩ ትእዛዝ ፈቅዶላቸው ይሆን? ወይንስ አቶ መለስ የወርቅ ዘር እንዳሉት ልዩ ክብር ሊገባቸው? ጠይቁ።



*አማራን ከርሃብ ጋር ያነፃፀረው ብሥራት አማረ*

በመሠረቱ ሐረጉን ሲሰቡት ዛፉ እየተወዛወዘ እንጂ በተለይም ባባ ጳውሎስ ዙሪያ ብዙ ማለት ይቻል ነበር። ለምሳሌ ዓለማዊ ሕይወት ምን ያህል ይጣፍጣቸው እንደነበር ሌላው ማረጋገጫ ንዋይ ብቻ ሣይሆን ማዕረግም የማይጠቅማቸው ነበሩ። ይህንን ሀቅ ከጓድ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ማዕረግ ጋር እያነፃፀርን ማየት እንችላለን። በቅድሚያ የኮሎኔል መንግሥቱን እነሆ፦

*ጓድ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም፣ የኢሕዴሪ፣ ፕሬዚዳንት፣ ያብዮታዊት ጦር ጠቅላይ አዛዥ፣ የሚንስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢና የኢሠፓ ዋና ፀሐፊ። (18 ቃላት)*

*ብፁዕ ወቅዱስ ዶክተር አቡነ ጳውሎስ፣ ቀዳማዊ ፓትሪያሪክ፣ ርእሳነ ሊቀጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት፣ የዓለም አብያተክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት፣ የዓለም ሃይማኖቶች ምክር ቤት ለሰላም ክብር ፕሬዚዳንት፣ ዓለም ዓቀፍ የሰላም አምባሳደር (34 ቃት)*





እንግዲህ ይኸ ሁሉ የማዕረግ ዲሪቶ ላንድ አባት ምን ይፈይድ ነበር? እንደ እውነቱ ከሆነ ለክብርና ለፀጋ ከሆነ "ብፁእ" ይበቃቸው ነበር። ከብፁእነት የበለጠም ማዕረግና ክብር ሊኖር አይችልም። ይህንንስ የሕወሓት ሰዎች እንዴት ታዩት ይሆን? ከሁሉም የሚያሣዝነውና የሚያሣፍረው ደግሞ "የሸዋና የጎንደር አማራ "እያሉ ለመከፋፈል መሞከሩ ነው። ጎሠኝነት ከኤች.አይቪ. የባሰ ከፉ ቫይረስ ነው የምለውም ለዚህ ነው።

ተጋዳላይ ብሥራት አማረ ከንቡሪእድ ኤርምያስ ከበደ ወጣ ይልና ደግሞ እንዲህ ይለናል፦

*"ታላቁ የትግራይ ሕዝባዊ ንቅናቄ ተፀንሶ የተወለደው <u>ብልሹ በሆነው ያማራዊነት ፍልስፍና ተግባር ምክንያት እንደሆነ ርግጠኛ መሆን እንችላለን። . . . ለትግራይ ሕዝብ የትግል ዋናው ምክንያት ኢትዮጵያዊነት ባማራዊነት ለማጥመቅ የተደረገው ጥረት በቂ ማስረጃ ነው"</u> (ሠረዝ የራሴ) (እንደ ላይኛው ገጽ 27)*

ለመሆኑ አማራዊነት የሚባል ፍልስፍናም ነበር እንዴ? የሚገርም ነው። ነበር ከተባለ ደግሞ ዛሬ የትግሬዊነት ፍልስፍና ሠፍኗል ማለት ነው። ደግሞስ ምናለበት "የትግራይ ሕዝባዊ ንቅናቄ ተፀንሶ የተወለደው ብልሹ በሆነው አማራዊነት ፍልስፍና ነው" ከማለት ይልቅ "ብልሹ በሆነው ዘውዳዊው ሥርዓት ነው" ቢል ኖሮ ሁሉንም ያሣተፈ መሆን በቻለ ነበር። የተፈለገው ግን አማራ ላይ ማነጣጠር ነው። እውነቱም ይኸ ነው፣ ታዲያ ሕወሓቶች ያማራ ዘርን ለማፅዳት አልተንቀሳቀሱም ማለት ይቻላል? ጠይቁ። አማራ ባሪያ ፈንጋይም ሆኖ ቀርቧል። እነሆ፦

*". . .የክርስትና ሃይማኖትን ካወቁ ጊዜ ጀምሮ አክሱማውያን ባርነትን የተቃወሙና ሌሎቹንም ያስተማሩ ሕዝቦች መሆናቸው ታሪክ ዘግቦታል። . . የሸዋ ፓሻዎች ግን እስከ 20ኛው ክ/ዘመን መጨረሻ ሩብ ዓመት ድረስ በባሪያ ንግድ ወንጀል ውስጥ ተዘፍቀዋል።አክሱምንና ሰሎሞናዊ የዘር ሐረግ መናፈቃቸው ሌላው ቅዠትና ስህተት ነበር። አክሱም ለመሆን መወለድን ወይንም ባህሉን መከተል ወይንም ሁለቱንም መሆን ግድ ይላል" ይለንና አያይዞ "የባሪያ ንግድ የጥቁር አፍሪካውያን ሰብዓዊ ክብር ያዋረደ ታሪክ ነው። ታላቁ አክሱም ግን ከባሪያ ንግድ ውስጥ ከመሣተፍ መቆጠቧ . . . ክርስቲያን መሆን በባሪያ ንግድ አለመግባት ነው። የሸዋ ገዥዎች ግን ገቢ ለመሰብሰብ ባሳዛኝ ሁኔታ ባሪያ ነግደው የኢትዮጵያን ንጹሕ ኢጆች የማቆሸሸ ውጤት አስከትለዋል . . ." (እንደ ላይኛው ገጽ 31-32)*

አፄ ምኒልክን ደግሞ እየዘረጠጠ እንዲህ ሲል ይዘልፉቸዋል:: *"የሀገር ፍቅር ስሜት የጎደለው ምኒልክ የኢትዮጵያን መሠረታዊ አንድነት ገዘግዞ በማበላሸት ያገሪቱን ብሔር ብሔረሰቦች ራሳቸውን ከሽያጭ እንዳይከላከሉና ማዕከሉን እንዲሸርሸሩ አድርጓል:: የቅኝ ግዛት ሥጋት ሳይኖርበት ለገንዘብና ሥልጣን ግዛቱንና ሕዝቡን ፈርሞ ለውጭ ኃይሎች የሸጠ መሪ ከምኒልክ በስተቀር በታሪክ አይገኝም:: . . ." (እንደ ላይኛው ገጽ 38)*

እውነት አፄ ምኒልክ ለውጭ ኃይሎች መሬት ሸጠዋል? ኢትዮጵያን አንድነት አበላሽተዋልን? እንዴት ነው ነገሩ ጎበዝ? ኧረ በርትታችሁ ጠይቁ:: ያስብን የባሕር በር፣ የጋንቤላ ለም መሬት መቸ ነው እየተቸበቸበ ያለው? እነዚህን አፄ ምኒልክ ናቸው እንዴ የሸጧቸው? አፄ ምኒልክ የውጫሌን ውል አንቀጽ 17ን አልቀበልም ብለው እስከነ ባለቤታቸው አድዋ ተራሮች ዘልቀው ጉርቦ ለጉርቦ ተናንቀው አንፀባራቂ ድል ያጎናፀፉ መሪ ነበሩ:: ይህንን አኩሪ ድል በርግጥ የሕወሓት ሰዎች አይቀበሉም፤ አያምኑም፤ ድሉን ቢያምኑም እንኳን ለራስ አሉላ ብቻ ነው የሚያሸከሟቸው:: እነሆ ብሥራት አማረ እንዲህ ይላል:-

*"ያድዋ ጦርነት የምኒልክን ታሪክ ትልቅ ሰው አስመስሎ አቅርቧል:: ኢትዮጵ <u>ብሔርተኛና ጀግና መሪ በምትፈልግበት ወቅት ያለቦታው</u> ምኒልክ ተገኙ:: ምኒልክ ወደደም ጠላ ያድዋ ጦርነት የማይቀር ታሪካዊ አጋጣሚ ነበር:: ምኒልክ ግዛቷ የተቀናነሰች አንስተኛ ኢትዮጵያን አፄ ብቻ ተብሎ ለመንግሥ እቅድ እንዳለው ጣሊያኖች ደርሰውበት ነበር:: <u>አዲሱ ታዛገቸው አገሩን በማስከበር ረገድ እንደ ዮሐንስ አገር ወዳድ አለመሆኑን ተገንዝበዋል::</u> (ሥርዝ የራሴ) በምኒልክ <u>ፍርሃትና ስግብግብነት ተፈጥሮ ብቻ</u> አገሪቷን በቅኝ አገዛዛቸው ሥር ለማስገባት ያነሳሳቸው ስሌት ለውድቀትና ለሽንፈት ዳርጓቸዋል:: የራስ አሉላን በሕይወት መኖር ዘንግተዋል:: አሉላ ባይኖር ኖሮ ኢትዮጵያ የኢጣሊያን ቅኝ ግዛት ትሆን ነበር:: . . ."* ይለናል::

ውድ አንባቢያን ጥላቻምኮ ልክና ገደብ አለው:: እውን አፄ ምኒልክ ፈሪና ስግብግብ ነበሩ? እውነት ያድዋ ድል የተገኘው በራስ አሉላ ብቻ ነው? ምን ዓይነት የበታችነትና የፍርሃት ምንጭ ነው ብሥራት አማረን የተጠናወተው? እውነት እንነጋገር ከተባለ ያድዋ ድል የሁሉም ጀግኖች ቅንብር ውጤት እንጂ የራስ አሉላ ቀርቶ ያፄ ምኒልክ ብቻም አይደለም:: በመጀመሪያ ደረጃ የሕወሓት ሰዎች የዘር ሐረግ እንሳብ ካላሉ በስተቀር በራስ አሉላ ጀግንነት የመመካትም ሆነ የመኩራት የሞራል ብቃት





ሊኖራቸው አይችልም:: የብሥራት አማረ ትረካም የቅጥፈቶች ሁሉ ቁንጮ ነው::

በርግጥ ራስ አሉላ አባ ነጋ ባድዋው ዘመቻ ወቅት ከነበሩት ስመ ጥር ጀግኖች መሀከል አንዱ እንደነበሩ ይህንን ሀቅ የሚክድ ኢትዮጵያዊ የለም:: በራስ አሉላ ጀግንነትም የማይኮራ ኢትዮጵያዊ የለም:: የሚያስገርመው ግን ራስ አሉላ "የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ወሰን ቀይ ባሕር ነው!" ያሉትን አንፀባራቂ መርህና መፈክር ወይንም ሕያው ቃል ጥላሸት ቀብተው "እበት ትል ይወልዳል!" እንዲሉ ተጋዳላይ ብሥራትና ድርጅቱ (ሕወሓት) ኤርትራን ተቀግተው አሥገንጥለው በራስ አሉላ ጀግንነት ለመደበቅ መሞከር ሰብቅ ነው:: እንዲያው ለመሆኑ አፄ ዮሐንስንና ራስ አሉላን ለማወደስና ለማሞገስ አፄ ምኒልክ መሰደብና መዋረድ አለባቸው? የትግራይን ሕዝብ "ታላቅና የወርቅ ዘር" ለማለት ያማራ ሕዝብ ማነስና በጨርቅ መመሰልስ አለበት? ኧረ ልናላምጥ የምንችለውን፣ እንጉረስ:: ለማንኛውም ስድቡ ይቀጥላል::

*"የምኒልክንና የሌሎችን የዘር ሐረግ የማጠናው ለዘመናችን ትክክለኛ እሴት ስለማይበት ሳይሆን ታሪክ በምኒልክና በሌሎች የውርስ ይገባኛል ጥያቄዎች የደረሰበትን መዛባት ለማቃናት ነው:: ምኒልክ የኃይለ መለኮት ሣሕለሰላሴ ዲቃላ ልጅ ነበር . . ." (እንደ ላይኛው ገጽ 37)*

ይህ ሁሉ ዙሪያ ጥምጥም የነጋሢ ዘሮች እኛ ነን:: ምኒልክ ዲቃላ ነው:: የነጋሢ ዘር ወይንም የሰለሞናዊ ሥርወ መንግሥት ብቃይ አይደለም ለማለት ነው:: የዘውዱ ሥርዓትኮ ከቀ.ኃ.ሥ በኋላ ያከተመ መሠለኝ:: አለ እንዴ? አጅሬ ሕወሓቶችኮ ሥልጣኑን በሥውር በዘውድ ስም ይዞት ይሆናል? ለዚህ ሣይሆን ይቀራል? ምርጫ በመጣ ቁጥር የሚይዘውን የሚጨብጠውን የሚያጣው:: -

ተጋዳላይ ብሥራት አማረ ያድዋን ድል የትግራይ ሕዝብ ብቻ ድልና ገድል አድርጎ የተረከባትን ደግሞ እነሆ:- *". . .እስከ ዛሬ ምንነቱ ባልታወቀ በሽታ እያንዳንዱን የቀንድ ከብት እንዳለ አለቀ:: ከኢጣሊያ እቅድ መመንጨቱንም የሚጠራጠሩ አሉ:: (በሽታውን ማለቱ ነው) . . .ይህ እቅድ አፍሪካውያንን በበታችነት ከሚቆጥሩ ያውሮፓ ኃያላን አገራት ኢጣሊያንን በመቋቋም ባሳየው ቆራጥ ድፍረት የትግራይን ሕዝብ ለመቅጣት የታቀደ እንደነበር የሚያምኑ በርካታ ናቸው" (እንደላይኛው ገጽ 39-40)*

ልብ እንበል ወገን ብሥራት አማረ ቀደም ሲል "ያድዋ ድል የተገኘው በራስ አሉላ አማካኝነት ነው:: ራስ አሉላ በሕይወት ባይኖሩ ኖሮ ኢትዮጵያ

በኢጣሊያን ቅኝ ግዛት ሥር ትወድቅ ነበር" ሲል በድፍረት ነግሮናል፡፡ አሁን ደግሞ ከዚያው ሣይወጣ ድሉን ለትግራይ ሕዝብ ብቻ ያሸክምና ለዚህ በቀል መልስ የሚሆን ኢጣሊያ የትግራይን ሕዝብ የብቻ ለመቅጣት ስትል የቀንድ ከብቶችን በመደዳ የሚጨርስ በሽታ በመልቀቅ ተበቀለች ይለናል፡፡

በመሠረቱ ብሥራት አማረ ያልታወቀ በሽታ የሚለው የታወቀና በየታሪኩ ተመዝግቦ የሚገኝ ነው፡፡ ይህ መቅሰፍትም ለትግራይ ሕዝብ ብቻ የመጣ ሣይሆን መላ ኢትዮጵያን የሸፈነ ነበር፡፡ በዚያን ዘመን አጠራርም "ጅል ቀን ወይንም ክፉ ቀን" እየተባለ የሚጠራው ነው፡፡ በዚህ ክፉ ቀን ጊዜም አንዲት እናት የሌሎችን ልጆች ስትበላ ሌላዋ እናት ደግሞ የገዛ ልጇን በልታለች፡፡ ከርሃቡ ወይንም ከጠኔው ብርታት የተነሣም ሊበሉ የማይገባቸው እፅዋት' ሥራሥሮችና ቅጠላ ቅጠሎች ሁሉ ተበልተዋል፡፡ የርሃቡን አግባብና ክስተት "ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሰ ነገሥት ዘኢትዮጵያ" በተባለው መጽሐፋቸው ጸሐፊ ትእዛዝ ገ/ሥላሴ እንዲህ ሲሉ ዘግበውታል፡-

*"ክረምቱን በዘመነ ማቴዎስ ላሙ፣ በሬው፣ አልቆ እንግዳ ነገር ስለሆነ ሰውም መቆፈሩን ትቶ በዝኖ ነበርና በዘመነ ማርቆስ (በቀጣዩ ዓመት ለማለት ነው) ዳር እስከ ዳር ጽኑ ርሃብ ሆነ. . ."* በማለት ዝርዝር ታሪኩን ዘግበውታል (ገጽ 175 -76) ይህንኑ ዋቢ በመጥቀስ እውቁ የታሪክ ተመራማሪ ሪቻርድ ፓንክረስት "The Ethiopian Royal chronicles" በተባለው መጽሐፋቸው በገጽ 172 ላይ በስፋት አስፍረውት ይገኛል።

በዚህ አጋጣሚ ይልቅ አንድ ቁም ነገር ጣል አድርጎ ማለፍ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ይኸውም ስለ ቁርጥ እንጀራ ታሪካዊ አመጣጥ ስንቶቻችን እናውቅ ይሆን? እንጀራን እየቆራረጡ ጠቅልሎ ወይንም ሸምልሎ በወግ በማዕረግ በሠርግም ሆነ በሌላ አጋጣሚ ወይንም በቤት ውስጥም ቢሆን በነፍስ ወከፍ ሳህን ይዞ ለየራስ መመገብ ዛሬ ባገራችን የተለመደና ባህል እየሆነ መጥቷል፡፡ ላያያዝም ሆነ ላቀራረብ ቀልጣፋ በመሆኑ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሣይቀር ተወዳጅ ሆኗል፡፡ ይህንን እንጀራ እየቆራረጡ ጠቅልሎ ለየራስ አንጠልጥሎ መብላት የእድሜ ባለጸጎች አይወዱትም፡፡ "ችጋር ጠሪ ነው" ይሉታል፡፡ ይህንን ሲሉ ከምንም ተነስተው አይደለም፡፡ "ክፉ ቀንን ወይንም ጅል ቀንን" ስለሚያስታውሳቸው ነው፡፡ ታሪካዊ አመጣጡ እንዲህ ነው፡፡

በዚያ ክፉ ርሃብ በገባበት ጊዜ ሕዝቡ ቁራሽ ፍለጋ ወደ ቤተ መንግሥት ወይንም ወደ እንጦጦ ያነዪ የንጉሠ ነገሥቱ መቀመጫ እንጦጦ ስለነበር





ርሃብተኛው ወደዚያው ይጎርፍ ጀመር፡፡ እናም እቴጌ ጣይቱ በመጀመሪያ በነፍስ ወከፍ አንዳንድ እንጀራ ለማዳረስ ሞከሩ፡፡ በኋላ ግን የርሃብተኛው ቁጥር ከቁጥጥር ውጭ በመሆኑ አንዳንድ እንጀራ ላንድ ላንድ ወይንም በነፍስ ወከፍ መስጠቱ ይቀርና ለሕይወት ማቆያ ያህል አንዷን እንጄራ ካራትና ካምስት በመቆራረስ እየጠቀለሉ መስጠት ተጀመረ፡፡ ይህነኑ ሂደት ሪቻርድ ባንክረስት ዘግበውት ይገኛል፡፡ እንግዲህ የቁርጥ እንጀራ ታሪካዊ አመጣጥ ጅል ቀን ወይንም ክፉ ቀን ነበር፡፡

እንግዲህ ስለ ቁርጥ እንጀራ ይህን ያህል ካልን ወደ ተጋዳላይ ብሥራት አማረ ዘለፋ እንመለስና የሚለንን እንመልከት፡፡ ብሥራት አማረ ታላቁን የትግራይ ሕዝብ ምንነቱ ያልታወቀ የቀንድ ከፍት በሽታ ገብቶ የብቻው ነጥሎ ማጥቃቱን ወይንም በርሃቡ የትግራይ ሕዝብ ብቻ መጎዳቱን ከተረከልን በኋላ ይቀጥልና የትግራይ ሕዝብ ጠላቶች ርሃብና በምኒልክ መሪነት አማራዎች ናቸው በማለት እንዲህ ይለናል፡-

*". . .ወቅቱ በትግራይ ሕዝብ ላይ ያነጣጠረ ክፉ ዘመን ነበር፡፡ <u>ተፈጥሮም ከጠላት ጋር በማበር ጠላት የተባለው አማራ መሆኑን ልብ እንበል፡፡ ከዳቻቸው</u> . . ."* (ሠረዝ የራሴ) ይለንና ቀጠል አድርጎ *"ምኒልክ ለተከታዮቹ ትውልዶች ያስተላለፈው ሌላው የጥፋት ትእይንት የካሂዲነት ባህሪ ብቻ ሳይሆን ፈሪነትንም ጭምር ነው፡፡" (እንደላይኛው ገጽ 40)*

እንዴት ነው ነገሩ ጎበዝ፤ ልክ እንደ ታላቅነት የፈሪነትም መስፈርቱና ሚዛኑ ግራ የሚያጋባ ሆነ፡፡ አገር ተዋግቶ ያስገነጠለና የባሕር በር የዘጋና ያዘጋ "ታላቅ" አድዋ ተራሮች ዘልቆ ጣሊያንን ውሃ ውሃ አሠኝቶ ያባረረ "ፈሪ!" ኸረ ጠይቁ፡፡ በነገራችን ላይ ይኸ "ታላቅ ታላቅ!" የሚለው ቃል መነሻው ሩቅ ነው፡፡ ካቶ መለስ አልፈት ጋር ብቅ ያለ መስሎኝ ነበር፡፡ እንደ ብሥራት አማረ አተራረክ ከሆነ የሕወሓት ያፍ መፍቻ ቋንቋ ሆኖ "ታላቋ ኤርትራ!-ታላቋ ትግራይ!" ከነዚህ ከተጠቀሱት ራቅ ሲባል ደግሞ ዛሬ ፀሐይ የደበዘዘባት ያነዪ ያልጠለቀባት "ታላቋ ብርታኒያ!" ነበረች፡፡ እንግዲህ ሕወሓትና ሻዕቢያ የሷ አርማ ወራሾች መሆናቸው ነው፡፡ ሶማሊያም ባለ አምስት ኮከብ አርማ ከባንዲራዋ ላይ አስቀምጣ "ታላቋ ሶማሊያ" ትል ነበር፡፡ ዛሬ ወደ መንደሮች ወረደች፡፡

ከዚህ ላይ ግን ሊተኮርበትና ሊሠመርበት የሚገባው ቁምነገር እንዴት ነው ከሕወሓት ሰዎች ጋር እንደ ዜጋ አብሮ መኖር የሚቻለው? አንድን ሕዝብ ከሌሎቹ ነጥለው መጥላታቸውና ማሣደዳቸው ሲገርመን ብሥራት

አማረ ከርሃብ ጋር አነፃፅሮ "የትግራይ ጠላቶች ሁለት ናቸው፡፡ ተፈጥሮና (ድርቅ ወይንም በሽታ) ጠላት (በምኒልክ የሚመራ አማራ ነው)" ማለቱ በምን ቃል መግለጽ ይቻላል? እውን ያማራ ሕዝብ ለትግራይ ሕዝብ የርሃብን ያህል የከፋ ጠላት ነው? እውን አማራን ርሃብ ነክቶት አያውቅም? ታሪክ ይፍረድ እንዳንል ታሪክን የሚደፈጥጡ እንጂ ለታሪክ ክብር የሚሰጡ አይደሉም፡፡ *ሥግነት ይፍረድ እንዳንል ሥግነትን አያውቁም፡፡* ምን ይሻላል ጎበዝ? እስቲ ጠይቁ፡፡

ብሥራት አማረ *"በትግራይ የሁለቱ ወያኔዎች አብዮቶች* (ቀዳማይና ያሁኑ ወያኔ ለማለት ነው) *መነሳት ምክንያት ምኒልክ አስቀድሞ ለሠራው ክህደት ቀጥተኛ መልሰና ውጤት ነው"* ካለን በኋላ አያይዞ አንድ የትግራይ አዛውንት ምናልባትም ከመጽሐፉ የፊት ሽፋን ኋላ ቀር ጠመንጃ አንግተው፣ ዝናራቸውን ታጥቀው ካጠገባቸው የመገናኛ ሬዲዮ ይዞ ለቆመው ወጣት ተጋዳላይ እጃቸውን በርቀት በመዘርጋት ባመልካች ጣታቸው አሻግረው "ያውና ያማራዎች አገር" በሚል በሚመስል መከረው ሲያስናብቷቸው እንዲህ አሏቸው ይለናል፡-

*"ኢትዮጵያ የናንተ ናት፡፡ አሁን የሚያቆማችሁ ኃይል የለም፡፡ ልጆቻችን ከነሱ ይበልጥ ጠቢብና አሳቢ እንደሆናችሁ የንጉሥ ምኒልክ ሰዎች አሁን ይማራሉ፡፡ እናንተን ለማሸነፍም ሆነ ለማስቆም የሞራል ብቃት የላቸውም፡፡ ትግራይ አንደዬም ተሸንፎ አያውቅም* (ሠረዝ የራሴ) . . . !" *(እንደላይኛው ገጽ 41)*

ይኸ ከባድ ፕሮፓጋንዳ ነው፡፡ እውነት የትግራይ ሕዝብ አንደየም ተሸንፎ አያውቅም? ሲሸነፍ የኖረው ታዲያ የትኛው ሕዝብ ነው? የትግራይ ሕዝብ አንድም ጊዜ ካልተሸነፈ አፄ ዮሐንስ መተማ ላይ ድል የሆኑት ማንን ይዘው ዘምተው ነው? በዚህ ሥልጡን ዘመንስ አንዱን ብሔር ጀግና ሌላውን ፈሪና ተሸናፊ አድርጎ የዘር መርዝ መርጨት ምን ዓይነት የፍርሃት ምንጭ ነው? ለመሆኑ ለነብሥራት አማረ አማራ ቅዠት የሆናቸው ለምንድን ነው? እንዲህ ዓይነት መመፃደቅስ ለምን አስፈለገ? ባንድ ወቅት የጎበዝ ወይንም ኃያል የሆነ በሌላ ጊዜ ሊኮስስ ይችላል፡፡ የበረቱ ይደከማሉ፤ የደከሙ ደግሞ ይበረታሉ፡፡ ዛሬ በተለያዩ ምክንያቶችና አጋጣሚዎች "ሟች አውሬ ገዳዩን ያስመሰግናል" እንዲሉ የትግራይ ልጆች ጎብዘው ሊሆን ይችላል፡፡ ነገ ደግሞ ሊኮስሱ ይችላሉ፡፡ ደግሞምኮ ፍልሚያው የስበስ በመሆኑ ይህን ያህል የሚያኩራራ አይመስለኝም፡፡ "የላም አሸናፊ መሆንም" ያሳፍራል፡፡ ደግነቱ ሀፍረትን አያውቁም፡፡





በመሠረቱ የብሥራት አማረን መጽሐፍ ከዚህ ባለፈ ማየት ሐመም መሥረቅ ነው፡፡ የዜግነት ርሾንም ጨርሰን ልናሟጥጥ እንችላለን፡፡ እስቲ ደግሞ ቀጥለን የሱ ቢጤዎች የሚሉንን እንያቸው፡፡ ብሥራት አማረ ኢሕአዴግ አዲስ አበባ በድል አድራጊነት ሲገባ የሰላምና መረጋጋት የፀጥታና አሥተዳደር አስተባባሪ ሆኖ ማገልገሉን ይገልጽና ትኩስ እንጀራ በቅጡ ሳይበላ ወይንም የድሉን ፍሬ ሳያጣጥም በ1984 ዓ.ም የመንግሥት ሥራ ለቆ በስደት ወደ አሜሪካን አገር መሄዱን ሲነግረን ለምንና በምን ምክንያት እንደተሰደደ ግን አልነገረንም፡፡ ለምን ስደትን መረጠ? ከነማንስ ጋር ተጋጭቶ ይሆን? ምናልባት በሰላምና መረጋጋት ስም ስንቶቹን ቀንበጦች በልቷቸው ይሆን? ልጆቻችሁ፣ ባሎቻችሁ፣ ወንድሞቻችሁ እንደ ወጡ የቀሩባችሁ ጠይቁ፡፡ በተረፈ ከተጋዳላይ ብሥራት አማረ ወደ ተስፋዬ ገብረአብ ስንሸጋገር ደግሞ የሚከተለውን እናገኛለን፡፡

ተስፋዬ ገብረአብ ኤርትራዊ ነው፡፡ ግን ደግሞ ተወልዶ ያደገው ደብረዘይት ያዳን ጤፍ እየበላ ነው፡፡ "የናት ጡት ነካሽ" እንዲሉ ወይንም የዘር ልጓም ስቦት እሱም የድርሻውን እንዲህ ይለናል፡-

*"ነፍጠኞች አቡቢንቲ የተባለ ሽቶ አንድ ብር ይሸጡልንና እነሱ ግን ሦስት እንቁላሎችን ባምሳንቲም ይገዛሉ፡፡ ወተትና እንጀራ መሸጥ በኦሮሞ ነውር ነው፡፡ እነሱ ግን አንድ እንጀራ መሸጥ ጀምረዋል፡፡ ይኸ ነው ሥልጣኔ፤ ቁንዲፍቱ መጥመቅ የኦሮሞ አይደለም፤ የሰው ሚስት መወሸም የኦሮሞ ባህል አይደለም፡፡ ነፍጠኞች ባህላችንን አቆሸሹት፤ መሬታችንን ነጠቁን፡፡ . . . ምኒልክ የተባለው ስግብግብ ይህን ሀብታም መሬት ሲያይ ጎመጀ፡፡. . ."(የቡርቃ ዝምታ ገጽ 93)*

የምኒልክ ጥላ ሞት ወይንም አፅም ወይንም የሙት መንፈስ ከትንሽ እስከ ትልቅ ለምን እንደሚያሸብራቸው አይገባኝም፡፡ የሚገርም ነው፡፡ ነፍጠኛውስ ቁንዲፍቱ ማውጣት አስተማራቸው፡፡ ዛሬ ኢሕአዴግ ቢራ ጠመቃ ይሆን ያሠለጠናቸው? ኸረ የሰው ሚስት መወሸምም በሌላውም ነውር ነው፡፡ ያማራም ባህል አይደለም፡፡ እንዲያውም ሥርዓተ ቁርባን አለ፡፡ ከቴ ለምን ይሆን አማራና ኦሮሞን ለማስተራረድ የሕወሓት ካድሬዎች ተግተው የሚሠሩት? እስቲ ጠይቁ፡፡

በመሠረቱ ተስፋዬ ገብረአብ እንኳን ላማራዎችና ለራሱ ወገኖች የሚታመን አይደለም፡፡ ከሃዲ ነው፡፡ ስለምኒልክና ስለነፍጠኝነት ብዙ ብሏል፡፡ ዛሬም በስደት ሆኖ እየጻፈ ነው፡፡ በሽታ ነውና ስላማራ መቸም ይጽፋል፡፡ እስቲ ደግሞ ትልልቆቹ ተጋዳላዮች ስላማራ ህዝብ ምን ይላሉ? ቀጥለን እንመልከት፡፡

# ለካ አማራ ጠፍቷል?!

ለረጅም ዓመታት በጥብቅና ሙያ ሲያገለግሉ የኖሩት አዛውንቱ የሕግ ባለሙያ አቶ ሙሉጌታ በሪሁን አንድ ቀን ከቤታቸው ምሳ ጋበዙኝና በልተን አብቅተን ቡና እየጠጣን እንዳለን "ትንሽ ብር አለችኝ አንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ገዝቶ ልገባነኝ" አሉኝ፡፡

"ሌሎች ባንኮች እያሉ ለምን አንበሳ ባንክን መረጡ?" አልኳቸው፡፡

"አንበሳ የኢትዮጵያውያን አርማ ስለሆነ እወደዋለሁ፡፡ ሰሞኑን ደግሞ፤ በቴሌቪዥን በማስታወቂያ አንበሳው ሲያገሣ ከፉኛ ቀስቅሶኛል" ሲሉ ቀልድ ቢጤም ጨመሩበት፡፡

"እንደኔ እንደኔ ግን ወደ ሌሎች ባንኮች ቢሄዱ ጥሩ ነው፡፡ አንበሳ ባንክ በሕወሓት ታጋዮች ስም የተቋቋመ ነው ይባላል፡፡ በኋላ አንድ ነገር ይናገሩዎና ወይንም ይሰሙና እንዳይናደዱ" ስል ምክር ቢጤ ሰነዘርኩላቸው፡፡

"ግዴለህም፤ በባንክ ውስጥ ጎሳ አይኖርም" አሉኝና ወጋችንን በዚሁ ቋጨን፡፡

ከ6 ወራት በኋላ ማታ ስልክ ደወለው "ጧት እቤቴ እንድትመጣ፤ ባስቸኳይ እፈልግሃለሁ" አሉኝ፤ በተቆራረጠ ትንፋሽ እልህ እየተናነቃቸው፡፡ ምን እንዳገኛቸው ብጠይቃቸውም "ጧት ስትመጣ እነግርሃለሁ፡፡ ምን አስቸኮለህ?" ብለው ስልኩን ዘጉት፡፡

ጧት ወደ ሥራ መሄዴን ትቸ ቀጥታ ወደሳቸው ቤት ሄድኩኝ፡፡ ስደርስ የሌሊት ልብሳቸውን (ፒጃማቸውን) አልቀየሩም፤ እንደለበሱ ናቸው፡፡ ጋቢ በላይ ደርበው ከሳሎኑ ጉብ ብለው ነው ያገኘኋቸው፡፡ ሰላምታ ተለዋውጠን ተረጋግተን ከተቀመጥን በኋላ፡-

"ምን ሆኑ? በደህናዎ አይደሉም?" ስል ጠየኳቸው፡፡ ጊዜ አላጠፉም፡-

"ያልከኝ ደረሰ፡፡ አንበሳ ባንክ እውነትም በተጋዳላዮች ደም የተቋቋመ መሆኑን ጄኔራል ሣሞራ የኑስ ነገሩን" በማለት ተረኩልኝ፡፡

*"የትምክህት አነጋገር ችግር ጋባዥ እንጂ እድገት አያስገኝም!"* በሚል ርእስ (ለፅናት ጋዜጣ ቅፅ፣ ቁጥር8 መስከረም 29ቀን 2003ዓ.ም) በወቅቱ የጻፉትን እነሆ፡-

*"ውድ አንባቢያን ከላይ ለተጠቀሰው ርእስ መነሻ የሆነኝ ነሐሴ 15 ቀን 2002 ዓ.ም ያንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ የቦርድ አባላት ምርጫ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ተሰብስበናል፡፡ . . . የስብሰባው ዋና ዓላማ ከዚያ በፊት በተካሄዱት ተከታታይ የቦርድ አባላት ምርጫዎች ከወገናዊነት የፀዱ ምርጫዎች ባለመሆናቸው ባባላት መሀከል ቅሬታን በማሣደራቸው ላንደየና ለመጨረሻ ጊዜ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መድረክ መሪነት በዕለቱ ስብሰባው ተጀመረ፡፡ በዚህ ስብሰባ ላይም ጀኔራል ሣሞራ የኑስም ያክሲዮን ባለድርሻ ስለሆኑ ገኝተዋል፡፡ . . . በመሆኑም እጃቸውን በማውጣታቸው ሰብሳቢው እንዲናገሩ እድሉን ሲሰጧቸው ቁጣ ባዘለና እልህ በተሞላበት አነጋገር፡-*

*‹. . .ባለፈው በተደረገው ምርጫ የተመረጡት ግለሰቦች የት ሄደው ነው? ሌላ ምርጫ የሚካሄደው? ይህንን ባንክኮ ያቋቋምነው በታጋዮች የሕይወት መስዋእትነት በተከፈለ፣ አካላቸውን ባጡ በትግራይ ልጆች ደምኮ ነው፡፡ ቀደም ሲል የተደረው ምርጫ ውድቅ የተደረገበትን ቃለ ጉባኤ እንዲሠጠኝ እፈልጋለሁ፡፡ ደርግን ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍለን ከሥልጣኑ አውርደነዋል፡፡ <u>አማራን ዳግም እንዳያንሠራራ አድርገን አጥፍተነዋል!›</u> (ሠረዝ የራሴ) በማለት ትዕቢትና ትምክህት በተሞላበት ንግግር ሲያደርጉ ከተሰብሳቢዎች መሀከል እሳቸውን ደግፈው በደስታ ያጨበጨቡ ነበሩ፡፡ አብዛኞዎቹ ግን በድንጋጤና በሃፍረት አንገታቸውን መድፋታቸውን አስተውያለሁ፡፡*

*" . . .በመሠረቱ የሕወሓት መሪዎች ከበረሃ ጀምረው ባማራ ሕዝብ ላይ ያላቸውን ጥላቻ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ሲያንፀባርቁ ኖረዋል፡፡ በተለይም ጠ/ሚንስትር መለስ ያማራን ሕዝብ ሳያንቋሽሹና ሣይዘልፉ ያለፉበት ጊዜ የለም፡፡ ይህ የጄኔራል ሣሞራ ንግግርም አዲስና እንግዳ ነገር አይደለም፡፡ እንግዳ ነው የሚያሰብለው በባንክ ውስጥም ጎሠኝነት መኖሩና ከ20 ዓመታት ያመራር ሂደቱም እነዚህ ሰዎች ከጎሣ ቁስል መዳን አለመቻላቸው ነው፡፡ ባንድ ወቅት ጠ/ሚንስትር መለስ፡-*

*‹ያማራን ሕዝብ እንዳያንሠራራ አድርገን አዳክመነዋል፡፡ እስከስታውንና ተረቱን ይዞ ይኑር› ማለታቸው አይዘነጋም፡፡ "ውድ አንባቢያን ፍትሕ የሠፈነበት ኅብረተሠብ፣ የዳኝነት ሥርዓቱ ነፃ የሆነበት ሥርዓት ቢኖር ኖሮ ጠ/ሚንስትር መለስንና ጀኔራል ሣሞራን ፍ/ቤት መገተር ይቻል ነበር፡፡ ግን ምን ይሆናል ‹አባቱ ዳኘ ልጁ ቀማኛ› ከሆነበት ሥርዓት ላይ በመድረሣችን ሕሊናችን እየቆሰለ የምንባለውን እያዳመጥን ዝም እንላለን" (ፅናት ቅፅ፣ ቁጥር 8 መስከረም 29 ቀን 2003 ዓ.ም)*



*የህግ ባለሙያው አቶ ሙሉጌታ በሪሁን*

ወገን የጀኔራል ሣሞራ ንግግር አያማችሁም? ልብ አንበል ጀኔራል ሣሞራ የኢትዮጵያ የመከለከያ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማጆር ሹም ተብለው የተቀመጡ ናቸው:: ግን ደግሞ ከ85 ብሔር ብሔረሰቦች መሀከል አንዱን (አማራን) መርጠው ወይንም ነጥለው "አማራን እንዳያንሠራራ አድርገን አጥፍተነዋል!" በማለት ባዳራሽ ውስጥ ለተሰበሰበ ሕዝብ ያደረጉት ንግግር አስደንጋጭና አሳሳቢ ነው:: እንቅልፍ የሚያስተኛም አይደለም:: የሕወሓት ሰዎች ምን እየሠሩና ምን እየቀበሩ እንዳሉ ደግማችሁ ደጋግማችሁ ጠይቁ:: አንዳንድ ጊዜ ልብ ብላችሁ አጢናችሁ ከሆነ የንፁሐን ደም እየተከተለ የሕሊና ሰላም የሚነሳቸው ይመስላሉ::

አማራ በዚህ ዘመን ጫካ ገብቶ ጥይት ተኩሶ አንድ ተጋዳላይ ሳይገልባቸው ይህን ያህል በመንፈሱ ለምን እንደሚሸበሩ ግራ የሚያጋባ ነገር ነው:: ይህንንም ጠይቁ::

ባማራ ሕዝብ አንድ የጠነከረ ባህል አለ:: "ለልጅ ክፉ ነገር አይነገርም" ይባላል:: ይህ መልካም ነገር ነው:: ክፉ ሥራ ቢሠራ እንኳን በጊዜው ይወቃቀሱበታል እንጂ ካለፈ በኋላ አይነሳም:: በጣም ነውር ነው:: ቁርሾና በቀሉ ወደ ትውልድ እንዳይተላለፍ ጥንቃቄ ይደረጋል:: ከልጆች ፊት አይነሳም:: "እሱን ነገር እርሱት፤ አታንሱት፤ በቃኮ አለፈ" እየተባለ ይደበቃል:: ወይንም እንደሞተ ይቆጠራል:: አሁን ግን አበጥሮ መነጋገሩ የግድ እየሆነ መጥቷል:: ከእንግዲህ በደረቅ ፕሮፓጋንዳ እየተቋሰሉ አብሮ





መኖር ከማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል:: ቁስሎቻችንና እባጮቻችን ሊፈርጡና ሊሽሩ የሚችሉት እውነቱን አውቀን መወቃቀስ ስንችል ብቻ ነው:: አለበዚያ እንደብሥራት አማረ የፈጠራ ታሪክ እየጻፍን አንድን ሕዝብ ከርሃብ ጋር እያነፃፀርን ጥላሸት የምንቀባ ከሆነ ሌላ ክፉ ብጉንጅ እያሳበጥን መሆናችንን ልናውቅ ይገባናል:: የሕወሓት ሰዎች በየጉያችን እባጭ እያስታቀፉን መሆናቸውን እያንዳንዱ ዜጋ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል:: ሌላው የሕወሓት ተጋዳላይ ያስታቀፈንን እባጭ (ብጉንጅ) ደግሞ እነሆ:-

## እናት ሲመታ እግር መቆም አይችልም!

የሕወሓት ሰዎች ወደፊት እንደምናየው ያማራ ወጣቶችን ለመብታቸው ሲሟገቱ፣ ሌላው ቀርቶ የሚፈፀምባቸውን ግፍ ለመናገር እንኳን እንዳይችሉ "ፊት የደረሰን አዝመራ ወፍ ይበላዋል" እንዲሉ እናት እናታቸውን በመቀጥቀጥ ሌሎች በእግራቸው ቁመው እንዳይሄዱ ፖሊዮ እንደያዘው ሽምድምድ ወይንም ልፍስፍስ ትውልድን ማፍራት ሆኗል:: የፖለቲካ ጫወታውንም ልብ ብሎ ላጤነ ሰው እንደ ዱላ ቅብብሎሽ ጨዋታ ዓይነት ነው:: ይህንን ያልተገነዘብነውና ያልተረዳነው የነሱን ቅጥፍራፊ የምንለቃቅመው ብቻ ነን:: ለማንኛውም አንዱ ተጋዳላይ ከዚሁ አዲስ አበባ አብነት ሠፈር የድርሻውን ካዛውንቶቹ ተጋዳላዮች ተቀብሎ ጥላቻውን በሚገባ ገልጧል::

ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ሐሳባቸውን እንድናወጣላቸው ግለሰቦች ይጽፉልናል:: የዚህ ተጋዳላይ ደብዳቤዎችም ከጄ የገቡት በዚህ ወቅት ነበር:: ለማንኛውም የመጀመሪያው ደብዳቤ እንዲህ ይላል:-

"ወቅቱ የወያኔ ሠራዊት የደርግን ሠራዊት እየጠረረገ ወደ አዲስ አበባ ቀርቧል:: በቅድሚያ ግን ትግሬና ወያኔ ያንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታዎች ስለሆኑ ትግሬ ስል ወያኔ፣ ወያኔ ስልም ትግሬ ማለቴ እንደሆነ ይታወቅልኝ" ሲል አስቀድሞ ይነግረናል:: ለኔ ግን ወያኔዎችና ትግሬዎች የተለያዩ አድርጌ ነው የምወስዳቸው:: በርግጥ ወያኔዎች የትግራይ ሕዝብ ልጆች መሆናቸው ይታወቃል:: የትግራይን ሕዝብ በመደዳ ግን"ትግሬ ማለት ወያኔ፤ ወያኔ ማለት ትግሬ" ብሎ መበየን ትክክል አይመስለኝም:: አንድ ሕዝብ በጅምላ በምንም መመዘኛ በፋኖ ስም አይፈረጅም:: ለማንኛውም አማራን የኮነነበትን ጽሑፉን እነሆ:-



የህግ ባለሙያው አቶ ሙሉጌታ በሪሁን

"<አማራና ረቂቅ ተንኮሎቹ፤> በሚል ርእስ በጋዜጣችሁ ባታወጡትም ባለፈው ደብዳቤዬ ስላማራ እኩይ ማንነትና ስለ ሕወሓት የመጨረሻ ግብ ጽፌላችሁ ነበር፡፡ ለነገሩ አመለካከታችሁን የሚጎዳ ጽሑፍ እንዴት ልታወጡ ትችላላችሁ?" ሲል ዝግጅት ክፍሉንም ወርፎታል፡፡ የሆነ ሆኖ "አማራና ረቂቅ ተንኮሎቹ" የሚለውን እንይለት፡-

"1ኛ. <ወጋ ነቀል> ዐማራ በነገር ጠቅ አድርጎ ለማፅናናት ይሞክራል፡፡ ወጋ ነቀል በየትም ብሔር የሌለ ያማራ እኩይ መታወቂያ ነው፡፡

2ኛ. <አሽሙረኛ> ዐማራ በቀጥታ ከመናገር ይልቅ አስመስሎ መዝለፍ ወይንም መስደብ ይቀናዋል፡፡

3ኛ. <እየሳቀ ሰውን ይገላል> ዐማራ ጥላቻውን በውስጡ ቀብሮ ውጫዊውን ገጽታውን እንደፈንዲሻ ያፈካል፡፡ ትግሬ ግን ያማራ ተቃራኒ ነው፡፡ ንዴቱን፣ ጥላቻውን፣ ባጠቃላይ የውስጥ ማንነቱን በፊቱ ላይ ይነበባል፡፡ የሚያሣዝነው ግን ሰው የሚወደው እየሣቀ የሚጎዳውን ነው. . ." ይለናል፡፡ ሌሎቹን ብሔረሰቦችም ትግሬን (ግልፁን) ጠልታችሁ (ድብቁን) ወይንም እየሳቀ የሚገላችሁን አማራን ትወዳላችሁ ሲልም ወቅሷል፡፡

ሌላው የዚህ ተጋዳላይ ጽሑፍ <የሕወሓት የመጨረሻ ግብ!> በሚል ርእስ "ትግሬ በሁሉም ብሔረሰቦች እጅግ በጣም የተጠላ ብሔር ነው፡፡ ትግሬን የሚወድ አንድም ብሔረሰብ የለም፡፡ የትግሬ ሕዝብ የሚጠላው በትግሬነቱ ብቻ ነው፡፡ ትግሬ ሆኖ ጥሩ ከመሆን የሌላ ብሔር ተወላጅ ሆኖ ከፉ መሆን ያስወድዳል፡፡ አንድ ሕዝብ በማንነቱ የሚጠላ ከሆነ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር እንዴት አብሮ መኖር ይችላል?" በማለት ይጠይቅና "ሕወሓት ይህንን ስለሚያውቅ የመጨረሻ ግቡ ትግራይን ገንጥሎ መኖር ነው፡፡ የሕወሓትን ሐሳብ እደግፋለሁ፡፡ በትግሬነቴ የምጠላ ከሆነ ተገንጥዬ መኖርን መቶ በመቶ እመርጣለሁ፡፡" የጥቅሱ መጨረሻ፡፡

ይህ ተጋዳላይ ከራሱም ጋር የተጣላ ይመስለኛል፡፡ አንድ ሰው በግል ምግባሩ ሊጠላ ይችላል፡፡ አንድ ሕዝብ ግን በጅምላ ሲጠላ አይቼም ሆነ ሰምቼ አላውቅም፡፡ "ክፉ ሰዎችን የገዛ ጥላቸው እየተከተለ ያሣድዳቸዋል" የሚባለው እንደ ሕወሓት አባላት ያሉትን ነው፡፡ ለመሆኑ የትግራይን ሕዝብ በጅምላ ወይንም በመደዳ ሌላው የኢትዮጵያን ሕዝብ ስለመጥላቱ የመለኪያ መሥፈርቱ ምንድን ነው? ይህ ተጋዳላይ የራሱ ፍርሃትና ጭንቀት ወይንም እሱ በሌሎች ሕዝቦች ላይ ያለውን ጥላቻ የፈጠረበት የፍርሃት ድፍቀት





እንጂ የትግራይን ሕዝብ በመደዳ የሚጠላ አንድም ዜጋ የለም፡፡ በርግጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የትግራይ ሕዝብ ጭምር ከሌሎች ወንድሞቹ ሊነጥለው የሚታገለውን ሕወሓትን አይወድም፡፡ ይህ ተጋዳላይም ከትግራይ ሕዝብ እንደ ሕወሓት ለመሸጎጥ ስለሚፈልግ "ወያኔ ስል ትግሬ ትግሬ ስልም ወያኔ ማለቴ ነው" ሲል ገና ከመግቢያው ላይ ሊያስተዋውቀን ሞክሯል፡፡ ይህ ግን ስህተት ነው፡፡

## "ሆዱ ጩቤ አፉ ቅቤ!"

". . .ባንዳንድ አካባቢዎች ‹እናንተ የዚህ ብሔረሰብ አባል ናችሁ (አማራዎችን ለማለት ነው) ይህንን አካባቢ ለቃችሁ ውጡ› እየተባሉ ነው" ተብሎ ገና ከማለዳው ለጠ/ሚንስትር መለስ ዜናዊ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፡-

". . .እኛ ዋንኛውን ያማራ ሕዝብ በወሬ አይደለም፣ በሩቅም አይደለም የምናውቀው፤ አርሶ አደር ነው፡፡ ያማራ አርሶ አደር እኛ በተግባር ነው የምናውቀው፡፡ ከኛ ጎን ተሰልፎ ሲዋጋ፣ ስንቅ ሲሠንቅልን ነው የምናውቀው፡፡ ጎጆውን እናውቃታለን፡፡ . . . ምን ዓይነት እንጀራ እንዳለው እኛ እናውቃለን፡፡ ከማንም በተሻለ ሁኔታ እድልኦ የለውም፡፡ ስለዚህ ያንን ሕዝብ እንደ ሕዝብ ጠላት የሚወስድ ካለ ያ ዘረኛ ነው!"

ጠ/ሚንስትሩ ይህንን የተናገሩት በ1983 ዓ.ም ሥልጣን ላይ እንደወጡ ነበር፡፡ ይህ ወቅት ደግሞ አነግ ያማራ ዜጎችን "ከክልሌ ውጡ" እያለ ያምስ የነበረበት ወቅት ነበር፡፡ በመሆኑም የጠ/ሚንስትሩ ንግግር መልካምና ካንድ መሪ የሚጠበቅ ነበር፡፡ ዳሩ ግን ወደ ውስጥ ስንገባና ከዚያ በኋላ እስካሁንም ድረስ ባማራ ሕዝብ ላይ የተወሰዱትንና በመወሰድ ላይ ያሉትን ርምጃዎች ስናጤን የጠ/ሚንስትሩ ንግግር "ሆዱ ጩቤ አፉ ቅቤ!" እንደሚባለው ዓይነት ናቸው፡፡

እውነት ነው፤ ያማራ ሕዝብ ከደርግ ወታደሮች እየደበቀ እያበላና እያጠጣ፣ የሚሄዱበትን ሥርጣስርጥና የቅርቅፍት መንገዶች እያመላከተ አዲስ አበባ እስከሚደርሱ ድረስ አሳልፏቸው ነበር፡፡ እነ አጅሬ ግን "አፉ ቅቤ ሆዱ ጩቤዎች ናቸውና" መልሰው መኗሪያ አሣጥተው ያሳድዱት ጀመር፡፡ በዚህ አጋጣሚ አንድ ሀቅ አስቀምጬ ማለፍ እፈልጋለሁ፡፡ እንዲህ ነው፡-

በቀድሞው አጠራር ጎንደር ክ/ሀገር ቆላማ አካባቢ የወያኔ ታጣቂዎች ወይንም ፋኖች ውሃ ይጠማቸውና ካንድ መንደር ውስጥ ገብተው ውሃ እንዲሠጧቸው ይለምናሉ፡፡ ይሰጧቸዋል፡፡ ተጋዳላዮቹ ከጠጡ በኋላ ሣንቲም አውጥተው የውሃውን ዋጋ እንከፈላችሁ ይላሉ፡፡

"እንዴ! ጥሩ ውሃኮ ነው የሠጠናችሁት፤ ጠላ አይደለምኮ" ይላሉ በመገረም ሴቶቹ፡፡

"ጥሩ ውሃ ቢሆንም፤ ወንዝ ወርዳችሁ አይደል የምትቀዱት? የጉልበታችሁን ዋጋ መክፈል አለብን፡፡ አለበለዚያማ እንደ ደርግ ወታደሮች ዘራፊዎች መሆናችን ነው!" በማለት ይገለገላሉ፡፡

"ቢሆንም እኛ ለጥሩ ውሃ ሣንቲም አንቀበልም" በማለት ሴቶቹ ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ተጋዳላዮቹ መራርቀው "እፉ ቅቤ ሆዱ ጩቤ" ፕሮፓጋንዳቸውንም ነዝተው ሄደዋል፡፡ ካንጀት ቢሆን ኖሮ ያ ሁሉ ትህትናና ለወገን አሣቢነት አዲስ አበባ ሲገቡ በኖ ባልጠፋ ነበር፡፡ "ጅብ እስቲነከስ ያነክስ ነውና!" አዲስ አበባ ገብተው ሲደላደሉ ግን ያማራን ዜጋ መኗሪያ አሣጥተው ባላሳደዱት ነበር፡፡

እንግዲህ እስካሁን ለማስቃኘት የሞከርኩት የጎሰኝነት ሥርዓት ምን ያህል ጨካኝና አድሏዊ መሆኑን ነው፡፡ ጎሰኝነት የኔ ከሚላቸው ጎሣዎች በስተቀር በዚች አገር ላይ ሌሎቹን እንዲኖሩ አይፈቅድም፡፡ አቅም ካለው ማጥፋት ነው፡፡ አቅም ካጣና የጊዜው ሁኔታ የማይፈቅድለት ከሆነ ደግሞ የሱ የበታች ሆነው ተሸቆጥቁጠው፣ ሰብአዊ ክብራቸው ተገፎ በጢሰኛ ወግ ዝቅ ሲልም በእንስሳ ወግ መኖር ነው፡፡ ይህንን ሀቅ ባማራ ሕዝብ ላይ የሚወሰደው ርምጃ ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል፡፡ የኦሮሞው ዜጋችንም ከዛፍ ዛፍ እንደሚዘል ጉሬዛ በገዛ ቀየው ካብራኩ የወጡ ጀሌዎች ሲያዘልሉት እያስተዋልን ነው፡፡

"በብሔር ብሔረሰቦች ሙዚቃና ዳንኪራ" ስም ወይንም ጥቁር መጋረጃ ጎሰኝነት ተከልሎ አገር እያጠፋ መሆኑን ዜጎች ልብ ልንል ይገባናል፡፡ እስከ መቸስ አንዱ ጎሳ የሌላው ጎሳ ጠላት ተብሎ እስበሳችን እንደ ዶሮ አውራዎች እየተተካተክን እንኖራለን? ዐላየሁም፣ አልሠማሁም፣ አልናገርም ከምንልበት ጊዜ ላይ አይደለንም ያለነው፡፡ ይች አገር አማራጮቿ ሁሉ በጎሳ እሾህ ታጥሮባት ወደ ገደል አፋፍ እየቀረበች ነው፡፡ ምሁራን አንድ ሊሉ ይገባቸዋል፡፡





የምሁራን ዝምታ ማብቃት አለበት፡፡ የምሁራን አድርባይነትና ጥቅመኝነት እጅግ አድርጎ ያሣፍራል፡፡ ምሁራን ታላላቅ ሰዎች ናቸው፡፡ ተፈርተው መከበር አለባቸው፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ ሞራላዊ ብቃት ኖሯቸው በተግባር ሲያሣዩ ነው፡፡ ማንንም ሣይፈሩ ለሰዎች ወይንም ለዜጎች ስቃይ ድምፃቸውን ማሰማት አለባቸው፡፡ በምንም መመዘኛ ምሁራን የጎሳ ጥልቆ ሊያጠልቁ አይገባቸውም፡፡ ኢትዮጵያዊ ካባ ነው መጎናፀፍ ያለባቸው፡፡ ለማንኛውም ቢያንስ ለብሔራዊ መግባባት ምሁራን ድምፃቸውን ማሰማት የሚገባቸው ጊዜው አሁን ነው፡፡

<><>